# ጠረጋ
# (FIRE ON THE MOUNTAINS)

በሬይሞንድ ዴቪስ

በኢትዮጵያ የአንድ
ቤተ ክርስቲያን አስደናቂ ታሪክ

ተርጓሚ በቀለ ገሙ

1986 ዓ.ም.

«. . . የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አስደናቂ ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ከተጻፈው ታሪክ ቀጥሎ ሁለተኛውን ደረጃ የሚይዝ ነው።»

ከሚስዮናዊው ኤል ዳቭሰን ሪፖርት የተወሰደ

ለኤስ አይ ኤም በአፍሪካ መቶኛ ዓመት፣
እንዲሁም በኢትዮጵያ 65ኛ ዓመት
ማስታወሻ

ለማንኛውም አስተያየት
የፖ.ሣ.ቁ. 31252
አዲስ አበባ

በት·መ·ሣ·ማ·ድ· ታተመ።

# ማውጫ


ገጽ

መቅድም

ክፍል አንድ፡እሳቱ ተቀጣጠለ . . . . . . . . . . . . . 7

ምዕራፍ 1. የእሳት ባሕር . . . . . . . . . . 7

ምዕራፍ 2. የዳና ማጀ ውሳኔ . . . . . . . . . . . 10

ክፍል ሁለት፥ እሳቱ ተለኮሰ . . . . . . . . . . . . . . 14

ምዕራፍ 3. የተገለጡ ምስጢሮች . . . . . . . . . 14

ምዕራፍ 4. ምቹ አጋጣሚዎች . . . . . . . . . 19

ክፍል ሦስት፥ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» . . . . . . . 26

ምዕራፍ 5. የመሠረት ድንጋዮች . . . . . . . . . 26

ምዕራፍ 6. ኢየሱስ ክርስቶስና ሰይጣን . . . . . . . 31

ምዕራፍ 7. የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . 36

ምዕራፍ 8. ክርስትናና ባሕል . . . . . . . . . . . 39

ክፍል አራት፥ የጦርነቱ እሳት . . . . . . . . . . . . . 43

ምዕራፍ 9. ጦርነቱ ተጀመረ . . . . . . . . . . . . 43

ምዕራፍ 10. ቶሮ . . . . . . . . . . . . . . . . 52

ምዕራፍ 11. በድጋሚ እስከምንገናኝ . . . . . . . . 56

ምዕራፍ 12. እግዚአብሔር ግን . . . . . . . . . . 57

ክፍል አምስት፥ በእሳት ተጠመቁ . . . . . . . . . . . . 63

ምዕራፍ 13. እሳቱ ተዛመተ . . . . . . . . . . . . 63

ምዕራፍ 14. በመከራ ውስጥ መዘመር . . . . . . . . 65

ክፍል ስድስት ፥ ቤንዚን መጨመር . . . . . . . . . . . 74

ምዕራፍ 15. ቋጠሮችን መፍታት. . . . . . . . . . 74

ምዕራፍ 16. ምግብ ለአካል-ምግብ ለነፍስ. . . . . . 80

ምዕራፍ 17. ሕልምና መጽሐፍ ቅዱስ. . . . . . . . 85

ምዕራፍ 18. ፈውስና ጸሎት . . . . . . . . . . . 89

ምዕራፍ 19. ተግባራዊ ቤተ ክርስቲያን. . . . . . . 93

ክፍል ሰባት - ቋሚ ብርሃናት. . . . . . . . . . . . . 99
ምዕራፍ 20. ናና . . . . . . . . . . . . . . . 99
ምዕራፍ 21. ባሎቴ . . . . . . . . . . . . . . 103
ምዕራፍ 22. አሞኜ . . . . . . . . . . . . . . 110
ምዕራፍ 23. ግፋቴ . . . . . . . . . . . . . . 113
ምዕራፍ 24. የአዳ ሚስት . . . . . . . . . . .116
ምዕራፍ 25. ላፋሜ . . . . . . . . . . . . . . 120
ክፍል ስምንት፥ ያልጠፋው እሳት . . . . . . . . . . . 123
ምዕራፍ 26. የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ . . . . 123
ምዕራፍ 27. ለምን በወላይታ ሆነ? . . . . . . . 127
መደምደሚያ . . . . . . . . . . . . . . . . ..132

# መቅድም

የወላይታ ቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ደራሲው ሬይሞንድ ዴቪስ እንዳሉት «ተአምራዊ ታሪክ» ነው። ታሪኩን የሠራው ሰው ሳይሆን ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። አዎን መንፈስ ቅዱስ ሳይፈቅድና ሳይሠራ ወንጌልን ማስተማርና መስበክ፥ በሕግ በተከለከለበት ጊዜና ቦታ ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር፥ በሰይጣናዊ እምነትና አምልኮ፥ በጠንቋዮችና ቃልቻዎች ማስፈራሪያ የታሰረውን ሕዝብ የምሥራቹን ቃል በማሰማት ነፃ ማውጣት የሚችል ማነው? መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር ፊደል ካልቆጠሩ፥ በቋንቋቸው የእግዚአብሔር ቃል ተተርጉሞ ካላነበቡና ካላጠኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገብተው ካልሠለጠኑ ሰዎች መካከል በአካባቢያቸውና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ዞረው የምሥራቹን ቃል የሚያውጁ ወንጌላዊያንና ድንቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መፍጠር የሚችል ማነው?

አዎን ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅዱሱ መንፈስ በሙላት ተሰጥቷቸው ስለነበር ወንጌል በኃይልና በሥልጣን ተሰብኮ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን አመኑ። አሮጌ ባሕልና ሰይጣናዊ አምልኮ ተወገደ፥ ጠንቋዮችና ቃልቻዎች ገቢያቸውን አጡ፥ አሊፈውም የአምልኮ መጣሪያዎቻቸውን በመጣልና በመሰባበር እጃቸውን ለወንጌል በመስጠት ተማረኩ። በወላይታ ሕብረተሰብ ውስጥ እግዚአብሔርን ማምለክ ሲጀመር አመለካከት፥ አስተሳሰብ፥ አለባበስ፥ አመጋገብ በአጠቃላይም አኗኗር ተለወጠ። ከሰይጣንና ደቀ መዛሙርቶቹ ዛቻና ሽብር በወንጌል ነፃ ስለወጣ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ፥ ቤተሰብና አካባቢ ሰላም ሰፈነ።

በበዓለ ሃምሣ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ሐዋሪያት ከተቀበሉት በኋላ ወንጌል በኃይልና በሥልጣን እየተሰበከ እንደሰደድ እሳት ሲቀጣጠል (ሐዋ. ሥራ 2 እና 3) ወዲያው የክርስቶስ ጠላቶች ሐዋሪያትን ማሳደድ እንደጀመሩ (ሐዋ. ሥራ 4) ሁሉ የወላይታ ክርስቲያኖችም ወንጌልን አምነው ስለተቀበሉና መልሰው ስለሰበኩ ባላባት አስተዳዳሪዎች፥ የአሮጌ አምልኮ መሪዎችና የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች አማኞችን ከሰሰዋል፥ አሳስረዋል፥ ገርፈዋል። በአዲስና አሮጌው እምነት መካከል በተፈጠረው ልዩነት ምክንያት ልጅ ከአባት (እናት)፥ ወንድም ከወንድም፥ ባል ከሚስት፥ ዘመድ ከዘመድ፥ ጓደኛ ከጓደኛ . . . ወዘተ ተለያይተዋል። ይህ የወላይታ አማኞች የከፈሉት ውድ ዋጋ ከስድሣ አምስት ዓመታት በፊት የተለኮሰውን የወንጌል እሳት እስከዛሬ ጠብቆ አቆይቶታል።

እንግዲህ ይህንን በእግዚአብሔር የተሠራ አስደናቂ ታሪክ ነው በሚቀጥሉት ገጾች የምናነበው። ታሪኩ የእግዚአብሔር አሰራር፥ የሚሲዮናውያን፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የአማኙ ሕዝብ ክርስቲያናዊ ተጋድሎ ታሪክ ነው። መጽሐፉን እንድተረጉመው ያነሣሣኝ ይህ በሀገራችን የተፈጸመ አስደናቂ ታሪክ ለምዕራባውያን አንባቢያን በቋንቋቸው የተጻፈ ቢሆንም በቋንቋችን ተተርጉሞ ለሀገራችን አንባቢያን ያለመቅረቡ ነበር። መጽሐፉ በውጭ አሥራ አራት ጊዜ ተደጋግሞ መታተሙና በሌሎች ሦስት የውጭ ቋንቋዎች መተርጎሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ በክርስቲያኖች ዘንድ

ተወዳጅ መሆኑን ያመለክታል። አሁን ደግሞ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ መቅረቡ በሀገራችን ለግል አንባቢያን፣ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጥኚዎች፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶችና ለመሳሰሉት እጅግ ጠቃሚ ነው።

የመጽሐፉ አርእስት በእንግሊዝኛ «ፋይር ኦን ዘ ማውንተንስ» የሚል ሲሆን በወንጌል እሳት የሰይጣን ሥራ ሁሉ ተጠራርጎ የጠፋ መሆኑን ስለሚያመለክት «ጠረጋ» ብዬ ተርጉሜዋለሁ። «ጠረጋ» ማለት ማንጻት፣ ማስወገድ . . . ወዘተ ማለት ሲሆን በወላይትኛ ደግሞ የሰደድ እሳት ማለት ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹት ድርጊቶች የተፈጸሙት በወላይታ ባሕልና ሥርዓት ውስጥ ይሁን እንጂ ጸሐፊው ይህንን ሥርዓት፣ ባሕልና ቋንቋ የማያውቅ የውጭ አገር ሰው ሲሆን የተጻፈውም ለውጭ አንባቢያን ነው። እኔ ደግሞ የወላይታን ባሕልና ቋንቋ የማውቅ መሆኔ በትርጉሙ ሥራ በጣም የረዳኝ ቢሆንም ታሪኩን ለሀገራችን አንባቢያን በሚስማማና በሚገባ መንገድ ተርጉሞ ማቅረብ ቀላል እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ በሰዎችና በታዎች አጠራር፣ ቀኖችንና ዓመታትን ከአውሮፓውያን ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ስለውጥ ይህንንና በመሳሰሉት ላይ ስሕተት ቢኖር አንባቢያን በይቅርታ እንደምታልፉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። በትርጉሙ ላይ ያላችሁን አስተያየት ደግሞ አጥብቄ የምሻ መሆኔን በተጨማሪ እገልጻለሁ።

ትርጉሙን በምሠራበት ጊዜ በምክር በእርማት በሌላም ሁሉ ለረዱኝ ወንድሞች እህቶችና ድርጅቶች ጥልቅ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቀለ ገሙ

# ክፍል አንድ፡- እሳቱ ተቀጣጠለ

## ምዕራፍ 1. የእሳት ባሕር

. . . በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን
የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።

1ኛ ቆሮ. 1፡21

ዳና ማጂ በከፊል እንቅልፍ ልብ ግድግዳ ተደግፈው ተቀምጠዋል። ሌሎች ግን ጭውውት ይዘዋል፥ ፊታቸውና መልካቸው ብልጭ ድርግም እያለ ከሚነደው እሳት ነበልባል የተነሣ ደምቋል። ወዲያው ዳና ማጂ በጭውውቱ ርዕስ በመደናገጥ ከሕልም እንደሚነቃ ሰው ባነኑ። ከድካምና መጫጫን ጋር እየታገሉ ከነቁ በኋላ ስለ አባያ ሐይቅ አብረዋቸው ያሉ ሰዎች የሚያወሩትን ማዳመጥ ጀመሩ።

«ይህ ስለ ሐይቁ የምትነግረን በጣም እንግዳ ነገር ነው፥ ነገሩ በርግጥ እውነት ነው?» ሲል ጠየቀ ሎላሞ።

«ኃይለ ሥላሴ ይሙት!» አለ የቤቱ ባለቤት። ቀጥሎም «እውነት ነው፥ ከዚሁ ካለንበት ቦታ ቢበዛ ከሁለት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ከሐይቁ ዳርቻ ብዙም ሳይርቅ ከድንጋዮች ስንጥቅ እጅግ ብዙና የማያቋርጥ ደመናማ እንፋሎት ሲወጣ ማየት ይቻላል። ይህም የሚሆነው ብዙውን ጊዜ በቀዝቃዛ ወራት ነው።»

ዳና ማጂ ቀና ብለው «ምንድነው እሱ? ሙቅ ውሃና እንፋሎት ከምድር ውስጥ ይወጣል? ከየት ነው የሚመጣው? እሳትስ የለም?» አሉ።

«እንግዶቼ ባይደከማችሁ ኖሮ አሁኑኑ ያን ሥፍራ እንድታዩት በወሰድኋችሁ ነበር። ከፈለጋችሁ ነገ ጧት ጉዞአችሁን ስትጀምሩ ይህንን በአይናችሁ እንድታዩት ወደዚያው እመራችኋለሁ። በጨለማ ስለሚያስፈራ ቀን በፀሐይ ብርሃን ብናየው ይመረጣል።»

ወዲያው እሳቱ መጥፋት ሲጀምር አንድ በአንድ እንቅልፍ አሸነፋቸውና ፀጥታ ሆነ፥ ቤቱም ጨለመ። ዳና ማጂ ግን የሰሙት አላስደሰታቸውም። ውሃውን ሊያፈላ የሚችል ሙቀት ከሆነ እሳት መኖር አለበት ብለው አሰቡ። ስለ እሳት ባሕር ሌላ መግለጫ ማግኘቱ ያጋጣሚ ጉዳይ አይመስለኝም፥ ለሁሉም እስቲ ነገ ጧት አየዋለሁ።

ነገር ግን ዳና ማጃ የጠበቁት የጧቱ ሰዓት ቶሎ የሚደርስ አልሆነላቸውም። ሲዞሩና ሲገላበጡ እንቅልፉም ሊወስዳቸው አልቻለም። እነዚያ ዋንዳሮ የተናገራቸው ቃላት በአንጎላቸው ደግመው ደጋግመው እየተመላለሱ በሀሳባቸው የሚፈጥሩትን አስፈሪ ሥዕላዊ መግለጫ ማጥፋት አልቻሉም። «እሱ የሚለውን መስማት አልነበረብኝም ገና በመጀመሪያ ሳየው አንድ የተለየ ነገር እንዳለው ይታወቀኝ ነበር» ብለው አሰቡ።

ዋንዳሮ ልዩ ሰው ነበር፥ ገራገር ነገር ግን ደፋርና ግልጽ። ዳና ማጃ በሰዎች ሁሉ ዘንድ የታወቁ የተፈሩና የተከበሩ፥ አንዳንዴ ትልቅ ሰው ወይም በአካባቢው አጠራር «ዳና» ስለነበሩ ቁጡና ዝምንተኛ፥ ከወላይታም ሆነ ከሌላ ጎሣ የሆኑ ብዙ ባሪያዎች ያሏቸው ናቸው። («ዳና» ማለት ሹም ማለት ነው።)

ዳና ማጃ በቆላማ የጥጥ እርሻቸው ሆነው ንብረታቸውን ሲቆጣጠሩና ሲጠብቁ ነበር አንድ ጉስቁል እንግዳ ሰው ባልተለመደ አኳኋን በድፍረት ሊያነጋግራቸው የጀመረው። «ጎዶ (ጌታዬ)! አንድ ቀን ንስሐ ሳይገቡና በኢየሱስ ክርስቶስ ሳያምኑ ቢሞቱ ወደ ገሃነም ወርደው በማይጠፋ የእሳት ባሕር ይቃጠላሉ።»

ሹሙ ለመስማት ባይፈልጉም ያለመፈለጋቸውን ስላልገለጹ ከመስማት አላመለጡም። በጎ ሰው እንዳልሆኑ ስለሚያውቁ ከሞት በኋላ ምን እሆን ይሆን እያሉ ሁልጊዜ ራሳቸውን ይጠይቁ ነበር። እንግዳው እንዲጠጋቸው እየጠቀሱ ስለዚሁ ጉዳይ የበለጠ እንዲነግራቸው ጠየቁት። ዋንዳሮ መዳንና ለኃጢአታቸውም ይቅርታ ለማግኘት የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ፈቃድ እንደሚያስፈልጋቸው ለዳና ማጃ በግልጽና በቀላሉ መሰከረላቸው። ዳና ማጃ ይህ የሚታመንበት ሰው የሚገኝበትን ቦታ ሲጠይቁት ዋንዳሮ ይህ ሰው አሁን በመንግሥተ ሰማይ እንዳለ፥ አንድ ቀን (ምናልባትም በቅርብ ጊዜ) ወደ ዓለም እንደሚመለስና በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ወደዚያው አስደናቂ ሀገር እንደሚወስድ ነገራቸው።

ዳና ማጃ በእሳት ስለሚቃጠለው ባሕር ከሰሙ ሳምንታትና ወራት ያለፉ ቢሆንም ያንን ደጋግመው ማስታወሳቸው አልቀረም። ትናንት እርሳቸውና ሎላሞ በስተደቡብ ከሶዶ አሥር ማይል ያህል ርቆ ከሚገኝ ቤታቸው ተነስተው ነበር ጉዞ የጀመሩት። በመሸባቸውም ጊዜ ለአዳር በአባያ ሐይቅ አጠገብ አረፉ፥ የተጓዙትም ሃያ ማይሎች ያህል ነበር። በዚህ ቦታ ከመሬት ውስጥ (ያውም ከሐይቅ አጠገብ) እንፋሎት መፍለቁ ሲሰማ እንዴት ያስደንቃል! ሀሳቡ በጣም ስለረበሻቸው እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም።

እንደማይነጋ የለምና ነጋ። ዳና ማጃ ድካም እየተሰማቸው ከሌሎች በመቀላቀል በኮርቻቸው ተቀመጡ። በሰውነታቸው ሕመም ይሰማቸዋል፥ ቀዝቃዛው ንፋስ አጥንታቸውን ከፉኛ ገርፎታል። በድንጋያማው የእግር መንገድ ከሚሰማው ከእንስሳቱ ኮቴ በቀር ፀጥታ ሰፍኗል።

ማዶ ከሰፊው ሐይቅ ባሻገር በተራሮች ጫፍ ላይ ፀሐይ ስትወጣ ትታያለች።

የፀሐይዋ ብርሃን በሐይቁ ሲንፀባረቅ እሳት ይመስላል። ወይ ጉድ! ምነው የማየው ነገር ሁሉ ዋንጻር የነገረኝን ታሪክ ያስታውሰኛል! ይህንን የመሰለ ሐይቅ ደግሞ ሊነድ ይችላልን?

ይኸውና ከፊት ለፊታቸው ጥቁር ግራጫና የተለየ ቅርፅ ካላቸው ድንጋዮች ውስጥ እንፋሎት ሲወጣ በግለጻው የፀሐይ ብርሃን በግልጽ ይታያል።

«ይህ መሆን ከጀመረ ስንት ዓመት ነው?» ሲሉ ጠየቁ ዳና ማጃ

«ማን ያውቃል? እኛ ከድሮ ጀምሮ እንደዚህ እንደነበረ እናውቃለን። ሁልጊዜ ስለማይጠፋው እሳት ሲነገር እንሰማለን። ትናንት እንኳን ከአንድ ሽማግሌ ጋር ስንጫወት እነዚሁ እንፋሎት የሚያፈልቁ ቀዳዳዎች ቁጥራቸው ከዓመት ዓመት እየጨመረ መሄዱንና አንድ ቀን ከሐይቁ ጠርዝ ሊደርስ እንደሚችል፥ ይህ ከሆነ ደግሞ ምናልባት የሐይቁ ውሃ በሙሉ ሊሞቅና ሊፈላ እንደሚችል ነግሮኛል። ብቻ እኔ ምን አውቃለሁ?»

ሰዎቹ ጎንበስ ብለው እጆቻቸውን በድንጋዮቹ ላይ ሲያሳርፉ ሙቀት እንዲያውም ግለት እንዳለ ተሰማቸው። በነፋሱ ኃይል ወዳሉበት አቅጣጫ ይጓዝ የጀመረው እንፋሎት ከአፍንጫቸው ሲገባ ሽታው እንግዳ ስለሆነባቸው ፈሩና በፍጥነት ወደኋላ አፈገፈጉ።

ዳና ማጃ ማመን አቅቷቸው ራሳቸው እየነቀነቁና የተመሰቃቀለ ጸጉራቸውን እያሻሹ «እኔ ይህንን አላምንም» አሉ። አብረዋቸው ያሉት ሁሉ በመርበትበት ሲንጫጩ እሳቸው ግን በጣም በመገረም ምንም አልተናገሩም፥ ፈጥነው ወደ በቅሎአቸው በመመለስ ጋልበው ጉዞአቸውን ጀመሩ።

ሙቀት፥ እንፋሎት፥ ፍል ውሃ። እሳት ከሌለ እነዚህ ሊኖሩ አይችሉም እሳት ግን አላየሁም ሆኖም ያለጥርጥር በምድር ውስጥ ያውም በቅርብ እሳት መኖር አለበት። አይከፋ (ምንም አይደል)! ከዚህ ቦታ ርቄ ከኖርኩ ጉዳት አይደርስብኝም ብዬ እገምታለሁ።

በተረከዞቻቸው ሲኮረኩሩት በቅሎው በመጡበት መንገድ እየተንገጫገጨ ይዞአቸው ሲኳትን ነገሩን ረስተውት ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዳና ማጃ ወንድም ታመመ። ተስፋ የቆረጡ ዘመዶች በቃሬዛ ተሸክመው አሥር ማይል ያህል ርቆ ወደሚገኝ ወደ ሶዶ ሚሲዮን ክሊኒክ ወሰዱትና የክሊኒኩ ነርስ ሕክምና አደረገችለት።

«አማኝ ነዎት?» ስትል ነርሷ ዳና ማጃን ጠየቀቻቸው።

«በዚህ ጠርሙስ ለወንድምዎ መድኃኒት ሞልቼ ብሰጥ ጠርሙሱን መልሰው ያመጡልኛል?»

«አዎን» ሲሉ መለሱ ዳና ማጃ። የሁለቱም ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ግን ተቃራኒው መሆኑን በልባቸው ያውቁታል።

ዳና ማጃ ነርሷ ለወንድማቸው የምታዘጋጀውን መድኃኒት ከሌሎችም ጋር በመሆን እየተጠባበቁ ፈረንጁ የሚናገራቸውን ያዳምጡ ነበር፥ ፈረንጁም የሚናገራቸው የዛን ቀደም ሲል ዋንጻር የነገራቸውን ሰው ስም እያነሣ ነበር።

በጣም እንግዳ የሆነባቸው ነገር አንድ ቀን ኢየሱስ ከሰማይ ተመልሶ ሲመጣ እርሱን ያወቁትንና የወደዱትን ወደራሱ ይወስዳቸዋል፥ ሌሎች ግን ስላላወቁ ይተዋቸዋል፥ እነርሱን ፍርድና የእሳት ባሕር ይጠብቃቸዋል ያለው ነበር።

ዳና ማጃም በጠርሙስ የተዘጋጀውን መድኃኒት እንደተቀበሉ ፈጥነው ሄዱ። መድኃኒቱም ባለቀ ጊዜ ለማስጨመር ወደ ሚሲዮኑ መምጣት ግድ ሆነባቸው። ነጭ ሰዎች አስደናቂና እንግዳ ነገር እንደሚያደርጉ ሰምተው ነበርና መጥፎ ነገር እንዳይደርስባቸውና እንዳያስቷቸው የሆነ መከላከያ እንደሚያስፈልጋቸው አሰቡ። በወላይታ ሰዎች ዘንድ ሌሎች ሰዎች ከሚያደርጉት አስማት፥ መተት ወይም ባልታወቀ ኃይል ምክንያት ከሚከሰት መጥፎ ነገር ለመከላከል ክታብ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መፈለግ የተለመደ ነበር። ዳና ማጃ ራሳቸው ሁልጊዜ ለሰይጣን መስዋዕት ያቀርባሉ፥ በጣዖትም ያምናሉ። አሁን ግን የነጮችን ማሳሳቻ ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለባቸው አልታወቃቸውም።

ነጮች ስለማያጨሱ ለመከላከያ ትንሽ ትንባሆ መጠቀሙ ሳይሻል አይቀርም ብለው በማሰብ ጥቂት የትንባሆ ቅጠሎችን በመቀንጠስ በኪሳቸው ያዙ፥ ይህም ዳግመኛ ወደ ሚሲዮኑ ማቢያ በሚሄዱበት ጊዜ ሊደርስባቸው ከሚችል ሁሉ ሊከላከላቸው እንደሚችል ተስፋ አደረጉ። በዚህ በመተማመንም ለተጨማሪ መድኃኒት ወደ ሚሲዮኑ ነርስ መጡ። ምንም ነገር ስላልደረሰባቸው የትምባሆው መተት የሠራላቸው መሰላቸው።

ዳና ማጃም የወትሮ ሕይወታቸውን ለብዙ ወራት ቀጠሉ።

## ምዕራፍ 2. የዳና ማኔ ውሳኔ

> እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ፡- ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም ተነስተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።
>
> የሐዋሪያት ሥራ 9፡6

«ይኸው! ይኸው!» ብለው ከፍ ባለ ድምፅ ጮኹ ዳና ማጃ። «ይህ ይሆናል ብሎ ዋንዳር የነገረኝ ነገር ነው። አስደንጋጭ ድምፅ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ እሳት፥ ጭስ! ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፥ ኢየሱስ የተባለው ወደ ምድር እየመጣ ነው ማለት ነው።»

ዳና ማጃ በይ ውስጥ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ወድቀዋል። በዚያን ዕለት በማለዳ ከቤታቸው ተነስተው ነበር ወደ ሶዶ ጉዞ የጀመሩት። በመንገዳቸው በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ብዙውም ሳያጤኑ በሐሳብ ተውጠው ይጓዛሉ። በቅሎአቸውም የጌታውን ቶሎ የመድረስ ፍላጎት የተረዳ ይመስል በፍጥነት እየገሰገሰ ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳን እሳቸው ባይጨነቁለትም

አንድ ያልተለመደ ድምፅ ለብዙ ደቂቃዎች ተሰምቷቸዋል። ድምፁ እየጨመረ ሲመጣ ግን ስሜታቸውን ስለሳበ ወደላይ ቀና ሲሉ አንድ ዓይነት ቅርጽ ያለው ነገር በአየር ሲበር ተመልከተው በጣም ደነገጡ። አውጥተውና አውርደው ምንነቱን ለመመርመር ጊዜ አልነበራቸውም ወዲያው ምድሩ ተንቀጠቀጠ፥ ሰማዩ ከባድ ድምፅ አሰማ፥ ከእሳቱ የተነሣ ደማቅ ብርሃን ሰማዩን ሞላው፥ ድንጋዮች ከመሬት ወደ ላይ ተወረወሩ፥ ምድሪቱ የምትፈነዳ መሰለች፥ ካልተለመደ አስደንጋጭ ድምፅ የተነሣ በቅሎአቸው ደንብሮ ዳና ማጃን እመሬት ጣላቸው፥ እሳቸውም ከፍርሃትና ድንጋጤ የተነሣ ልባቸው በኃይል እየመታ በወደቁበት ቀሩ።

ድምፆቹ መሰማታቸውን ለሰዓታት ከቀጠሉ በኋላም ፀጥታ ሲሰፍን ዳና ማጃ እየተጯጯናቸው ቀና ብለው በእግራቸው ቆሙ። ታላቅና ኩሩ አለቃ በዚህ ሁኔታ ላያቸው ምስኪንና አሳዛኝ ሆነው ልብሶቻቸው ተመሰቃቅለው በጭቃ ተለውሰው ፊታቸው በፍርሃትና መደናገጥ ተሞልተው ነበር። በጣም ተቸግረው በቅሏቸውን ከያዙ በኋላ እላዩ ላይ ወጡ። አሁን አንድ ነገር ማድረግ ብቻ ይቀራቸዋል፥ ይኸውም በተቻለ ፍጥነት ኢየሱስን ማመንና መከተል ነው። ኢየሱስ የመጣ እንደሆነ በወላይታ ብዙ ጊዜ ላይቆይ ስለሚችል አብረው ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ ዳና ማጃ መዘጋጀት ነበረባቸው። ስለዚህም ማድረግ ያለባቸውን ዘርዝሮ የሚነግራቸው ሰው ፈለጉ።

በቅሎአቸውን በፍጥነት እየጋለቡ በአቅራቢያ መኖሩን ወደሚያውቁት ወደ አንድ ክርስቲያን ሰው ቤት ሄዱ። ላባኒያ ጎዶ (አባ ካባኒያ) እቤት ባይገኝም ባለቤቱ ነበረች። እሷም ዳናን ከሩቅ ስታያቸው በጣም ፈራች። «ወደ ቤት አላስገባቸውም፥ ባለቤቴም የሄደበትን አልነግራቸውም፥ ባሪያ የሚያደርጉትን ሰው ይዘው ሊሄዱ አይደል!» አለች በልቧ። ምንም እንኳን ባለቤቷ የሄደው ለጥምቀት አገልግሎት መሆኑን ቢታወቅም ይህንን ላለመንገር «የሄደበትን አላውቅም» ብላ መለሰችላቸው።

ዳና ማጃ ትተው ወጡ። በመንገዳቸውም በቡድን የሚሄዱ ሰዎችን አገኙና «ወዴት ትሄዳላችሁ?» ብለው ጠየቋቸው። ወደ ጥምቀት አገልግሎት የሚሄዱ ቢሆንም ይህንን ለዳና ማጃ ለመንገር ጥቂት አመነቱ። ላባኒያ ጎዶ ከተጓዦች አንዱ ነበርና መልሶ ለጓደኞቹ እንዲህ አላቸው «ጌታ ኢየሱስ ለዘጠና ዘጠኙ በጎች ሲል የጠፋውን አንድ በግ አልተወውም፥ እኛስ ለዚህ ሰው ለመመስከር ለምን እንፈራለን? ስለ ጌታ ኢየሱስና ስለ ሥራው ልንነግራቸው ይገባል»። በዚያው በነበሩበት መንገድ ላይ መሰከረላቸው። ቀጥሎም «እኛ አሁን የምንሄደው ለጥምቀት አገልግሎት በመሆኑ አብረን እንሂድና ያዩታል» ሲላቸው ዳና ማጃ ለመሄድ ተስማሙ።

ወደ መጠመቂያው ወንዝ ሲደርሱ በወንዙ በሁለቱም በኩል ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ሲመለከቱ አዩ። እሳቸውም በጥምቀት አገልግሎት ሲገኙ የመጀመሪያ ጊዜያቸው በመሆኑ በሕዝቡ መሐከል ሆነው ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን ሁሉ በጉጉት ይመለከቱ ጀመር። አስቀድመው ወደዚያ እንደደረሱ ከሚጠመቁት ውስጥ ጥቂቶቹ ቀድሞ ባሪያዎቻቸው ሆነው ግን ያፈነገጡ ስለነበሩ እሳቸውን ሲያዩ ደግመው ባሪያ ሊያደርጓቸውና

ሊወስዷቸው የመጡ መስኳቸው በሌላ አቅጣጫ ከወንዙ ወጥተው ወደ ማዶ ከተሻገሩ በኋላ ተሰወሩ። ዳና ማጃ ግን አእምሮአቸው በመንገድ ባጋጠማቸው ጉዳይ ተረብሾ ስለነበር የሚጠመቁ ሰዎችን ማንነት ልብ አላሉም ነበር።

ከዚያም በኋላ ሁሉም ለጌታ ራት (ቁርባን) አገልግሎት ወደ አንድ ሽማግሌ ቤት ሄዱ። በዕለቱ የተጠመቁት የጌታን እራት ሲወስዱ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው መሆኑ ነበር። ያልተጠመቁ አማኞች ዳና ማጃም ጭምር ውጪ እንዲቀመጡና እንዲጠብቁ ተደረገ። ዳና ማጃ በቤቱ ውስጥ የሚከናወነውን ያዩ ዘንድ መግባት ባለመቻላቸው ተናድደው ነበር።

ወዲያው ራሳቸውን በራሳቸው «ለምን ውጪ እቀመጣለሁ? ዳና እንደመሆኔ መጠን ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መግባት አለብኝ» አሉ። ሆኖም ትልበተቻቸው ስለ ዛሉ ከመሬት እንኳን ሊነሱ አልቻሉም። ዳግመኛም ሊነሱ ሞከሩ፥ አሁንም አልቻሉም። በዚህ ሁኔታ ቁጭ ብለው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩት በአፋቸው የሆነ ነገር ሲጨምሩ እየተመለከቱ ሲገረሙ ከቆዩ በኋላ አገልግሎቱ ተጠናቅቆ ሰዎቹ ከቤት ወጡ።

በዚያን ሰዓት የዳና ማጃ በዚያ መኖር በሁሉም ዘንድ ታወቀ። ወዲያው የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ፥ ሽማግሌዎችና ላባኒያ ጎዶ ወደ እሳቸው ቀርበው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ማወቅና ከእርሱም የሚገኘውን ደስታና ሰላም መለማመድ እንዴት ያለ ድንቅ ነገር እንደሆነ ነገሩዋቸው።

ከሽማግሌዎቹ አንዱ ዋንዳር ነበር።

«ሳር ሳር (ሰላም ሰላም) ዕለቱን በሰላም አሳለፉ?» ሲል ጠየቀ ዋንዳር።

«በሰላም? በዚህ ዓይነት ጊዜ ማን ሰላምን ሊያገኝ ይችላል? በዛሬው ዕለት ምንም ሰላም አልነበረኝም። እንዲያውም ዛሬ በከፋት በተመላው ረዥም ሕይወቴ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈርቼ ነበር። እስቲ ንገረኝ ዋንዳር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ?» ሲሉ ከፍ አድርገው ተናገሩ ዳና ማጃ።

«ዳና ማጃ! ኢየሱስ ክርስቶስ እስካሁን አልመጣም። ነገር ግን በቶሎ ይመጣ ይሆናል» ሲል ዋንዳር መለሰላቸው። ቀጥሎም «ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ቢሆን ኖሮ እርስዎ እኔንና ሌሎች በዚህ ያሉትን ሊያዩአቸው አይችሉም፥ ምክንያቱም እርሱ እኛን ወደመንግሥተ ሰማያት ይወስደን ነበር። በኢየሱስ ማመንና እስኪመጣም ተዘጋጅቶ መጠባበቅ እንዴት ጥሩ ነገር መሰልዎት ዳና ማጃ! » አላቸው።

በዚህን ጊዜ ዳና ማጃና ዋንዳር ከላባኒያ ጎዶ ጋር በመሆን ወደ ላባኒያ ጎዶ ቤት የሚያመራውን መንገድ ይዘው እየሄዱ ነበር።

«ታዲያ ዛሬ ወደ ሶዶ ስሄድ ያየሁት ምንድነው? በጣም ትልቅ ድምፅ ሰምቼ ወደ ሰማይ ብመለከት አንድ ትልቅ ነገር አንዳች ሌላ ነገር ሳይጎትተው ወይም ሳይገፋው በአየር ላይ ሲበር አየሁት። አመለኛ በቅሎዬ ደንብሮ በመሬት ጣለኝ። መሬት ተንቀጠቀጠ፥ ድንጋዮችና ቆሻሾች ወደ ላይ በረሩ፥ ዛፎችና ቤቶች በፊቴ ተናዱ፥ ይህንን እናንተ አላያችሁምን? አልሰማችሁም?»

«አዎን እኛም አይተናል፥ ሰምተናልም። ፈርተንም ነበር። ነገር ግን ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት እንዳልነበረ እናውቃለን» ሲል መለሰ ዋንዳሮ። በመቀጠልም «እነዚያ እርስዎ ያዩዋቸው ወራሪው ጠላታችን ሀገራችንና ንጉሣችንን ለማንበርከክ የሚጠቀማቸው የጦር መሣሪያዎች[1] (መኪኖች) ናቸው። ጠላታችን በአየር መብረርም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የጠላታችን ሰዎች ከብረት በተሰሩ ትናንሽ ቤቶቻቸው[2] ውስጥ ገብተው ከቤቶቻቸው ጋር በመሬት እንደፈረስ እየሮጡ በበሮችና በመስኮት በኩል በጠመንጃቸው ወደ ውጪ ይተኩሳሉ» አሏቸው።

ዳና ማጃ በጣም ፈርተውና ግራ ገብቶአቸውም ስለነበር የሚነገራቸው ሊገባቸው አልቻለም። ወንጌል እንዲመሰከርላቸው እንዲረዱም መረጋጋት ነበረባቸው፥ ስለዚህም ላባኒያ ጎዶ ቤት ከደረሱ በኋላ ሙቅ ውሃ ቀርቦ ላባኒያ ጎዶ እግራቸውን አጠበ፥ ከልብሳቸው ጭቃ ተራገፈ፥ እሳት እንዲሞቁ ታስቦ ተቀጣጠለ፥ የላባኒያ ጎዶ ባለቤት ትኩስ የወላይታ ቡና በጨው አቀረበችላቸው። ወዲያው ዳና ማጃ ተዝናንተውና ተረጋግተው ለመስማት ዝግጁ ሆኑ።

ደጋግመው ስላዩትና ስለሰሙት ነገር ሲያስቡ ይዘገንናቸዋል፥ ይንቀጠቀጣሉም። ዳና ማጃ በእርግጥ በሕይወታቸው ፈርተው አያውቁም። በመንጠቅና በመፈንገል የሰበሰቧቸው ከመቶ በላይ ባሮች ያሏቸውና ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ለማንም ለምንም ፈርተውና ሰግተው የማያውቁ ናቸው።

በእሳት የሚቃጠለው ባሕር ትዝታ ዋንዳሮ ከነገራቸው ቀን ጀምሮ ለወራት ከአእምሮአቸው አልጠፋም። አሁን ደግሞ እሳቸው ካላቸው ኃይልና ሥልጣን የበለጠ ነገር መኖሩን ስላዩ ዳና ማጃ በለሰለሰ ድምፅ፥ በሽንፈት መንፈስና በልመና መልክ ዋንዳሮን ያነጋግሩታል።

«ዋንዳሮ አንተ አትፈራም? ዛሬ ያየነውና የሰማነው ነገር ሁሉ በፍርሃት ውሃ የሚያደርገን አይደለም ወይ? አንተና ጓደኛህ ላባኒያ ጎዶ ከማንም የማትበልጡ ተራ ሰዎች ስትሆኑ ይህ ሁሉ ነገር እንዴት አያስፈራችሁም? አያስደነግጣችሁም? አይደንቃችሁም?»

«እርግጥ ነው ዳና ስለጣሊያን ወታደሮችና መሣሪያዎቻቸው ስንሰማና ስናያቸው አንዳንድ ጊዜ እኛም እንፈራለን፥ ነገር ግን እኛ በልባችን ሰላም አለን ምክንያቱም እኛ እግዚአብሔርን እናምናለን፥ በርሱም እንተማመናለን። እኛ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳዳነንና እንደሚጠብቀን እናውቃለን።»

---

[1] የጣሊያን ወራሪ ኃይል የተጠቀመባቸው አውሮፕላኖችና ሌሎች መሣሪያዎች ናቸው። ወቅቱ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረር ውጊያ የምታካሂድበት ጊዜ ነበር። ዳና ማጃ ያመኑት በ1929 አካባቢ ጦርነቱ በሚካሄድበት ወቅት ነበር።

[2] ትናንሽ ቤቶች የተባሉት የጠላት ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ናቸው።

ዋንዳር ቀና በማለት የዳና ማጃን ዓይኖች ከፊት ለፊት ትኩር ብሎ እየተመለከተ «እርስዎም ይህ ዓይነት ሰላም ሊኖሮት ይችላል» አላቸው።

«ከሀሳቤ ጋር መታገል አቅቶኛል ዋንዳር። ስለሚገድሉ የጦር መሣሪያዎች እኔ ግድ የለኝም። እኔ አሁን ማወቅ የምፈልገው በእግዚአብሔር ቤት ቦታ ይኖረኝ እንደሆነ ነው» ብለው መለሱ።

ዋንዳር አይኖቹ በደስታ እየተንጸባረቁ በፍጥነት ተነስቶ በእግሩ ቆመ። «ላባኒያ ጎዶ በሌሊት መጥቶ በኢየሱስ እግር ሥር ስለወደቀው ነገር ታሪክ ከመጽሐፉ አንብብልን። ዳናም እንደዚያ ሊያደርጉ ይፈልጋሉ» ሲል ተናገረ።

በዚህ ዓይነት በዚያን ሌሊት፥ ባለብዙ ባሪያና ብርቱ ባላባት የነበሩት ዳና ማጃ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥተው እርሱን አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ።

ዳና ማጃ ወደ ጌታ የመጡት በወላይታ እንደሚባለው በሁለቱም እጆቻቸው በሙሉም ልባቸው ነበር። በተፈጥሮአቸው መሪ በመሆናቸው ለኃላፊነት የተገቡ ነበሩ። ሰዎች ከፍተኛ እምነት ስለጣሉባቸው መሪነታቸውን በደስታ ነው የተቀበሉት።

በ1929 ዓ.ም. ከማመናቸው በፊት ከሚስዮናውያን ጋር ያደረጉት ግንኙነት በጣም ትንሽ ነበር። ያመኑት በዋንዳር ምስክርነት መሆኑን ራሳቸውም ይናገራሉ። ሚስዮናውያኑ አማኙ ዳና ማጃን ሳያዩዋቸውና ሳያውቋቸው ሀገር ለቀው ወጡ። ስለሆነም እግዚአብሔር ካለምንም የውጪ ርዳታ ወይም በጥቂት የውጪ ርዳታ በጥቂት ተራ ክርስቲያኖች አማካይነት ለሠራው ሥራ ዳና ማጃ ቋሚ ምልክት ናቸው። እነዚህ ክርስቲያኖች በጣም አነስተኛ ትምህርት ቢኖራቸውም በነበራቸው ሁሉ ታዝዘዋል።

ዳና ማጃ የመላው ወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪና ኃላፊ ሊሆኑ ነው።

# ክፍል ሁለት፡- እሳቱ ተለኮሰ

## ምዕራፍ 3. የተገለጡ ምስጢሮች

መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ።

ኢሳ. 30፡21

በ1920 ዓ.ም. መጋቢት ወር ዕቃ የተጫነባቸው የብዙ እንስሳት ሰልፍ የአዲስ አበባን መሬት ለቅቆ ጉዞ ጀመረ። መንገድ የሚባል ነገር ስላልነበረ ለተጓዡ የተወሰነ መሪ መስመር አልነበረውም። ከከተማው ወጥቶ ወደየትኛውም አቅጣጫ ለመሄድ ጠባብ የእግር መንገዶችን በመከተል ተራሮችንና ኮረብታዎችን እየተጠማዘዙ ሣርማ ሜዳዎችንም እያቋረጡ መጓዝ

ያስፈልጋል። እነዚህ መንገዶች ለብዙ ዓመታት ብዙ ሰዎች፥ በቅሎች፥ ፈረሶችና አህዮች የተጓዙባቸው ናቸውና።

ጉዞው የተመራው በዶክተር ቶማስ ላምቤ ሲሆን ዓላማው በምዕራብ ኢትዮጵያ ጂማ ከተማ ለመድረስ ነበር። ዶክተር ላምቤ የህክምና ዶክተርና የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው ሚስዮናዊ ከመሆናቸውም በላይ ከመጀመሪያው የሚሲዮን ጓድ ሦስቱ አባላት (ሮውላንድ ቢንግሃም፥ አልፍሬድ ባክስተን እና ራሳቸው) አንዱ ሆነው ለደቡብ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የወንጌልን በር ለመክፈት በቅርቡ ራእይ የመጣላቸው ሰው ነበሩ። ለዚህም ነው በአዲስ አበባ በሆስፒታል ውስጥ የጀመሩትን ሥራ ትተው ወደማያውቁት ቦታ ጉዞ የጀመሩት።

የተጓዡን መስመር ከፊት ጫፍ ሆነው የኋላውን ጫፍ (መጨረሻ) ማየት ያዳግት ነበር። ሩብ ማይል ያህል ርዝመት ባለው በዚሁ መስመር ውስጥ ስድሣ አምስት በቅሎች፥ ሃያ አህዮች፥ ዘጠኝ ፈረሶች፥ በራሳቸው ዕቃ የተሸከሙ ሃያ አምስት፥ በቅሎችን የሚነዱ ሃያ ሁለት እና ሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚያበረክቱ ሰዎች ነበሩበት። በበቅሎችና አህዮች የተጫኑት ድንኳኖች፥ የሸራ አልጋዎች፥ ስንቅና የግል መገልገያዎች ነበሩ። በእንስሳቱ ላይ ዕቃዎቹን የሚጭኑት ለጓሚዎች ወይም ጫኞች ሲሆኑ የሚሰበሩ ወይም በእንስሳት ሊጫኑ የማይችሉትን ሰዎች እንዲሸከሟቸው ተደርጓል። ዘጠኙ ፈረሶች ዶክተር ላምቤና አብረዋቸው የሚጓዙ ሚስዮናውያን የሚቀመጡባቸው ነበሩ። እነዚሁ ሚሲዮናውያን ሚሲስ ላምቤ (የዶክተር ላምቤ ባላቤት)፥ ሴት ልጃቸው ቤቲ፥ ሚስተር ጆርጅ ሮድ፥ ባለቤታቸውና ትንሽ ልጃቸው ጆርጅ፥ እና ሦስት ያላገቡ ሰዎች ነበሩ። እነዚህን ሦስቱን ዶክተር ላምቤ አንዳንድ ጊዜ ሲ.አ.ዲ ልጆች ብለው የሚጠሯቸው ሲሆን ስሞቻቸው ግለን ኮይን (ሲ)፥ ዋልተር ኦህማን (አ) እና ክላረንስ ዱፍ (ዲ) ይባላል።

ጂማ ከአዲስ አበባ ሁለት መቶ ማይል ያህል ይርቃል። ቡድኑ በቀን ጉዞው አሥራ ስምንት ማይሎችን መሸፈን ቢችልም በዚህ ፍጥነት የተጓዘባቸው ቀናት ጥቂት ናቸው። የሚመራቸው ኢትዮጵያዊ በሀገሩ እርሱ የማያውቀው መንገድ እንደሌለ አረጋግጦላቸው ነበር። ነገር ግን ከጥቂት ቀናት ጉዞ በኋላ ዶክተር ላምቤ ቡድኑ ወደ ጂማ ሳይሆን ቀጥታ ወደ ደቡብ እየመራ መሆኑን ተገነዘቡ። ቢሆንም ጉዞው በያዙት መንገድና አቅጣጫ እንዲቀጥል ወሰነው በመጨረሻ ከምባታ አውራጃ ደረሱ። ወደ ምዕራብ የሚያስኬደውና ወደ ደቡብ የሚመራው መንገድ የሚለያየው በዚሁ ሥፍራ በመሆኑ ቡድኑ የምዕራቡን መንገድ በመከተል የኦሞን ወንዝ አቋርጦ ወደ ጂማ ሊደርስ ይችላል።

በከምባታ ዶ/ር ላምቤ የአውራጃው ገዥ የነበሩትን ደጃዝማች መሸሻን አገኙአቸው። ደጃዝማች መሸሻን ዶ/ር ላምቤ በምዕራብ ኢትዮጵያ (ወለጋ) በሚኖሩበት ጊዜ ያውቋቸው ነበር። በተለምዶ እንግዳ ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ዶ/ር ላምቤና ቡድናቸው በሆግዕና የእረፍት ቀይታ

እንዲያደርግና የአገር ገዥውን እንዲገበኝ ተማፀኑ። የሕክምና ዶክተርነታቸው ገንኖ በሰፊው ተወርቶ ስለነበረ በዚህ መስከ የሚፈለጉበት ብዙ ሥራ ከመኖሩም በላይ የገገርው ቤተሰብም እርዳታቸውን ይሻል። ደጃዝማች መሸሻም ዶ/ር ላምቤ በካምባታ ቢቆዩና ክሊኒክ ቢያቋቁሙ በጣም ደስ እንደሚላቸው ቢገልጹም ዶ/ር ላምቤ «አይሆንም፥ የሥራ ፈቃዳችን ለጂማ ነው» በማለት ደጋግመው አስረዷቸው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በየትም ሥፍራ እንዲሠሩ የሚያስችላቸው ፈቃድ አልነበራቸውም። ከአዲስ አበባ እንዲወጡ የተፈቀደበት ደብዳቤ የጉዞአቸው ዓላማ ጥናታዊ ጉብኝትና «አየር እንዲወስዱ የተፈቀደ» መሆኑን ይገልጻል። በሆሳዕና ሳሉ ዶ/ር ላምቤ የወላይታ ገዥና ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ወዳጃቸው የሆኑት ደጃዝማች ይገዙ መታመማቸውንና የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ሰሙ። ከዚህም የተነሣ ጉዞአቸውን ወደ ደቡብ በማቅናት ከብዙ ቀናት በኋላ የወላይታ አስተዳደር ማዕከል ወደሆነችው ሶዶ ከተማ ገቡ። የመምጣታቸው ወሬ ቀድሞአቸው ተሰምቶ ነበርና ሶዶ ሲገቡ ለድል አድራጊ ሠራዊት የሚደረግ ዓይነት አቀባበል ተደረገላቸው።

የወላይታ ገዥ ዶ/ር ላምቤና ሰዎቻቸው በግዛታቸው እንዲቆዩና እንዲሠሩ ጋበዟቸው። በአውራጃዎቹ ምንም ዓይነት የሕክምና እርዳታ ማግኛ ያልነበረ በመሆኑ አስተዳዳሪዎቹ ዶ/ር ላምቤን የመሰለ ብቁና ትሁት ሰው በአካባቢያቸው እንዲቆይ መፈለጋቸው አያስደንቅም ነበር። በተጨማሪም ደጃዝማች ብሩ የተባሉ ሌላ ባለሥልጣን የጎረቤት አውራጃ ማለትም የሲዳማ ገዥ ሆነው እንደሚሠሩ ሚሲዮናውያኑ አወቁ። በኢትዮጵያውያን ባሕልና ትህትና መግለጫ መሠረት ዶ/ር ላምቤን የመሰለ ክቡር እንግዳ ወደ አካባቢው ሲደርስ የገዥውን ቢሮ ያለመጎብኘትና ለባለሥልጣኑም እጅ ሳይነሱ መቅረት ያልተለመደ ነበር። ስለዚህም የይርጋለም ጉዞ ብዙ ቀናት የሚጠይቅ በመሆኑ ሌሎቹ ሶዶ እንዲቆዩ ተደርጎ ዶ/ር ላምቤና ክላረንስ ዱፍ ጉዞ ጀመሩ። ይርጋለም ከሶዶ በስተምሥራቅ ርቆ የሚገኝና የሲዳማ አውራጃ ዋና ከተማ ነበር። እነዶ/ር ላምቤ እዚያ እንደደረሱ ገዥው ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉላቸው፥ ስጦታም አምበሸበሹላቸው። በተጨማሪም በዚያ እንዲቀሩ ለመኗቸው።

ሚሲዮናውያኑ አዲስ አበባ ከመልቀቃቸው በፊት ራስ ተፈሪ (በኋላ ንጉሥ ሆነው ኃይለ ሥላሴ የተባሉት) ከሚሲዮናውያኑ ጋር ባደረጉት ውይይት ከአዲስ አበባ ውጭ ሚስዮን ለማቋቋምና ለመሥራት ሙሉ ፈቃድ መስጠት የማይችሉ፥ ነገር ግን በጉዞአቸው ላይ የሚያገኙአቸው ገዥዎች (ወይም አስተዳዳሪዎች) ይህንን ከፈለጉ ከፈቀዱና ቦታ ከሰጧቸው እሳቸው እንደማይቃወሙ ገልጸውላቸው ነበር። የገዥዎቹ የተደጋገመ ጥሪና ጥያቄ ከራስ ተፈሪ አገላለጽ ጋር ሆኖ ሲገመገም ምናልባት እግዚአብሔር በአስደናቂ መንገድ የሥራ ፈቃድ እንደሚገኝ ለጊዜው ማረጋገጥ ወደማይችሉበት ወደ ጂማ ከመሄድ ይልቅ በነዚሁ አካባቢዎች እንዲቆዩ እየመራቸው ሊሆን እንደሚችል አሰቡ።

ሚሲዮናውያኑ በወላይታ ለመቆየት በመወሰናቸው የወላይታ ገዥ እጅግ ተደሰቱ። እሳቸውም ከሸለቆው አልፎ የሚታይ ከዳሞት ተራራ በታች የሚገኘውን ውብ ኮረብታማ ቦታ ለዶ/ር ላምቤና ለሚስተር ሮድ አሳዩአቸው። ቦታው ጥሩ ውሃ ያለበት በመሆኑ የሚሲዮኑ ጣቢያ እንዲሆን ሀሳብ አቀረቡ። አስቀድመው ለመድረስ ያቀዱት ሥፍራ ጅማ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በኃይሉ ወደ ወላይታ ያመጣቸው በመሆኑ በእርሱ የነበራቸው ፅናትና እምነት በየዕለቱ ያድግ ነበርና እንደሐዋርያው ጳውሎስ እነርሱም «ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደጠራን መስሎናልና» አሉ (ሐዋ. ሥራ 16፡ 10)።

በአንድ በኩል በሶዶ (የአስተዳደሩ ማዕከል እንድትሆን በተቆረቆረች ከተማ) ካሉት ዋናው ገዥና ከጽ/ቤታቸው በሌላ በኩል የሚሲዮኑ ጣቢያ የሚሠራበት መሬት ባለቤት ከሆነው የወላይታ ሕዝብ ተቀባይነት አገኙ። ምንም እንኳን የወላይታ ገዥ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባልና የተማሩ አማራ፥ የሚስዮኑ ቡድን እንዲቆይ የጠየቁና መሬትም የሰጡ ቢሆንም ሚሲዮናውያኑ የሚያገለግሉትና የሚሠሩት በአማራዎቹ መካከል ሳይሆን ቋንቋቸው በጽሑፍ ባልዋሉባቸው የወላይታ ሕዝብ መካከል ይሆናል።

በዳሞት ተራራ ግርጌ ከሶዶ አንድ ማይል ርቆ ወላይታዎች ኦቶና ብለው በሚጠሩት ቦታ ጣሪያቸው በሣር የተከደኑ ብዙ ቤቶች በጭቃ ተገንብተው ተሠሩ። (በዝናብ ወራት ከጭቃው ልስን ውስጥ ሣር ያቆጠቁጥ ነበር) ደግሞ ባልሆነ ጨርቅ በመጋረድ ክፍሎቹን ከመጋለጥ ማዳን በመጠኑ የተቻለ ይሁን እንጂ መስኮቶቹ መስታወት አልነበራቸውም። መጋረጃዎቹ ዓመቱን በሙሉ ሌሊት ለአሥራ ሁለት ሰዓታት የሚነፍሰውን ቀዝቃዛ ነፋስ ለመከላከልም ብዙ አልረዱም። የሶዶ ከተማ በሰባት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ በመሆኑ ሌሊቱ ይቀዘቅዛልና።

ክፍሎቹ አንዱ ከሌላው በደንብ ያለመለየታቸው ሚስዮናውያኑ ከወላይታ ሰዎች አስደሳችና ጥሩ መግባቢያ የሆነ ቋንቋቸውን እንዲማሩ ረድቷቸዋል። በአቋማቸው ቀጠን፥ በቆዳቸውም ቀለም ጠቆር ያሉ ወላይታዎች ከሚሲዮኑ ግቢ በብዛት በመምጣት የሚስዮናውያኑን እንቅስቃሴ አንድ በአንድ በጥንቃቄ እየተመለከቱ በአድናቆት እርስ በርሳቸው ይነጋገራሉ፥ ይጠያየቃሉ። የማጥኖችና ሻንጣዎች እሽግ እየተከፈተ ከውስጣቸው አዳዲስና የተለየ ዕቃ በወጣ ቁጥር «ሃጌ አይቤ! ሃጌ አይቤ!» እያሉ ቅንድቦቻቸውን ወደላይ ሰበው ዓይኖቻቸውን እየከፈቱና ግንባራቸውን እየቋጠሩ ይደነቃሉ።

በዚያን ጊዜ ወላይታዎቹ ስለ እያንዳንዱ ዕቃ «ይህ ምንድነው?» እያሉ የሚጠይቁ መሆናቸውን ሚሲዮናውያን ተረዱ። ራሳቸውም ወደየዕቃው እያመለከቱ «ሃጌ አይቤ» በሚሉበት ጊዜ የዕቃው ስም በወላይትኛ እየተነገራቸው ጠቅላላ የስም ዝርዝር ተዘጋጀ።

ዋልተር እህማንና ክላረንስ ዱፍ በየቀኑ የወላይታዎችን ቤት ይጎበኙሉ፥ አብረዋቸው በመቀመጥ ምንም እንኳን ቋንቋው ባይገባቸው የሚሉትን ያዳምጣሉ። ነገር ግን አፍሪካውያኑ (የወላይታ ሰዎች) ቋንቋቸውን ለሚማሩ (እንዲማሩ) በመጨነቅ ቀስ እያሉ ቀለል ያሉ አባባሎችንና አረፍተ ነገሮችን ይደጋግሙ ነበር። ማታ ማታም ሁለቱ ፈረንጆች ቀን ቀን በማስታወሻ የያዟቸውን አዳዲስ ቃላትና አረፍተ ነገሮችን ያጠናሉ፥ ይከልሳሉ።

ተራ ሰዎች እንደሚሉት ሳይሆን የጎማ ቋንቋዎች ግልጽ የሆኑ ሕጎችና ሰዋስው አላቸው። ጎማው (ወይም ማህበረሰቡ) ከሌሎቹ የሀገር ክፍሎች ተለይቶ የሚኖር ወይም የማይገናኝ በሚሆንበት ጊዜ ቋንቋው ያልተቀላቀለና የተለመደ ይሆናል። በወላይታም ስለ ቋንቋው ሰዋሰዋዊ አተነባበር መጠየቅ የማይቻል ነበር። ሚስዮናውያን በቋንቋው ከሌላው ጋር መነጋገር ቢችሉም የሚያነጋግራቸው የወላይታ ሰው የራሱን ቋንቋ ሰዋስው ሳያውቅ የኖረ በመሆኑ ሕጉንም መግለጽ አይችልም ነበር። ቋንቋውን ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ የተማሩት በመሆኑ ለምን በዚህ አኳኋንና መልክ እንደሚናገሩ ሳያውቁ ግን በትክክል ሲናገሩና ሲግባቡ ኖረዋል።

የወላይታ ቋንቋ ምስጢር በጥረት፥ በትዕግሥት በመማርና በፀሎት ቀስበቀስ ተገለጠ። ሚሲዮናውያንም ቋንቋው በያዘው መልክ የሚነገርበትን ምክንያት ከማወቃቸው በፊት ቀለል ባሉ ዓረፍተ ነገሮችና አባባሎች ሰዎችን ማነጋገርና መልሳቸውንም መስማትና መረዳት ቻሉ።

የሕንፃ ሥራ ነሐሴ 1920 ዓ.ም. ሲያልቅ ከአንድ ወር በኋላ ከላረንስ ዳፍ ከከምባታ ሕዝብ ጋር ለመሥራት ሶዶን ለቆ ሄደ። ቀደም ሲል ግለን ከይን ከዶ/ር ላምቤ ጋር በሲዳማ ሥራ ለመጀመር ሄደው ነበር።

# ምዕራፍ 4. ምቹ አጋጣሚዎች

. . . ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን
ለማስፋፋት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።
ፊልጵስዩስ 1፡12

«የዚያ ሰው ስም ማን ነበር ያልሽኝ?» ብለው ጠየቁ አሮጊቷ ከሚስዮናዊቷ ሴት ጋር ቆመው በጉጉት ፊቷን እየተመለከቱ።

«ስሙ ኢየሱስ ነው»

«በስሙ ብናምን እርሱ ይረዳናል ብለሽኛል አይደል?»

«አዎን በእርሱ ቢያምኑና ስሙንም ቢጠሩ እርስዎ ይድናሉ።»

ሰልማ በርግስተን በቅሎዋ ላይ ወጥታ ወደ ቤትዋ መንገድ ጀመረች። ጥቂት እንደሄደች በኋላ ድምፅ ስለሰማች በኮርቻ ላይ እንዳለች ዞራ ብትመለከት አሮጊቷ እየሮጡ ሲከተሏት አየች።

«እባክሽን ታገሽኝ፥ የነገርሽኝን ማስታወስ አልቻልኩምና እንደ ገና ብትነግሪኝ ስሙ ማን ነበር?»

ሚስዮንዋ እንደገና ነገረቻቸው። እየመሸባት ስለሆነ ፈጥና ከቤትዋ ለመድረስ በቅሎውን በተረከዝዋ እየኮረኮረች ጉዞዋን እንደገና ጀመረች።

«ቆዩ ቆዩ ቆዩ! ልጇን ልጥራው። እኔ ስላረጀሁ ቶሎ እረሣለሁ። አንዱ ልጄን ልጥራው። የኢየሱስን ስም ለመጥራት በምፈልግበት ጊዜ ልጄ እንዲያስታውስ ይረዳኛል።»

ሰልማ በርግስተን ሶዶ የመጣችው በ1921 ዓ.ም. ከሚስተር ኤርል ሉዊስ (ከባለቤቱ ጋር) እና ከነርሷ ሩት ብሬይ ጋር ነበር። ወላይታዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ምሥራቹን ከወንጌል ሲሰሙ አፀፋውን የሚገልጹት በዚህ (አሮጊቷ ባሳዩት) ዓይነት ድርጊት ነበር። ከእነርሱ ማንም አስቀድሞ ወንጌልን የሰማ አልነበረምና ለብዙ ዘመናትና ትውልድ እንዳለፉት ቀደምት አባቶቻቸው በፍርሃትና በጣዖት አምልኮ ይኖሩ ነበር። ስለሆነም የጋረዳቸውን ጨለማ በወንጌል ብርሃን ለመግፈፍ የነበረው ብቸኛ መንገድ የሚሲዮናውያን ወደዚያ መሄድና ወንጌልን መመስከር (መስበክ) ነበር።

ወዲያው ለመንግብኘትና ሰዎችን ለማነጋገር የሚያመቸው በለቅሶ ጊዜና ቦታ መሆኑ ለሚሲዮናውያን ግልጽ ሆነ። ለቅሶ በወላይታ ሕዝብ ሕይወት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ ነውና። አንድ የወላይታ ሰው ዘመዱ፥ ወዳጁ ወይም ደግሞ በሌላ መንገድ የሚያውቀው ሰው ቢሞት ብዙ ማይሎች ርቀት በእግሩ ተጉዞ ለለቅሶው መድረስ የተለመደ ነገር ነው። በሚሲዮን ጣቢያም ሆኖ ከሩቅ የለቅሶ ዋይታና ዝማሬ ሁልጊዜ ይሰማ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ማታ ሁለት ሴት ሚስዮናውያን የአካባቢውን ነዋሪ እንቅስቃሴና ሁኔታ ሲመለከቱ ለቅሶ ያለ ስለመሰላቸው ሐዘናቸውን ለመግለጽ አራትና አምስት እየሆኑ ተቀራርበው ወደተሠሩት የመኖሪያ ቤቶች አመሩ። ወደ አንዱ ቤት ተጠግተው ሲመለከቱ ብዙ ሰዎች ያለቅሳሉ። ወደ ትልቅ ሣር ቤት ውስጥ እንዲገቡና በክብር ቦታ እንዲቀመጡ ተደርጎ ሲያስተዛዝኑ ቆዩ። የሞተው ሰው ሳይሆን ላም መሆኗን ሲያውቁ ግን በጣም ገርሟቸው ነበር።

ሁለቱ ሴቶች በቂ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ለመውጣት ሲዘጋጁ ምግብ እየተዘጋጀላቸው መሆኑ ተገለጸላቸው። ጊዜው የመሸ በተለይም ጎጆው ውስጥ በጣም የጨለመ ከመሆኑ የተነሣ ሊበሉት ያለውን ምግብ እንኳን መለየትና ማየት አይቻልም ነበር። በዚህ ብቻ አላበቃም። የወላይታ ሰዎች በጣም እንግዳ ወዳድ ስለሆኑ ለሚሲዮን እንግዶቻቸው ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ለማሳየት ምግብ በእጃቸው አንስተው ያጉርሱዋቸው ነበር። ሚሲዮናውያኑም አለመጣፈጡን ብቻ ሳይሆን የሚበሉት ምን እንደሆነ አያውቁም ነበር።

በኋላ ግን የበሉት ቆጮ (እንሰት) መሆኑን አወቁ። ቆጮ ከወላይታ ዋና ምግቦች አንዱ ነው። ቆጮ ለማዘጋጀት የእንሰቱ መካከለኛውና የታችኛው አካል ተፍቆ መሬቱ ተቆፍሮ በተዘጋጀ ማከማቻ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ይህ ማከማቻ እንደማቀዝቀዣ የሚቆጠር ነው። ከዚያም ሴቶች በባዶ እግር ረጋግጠው ካደቀቁና ከቀላቀሉት በኋላ በኮባ ተሸፍኖ ለወራት ማከማቻው ውስጥ እንዲቆይና እንዲቦካ ይደረጋል፣ በደንብ የበሰለ (የቦካ) መሆኑ ሲረጋገጥ ተቆርጦ ይጋገራል።

አብዛኞዎቹ ሚሲዮናውያን ቆጮውን ጣፋጭ ሆኖ አላገኙትም። ነገር ግን በወላይታ ሰዎች መልካም ጠባይ፣ ፍቅርና እንግዳ አቀባበል ልባቸው ተማረከ። ሚሲዮናውያን ከወላይታዎች ጋር በወላይታ ቤት ውስጥ ሆነው የወላይታን ምግብ ለመመገብ ፈቃደኛ መሆናቸው የመጡበትን የወንጌል መልዕክት ለማሰማት የሰዎቹን ልብ ለመክፈት ጠቃሚ ነበር።

«ቀድሞ እንኖር የነበረው በስተምዕራብ አሞ ወንዝ አጠገብ ኪንዶ በሚባለው ቦታ ነበር። ያኔ ቁጥራችን ጥቂት ነበር ነገር ግን በኋላ በቁጥር አደግን። በኋላም ብዙ ልጆች ያሉት ንጉሥ መጣ። እርሱም ልጆቹ አዳዲስ መሬቶችን (ግዛቶች) እንዲይዙ እና እንዲገዙ ላካቸው። ልጆቹም መሬቶቹን ኩሎ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ሌላ ሌላም እያሉ በየራሳቸው ስም ጠሯቸው። ከተወላጆቻቸው የተለያዩ የወላይታ ቋንቋ ያነጋገር ስልቶች ተፈጠሩ።

«ሶዶ? ሶዶማ የማራቆች ነበር። ማራቆ ለሐዲያ ብሔረሰብ የተሰጠ የወላይታ አጠራር ነው። የንጉሡ ታላቅ ልጅ ዳሞቴ ሲሆን እርሱም ከአባቱ በኋላ በኪንዶ የወላይታ ንጉሥ ሆነ። ዳሞቴ የወንድሞቹን አዳዲስ አገሮች በአንድ ላይ አዋህዶ አንድ ትልቅ መንግሥት ከመመሥረቱም በላይ ግዛቱን ለማስፋፋት ከኪንዶ ብዙ ወታደሮችን ይዞ ወደ ምሥራቅ በመዝመት ማራቆችን ከሶዶ ከአቶናና ከዳልቦ አባረራቸው። ምሽጉ አድርጎ የተጠቀመው ይህ ከአቶና በላይ የሚታየውን ተራራ ነበር። በኋላም ተራራውን በስሙ ዳሞታ ተራራ ብለው ሰየመው።

«በኋላም ከሶዶ በስተምሥራቅና በዓባያ ሐይቅ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሲዳማዎችና የአርሲ አርሞች ወደ ሲዳማና ቢላቴ ወንዝ ማዶ ተባረሩ።

«ይህ የተፈፀመው ከብዙ ትውልድ በፊት ቢሆንም የንጉሥ ዳሞቴ መቃብር በኪንዶ አሁንም አለ። የክብር ቦታ በመሆኑ ጦርና ጋሻ የያዙ ወታደሮች መቃብሩ ያለበትን ትልቅ የጭቃ ቤት በየማዕዘናቱ ቆመው ቀንና ሌሊት ይጠብቁታል» እያሉ ታሪካቸውን ይነግሯቸው ነበር።

*　　　*　　　*

የቋንቋ ችሎታቸው በማደጉ ዋልተር አህማንና ኤርል ሉዊስ በሶዶ አካባቢ ባሉ መንደሮች ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ወዳጅነት መፍጠር ቻሉ። የወላይታ ሕዝብ በርኩስ መንፈስና ሰይጣን አምልኮ በመዘፈቅ እግር ተወርች ታስሮ ቢቆይም ከመጀመሪያ ጀምሮ ለወንጌል ያላው ግምት አዎንታዊ ነበር። አብዛኛውም ሕዝብ ርኩስ መናፍስት፥ ጠንቋዮችና ቃልቻዎች ዕለታዊ ኑሮውን ስለሚቆጣጠሩት በፍርሃት ይኖር ነበር።

አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስን ለመከተል ሲወስኑ ተቃውሞ የተነሳባቸው በመሆኑ ከእነርሱ ጋር ወዳጅነት የመሠረቱ (እና ወንጌልን አምነው የተቀበሉ) ሰዎች ቀስ በቀስ ግንኙነታቸውን እያላሉ መምጣታቸውን ሚሲዮናውያኑ ተገነዘቡ። በኋላ ሊታወቅ እንደተቻለው በአካባቢው ያለ ታዋቂ ቃልቻ ሰዎች ወደ ሚሲዮናውያን እንዳይመጡ ይከለክላቸው ነበር። ቃልቻው ሚሲዮናውያን አራት ዓይን ያላቸውና ወላይታዎችን እየበሉ ደማቸውን ወደ ሀገራቸው የሚልኩ ናቸው በማለት ሕዝቡን ያሳስት ነበር። አራት ዓይን አላቸው ያለው ሚስተር ሉዊስ መነጽር ማድረጉን በማየቱ ነበር።

የተቃውሞ አነሣሥ በዚህ መልክ መሆኑን እንደተረዱ ዋልተር አክማንና ኤርል ሉዊስ ወደ አሳሳቹ ሰው (የቃልቻው ረዳት) ሄደው «ወደ ቤታችን መጥተህ ውስጡንና ያለንን ሁሉ ፈትሽ» አሉት። ሰውየው በጣም በመፍራት ለመሄድ ያልፈለገ ቢሆንም እንደምንም አድርገውና አባብለው ወሰዱት። በጣም እየፈራና እየተንቀጠቀጠ ሄዶ ቤት እንደገባ ምግብ አቀረቡለት፥ በቤታቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች፥ በአልጋዎቻቸው ሥር፥ በሣጥን ውስጥ . . . ወ ዘ ተ ምንም የሚያስፈራ ነገር እንደሌለ አሳዩት። እርሱ የሚሲዮናውያንን ቤት መጎብኘቱ የብዙዎችን ጥርጣሬና ፍርሃት አስወገደው።

መወገድ ያለባቸው ሌሎች እንቅፋቶችም ነበሩ። የወላይታ ቤቶች አንድ በር (በፊት በኩል) ብቻ አላቸው። ሚሲዮናውያኑ ዞረው ሰዎችን በሚጎበኙበት ጊዜ አንዳንድ ቤቶች የተለዩ (ሁለት በሮች ከፊትና ከኋላ ያላቸው) ሆነው አገኟቸው። እነዚህ የሰይጣን ቤቶች ተብለው መታመናቸው ወላይታዎች ሚሲዮናውያንንና ቤቶቻቸውን የሚፈሩበት ሌላውን ምክንያት የሚያስረዳ ሆነ። የሚስዮን ቤቶች ሁለት በሮች (ከፊትና ከኋላ) ያላቸው በመሆኑ ይህም ቃልቻው ከነገራቸው ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ሰዎቹ ይበልጥ እንዲጠረጥሩ አደረጋቸው።

የሰይጣን አምልኮ በወላይታዎች መካከል የተለመደ ሆኖ የራሱ የሆነ የአመላለክ ሥርዓት ነበረው። የተለያዩ መስዋዕቶች ያሉበት ሲሆን ሥርዓቱ በአብዛኛው የብሉይ ኪዳንን ይመስላል። በዓመቱ መጀመሪያ ቀን በትንሹ

የአይሁድ ፋሲካ የመሰለ ክብረ በዓል ይከበራል። መስዋዕቱ ግን ለእግዚአብሔር በመሆን ፋንታ ለሰይጣን ይሆናል። በሬ ለመስዋዕት ከታረደ በኋላ ሥጋው ከአንድ ወገን (ጎሣ) ለሆኑ ለአራት ወይም አምስት ቤተሰቦች ይከፋፈላል፥ ደሙ በቅል ወይም በገበቴ ተይዞ በመቃንና ጉበን (በበር) ይረጫል፥ በቤተሰቡ አባላት በግንባራቸው መሐል በደም ነጥብ ይደረግባቸዋል፥ ሥጋውም ከያንዳንዱ ዓይነት ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እንዲደርሰው ይደረጋል። በመጨረሻም ምሽቱ ሲደርስ የቤተሰቡ (የጎሣው) መሪ ተንበርክኮና እጆቹን ወደላይ አንስቶ ለሰይጣን ፀሎት ያደርሳል፥ ከዚያ በኋላ ግብዣ ይበላል፥ ግብዣውም ጥሬ ሥጋ ይሆናል።

* * *

«ውሃ የሚቀዳላችሁ ማንነው?» ብለው ጠየቋቸው ሠራተኞቹ።

«ራሳችን» ብሎ ኤርል ሉዊስ መለሰ።

«አትክልታችሁን የሚኮተኩት፥ ከብቶቻችሁን የሚጠብቅ፥ ምግብ የሚሠራላችሁ ማንነው?»

«እኛም እነዚህን መሥራት እንችላለን፥ እስካሁንም ስንሠራ ቆይተናል። እናንተ ብትሠሩ እኛ የምንከፍለው ገንዘብ ስለሌለን ራሳችን ደስ ብሎን እነዚህን እንሠራለን። በርግጥ ሥራዎቹ ብዙ ጊዜ የሚወስዱብን በመሆኑ ስለ ኢየሱስ ለሰዎች ለመመስከር ጊዜ ስለሚያንስብን እናዝናለን።»

በ1921 ዓ.ም. የተከሰተው የኤኮኖሚ ቀውስ በዓለም ዙሪያ በሚኖሩ ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ነበረው። ሚሲዮኖች ሁሉ በኢትዮጵያ ያሉትም ጭምር የሚያገኙት ድጋፍ በአብዛኛው ቆመ። በቂ ገንዘብ እስከሚገኝ ሥራው እንዲቀነስ፥ ተጨማሪ ሠራተኞች እንዳይላኩና እንዳይሠማሩ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሚሲዮናውያኑ በአሉታ መለሱ። ያላቸውን ሁሉ ከሌሎች ጋር ለመካፈል ደስተኞች ከመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያቀርብ እምነት ነበራቸውና።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለብዙ ወራት ገንዘብ ሳይላክ ቆየ። ሚሲዮናውያን ሠራተኞችን ማግኘት አስቸጋሪ እንደነበር ስለሚያውቁ እያንገራገሩ ችግሩን ለሠራተኞች ለማሳወቅ ወሰኑ። እነዚሁ የወላይታ ሰዎችና ወጣት ሠራተኞች በሚሲዮን ቤቶች ጓሮ ያሉትን እርሻዎች እያረሱ አትክልቶቻቸውንም እየኮተኮቱ ለባላባቶች ግብር መክፈያ የሚውል ገንዘብ ያገኛሉ። ሠራተኞቹ በበጋ ወራት ማለትም በራሳቸው እርሻ ዘር ከዘሩበት አንስቶ ያንን እስከሚሰበስቡበት ጊዜ ድረስ በሚሲዮኑ ተቀጥረው ለመስራት የሚገኙ ሲሆን ለእርሻቸው በሚፈለጉበት ጊዜ ግን ከወጣቶች በቀር ሌሎችን ማግኘት አስቸጋሪ ነበር። ሚስተር ሉዊስና ሌሎችም ራሳቸው ያለምንም ገንዘብና ወደፊትም ገንዘብ የማግኘት ተስፋ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ቢሆንም ወላይታዎቹ «በእምነት» እንዲሠሩላቸው መጠየቅ የሚከብድ መሆኑ ታያቸው። ስለሆነም የሚከፈል ገንዘብ ስለሌለ ከወሩ መጨረሻ አንስቶ አገልግሎታቸው የማይቀጥል መሆኑ ለሠራተኞቹ ተነገራቸው።

ግስታወቂያው ሠራተኞቹን በጣም አስደነቃቸው። እስካሁን ሚስዮናውያን የሚሠሩት በመንግሥት እርዳታና ክፍያ ያለመሆኑን ማመን አቅቷቸው ነበር። (አገረ ገዥው ሚሲዮናውያኑን በአካባቢው እንዲሠሩ በመጠየቃቸው፥ በመፍቀዳቸውና ለጣቢያውም መሬት በመስጠታቸው ሕዝቡ ሚሲዮናውያን በመንግሥት ድጋፍ ይሠራሉ ብሎ ቢያምን አያስደንቅም) አሁን ግን በመገረም እርስ በርሳቸው ተያዩ፥ ሚስዮናውያኑ የነገሩዋቸውን ሁሉ ለማመን ተገደዱ። ከዚያን በፊት እንደሰሙት ሁሉ ሚሲዮናያን የሚሠሩት (የሚያገለግሉት) እግዚአብሔር ልኮአቸውና በሀገራቸው ያሉ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ገንዘብ እየላኩላቸው መሆኑን አመኑ።

የወሩ መጨረሻ በደረሰ ጊዜ ሠራተኞቹ የአገልግሎታቸው ዋጋ ተከፈላቸው፥ እግዚአብሔር በቂ ገንዘብ ሲልክ (ሲሰጥ) ግን በድጋሚ ለሥራው እንደሚጠሩ ተነገራቸው። ሰዎቹ ግን (ሠራተኞቹ) ፈንጠር በማለት ለብቻቸው በዝቅተኛ ድምፅ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ ተመልሰው በወኪላቸው አማካይነት «እኛ ትተናችሁ አንሄድም፥ ሥራችንን እንቀጥላለን፥ ለአገልግሎታችን ምንም አናስከፍላችሁም፥ እኛ ገንዘብ አንፈልግም» ብለው መለሱ።

«የለም! የለም! እንደዚያ እንድታደርጉ አንፈልግም»።

«ግድ የለም! እንሠራላችኋለን፥ በወሩ መጨረሻ እግዚአብሔር ገንዘብ ከሰጣችሁ ትከፍሉናላችሁ፥ ያለበለዚያም ምንም ዕዳ አይኖርባችሁም።» ከአንድ ሰው በስተቀር ሁሉም ተስማምተው ወደ ሥራቸው ተመለሱ።

ከዚህ ሁኔታቸውም የተነሣ የወንጌልን መልዕክት ለመስማት ፍላጐት እንዲያድርባቸው ወሳኝ ጊዜ መጣ። በየቀኑ ጧት ጧት በፀሎት ሰዓት እግዚአብሔር ፍላጐቶችን ለማሟላት የሚያስችል ገንዘብ እንዲሰጥ ሠራተኞቹ ይጸልዩ ነበር። የወሩ ቀናት ካለፉ በኋላ ፖስታ (ደብዳቤ) ደረሰ። በዚያን ጊዜ ከሁለት መቶ ሃምሣ ማይል የበለጠ ርቆ ከሚገኘው ከአዲስ አበባ ከተማ ፖስታ የሚመጣው በሰው ራስ ተሸክሞ ተራራውን ወጥቶና ወርዶ በመጓዝ ነበር። ደብዳቤውን የላከችው ሚሲስ ሉዊስን በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ያስተማረቻት አንዲት ሴት ነበረች። በፖስታው (በደብዳቤው) ውስጥ አምስት የአሜሪካን ዶላር ነበረበት። ይህ ገንዘብ በሶዶ ከሚገኙት የሕንድ ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ብር ተለውጦ (ተመንዝሮ) ለሠሩት ሁሉ ለመክፈል በቂ ገንዘብ ከተገኘ በኋላ ጥቂት ተረፈ።

የሆነው ነገር ሁሉ በእነዚሁ ዕድሜያቸው ከስምንት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚሆን የወላይታ ሠራተኞች ላይ ከፍተኛ ስሜት አሳደረ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር ፀሎታቸውን ሰምቶ መልስ ሲሰጥ ማየታቸው ነውና። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሚሲዮናውያን ሥራ ላይ ዝንባሌያቸው በማደጉ ትምህርታቸውንም በፍላጐትና በደስታ ማዳመጥ ጀመሩ።

ነገር ግን በከፍተኛ ፍላጐት ወንጌል የሚሰሙ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ በመጣ ጊዜ በዕድሜአቸው ጠና ያሉ ሰዎችና ሽማግሌዎች ግን «ይህን የማይረባ ነገር እኛ አናምንም አንዳችንም ብንሆን ይህንን አዲስ መንገዳችሁን አንከተልም» እያሉ ያቀሉት ነበር።

በዚያን ጊዜ የሉዊስ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ተወለደ። አፍሪካውያን ልጅ ይወዳሉ። የልጅ መወለድ የእግዚአብሔርን በረከት የሚያሳይ ነው ብለው

ያምናሉ። ሰዎች ከየቦታው ወደ ሉዊስና ባለቤቱ ለሰላምታና የደስታቸው ተካፋይ ለመሆን ቢጎርፉም ደስታቸው ወዲያው ወደ ልቅሶ ተለወጠ። ምክንያቱም ሕፃኑ በሦስተኛው ቀን ሞተ። አሁንም ሐዘናቸውን ለመግለጽ በባህላቸው መሠረት ብዙ ሰዎች ይመጡ ነበር።

ጧት በማለዳ ከሚሲዮኑ ቤት በስተኋላ ትንሽ መቃብር መቆፈር ሲጀመር ግቢው በሰው ተሞላ። በሰዎችም መካከል አስቀድመው ወንጌልን አጥብቀው ይቃወሙ የነበሩ ሰዎችን ስለተመለከቱ ሉዊስና ባለቤቱ ሐዘናቸው ከደስታ ተቀላቀለ። በወላይታ ባህል መሠረት አንድ ሰው የመጨረሻ ጠላቱ ወይም የጠላቱ ቤተሰብ አባል እንኳን ቢሞት በለቅሶው ሥነ ሥርዓት መገኘት አለበት፥ አለዚያ ለሞቱ ምክንያት ከሆነው መጥፎ መንፈስ ጋር ግኑኝነት እንዳለው ይጠረጠራል። ስለዚህ ብዙዎች ወደነሉዊስ የመጡት ከሐዘን ይልቅ ይህንን በመፍራት ነበር።

በለቅሶው ከተገኙት ውስጥ የወላይታ ገገር ካጀቢቸው በመቶ ከሚቆጠሩ ባለሥልጣኖችና ወታደሮች ጋር ይገኙበታል። ገዥው ወደሚሲዮኑ ግቢ ሲቃረቡ ከበቅሎአቸው ወርደው ባርኔጣቸውን በእጃቸው ይዘው ወደግቢው ከገቡ በኋላ ወደ ሚስተር ሉዊስ አመሩ። ሚስተር ሉዊስን በአንዱ እጃቸው ጨብጠው በሌላ እጃቸው አቅፈው ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ «ዳዊት እንዲህ አለ ‹እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም›» ብለው ነገሩት። (በዘራቸው አማራ በሃይማኖታቸው ደግሞ ኦርቶዶክስ በመሆናቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ትውውቅ አላቸው።) ወደ ቤት በመግባትም ሚሲስ ሉዊስን በብዙ አጽናኑአት። የእሳቸው መምጣትና በዚያ መገኘት በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ስሜትን አሳደረ።

ብዙ ሕዝብ ከሩቅና ከተለያዩ የወላይታ ከፍሎች (ወረዳዎች) ከለቅሶው በኋላ እስከ ሰባት ቀናት ድረስ ይመጣ ስለነበረ ለሚሲዮናውያኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ጥሩ አጋጣሚ ሆነላቸው። ለሰው የሐዘን ምክንያት የሆነውን ነገር እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ፍላጐትን ለማስገባት መክፈቻ ቁልፍ አድርጐ ተጠቀመ።

ለቅሶው ካለፈ በኋላ ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ማታ በሚሲዮን ጣቢያ አቅራቢያ በሚገኝ አንድ ቤተሰብ ላይ የሚያሳዝን ድርጊት ተፈፀመ። ባሪያ ፈንጋዮች ቤቱን ሠርስረው መግባታቸውን የቤተሰቡ አባላት አውቀው ከነቁ በኋላ ጮኸው ሲነሡ ወዲያው ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ተገደሉ። ሴቷ የብዙ ልጆች እናት ስትሆን የመጨረሻ ልጅዋ ዕድሜው ከሁለት ዓመት ያነሰ ነበር። ትላልቆቹን ልጆች ዘመዶቻቸው ወሰዷቸው። ትንሹ ግን ከብቶችንም ሆነ ፍየሎች በመጠበቅ ማንንም የማይጠቅም፥ በረሃብም የተጎሳቈለና በሽተኛ በመሆኑ የፈለገው አልነበረም።

ቀስ በቀስ ከሐዘኗ ብርታት ካገኘች በኋላ ሚሲስ ሉዊስ በአካባቢው ያሉትን ቤቶች መጎብኘት ስትጀምር ይህንን አሰላ የተባለ የተረሳና የተጎሳቆለ ልጅ አየች። የራሷን ልጅ ያጣችና በሐዘን ያለች በመሆኗ የሕፃናትን ችግር ተመልክታ ለመርዳት ትፈጥናለች። አሰላንም እንደተመለከተች በልቧ «እንደሱ ያለ ልጅ ቢኖረኝ ተንከባክቤ አሳድገው ነበረ» አለች።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የአሰላ እህት ከወንዝ ውሃ ቀድታ እንሥራውን በጀርባዋ እንዳዘለች ስትመለስ በመንገድ ሚስተር ሉዊስ አገኛት። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «አየህ! አሰላን ለእናንተ ልንሰጥ ነው» አለችው።

ሚስተር ሉዊስም በኋላ ስለዚሁ ሲናገር «ብዙውን ጊዜ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ነገር ሲናገሩ ከልባቸው እንዳልሆነ ስለማውቅ አላመንኩም» ብሎ ነበር። ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ቀን ጧት በብርድና በዝናብ ውስጥ ያቺ ሴት ልጅ ከዘመዶቿ ጋር አሰላን ይዛ ሚስተር ሉዊስ ቤት መጣች። ሁሉም ቤት ገብተው ከተቀመጡ በኋላ ሚሲስ ሉዊስ የሚበላ ነገር አቀረበችና በልተው ሲጫወቱ ቆዩ። ድንገት ጨዋታውን አቁመው «አሰላን ሰጥተናችኋል» ካሉ በኋላ ቤቱን ለቀው ሄዱ።

የሉዊስ ወጥቤት ሠራተኛ ወልዴ ይህንን ሰምቶ መጣና «ምን ልታደርጉ ነው» አላቸው በመገረም።

«እንግዲህ ትንሽ ልጃቸውን የሰጡን ይመስላል» አለ ሚስተር ሉዊስ።

«አይደረግም!» አለ ወልዴ። «እነሱ ግን ያደረጉ ይመስለኛል» አለ ሚስተር ሉዊስ እንደገና። ወልዴ ይበልጥ ተገረመ፥ «ልጁ ሊሞት ጥቂት የቀረው መሆኑን ሰው ሁሉ ያውቃል፥ ቢሞት ግን ቃልቻው (ጠንቋዩ) እናንተ ናችሁ የገዳላችሁት ይላችኋል፥ የመጣችሁትም ልጆቻችንን ለመብላት፥ ደማቸውንና መንፈሳቸውን (ነፍሳቸውን) ወደ ሀገራችሁ ለመላክ ነው ብሎ ሕዝቡን ያሳምንባችኋልና ሕፃኑን ልትወስዱት አትችሉም።» .

ሆኖም ሉዊስና ባለቤቱ ለሕፃኑ ልባዊና የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ከማድረግና እግዚአብሔር ሕይወቱን ከሞት እንደሚጠብቅ ከማመን በስተቀር ምንም ማድረግ አልቻሉም ነበር። እግዚአብሔር እንዲያሳድገው፥ ሕይወቱን እንዲታደግና የተደቀነበትን የሞት ፈተና ወደ በረከት እንዲለውጠው በየቀኑ ይጸልዩ ነበር።

ይህን ዮሐና (ዮሐንስ) ብለው የሰየሙትን ሕፃን ገላውን እያጠቡ፥ እያለበሱና ከበሽታው እንዲፈወስ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረጉለት በፍቅርና በጥንቃቄ አቆዩት። ወራት ሲያልፉ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ዮሐና ቀስ በቀስ እንደማገኛውም (ጤናማ) ሕፃን ሆነ። አሰላ የተባለው የወላይታ ስሙ ደስታ ማለት ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በነሉዊስ ቤት ቦታ እስከሚያዘጋጅለት ድረስ በሕይወቱ ደስታ የሚል ነገር አልነበረም።

ዮሐና ቤታቸው ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ቀናት ሰዎች ለወንጌል መልዕክት የሰጡትን አጸፋ ተመልክተው ሉዊስና ባለቤቱ እንደጻውሉስ «. . . ይህ የደረሰብኝ» (የአንድያ ልጃቸው ሞትና ወላጅ-አልባ ልጅ ማሳደግ) «በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ» ይሉ ነበር። ብዙ የወላይታ ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት ግልጽ ስሜትና ምላሽ ሰጡ።

## ክፍል ሦስት፡-«ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ»

### ምዕራፍ 5. የመሠረት ድንጋዮች

. . . ከእርሱ የተቆረጣችሁበትን ድንጋይ
ከእርሱም የተቆፈራችሁበትን ጉድጓድ ተመልከቱ።
ኢሳ. 51፡1

«ሕፃኑ ሲወለድ ቅበረው፥ በምመለስበት ጊዜ እዚህ ቤት ላየው አልፈልግም፥ ልጅ ይብቃኝ ባሪያም ይብቃኝ፥ የምልህን ትሰማለህ? ቅበረው ብዬሃለሁ!»

ጌታው በጣም ለሚያምነው ባሪያ ይህንን ጥብቅ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወላይትኛ ተናጋሪ በሆነው በኩሉ ከሚገኝ መንደሩ ተነስቶ የአሞን ወንዝ ሸለቆ ተሻግሮ ሄደ፥ ብዙ ወራትም አሳለፈ። ልጅ አልፈለገም፥ ያልፈለገበት ምክንያት ግን አልታወቀም። ሆኖም የወላይታ ሰው ልጅ ካልፈለገ ሕፃኑ እንደተወለደ ከነነፍሱ ይቀብረው ነበር።

አባቱ መንደሩን ለቆ እንደሄደ ወዲያው ሕፃኑ ተወለደ፥ እናቱም ብሩ ብላ ሰየመችው። አባቱን ብትፈራውም ብሩን በጣም ከመውደዷ የተነሣ ባሪያው (እንኳንስ ሊቀብር) ሊነካው አልፈቀደችለትም። ሕፃኑ እያደገ ሲመጣ በጣም ወደደችው።

የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ፈሩ፥ ተጨነቁም። አባቱ ተመልሶ ሕፃኑን በሕይወት ሲያገኝ ምን ያደርገው ይሆን? ከሕፃኑ አልፎ ሌላውን ሁሉ እስከመግደል ይደርስ ይሆናል በማለት ስጋት ያዛቸው።

የእግዚአብሔር ዓላማ ግን ብሩ እንዲተርፍ ሆነ። ምንም እንኳን እነዚህ ድርጊቶች የተፈፀሙት ሚሲዮናውያን ወላይታ አውራጃ ከመግባታቸው በፊት በምዕተ ዓመቱ የመጀመሪያ አሥር ዓመታት ውስጥ ቢሆንም እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ሊያደርግ ያለውን ያቅድ ነበር። ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን የመሠረት ድንጋዮች ከተለያዩ ቦታዎች (ካባዎች) ተቆፍረው የተለያዩ ግለሰቦች ተዘጋጁ። ብሩም ከእነዚህ አንዱ የሚሆን ነበር።

የብሩ አባት የሚመለስበት ጊዜ ደረሰ። ወደ መንደሩ ሲቃረብ ባሮቹ ሊቀበሉትና የሆነውን ሁሉ ሪፖርት ለማድረግ ወጡ። ስለ እርሻው፥ ስለሰብሉ፥ ስለ ከብቶቹ፥ ወዘተ ነገሩት። ከዚያም «ሕፃኑስ»? ብሎ ጠየቀ። በጣም እየፈሩ «ሕፃኑ በሕይወት አለ፥ እንዳንቀብረው እሜቴ ከለከሉን፥ ስለዚህ በሕይወት አለ፥ እያደገም ነው» ብለው መለሱ። በሰማው ዜና ተቆጥቶ የባሮቹ አለቃ ሄዶ ሕፃኑን እንዲያወጣለት አዘዘ።

ከጎረቤት ሴቶች አንዳንዶቹ አስቀድመው ይህ እንደሚሆን ጠርጥረው ነበርና አንደኛዋ ሴት ሕፃኑን መንጭቃ በመውሰድ በእንስት ውስጥ እየሮጠች በጎማው ውስጥ ታዋቂ ወደሆነው አጎቱ ቤት ወሰደችው። የብሩ አጎት ታሪኩን ከሰማ በኋላ ወደ አካባቢው ጭቃሹም በመሄድ የአባቱን ውሳኔ የሚሽር ትዕዛዝ

አመጣ። በዚህን ጊዜ አባት ሕፃኑን ለመቅበር ጉድጓድ ያዘጋጅ ነበር። ሕፃኑን ቢጐዳ በመቅሠፍት እንዲወድቅ በሹሙ እርግማን ተጣለበት። ከእጉል እምነቱና ከእርግማኑ ፍርሃት የተነሣ የሕፃኑንም ሕይወት ለማጥፋት ፈራ።

የብሩ አባት ምንም እንኳን አሁን ብሩን መግደል ባይችልም ከባሪያም በባሰ ሁኔታ የየው ጀመር። ብሩ አባቱን እየፈራና በአካባቢው ያለውን ሁሉ እየጠላ አደገ። በአሥራ ሁለት ወይም አሥራ ሦስት ዓመት ገደማ ከቤት ጠፍቶ አዲስ አበባ ኮበለለ። በዚያ ከስዊድን ሚሲዮን ጋር በመገናኘት ወንጌል ሰምቶ ክርስቶስ አዳኙ እንደሆነ አምኖ ተቀበለ። ስዊድን ሚሲዮን ት/ቤት ገብቶ አማርኛን ማንበብ ተማረ፥ ለእግዚአብሔር ቃልም ትልቅ ፍላጐት አደረበት።

በ1920 ዓ.ም. የመጀመሪያው የኤስ.አይ.ኤም. ቡድን ወደ ደቡብ ለመንቀሳቀስ ማቀዱንና መዘጋጀቱን ብሩ በማወቁ ራሱን ለሚሲዮኑ አሳወቀ። ሚሲዮኑ ቀጥሮት ሊወስደው ተስማማ። ከዚህም የተነሣ ለብዙ ዓመታት ወደ ተለየበት ወደ ወላይታ እንደገና ተመለሰ። ሥራው ገና ሲጀመር ብሩ በተለይም በዚያ በቂ ባልነበረው የእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀቱ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቷል። ሥራውና የሥራ ግንኙነቱ በግንባር ቀደም ከዋልተር ኦህማን ጋር ነበር። ጌታ በብሩ ሕይወት ለመሥራት የዋልተር ኦህማንን ተጽዕኖ ተጠቅሟል። ብሩ በክርስቶስ ያለው እምነቱና ተግባሩ ሥር ሰደደ። እግዚአብሔርም በብዙ መንገዶች ብሩ የወደፊቱ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ መሪ እንዲሆን ያዘጋጀው ነበር።

* * *

ከዕለታት አንድ ቀን ሰልማ በርግስተን አንድ የተጨነቀና የተረበሸ ልጅ አጥሩን ተደግፎ ቆሞ አየች። ልጁ ለሚሲዮኑ ተቀጥረው ሲሠሩ ወንጌል ሰምተው ካመኑ በኋላ ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈው ከሰጡት ውስጥ አንዱ ስሙም ጎዳና የሚባል ነበር።

ጎዳና የተጨነቀው በዕለቱ ከሥራ መልስ ለማደር የሚገባበት ቤት ስለሌለው ነበር። አባቱ ሞቷል፥ የሚኖረው ከእናቱ ጋር ነው። ባለፈው ቀን ሥራ ውሎ ቤቱ ሲመለስ የቤቱ በር ያለወትሮው በመዘጋቱ ለመክፈት ቢሞክር በጥብቅና በአስተማማኝ ሁኔታ የተዘጋ በመሆኑ አልቻለውም።

ከጎጆው ውስጥ እናቱ ለጎዳና ጥሪ መልስ ሰጠች፥ «እዚህ ቤት መኖርና ማደር አትችልም፥ በዚህ ቤት ውስጥ ይህ ኢየሱስ የሚባል ነገር አይኖረንም፥ ጠቦትህን ከቤቱ ጓሮ አስሬልሃለሁና ይዘህ ወደምትሄድበት ሂድ» አለችው።

«ታዲያ ጠቦትህን ይዘህ ወዴት ነበር የሄድከው?» ብላ ጠየቀች ሚሲስ ስርግስተን። ጎዳና ጠቦቱን ወደ አጎቱ ቤት እንደወሰደውና በእዚያ እንዳደረ ነገራት። አሁን ግን ተጨንቋል። ጠቦቱን ይዞ የት ሄዶ ነው ሌሊቱን የሚያሳልፈው? እርሱ ቤቱን መልቀቅ ያለበት መሆኑ ሳያንስ ጠቦቱም ተጨምሮ መባረሩ በጣም አሳሰበው።

«ዛሬ እንግዲህ ለራስህና ለጠቦትህ ማደሪያ ለመፈለግ ከሥራ በጊዜ መውጣት ትችላለህ» ብላ ነገረችው ሚሲስ በርግስተን።

ከሥራ እንደወጣ ጎዳና ጠቦቱን ወደ አንቱ ቤት መልሶ ወሰደው። አንቱ ቀደም ሲል ወንጌልን የሰማና ያመነ ሲሆን ጎዳና ከጠቦቱ ጋር በእርሱ ቤት እንዲኖር ፈቀደለት። በዚህም ደግሞ እግዚአብሔር ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን የመሠረት ድንጋዮችን ያዘጋጅ ነበር።

*　　*　　*

ዋንዳር የእግዚአብሔር ጥበብ ሕያው ምስክር ነበር። ከውጭ የሚታይ ምንም ዓይነት የተለየ ባሕሪይ ስለሌለው ሰዎች መሪ ይሆናል ብለው አይገምቱትም። ሆኖም «ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል።» ሰዎች ያልተስተካከለ ጥሬ ድንጋይ ሲያዩ እግዚአብሔር ግን የከበረ እንቁ አየ። የራሱ የዋንዳር ምስክርነት ማንነቱንና ጥቅሙን ያረጋገጠ በመሆኑ የሰዎች ግምት ስሕተት ሆኖ ቀረ።

«በአንድ ቀዝቃዛና ብርዳም ቀን ገና ፀሐይ ሳትወጣ እሁድ ገበያ ለመሄድ ከቤቴ ወጥቼ ስጓዝ አቶና ከነጮች መንደር ደረስኩኝ። መንደሩን በሚያቋርጠው መንገድ ሳልፍ በአንድ በልዩ ዓይነት ቤት አጠገብ ቆሞ የነበረ አንድ ነጭ ሰው ጠራኝ። ሌሎች ወላይታዎች አብረውት ቆመዋልና መሄዱ አደጋ የሌለበት መሆኑን አውቄ ተጠጋሁ።

«ውጪ በጣም ቀዝቃዛና ይዘንብም ስለነበረ ሁላችንም ወደ ትንሹ የሣር ቤት ውስጥ እንድንገባ ተጋበዝን። በቤቱ ውስጥ ነጮች ካከማቹት መድኃኒት የተነሣ እንግዳ የሆነ ሽታ ነበር። መድኃኒቱ ታመው ለእርዳታ ለሚመጡ ሰዎች የሚሰጥ ነበር። ነጩ ሰው በመካከላችን ሆኖ በወለሉ ተቀመጥን። እርሱም ጢም የሌለው፥ ፊቱ የገረጣ (የነጣ)፥ ልብሶቹም እንግዳ የሆኑ ለግላጋ ወጣት ነበር። ቋንቋችንን በደንብ ባይችለውም የሚናገረውን ስለወደድኩ አዳመጥኩት። በኋላም ከሰባት ቀናት በኋላ እንድንመለስ ጋበዘን እኔም ለመሄድ ተነሣሁ።

«እንደገናም ነጩ ኢየሱስ ስለተባለው ሰው ሲናገር ሰማሁ። ይህ ሰው ወደዚሁ አለም በእግዚአብሔር የተላከ ሲሆን እርሱም ብዙ ድንቅ ሥራዎችን አከናውኗል ሲል ነገረን። ነጩ ወጣት በእጁ የያዘውን መጽሐፍ እግዚአብሔር እንደሰጣቸውና እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማንም ሰው (ወላይታም ጭምር) ለኃጢአቱ ይቅርታ እንዲሁም ለልቡ ሰላምን ቢፈልግ የኢየሱስ ተከታይ በመሆን ሊያገኝ ይችላል እንደሚል ነገረን። ለሁሉም ይህ በውስጤ እንደማር ስለጣፈጠኝ ደግሜ መምጣትና ይበልጥ መስማት እንዳለብኝ አሰብሁ።

« ከሰባት ቀናት በኋላ እንደገና አቶና መጣሁ። ነጭ ሰው እኛ ብዙ መጥፎ ነገሮችን በመሥራት እግዚአብሔርን ያስቆጣን መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ተናገረ። እርሱ ይቅርታ እንዲያደርግልንና ኃጢአታችንን እንዲወስድልን እኛ በኢየሱስ ማመን አለብን። በቀጥታ ወደ እኔ በማመልከት ማመን እንደምፈልግ ቢጠይቀኝም አባቴ ጠንቋይ እንደሆነ ነገርኩት። አባቴ በራሱና በሁምቦ ተራራ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ (መጥፎ) መንፈሳዊ መሪ ነበር።»

ዋንዳር ወንጌልን ለሦስተኛ ጊዜ ከሰማ በኋላ ልቡን ከፈተ፥ ራሱንም ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፎ በመስጠቱ ሕይወቱ ወዲያው ተለወጠ። ማንበብን መማር ቢፈልግም የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ነበር። አማርኛ ብሔራዊ ይሁን እንጂ አብዛኛው የወላይታ ሕዝብ አያውቀውም።

አማርኛ በትንሹ የእብራይስጥ ቋንቋን የሚመስል ሲሆን በእያንዳንዳቸው ሰባት ዓይነት የድምፅ አናባቢዎች ያሏቸው ሰላሳ ሦስት ድምፅ ሰጪ ፊደሎች አሉት። በተጨማሪም በርካታ ድምፆች ያሉት ሲሆን ይህም የፊደሎችን ብዛት ሁለት መቶ ሃምሣ ስድስት ያደርገዋል። ይህ እንኳንስ ለዋንዳር በደንብ ለተማረ ሰውም አስቸጋሪ ሥራ ነበር። እንዲያውም የሱ የመማር ችሎታ ከአብዛኛዎቹ ያነሰ ነበር። ሆኖም ትምህርቱን ለመከታተል አሥራ አምስት ማይሎች ርቆ ከሚገኝ መንደሩ በሳምንቱ ውስጥ በብዙ ቀናት ወደ ሚሲዮኑ ጣቢያ ይመላለስ ነበር።

ሚሲስ ሉዊስ ብዙ ወጣት ክርስቲያኖችን ማንበብ አስተምራለች። ዋንዳር ግን የአማርኛ ፊደሎችን መያዝና መረዳት ባለመቻሉ ሚሲስ ሉዊስ ብዙ ለፋች። ከክፍል ጓደኞች ወደኋላ በመቅረቱ እርሱም ተስፋ ቆረጠ። ሚሲስ ሉዊስም ታምማ ለረጅም ጊዜ ውሎዋ በመኝታ ክፍሏ ሆነ። ለዋንደሮ ካላት ሀሳብ የተነሣ በሳምንት ሦስት ጊዜ በተለየ ልታስተምረው ጀመረች። ሁልጊዜም አንገቱን ዝቅ አድርጎ እግዚአብሔር ተጨማሪ ፊደል ለመማር እንዲረዳው ሲጸልይ ታስተውለዋለች። በመጨረሻ ትምህርቱ ግልጽ ሲሆንለት የምሥጋና ፀሎት በያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ደጋግሞ ያደርጋል። በአንድ ቀን አንዲት ፊደል እንኳን በደንብ ተምሮ ሲያውቅ በዚህ ደስ ይለዋል።

ከሚሲስ ሉዊስ ትዕግሥት ከተሞላበት እርዳታ የተነሣ ዋንዳሮ አማርኛ በደንብ ባያቀላጥፍም በጥሩ ሁኔታ ማንበብ ቻለ።

አንድ ቀን ዋንዳር በእሁድ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ እንዳለ ተነስቶ ለመናገር አስፈቀደ። በዚህ ንግግሩ ወንጌልን ለመስማት የሚመጣው ሕዝብ ቁጥር እያደገ በመምጣቱ ስብሰባው ከሚካሄድበት የሚስዮኑ ክሊኒክ ሕንፃ አቅም በላይ መሆኑን አስታውቆ ሕዝቡ የራሱን ቤት ተጋግዞ እንደሚሠራው ሁሉ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ቤት በአንድነት መሥራት እንዳለበት ጠቆመ።

ጥቆማው በአማኞች ተቀባይነት አግኝቶ በሚሲዮኑ ጣቢያ አጠገብ በተመደበው ቦታ ቀን እርሻቸውን እየሠሩ ከሰዓት ዘግየት ብሎና ማታ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ጀመሩ። ቤቱ የሚሠራው እንደ አብዛኛዎቹ የሚሲዮኑ ቤቶች ከጭቃ በተሠሩ ጡቦች ነበር። ሚስዮናውያንም በኩራዝና በፋኖስ መብራት ሥራው ሲካሄድ አብረው በእጃቸው በመሥራት ይረዷቸው ነበር። ማታ ማታ ከምሽቱ በሦስት ሰዓት አካባቢ ሴቶቹ ቡና አፍልተው ከቦቆሎ ቆሎ ጋር ያመጣሉ። ይህም ከተበላና ከተጠጣ በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተካሂዶ ሰዎች ወደየቤታቸው ይሄዳሉ።

አንድ ቀን ማታ በእሳት ዙሪያ ተቀምጠው (እሳት እየሞቁ) ልምዳቸውን ሲያካፍሉ ዋንዳሮ እንዴት ሊያምን እንደቻለና ውጤቱንም ይነግራቸው ነበር። «እውነቱን ነው የምላችሁ! ያኔ ያደረግሁት እስካሁን አይገባኝም። በቆምኩበት

ጊዜ እግዚአብሔርን ማመንና የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን መፈለጌ ከውስጥ ሲገለጽልኝ በእኔ አንድ ነገር ሆነ። ከዚያን ጊዜ አንስቶ እስካሁን ልቤ በደስታ ተሞላ፥ አይቼው የማላውቀው አዲስ ሰላምም በውስጤ ሰፈነ።

«በኋላ ሌሎችም አመኑ። ብዙ ሰዎች በማምንቱ ቀናት ሁሉ ከሁምቦ እስከ ሶዶ ከእኔ ጋር ይመላለሱ ነበር። ፈረንጁ ሰውዬ እኛ ከፈለግን ወደምንኖርበት መንደር መጥቶ ለተወሰነ ጊዜ ከእኛ ጋር ለመቆየትና ስለ ኢየሱስ የበለጠ ለማስተማር ፈቃደኛ መሆኑን አስታወቀ።

«በዚያን ጊዜ የሁለት ዓመት ልጄ ታመመ። ጠንቋዩ አባቴ ልጄ የታመመው እኔ የአባቴን ሃይማኖት ስለተውኩ መሆኑን ገልጾ ወቀሰኝ። እኔ የቤተሰባችንን ጣዖቶች ትቼ ኢየሱስ የተባለ አዲስ አምላክ መከተል ስለጀመርኩ አሁን ደግሞ ኢየሱስን ክጄ ወደ ቤተሰባችንና ጐሣችን እምነት ተመልሼ እንደገና ለሰይጣንና ሌሎችም ርኩስ መናፍስት መስዋዕት ካላቀረብሁ የታመመው ልጄ እንደሚሞት አረጋገጠ። ይህም በአካባቢው ባሉ መንደሮች ሁሉ ተነገረ፥ ታወቀ። ነገር ግን አንድ በኔ ውስጥ ያለ ድምፅ ይህንን እንዳላደርግና እንደቅድመ አያቶቼ፥ ሰይጣንና ርኩስ መናፍስትን ወደ ማምለክ እንዳልመለስ ይመክረኛል። ስለዚህም «ለርኩስ መናፍስት መስዋዕት አላቀርብም፥ በእኔ ወይም በልጄ ላይ ምንም ነገር የሚደርስ ቢሆን ይህንን አላደርግም» ብዬ ነገርኩት።

«ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጄ ሞተ። በባህላችን መሠረት ለለቅሶና ዋይታ የመጡ ሰዎች ፊታቸውን መቧጨርና መቆራረጥ ደረታቸውንም መምታት ጀመሩ። እኔም ይህን እንዳያደርጉና እንዲያቆሙ እኔ ራሴ ምንም የማላማርርና የማላዝን ስለሆንኩ እነሱም እንዳያለቅሱ አጥብቄ ነገርኋቸው። እርግጥ ነው የልጄ ሞት ለእኔ ትልቅ ጉዳት በመሆኑ ተሰምቶኛል። ነገር ግን በውስጤ ከፍተኛ ሰላምና የደህንነት ስሜት ስላለ እነርሱ እንዲያለቅሱ አልፈለግሁም።

«ባለቤቴ ገና ወጣት ሴት ነበረች። እሷም በሰይጣንና በማያምኑት አምልኮ ሥርዓት ተውጣ ስለነበር ዋይታዋን፥ ፊቷን መቧጨርና ሌሎችንም ማድረግ ቀጠለች፥ እግዚአብሔርንም ሰደበች። የምታደርገውን እንድታቆም ብነግራት በጣም ተቆጣች። ለቅሶው ከሰባት ቀን በኋላ ሲያበቃ ትታኝ ወደ ወላጆቿ እንደምትሄድ ነገረችኝ። ለቤተሰቡ ፍቅር የሌለው ከመሆኑ የተነሣ ለአባቱ ጣዖት መስዋዕት አቅርቦ የራሱን ልጅ ሕይወት ለማዳን ከማይፈልግ ሰው ጋር መኖር እንደማትችል ከገለጸች በኋላ ቤቱን ለቃ ሄደች።

«ከዚያን ወዲህ ለብዙ ጊዜያት ይህ ነጭ ሰው ከእግዚአብሔር መጽሐፍ የሚያነብልን ቃል እውነት መሆኑን አረጋግጫለሁ። እርግጥ ነው የዚህን ዓለም እውቀት ያልተማርኩ ተራ ወላይታ ነኝ፥ ቢሆንም ከመጽሐፉ የተማርከው የእግዚአብሔር ቃልና ኢየሱስን መከተልህ በውስጥህ ሰላምን አይፈጥርም ብሎ ሊያስተምረኝ የሚቃጣ የለም። እግዚአብሔር ኃጢአቴን ይቅር እንዳለልኝና ልጁ እንዳደረገኝ በልቤ አውቀዋለሁ።»

በዋንዳሮ ሕይወት የተከሰተውን ለውጥ ተመልክታ ባለቤቱም ወደርሱ ተመለሰች። ያሁን መልካም ጠባዩ ከድሮ የተለየ በመሆኑ ተቀርበው፥ ታዳምጠውና ለእሷም ሆነ ለሌላው ሁሉ የሚመሰክረውን መልዕክት አመነች። አብረውም በታማኝነት ጌታን ለብዙ ዓመታት አገልግለዋል።

# ምዕራፍ 6. ኢየሱስ ክርስቶስና ሰይጣን

ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ . . .

የሐዋ. ሥራ 26፡18

ዲያማ የተወለደውና ያደገው በማያምን አካባቢ በመሆኑ ብዙ ዓይነት የጥንቆላ ብልሃቶችን ተምሯል። ከእስላሞችም ጋር በመገናኘት የሃይማኖታቸውን ትምህርት ለማወቅና ለመከተል ሞክሯል።

በኋላም የሚያውቃቸውን ሃይማኖቶች ሁሉ እየሞከረ ሲያነማና ሲጥል ቆይቶ ዕድሜው ሃምሣ ዓመት ያህል በሚሆንበት ጊዜ ከሚሲዮናውያን ጋር ተገናኘ። በጣም ያስጨነቀውን የልቡን ፍላጐት ለማሟላት ሲል ትንሽ ተስፋ ፍለጋ ቢንከራተትም ባለማግኘቱ ጭራሽ ብስጩ ሆነ። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የመዳንን ቃል ለመስማት ሁልጊዜ ወደ ሚሲዮኑ ይመጣ ነበር።

በመጨረሻም ቃሉን ደጋግሞ ከሰማ በኋላ እየፈራና ብዙም እርግጠኛነት ሳይኖረው ዲያማ ክርስቶስን አምኖ መቀበሉን ገለጸ። ጽኑ ያልሆነ ተለዋዋጭ ጠባይ ያለው ከመሆኑ የተነሣ የተለማመዳቸውን ሌሎች ኃይማኖቶችን ትቶ ሙሉ በሙሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ባለመተማመኑ በሕይወቱ ወዲያውኑ ለውጥ ሊታይ አልቻለም።

ምንም እንኳን በዚህ ጊዜ ዲያማ በራሱ አልፎ አልፎ ሽበት የጀመረው ጠና ያለ ሰው ቢሆንም ንባብ ለመማር ትልቅ ጉጉት ነበረው። ከዚህም የተነሣ በሚሲዮኑ የቀን ት/ቤት ገብቶ ከአሥራ አራትና አስራ አምስት ዓመት ልጆች ጋር ተቀምጦ ተማረ። እንደዋንዳሮ ሳይሆን ዲያማ አማርኛ በደንብ መናገር የሚችል ስለነበረ ንባብ ለመማር ብዙ ባለመቸገሩ ጥሩ እድገት አሳየ።

መጽሐፍ ቅዱስ በማንበቡ የዲያማ ሕይወት በመለወጥ ወላዋይና ፈሪ የነበረው ልበ - ሙሉና ጀግና ክርስቲያን ሆነ። እስካሁን ይጠራበት የነበረ ዳርጌ የተባለ ስሙን ዲያማ እንዲባልለት ጠይቆ አስቀየረ። እንዲህም አለ «ከአሁን ጀምሮ ዳርጌ ተብዬ መጠራት አልፈልግም፥ ይህ ስም እኔ ሰይጣንን በማመልከበት ጊዜ የነበረኝና በጠንቋዩም የምታወቅበት ነው፥ ወደፊት በዚሁ መንገድ መታወቅ ስለማልፈልግ አባቴ ዲያማ ብሎ የሰየመኝን የመጀመሪያ ስሜን እፈልገዋለሁ።»

ዲያማ በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የተሞላ በመሆኑ በየትም ቦታ ስለ እርሱ መናገር ይወዳል። ዘበኛ በመሆኑ ሳይተኛ መጠበቅ ቢኖርበትም ማታ ማታ አጭር እንቅልፍና እረፍት ያደርጋል። ቀን ቀን ሰዎችን ለማግኘትና ለማነጋገር በቂ ጊዜ ይኖረዋል። በርካታ የወላይታ ለቅሶች ሟቹን ለማክበርና ለዘመዶቹ ኃዘናቸውን ለመግለጽ ለሚመጡ በሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

ለመመስከር ምቹ ሁኔታ ይፈጥሩለታል። ዲያሣ ከሰዎች ጋር ተቀምጦ ስለ ወደፊቱ ሕይወት በዝግታ ይነግራቸዋል።

አንድ ቀን ጧት የለቅሶና የዋይታ ጩኸት የኦቶናን ሚሲዮን ግቢያ ከግዶ ጋራ የሚለየውን ትልቅ ሸለቆ አልፎ ይሰማል። የሞተው አንድ ሀብታም የወላይታ ሰው ሲሆን ቤቱም በአትክልትና በዛፎች አሸብርቆ ከኦቶና ይታያል። ዲያሣ ሸለቆውን አቋርጦ እየተሻገረ ብዙ ጊዜ የመሰከረለት ቢሆንም ሰውየው ኩሩ በመሆኑ ሳይቀበለው ቆይቶ ዛሬ ግን ያለክርስቶስ ወደ ዘለዓለማዊ ጥፋት ሄደ።

ዲያሣ ብዙ ጠንቋዮችና ሌሎች ሕዝቦች በለቅሶው እንደሚገኙ በማወቅ በማለዳ ሸለቆውን አቋርጦ ወደ ለቅሶ ቦታ ሄደ። ከመቀመጡ በፊት በወላይታ የተለመደውን የአለቃቀስ ወግና ሥርዓት ሳይጠብቅ ወደ አልቃሾቹ ቀርቦ የተሰማውን ሐዘን ገለጸ። ሌሎች ግን በሐዘንተኞች ፊት ይሄዱና ይመለሱ፥ በአክሮባት ይወድቁ፥ በጥፍሮቻቸውም ሰውነታቸውን ይነጩ፥ ደረታቸውንም ይደልቁ ነበር። ከዚህም በላይ ትንሽ ጭብጥ የአጋም እሾህ ይዘው ጉንጫቸውን በፊታቸውና በልብሳቸው ደም እስከሚፈስ ይገርፉና ይቦድሱ ነበር። በዚህ የእብድ ዓይነት ሥራ ነበር ሟቹን የማጣት ጥልቅ ሐዘንና የሐዘናቸውንም ልባዊነት ለማሳየት ተስፋ የሚያደርጉት።

ዲያሣ በተቃራኒው በፀጥታና ሐዘን በተሞላበት ሁኔታ በመራመድ ወደ ሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች ቀርቦ ከኢየሱስ ቃል «ልባችሁ አይታወክ፥ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፥ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር» አላቸው። ለሟቹ ሰው አሁን ባይቻልም በሕይወት ላሉ ዘመዶቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመንና ለመዳን ዕድል እንዳለ አረጋገጠላቸው። ከዚያም ወደ ዛፍ ጥላ ሥር ሄዶ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተቀመጠና መመስከሩን ቀጠለ።

በዚያ እንዳለ ከሱ ብዙም ሳይርቅ ዋናው ጠንቋይ (የጠንቋዮች ጠንቋይ) ተቀምጦ አየው። ጠንቋዩ የተለየና በራሱ ላይ ሰባት ለየብቻ የተገመዱና የታሠሩ ፀጉሮች ያሉት ሲሆን በመላው ወላይታ የተፈራና በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎችን በመርገም የገደላቸው መሆኑ የሚታመንለት ሰው ነበር። ቤቱ ሦስት ግቢዎች ያሉት ሲሆን ወደ ሦስተኛው ግቢ ማለትም ጠንቋዩ ርኩስ መናፍስትን በመጥራት ሰይጣንን የሚገናኝበት ትንሽ ጎጆ ቤት ውስጥ መግባት የሚችለው ራሱ ጠንቋዩ ብቻ ነበር። ግቢው በጦር አጥር የታጠረ ሲሆን እያንዳንዱ ጦር የመጣው እርሱ ረግሞ ከገደለው ሰው ቤት ነበር። የረገመው ሰው ከሞተ በኋላ የሟቹን ጦር ዘመዶቹ ለጠንቋዩ የማምጣት ግዴታ ነበረባቸው። ስለዚህ ሰዎች ይህንን ጠንቋይ ቢፈሩና በፊቱ ቢንቀጠቀጡ አያስደንቅም።

ዲያሣ ግን አልፈራም። ሰዎቹ አሁን እንደሚያደርጉት ማልቀስ እንደሌለባቸውና ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይሉ ሰዎችን ከሰይጣን ሥልጣን ነፃ እንደሚያወጣቸው መመስከሩን ቀጠለ። ሰዎችም የዲያሣ ንግግር ጠንቋዩን የማያስደስትና የሚያስቆጣ መሆኑን አውቀው በመፍራት ዲያሣን ዝም ለማሰኘት ሞከሩ።

«ተጠንቀቅ አንተ ሰው! ሌላ ትርፍ ቃል እንዳትናገር» አሉት።

ዲያሜም ዝም ከማለት ይልቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገር ጀመር። በመጨረሻ ጠንቋዩ ራሱ «ዝም በል!» በማለት በኃይለ ቃል አዘዘ።

«ማን ነህ አንተ ዝም በል የምትለኝ?» አለ ዲያሜ። ሰዎቹ በተለይም የዲያሜ ወገኖች በድፍረቱ በጣም ደነገጡ፣ ፈሩም። ዲያሜ በእርግማኑ እንዲሞትባቸው ስለማይፈልጉ «ዝም በል፣ ሌላ ነገር እንዳትናገር» በማለት አባበሉ።

ዲያሜ ግን ለጠንቋዩ መመለሱን ቀጠለ «ዝም በል የምትለኝ አንተ ማን ነህ? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ይህንን መልዕክት በየትም ቦታ ላሉ ሰዎች ሁሉ እንድናገር አዞኛል»።

ጠንቋዩም በጣም ተቆጥቶ «ማን እንደሆንኩ አታውቅም?» አለ።

ዲያሜ «አንተ ማን እንደሆንክ አውቃለሁ፣ አንተ ጠንቋይ ነህ፣ አንተ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝህ መሆኑን እንደማታውቅም አውቃለሁ» ብሎ መለሰ።

«አንተ የጠንቋዮች ሁሉ አውራ ጎቻ ጎዶን አትፈራም?»

«አልፈራም፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስን እፈራለሁ፣ አከብራለሁ። አንተ ሰዎችን በፍርሃት በማጥመድ ችግር ትፈጥርባቸዋለህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አዳኝ ነው። እርሱ ሰዎች በስሙ ቢያምኑ ያንተን ሥልጣን በመስባበር ሕይወትን፣ ብርሃንንና አርነትን ይሰጣል።»

የዲያሜ ድፍረትና ንግግር ጎቻ ጎዳን በጣም አስቆጣው። «ይህ መንፈቀ-ዓመት ሳያልቅ ከፈታችን መስቀል (በዓል) በፊት ከነጭ ሰዎች አገልጋዮች አንዱ ይሞታል!» ብሎ ጮኸ ጠንቋዩ።

«የነጮችን ትምህርት የሚከተሉ ብዙ ሰዎች አሉ፣ ትምህርቱ እንኳን የነጮች ሳይሆን የእግዚአብሔር በመሆኑ ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን እንከተላለን። እንግዲህ እንዳጋጣሚ ከእነዚህ አንዱ ሊሞት ይችላል፣ እኔን የምትለኝ ከሆነ ለምን በስሜ አትጠራኝም?» አለ ዲያሜ በዝግታ።

ጎቻ ጎዶ ይበልጥ ተቆጣ። የአንድ እጁን ሌባ ጣት በረዥም ጥፍሩ መሬት ላይ ተከለና በሌላ እጁ ጣት ወደ ዲያሜ እያመለከተ በጐረና ድምፁ ቃሎችን ይተፋ ጀመረ።

«ከመንፈቀ ዓመት መጨረሻ በፊት የፈታችን መስቀል ሳይደርስ ትሞታለህ!»

እርግማኑን የሰሙ ሰዎች ለመተንፈስ እንኳን ባለመቻላቸው ፀጥታ ሆነ። አንድ ዓይነት ኃይለኛ መቅሰፍት እዚያው በዲያሜ ላይ ይወርዳል ብለው ስላሰቡ ከቆሙበት ወደኋላ አፈግፍገው አይናቸውን አፍጠው ይመለከቱ ነበር።

ዲያሜ ወደ ሕዝቡ መለስ ብሎ እጆቹን በማንሣት የተቃውሞ ጩኸት እንዳይኖር እየተከላከለ እንዲህ አላቸው፣ «ይህ ክፉ ሰው ያለውን ሰምታችኋል፣ አባቱ ሰይጣን የውሸቶች ሁሉ አባት ነው። እንግዲህ ይህንን የሰማችሁ ሁሉ ተመልከቱ። ይህ እርግማን ከሠራና እኔ ከሚመጣው መስቀል

ወይም ስድስት ወር በፊት ከሞትኩ ሰይጣንን አምልኩ፥ ተከተሉትም። እኔ ካልሞትኩና በሕይወት ካለሁ ግን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሳችሁ የግል አዳኛችሁ በማድረግ ከእኔ ጋር አብራችሁ እግዚአብሔርን እንድታመልኩ እፈልጋለሁ!»

ዲያማ የተናገረውና ያደረገው በወላይታ ተደርጐ አይታወቅም። የተፎከከረው ከወላይታ አውራ ጠንቋይ ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከሰይጣን ጋር ስለሆነ መንፈስ ቅዱስ በኃይል እንደሞላውና እንዳበረታው እንዳደፋፈረውም አይጠረጠርም።

ኤልያስ እንኳን ፈርቶ እንደነበረ፥ ዲያማም በዚያን ቀን ማታ ሥራ ከመግባቱ በፊት እየተንቀጠቀጠ ያደረገውን ሁሉ ሊነግረው ወደ ሚስተር ሉዊስ ሄደ።

«መምህር የሠራሁት ትክክል ነውን?»

ሚስተር ሉዊስም «አዎን ትክክል ነው፥ አትፍራ፥ ማሰብ ያለብህ ሰይጣንን የተጋፈጥክ መሆንህን ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰይጣንም የበለጠ ኃይለኛ ነው። እርሱ ራሱ ‹አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።› እንደገናም ‹ሥልጣን በሰማይና በምድር ተሰጠኝ› ብሏልና። እርሱ ከማንም ከምንም የበለጠ ኃይለኛ በመሆኑ ከሰይጣንም በላይ ነው። አየህ ዲያማ! አንተ በክርስቶስ የምታምንና ነፍስህንም ለርሱ አሳልፈህ የሰጠህ ስለሆንክ እርሱ ይጠብቅሃልና የሰይጣን እርግማን ሊጎዳህ አይችልም።» ሁለቱም አብረው ከእግዚአብሔር ቃል ጌታ የማይተዋቸውና የማይለያቸው መሆኑን የሚያረጋግጠውን ክፍል ካነበቡ በኋላ ዲያማ ብርታት አገኘ።

«እስቲ እንጸልይና ጉዳዩን ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንስጥ። አንተ ግን በምትሔድበት ሁሉ ስምትበላውም ምግብ ሁሉ በጣም መጠንቀቅ አለብህ፥ እርግማኑ በአንተ ላይ እንዲፈጸም ጠንቋዩና ደጋፊዎቹ የማይሞክሩት መንገድ አይኖርምና። ምግብ ስትበላ መርዝ ሊጨምሩበት ስለሚችሉ በነዚሁ ስድስት ወራት ውስጥ የትም ስትሄድ ምግብም ስትበላ ራስህን ጠብቅ።»

ሁልጊዜ ማታ ማታ ዲያማ ለሥራ ሲመጣ አብረው ይጸልያሉ። ዲያማም እግዚአብሔር ብርታትና ድፍረት ስለሰጠና ከፍርሃትም ነፃ ስላወጣው ልቡ ሰላም አገኘ። በሰይጣን ባርነት ታስሮ ነፃ የወጣ (ዲያማና ሌሎች አማኞችን የመሰሉ) እንጂ ሌላ ሰው መጥፎውን መጋፈጥና ከሰይጣን ኃይል ነፃ ወጥቶ አርነትን መለማመድ ማለት ምን እንደሆነ ሊገባው አይችልም።

የስድስቱ ወራት መጨረሻና የመስቀል በዓል ደረሰ። በዓሉ የሚከበረው ከሚሲዮኑ ጣቢያ ስድስት ወይም ሰባት ማይሎች ያህል ርቆ በዋናው ጠንቋይ በጎቻ ጎጆ ቤት አጠገብ ባለው ሜዳ ነበር። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችም በሜዳው ተሰበሰቡ። በቦታው ምን እንደተፈጸመ ሚስተር ሉዊስ ሲገልጽ «ዲያማ ከፈረሶቹ በአንዱ፥ ደሲታ (ሌላው አማኝ) በሌላው ፈረሴ ተቀምጠው ከእኔም ጋር ሸለቆውን ተሻግረን ወደ ጠንቋዩ ቤት ሄድን። ሜዳው ከስድስት መቶ በሚበልጡ የፈረስ ጎግስና የጦር ውርወራ በሚጨወቱ ፈረሰኞች ተሞልቷል። እኛም ወደ ውስጥ ገብተን ጠንቋዩ ወደ ተቀመጠበት ስንጠጋ በፊቱ ሰባት የሰይጣን ከበሮች ባለማቋረጥ እየተመቱ (ሰይጣናዊ) ዳንስና ጭፈራ ሲካሄድ ተመለከትን። አንድ ትልቅ ዋርካ ተቆርጦ ተጥሏል፥ ቅርንጫፎቹም አልተመለመሉም። ዋርካው በወደቀበት የሚያድግ ለማስመሰል የተደረገ ሲሆን

ትናንሽ ጭብጥ ሣሮችም በቅርንጫፎቹ ታስረዋል። ሰዎችም የከበሮውን ምት እየተከተሉ ይደንሱ ነበር።

«ድንገት የከበሮው አመታት ተቀየረ፥ ይህም ሰዎች ሁሉ ወደ አንድ ቦታ የሚሰበሰቡበት ሰዓት መሆኑን የሚያመለክት ነበር። ሰዎችም ሁሉ ጠንቋዩ ከመኻላቸው ሆኖ ለሰይጣን መስዋዕት ለማቅረብ ተጠጋግጠው ተሰበሰቡ። እኛም የቆምነው በብዙ መቶ በሚቆጠሩ ሰዎች በተከበበው በራሱ በሽማግሌው ጠንቋይ አጠገብ ነበር። አሁንም መቺዎቹ የከበሮውን አመታት ሲቀይሩ ዳንሱም ልዩ መልክ ያዘ፥ የመስዋዕቱ ማቅረቢያ ዝግጅት ሲደረግ ሰዎች ሁሉ ለሰይጣን አምልኮና ክብር መዘመር ጀመሩ።

«ዲያሣ በፍጥነት ተነስቶ በእግሩ ቆመና ‹ጎቻ ጎዶ! ታስታውሰኛለህ? በዛሬው ቀን በሕይወት አትኖርም ብለህ የነበርከው ሰው ነኝ። አንተ እስከ መስቀል ድረስ አትኖርም ብለኸኝ ነበር፥ እኔ ግን ይኸው ጤነኛ ሆኜ እኖራለሁ። አንተ ውሸታም፥ አንተ የምታመልከው ሰይጣንም ውሸታምና ኃይል የሌለው መሆኑን መመስከር እወዳለሁ› ብሎ ተናገረ።

«ዲያሣ ወደ ሕዝቡ መለስ ብሎ ‹ያኔ ምን ብዬ እንደ ነበር አሁን ታስታውሳላችሁ? እኔ ብሞት ለሰይጣን ተገዙ፥ እርሱንም አገልግሉ፥ ባልሞትና በሕይወት ብኖር ግን ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ብዬ ነበር። ዛሬ እዚህ ካላችሁት ውስጥ ያኔ በዚያ ቦታ የነበራችሁት ብዙዎቻችሁ በእርግጥ ይህ ከሆነ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ቃል ገብታችሁ ነበር። ይኸው እኔ በሕይወት አለሁ ጤናማም ነኝና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሳችሁ አዳኛችሁ አድርጋችሁ እንድትቀበሉት እፈልጋለሁ።›

«ዓይኖች ሁሉ በጠንቋዩ ላይ ተተከሉ፥ ማንም ሊንቀሳቀስ ወይም ሊናገር አልደፈረም። እስካሁን ማንም የዚህን የሰይጣን ካህን የዕድሜ ልክ ሥልጣን ደፍሮ የተጋፈጠ አልነበረም። የሰዎቹ ፊት በፍርሃት ጨለመ። ምን አስደንጋጭ ነገር ይፈፀም ይሆን? ዲያሣ እዚያው በሞት ይመታል፥ እያሉ እሱን ለመንካት ካለመድፈራቸውም በላይ ጎቻ ጎዶን የተጋፈጠ ሊኖር እንደሚችል ባለማመን በአጠገቡ የቆሙት በፍርሃት ወደኋላ አፈገፈጉ።

«የከበሮ ምት ቆሞ መችዎቹም ሆኑ ደናሾቹ ሁሉ በቆሙበት ቀሩ፥ በጠቅላላ ፀጥታ ሆነ፥ ጠንቋዩ በቁጣ አፍጦ ዲያሣን ያይ ነበር። ዲያሣና አብረውት የሄዱት በአንድ ወገን ሕዝቡ ደግሞ በሌላ ሆነው የሰይጣን ወኪል እና የእግዚአብሔር ልጅ ለተወሰነ ጊዜ ፊት ለፊት ተፋጠጡ። ጠንቋዩም ተጨንቆና ተደናግሮ እጆቹም ተዝለፍልፈው በወደቁ ጊዜ ተነስቶ እንደተገረፈ እንስሳ ሮጦ ወደ ግቢው ገባ።

«መተትና አስማቱ ሲሰባበር በቦታው የነበረው ጫጫታና ሁካታም አበቃ፥ ሰዎችም ሁሉ በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ሥፍራውን ለቀው ሄዱ፥ ጠንቋዩም በሕዝቡ ላይ የነበረው የኃይል ይዞታ ሲሰባበር የእርሱ ሰይጣናዊ በዓልና ስብሰባ ማድረግም አብሮ አከተመ።»

# ምዕራፍ 7. የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን

. . . በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና።

ሮሜ 8፡29

«ምንም ሥራ አልሠራንም፥ ሁሉም ገና ነው» አለ ደሲታ እየተገረመና መጽሐፍ ቅዱሱን በእጁ ይዞ ወደ ኤሪል ሉዊስ እየመጣ።

«ምንድነው እሱ?» ብሎ ጠየቀ ሉዊስ።

«‹አመኑ ተጠመቁ›፥ እዚህ የማነበው ያመኑት ተጠመቁ የሚል ነው፥ እኛ ግን ሁሉንም ገና አላደረግንም።»

ደሲታ በአቶና ሚሲዮን ጣቢያ ከሚሠሩ ወጣት ወላይታዎች አንዱ ነበር። ደሲታና ወልደ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያወላውል አቋም ከወሰዱት ውስጥ የመጀመሪያዎች ነበሩ። (ወልዴ የሉዊስ ወጥ ቤት ሠራተኛ የነበረ ነው።) ደሲታ ይህንን ሲያደርግ ባለቤቱ የነጭ ሰው ኃይማኖት ስለተቀበለ ድሮ ይደበድበኝ የነበረውን በማቆሙ ሌሎች ሴቶች «ባልሽ ሴት እንጂ ወንድ አይደለም» እያሉ ይሰድቡኛል በማለት ጥላው ሄደች። እርሱ ብዙ ቢነግራትና ቢመክራት «ፈጽሞ አልመለስም» ብላ ነጎደች።

ደሲታ ባለቤቱን አሳምኖ ከእርሱ ጋር እንድትኖር ማድረግ ቢችል ምናልባት እርሷና መላ ቤተሰቧ በተንካኩበት የጥንቆላ ሥራ ይጠመድ ነበር። እናቱም በጥንቆላ የሚያምኑ ስለነበረ በኑሮው ችግር ፈጣሪ ነበሩ። ባለቤቱ ጥላ በመሄዱ ግን ክርስቶስን ለመከተል በወሰደው ውሳኔ ጸና። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደሲታና ሌሎች ሁለት ክርስቲያኖች በሉዊስና ባለቤቱ ለሞተው ልጃቸው መቃብር እንዲቆፍሩና በቀብሩ እንዲረዱ ተመረጡ፥ በዚያ ክርስቲያኖች ለሞትና ሐዘን ያላቸውን ስሜትና መተባበር ተመልክቶ እንደገና የሚያገባ ከሆነ ክርስቲያን ሚስት ማግባት አለብኝ ብሎ ወሰነ።

ደሲታ የአማርኛ ፊደል በመጀመሪያ በሃያ አምስት ዓመቱ አካባቢ ከሚሲስ ሉዊስ የተማረ ሲሆን ጎበዝ ተማሪ ስለነበረ ሌሎችንም ለማስተማር የሚችል ሆነ። ለቀድሞው አውራጃ ገዥ ለብዙ ዓመታት የሠራ በመሆኑ አማርኛ መናገር ስለሚችል ፊደል መማር አላስቸገረውም። አማርኛ እና መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ የሚያነብ በመሆኑ ለሌሎች ክርስቲያኖች ጎበዝና ንቁ መሪ ሆነ። የአዲስ ኪዳን አማኞች መጠመቃቸውን አንብቦ ስለነበረ የጥምቀት አገልግሎት እንዲኖር ሀሳብ አቀረበ።

ከዚህም የተነሣ ጠቅላላ የሚሲዮናያን ኮንፍራንስ በ1926 ዓ.ም. በሶዶ ተጠርቶ ለመጠመቅ የሚፈልጉ ክርስቲያኖች እንዲገኙና በተለይ ለጥምቀቱ አገልግሎት በተዘጋጀ ልዩ ስብሰባም እንዲሳተፉ ተጠየቀ። ሊጠመቁ ከሚጠበቁት ሃያ ሦስት ሰዎች ውስጥ አሥራ ስድስቱ በልዩ ስብሰባው ተገኝተዋል። ከእነዚህ

ውስጥ ደሲታና እውነተኛ ክርስቲያን መሆኗን አረጋግጦ ያገባት አዲስ ሚስቱ ማሚቴ ይገኛሉ።

በመጀመሪያው ስብሰባ እያንዳንዱ የሚጠመቅ አማኝ በግል ስለ ክርስትና ልምምዱ ሚሲዮናውያን ሁሉ ባሉበት ተጠይቆ ከአሥራ ስድስቱ ውስጥ አሥራ ሦስቱ ለጥምቀቱ ብቁና ዝግጁ ሆኑ።

ከዚያም ጥምቀት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራራ ውይይት ተካሂዶ መዳን በእምነት ብቻ እንጂ አንድን ነገር በመሥራት ወይም ባለመሥራት የማይገኝ፥ ጥምቀትም ቢሆን የሚያድን ሳይሆን ለወላጆቻቸው፥ ዘመዶቻቸውና ጎረቤቶቻቸው አማኞቹ ኢየሱስ ክርስቶስ በእነሱ ስለሚኖር አዲስ ሰዎች ለመሆናቸው ምስክር እንደሆነ ተገለጸላቸው።

በመጨረሻ ደሲታ ተነስቶ የሚጠመቁ የወላይታ አማኞችን ተመለከተ፥ እንዲህም አላቸው።

«ከኛ ውስጥ ጥቂቶቻችን በመዋሸት እርስ በርሳችንን ሆነ ነጮችን ማታለል እንችላለን። ነገር ግን ማናችንም ቢሆን እግዚአብሔርን ማታለል ወይም ማሞኘት አንችልም። አንዳንዶቻችን ጋያ ማጨስ ብንተውም ትንባሆ መትከልና አዘጋጅተን ለሌሎች መሸጥን አልተውንም፥ አንዳንዶቻችን ቦርዴ (የሚያሰክር ባሕላዊ መጠጥ) ወይም ጠላ መጠጣት ብናቆምም መጠጡን በቤታችን አስጠምቀን በገበያ ወይም በቤታችን መሸጥ አላቆምንም፥ ሚስቶቻችንም ይህን ማድረግ አላቆሙም። ታዲያ ለእግዚአብሔር ነው የምንዋሸው? እግዚአብሔርን ነው የምናታልለው?

«እግዚአብሔር ልባችንን ያያል፥ እርሱና እኛ እነዚህ አሮጌ ነገሮች ከልባችን ተጠራርገው መውጣት ያለማውጣታቸውን እናውቃለን።»

ከዚያም ወደ ሚስዮናውያኑ በመዞር፡-

«እናንተ ለጥምቀቱ መርምራችሁናል፥ እኛስ ራሳችንን ብንመረምር ትቃወማላችሁ?» ብሎ ጠየቀ።

«በፍጹም! በፍጹም አንቃወምም» ብለው መለሱ ሚሲዮናውያን።

ደሲታ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቶ የሐናንያና የሰጲራን ታሪክ ለአማኞቹ አነበበላቸው። የኢየሱስ ተከታዮች ነን በሚሉ በእነዚህ በሁለቱ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት እንደመጣባቸው ሲያውቁ በጣም ተደነቁ። ከዚህ ቀጥሎ በተደረገው ምርመራ ክርስቲያኖችን በጣም የሚያሳስብ ነገር ግርዘት መሆኑ ተረጋገጠ።

በወላይታ ባሕላዊና ሕብረተሰብአዊ ወግ መሠረት ግርዘት ለአካል ንጽሕናና ጤና ብቻ የሚደረግ ነገር አይደለም። ግርዘት ልጅ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ተካፋይ ሊሆን የሚችል መሆኑ የሚታወቅበት ሥነ ሥርዓትም ነው፥ በዚህ ሥነ ሥርዓት አማካይነት ልጁ ያደገና የጕለመሰ ኃላፊነትንም ለመሸከም የተዘጋጀና የሚችል የጎሣው ወንድ አባል መሆኑ ይታወቅለታል። በመንፈሳዊ መልኩ ደግሞ ያልተገረዘ ወንድ ለመናፍስቱ መስዋዕት ሲቀርብ በሥነ ሥርዓቱ ተካፋይ እንዲሆን አይፈቀድለትም። (በወላይታ ባሕል ግርዘት የሚፈፀመው በሕፃንነት ዕድሜ ሳይሆን ለአቅመ-አዳምና ሔዋን ሲደረስ ነው)።

ከዚህ ባሕላዊ መልኩ የተነሣ እያንዳንዱ የሚጠመቅ ሰው በቀድሞ የወላይታ ባሕልና ወግ መሠረትና ዓላማ ለመገረዝ ራሱን አሳልፎ እንዳይሰጥ ቃል እንዲገባ ለመጠየቅ አማኞች ሁሉ ወሰኑ። (ግዴታው ለአማኞች ሁሉ ማለትም ለወንዶችም ለሴቶችም ነበር፥ የሁለቱም መገረዝ ባሕላዊ ዓላማ ተመሳሳይነት አለው፥ የሴቷ መገረዝ ለማግባትና ልጅ ለመውለድ . . . ወዘተ መድረሷን ያመለክታል፥ የተገረዘ ወንድ ያልተገረዘችውን ሴት በሚስትነት አያገባትም)። በዚህ የሥነ ሥርዓት ጉዳይ ላይ ከተደረገው ውሳኔ የተነሣ ሊጠመቁ ከተጠበቁት ውስጥ ባለመስማማት ሦስቱ ሲለዩ አሥር ብቻ ቀሩ።

ታህሣሥ 1 ቀን 1926 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሚሲዮናውያን ወደ ወላይታ በገቡ በአምስት ዓመት ተኩል የመጀመሪያዎቹ አሥር የወላይታ ክርስቲያኖች በሚስዮኑ ግቢ በነበረው ሰፊ ጉድጓድ ውሃ ተጠመቁ። እነሱም ስምንት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ነበሩ፥ ደሲታ፥ ማሚቴ (የደሲታ ባለቤት)፥ ጬራሞ፥ ፓካሬ (የጬራሞ ባለቤት)፥ ዲያሣ፥ አሬቦ፥ ብሩ፥ ዋንዳሮ፤ ጎዳና፥ እና ካዎና ቃባ ናቸው።

ከሁለት ሳምንት በኋላ ለአማኞቹ የጌታ ራት (ቁርባን) አገልግሎት ሲካሄድ የተዘጋጁት የተለመዱ የወላይታ ምግቦች ማለትም የቦቆሎ ቂጣና በውሃ የተበጠበጠ ማር ነበር። በሥነ ሥርዓቱ ላይ ማሚቴ እንዲህ ብላ ነበር፥ «ክርስቶስ ለእኛ ሲል መሰበሩንና መሰቃየቱን የሚያመለክቱትን እነዚህ ትናንሽ የቂጣ ስባሪዎችን እስካየን ድረስ እግዚአብሔር እንዴት እንደወደደን አልገባኝም ነበር።»

ደሲታም ቁርባኑን ከወሰደ በኋላ አፀፋውን ሲመልስ እግዚአብሔር ጽድቅን እንደሚፈልግ በማሳሰብ ነበር፥ «‹ሳይገባው አይብላ› የሚለውን ቃል እያሰበ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው ራሱ የማይበላውን ምግብ ሌላው እንዲበላ አይጋብዘውም።»

አንድ ሰው «ይህ ማለት ለምግብ ብቻ ነው?» ብሎ ጠየቀ።

«አይደለም! ክርስቲያኖች ሆነን ማድረግ የማይገባንን ነገር ሁሉ ሌላው እንዲያደርግ መፈለግ የለብንም ማለት ነው።

«ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ ጠባብ ነው፥ አዎን ኃጢአትን ላልተወና ላልጠላ ሊያልፍበት እስከማይችል ጠባብ ነው። ነገር ግን ኃጢአቱን ተናዝዞ ወደ እግዚአብሔር ለሚመጣ ትልቅና ግዙፍ ኃጢአተኛ እንኳን የእግዚአብሔር መንገድ እጅግ ሰፊ ነው።»

ስምንቱ ወንዶች ከተጠመቁ በኋላ በመደበኛው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በየተራ ይሰብካሉ። ወዲያው ሦስት ሽማግሌዎች ተመርጠው ኃላፊነት እንዲሸከሙ በወሰኑት መሠረት ደሲታ፥ ዲያሣና ጎዳና ተመርጠው ሁለተኛው የጥምቀት አገልግሎት ሲደርስ የሚጠመቁትን አማኞች በመመርመርና በማጥመቅ አገለገለዋል።

የሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት እድገት የታየባቸው ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች በሳምንት አራት ምሽቶች ይካሄዳሉ፥ ሁልጊዜ ቅዳሜ ማታ አንድ ሚስዮናዊ በገጠር ዞረው እሁድ እሁድ ሲሰብኩ የሚረዳቸውን ልዩ መልዕክት ለወላይታ ሰባኪያን ይሰጣል። ሁልጊዜ እሁድ ማታ አገልጋዮቹ

ልምምዳቸውንና ሳምንቱን በሙሉ ጌታ ያደረገላቸውንና የባረካቸውን ሪፖርት ያደርጋሉ።

ሌሎችም በርከት ያሉ የሚሲዮን ጣቢያዎች መጀመሪያ በደቡብ ምዕራብ በጎፋ ቀጥሎ በአባያ ሐይቅ አጠገብ በጋሞ ተቋቋሙ። የሚሲዮናውያን ብዛት ጨመረ፥ የክርስቲያኖች ቁጥርም ቀስ በቀስ እያደገ ሄደ።

## ምዕራፍ 8. ክርስትናና ባህል

. . . አዲስ ፍጥረት ነው፥ አሮጌው ነገር አልፎአል፥ . እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

2 ቆሮ. 5፡17

«ቦርዴ[1] ከሌለ ቤት መሥራትም የለም! »

የቁጣ ድምፆች የጧቱን አየር ሰንጥቀው ይስተጋባሉ። «ቦርዴ ከሌለ ቤት መሥራትም የለም፥ ቦርዴ ካላቀረብክልን በቤትህ ሥራ አንረዳህም!»

ነገር ግን ከምግብና ቡና በቀር ቦርዴ የሚቀርብ አልሆነም። በብዛት መጥቶ የነበረው ሕዝብ ቀስ በቀስ ወደየቤቱ እየተመለሰ ተመናምኖ ጥቂቶች ማለትም የአዲሱን ቤት ሥራ በዚያን ዕለት ለማስጀመር አቅዶ ሳይሳካለት በመቅረቱ የተረበሸው ዲያሳ እና በምግብና ቡና ዝግጅት የረዱት ጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ ቀሩ።

*　　　*　　　*

በወላይታ ኑሮ ከጥንትም ጀምሮ የጋራና ባሕሉንም የሚመስል ነው። አዲስ መሬትን ማረስ፥ ቤት መገንባት፥ በዓል ማክበር፥ የሞተውን መቅበር እና የመሳሰሉት የሚካሄዱት በጋራ (በደቦ) ሲሆን በዚህም ሁልጊዜ ቦርዴ በብዛት ይጠጣል።

አንድ ሰው (ለምሳሌ ያህል) ቤት መሥራት የሚፈልግ ቢሆን ማድረግ ያለበት ሥራውን የሚጀምርበትን ቀን መወሰንና ማሳወቅ ሲሆን ቀኑ ሲደርስ ዘመዶችና የጎረቤት ሰዎች በግል አንዳንድ እስር ሣር ወይም እንጨት ይዘው ይመጣሉ። ለዚህ የሚመለስላቸው ውለታ የሚጠጡትን ቦርዴ ማቅረብና ራሳቸውም ቤት በሚሠሩበት ጊዜ በዚህ ዓይነት መርዳት ነው።

የወላይታ ክርስቲያኖችም የጀመሩት አዲስ የሕይወት መንገድና ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ታማኝነት ከአሮጌው ጎጂ አኗኗር የሚለያቸው መሆኑን ተመለከቱ። ክርስቲያኖች የሚያሰክር መጠጥ መጠመቅም ሆነ መጠጣት ስላቆሙ ነበር ዲያሣ ለደቦው ቦርዴ ያላቀረበው። ቦርዴ ካልቀረበ ቤቱን አንሠራም ያሉ ወዳጆቹና ጎረቤቶቹ በብዛት የቀረበውን ምግብና ቡና እንኳን እያዩ ሀሳባቸውን አልቀየሩም፥ ስለሆነም ለመሥራት ባለመፈለግ ተመልሰው ወደየቤታቸው ሄዱ።

[1] ቦርዴ ከገብስና ከበቆሎ የሚጠመቅና የሚያሰክር ባህላዊ መጠጥ ነው።

ከዚህም የተነሣ አማኞችና ሚሲዮናውያኑ አዲስ፥ ከባድና ያልለመዱት ችግር ስለአጋጠማቸው ተሰብስበው ተመካከሩ፥ የእግዚአብሔርንም ምሪት ጠየቁ።

በመጨረሻም ምንም እንኳን ባሕሉ የቆየ ቢሆንም ከክርስቲያን ጥሪና ምስክርነት ጋር የሚጋጭና የሚፃረርም ስለሆነ በርዱ ላለማቅረብ በወሰኑት ውሳኔ ላይ ለመጽናት ተስማምተው ከዚህም የተነሣ የሚመጣውን ችግር ለመቋቋም ራሳቸው ተረዳድተው ቤቶቻቸውን ለመሥራት ወሰኑ። ሚሲዮናውያን እንኳን ሳይቀሩ በቤቶቹ ሥራ ከልብ በመሳተፍ በዚህ ለእነሱ ባልተለመደና እንግዳ በሆነ ሥራ ክርስቲያኖችን ረድተዋል።

ለብዙ ቀናት ክርስቲያኖች አዲሱን ቤት ሲሠሩ ተመልክተው ያላመኑ ጎረቤቶችና ዘመዶች ግራ የተጋቡ ቢሆንም ከልብ መሥራታቸውና ጽናታቸው ልባቸውን ነክቷል። ስለሆነም ቤቱን ሠርቶ ለመጨረስ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል እስከተሰበሰበና ከዚያም እስከሚበልጥ ድረስ አንድ በአንድ እየመጡ ይረዱ ጀመር።

*　　　*　　　*

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተ ክርስቲያኖቹ ፍጹም ተለውጠው ከአሮጌው አኗኗር ስለተለዩ አዲስ የአኗኗር መመሪያ ወጥቶ በሥራ ላይ ዋለ። መመሪያ የተዘጋጀው የወላይታ ባህልና ክርስትና ስለተጋጩና ሊስማሙ ስላልቻሉ እንጂ በነጮች ግፊት አልነበረም። ይህ በእምነት ጸንቶ የመቆም ሥነ ሥርዓት መመሪያ አዲስ ክርስቲያኖችን ይበልጥ ብረቱ አድርጎአቸዋል።

በሌላ በኩል መመሪያው በዘመዶችና ወላጆች መካከል እንኳን ሳይቀር ብዙ ችግር (ያለመደሰትና ያለመግባባትን) አስከትሎ ነበር። አንዳንድ ያላመኑ ወዳጆች በርዱ ባይቀርብላቸውም ቤት ሲሠራ ለመርዳት ፈቃደኛ ሲሆኑ ሌሎች ይህንን ሐሳብ አልተቀበሉም። እነርሱ ያለበርዱ የሚሠራ ቤት አይረባም ወይም ፀንቶ አይቆምም ብለው ያምናሉ። የጥንቱን የወላይታ ልማዶችን ካጠፉት ከቅድመ አያቶች መናፍስት ሕዝቡ ነፃ አልወጣም ነበር።

ገና ከመጀመሪያው ክርስትና በወላይታ ክርስቲያኖች ዘንድ ከውጭ እንደመጣ ሳይሆን የእነሱና የተለመደ ነገር ሆነ። ይህም ሚሲዮናውያኑ የተመኙት ነበር። ሚሲዮናውያኑ የወላይታ የአኗኗር ዘይቤ በተቻለ መጠን ተጠብቆ እንዲቆይና በወላይታ ቤተ ክርስቲያንም ከመሠረታዊው ክርስትና ውጪ የሆነው የምዕራባውያን ባሕላዊ ዘዴ እንዳይለመድ ነበር የፈለጉት።

ከዚህም የተነሣ ወላይታዎቹ ቤተ ክርስቲያናቻቸውን የሚሠሩት በራሳቸው ቤት ቅርጽና መልክ ነበር። ምንም እንኳን በሚሲዮኑ ውስጥ የተሠራው የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎችም የጣቢያው ቤቶች በጭቃ ጡብ የተሠራ ቢሆንም ክርስቲያኖቹ ቤቱን እንደ ስብሰባ አዳራሽ እንጂ እንደ ቤተ ክርስቲያን አይቆጥሩትም ነበር። የወላይታ ቤት ክብ ሆኖ ከግንድና ከሣር የሚሠራ ነው። በመጀመሪያ በይ መሰል ክብ ጉድጓድ ተቆፍሮ ግድግዳ እንዲቆም ይደረጋል። ግድግዳውም ከታች አንስቶ እስከ ላይ ድረስ በሲባጉ ወይም በወፎች ይታሠራል። ቤቱ አንድ በር ብቻ ያለው ይሆንና መስኮት አይኖረውም።

የመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያናት የተሠሩት ሚስዮናውያን ከወላይታ ለቀው ከወጡ በኋላ ሲሆን ቤቶቹ ከመኖሪያ ቤቶች ጋር ሲነፃፀሩ ሰፊና ለአየር ማስገቢያም ሲባል ብዙ በሮች ያሏቸው ነበሩ። ወላይታዎች «ዎሣ ኬታ» ማለትም «የፀሎት ቤት» ይሏቸው።

የወላይታ «ፀሎት ቤቶች» ወንበር አያስፈልጋቸውም፥ አማኞቹ ለፀሎቱ በሚሲዮን ጣቢያ ይሰበሰቡ በነበረበት ጊዜም ምንም ዓይነት መቀመጫ አይጠቀሙም ነበር። አማኞቹ ቤተ ክርስቲያን በሚገቡበት ጊዜ ቤቱ ብዙ ሰው እንዲይዝ የገባ ሁሉ ያለ መስመር በተገኘው ቦታ ዝም ብሎ መቀመጥ አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶችና ወንዶች ተለይተው ይቀመጣሉ፥ ተናጋሪውም (ሰባኪው) የመሰበኪያ ሰገነት የለውም።

የምዕራባዊያንን ቤተ ክርስቲያን የዝማሬ ቃና የወላይታ ክርስቲያኖች አልወደዱትም፥ ሚሲዮናውያኑ መዝሙሮቹን ተርጉመው ያቀረቡ ቢሆንም ከወላይታ የአዘማመር ስልት ጋር የማጣጣምና ለወላይታ ክርስቲያኖች ጆሮ የሚጥም የሚገባቸውና የሚያደንቁትም ሆኖ አልተገኘም። ቀስ በቀስ የወላይታ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ስልት ማጠናቀር ጀመሩ።

የወላይታ አዘማመር ሁለቱ ድምፆች የሚደጋገሙበት ዜማ ነው፥ መሪው ሲዘምር ጉባኤው በጋራ ተቀብሎ አዝማቹን በመዘመር አጸፋውን ይመልሳል። የወላይታ ክርስቲያኖች በየትም ለመዘመር በሚችልበት ቦታ ማለትም በሥራ ላይ ሆነው በጉዞ ላይ ሁሉ ይዘምራሉ።

ይህም ወላይታዎች የሚረዱትና ሐሳባቸውንም በበቂ ሁኔታ ሊገልጹ የሚችሉበት የአዘማመር ስልት ነው። ቃሎቹና ዜማዎቹ የሚፈልቁት እንዲያው ከልምዳቸው፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ካላቸው ፍቅርና ለክርስትና ሕይወት ካላቸው ግንዛቤ ነው። በመዘመር ተመስጦ የሚገኝ አንድ የመዝሙር መሪ ወዲያው አንድ አዲስ መዝሙር ሊያጠናቅርና ሊያስዘምር ይችላል።

በጣም ተወዳጅ ከነበሩት መዝሙሮች አንዱ «እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው» የሚል ነው። መሪው ወይም ዜማ አውራጅ «እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው» ብሎ ሲዘምር ጉባኤውም «እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው» ብሎ ይቀበላል።

እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ሰጪ ነው (መሪ)

እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው (ተቀባይ)

እግዚአብሔር የሚያሸከመው ቀላል ቀንበር ነው (መሪ)

እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው (ተቀባይ)

እግዚአብሔር ለወንዶችም ለሴቶችም የሚሰጥ ነው

እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው

እግዚአብሔር ሰላምና ደስታ የሚሰጥ ነው

እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው

እግዚአብሔር ከሰዎች በላይ ነው
እግዚአብሔር የሕይወት ቃል ነው።

በለቅሶ በተለይም በቀብር ጊዜ የሚዘመር ደግሞ «እንነሣለን» የሚል ነው።

እግዚአብሔር ከመቃብር ውስጥ ሲጠራን (መሪ)
እንነሣለን (ተቀባይ)
እርሱ ለርሱ ለሆኑት ሲመጣ (መሪ)
እንነሣለን (ተቀባይ)
በፊት የሞቱትም ሁሉ ሲነሡ
እንነሣለን
እግዚአብሔር ከመቃብር ያስነሳናል
እንነሣለን
እርሱም በማንጠብቅበት ሰዓት ይመጣል
እንነሣለን

ከዚያም መዝሙሩ ሳይቋረጥ መሪው የመልዕክቱን አዝማች ይቀይርና
ይህ(ች) ዛሬ የተለየን (ች) ወንድማችን (እህታችን)
ይነሣል (ትነሣለች)
መቃብር ይዞት (ይዟት) አይቀርም
ይነሣል (ትነሣለች)
እንደገና እናየዋለን (እናያታለን) . . .
በዚያ በሽታ በሌለበት ሀገር እናየዋለን . . .
በዚያ ችግር በማይታወቅበት አገር እናየዋለን . . .
በዚያ ግብር በማንጠየቅበት አገር እናየዋለን . . .
በዚያ ረሐብ በሌለበት ሀገር እናየዋለን . . .
በዚያ አዳዲስ ልብሶች ለብሰን እናየዋለን . . .
በእርግጥ እናየዋለን፥ እናየዋለን . . .
እንነሳለን
በኢየሱስ ቤት እንገናኛለን
እንነሣለን
በኢየሱስ ቤትም ለዘለዓለም እንኖራለን

# ክፍል አራት፡- የጦርነቱ እሳት

## ምዕራፍ 9. ጦርነቱ ተጀመረ

እናንተ በዚህ ሰልፍ የምትዋጉ አይደላችሁም . . .
2 ዜና መዋዕል 20፡17

ደጃዝማች አበበ ወደ እኔ ዞረው «አንተና ሚስተር አህማን ኢጣሊያኖች ናችሁ፥ እኔና ሚስተር ፎርስበርግ ግን አማሮች ነን» ብለው ተናገሩ።

እኛ ጎፋ በሚገኘ በሚስተር ፎርስበርግ ቤት ጥሩ ምሳ ከበላን በኋላ ተቀምጠን ሳለን ነበር ደጃዝማች አበበ ይህንን ከከፊል ፈገግታ ጋር የተናገሩት። አመጣጣቸውም ለወዳጅ ጥየቃ ብቻ እንዳልሆነ ካወቅነውም በላይ ካለምንም መጠለያ ከሚሲዮኑ ጣቢያ በታች ባለው ሸለቆ ሌሊቱን ሰፍረው ያደሩ በመቶ የሚቆጠሩ የጎፋ ወታደሮችን አስታወስን። ጨዋታችን የሚጥም ይሁን እንጂ የገኘው አምስት የአንበሳና የነብር ግልገሎች ወዲያና ወዲህ እየተሯሯጡ ወደ እኛም በመቅረብ እግሮቻችንን እያሸተቱ ሲጫወቱ ስለ ሰጋን አእምሮአችን አላረፈም ነበር።

ጊዜው 1928 መስከረም ወር መጨረሻ ሳምንት ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሁ ገና አንድ ዓመት አልሆነኝም። እኔ ዋልተር እና ማርሴላ አህማን ለአዲስ ሚሲዮን ጣቢያ የሚሆን ቦታ ለመፈለግ በበቅሎ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ተራሮች እያቋረጥን ተጓዝን። በጋሞና በጎፋ ጣቢያዎች መካከል ያለው መንገድ የአንድ ሣምንት ጉዞ የሚጠይቅ ሲሆን ለአዲሱ ሥራችን ቦታ የፈለግነውና ለማግኘት ተስፋ ያደረግነው በእነዚህ ጣቢያዎች መካከል ነበር። የዝናቡ ወቅት እያበቃ ቢሆንም ወንዞች ሞልተው ይፈሳሉ፥ ከተራራው ላይም ከፏፏቴዎች ውሃ በብዛት ሲወርድ ይታያል። አረንጓዴ ምንጣፍ የሚመስለው የገጠር መሬት ማርከን በየቦታው መቆም ነበረብን። በእነዚሁ ባረፍንባቸው ቦታዎች ሁሉ ያገኘናቸው እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ገና ስለ ኢየሱስ ሰምተው የማያውቁና ሳይዘገይ መስማት እንዳለባቸው ማወቅ ቻልን።

ከሶዶ ጎፋ ጉዞ አንድ ሳምንት ያህል የወሰደብን ሲሆን በጎፋ አንድ ዓመት ያህል ከቆዩ ከፎርስበርግ ቤተሰብ ጋር ባለፉት አራት ወይም አምስት ቀናት የሚያስደስት ቆይታና ኅብረት አድርገናል። ነገር ግን በጨዋታችንና በወጋችን መሀል በወቅቱ ይነፍስ የነበረውን የጦርነት ወሬ ማንሣታችን አልቀረም።

በ1927 ዓ.ም. ኢጣሊያ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ-ሶማሌ መካከል ባለው በረሃማው ግዛት የድንበር ውዝግብን ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያን ለመውረር ታስፈራራና ትዘጋጅ ነበር። ዋናውና ግልጽ ዓላማ ግን የኢጣሊያው አምባገነን ዱቼ ሞሶሎኒ ኢትዮጵያንም ጠቅልሎ ለራሱ ሊፈጥር የሚመኘውን የምሥራቅ አፍሪካ ግዛት እውን ለማድረግ ነበር።

የሞሶሎኒን ፍላጐት ለማርካትና ቀጥተኛ ግጭትን ለማስቀረት እንግሊዝና ፈረንሳይ ከእርሱ ጋር ለወራት ድርድር ሲያደርጉ ቆይተው አልተሳካላቸውም። ከዚያን በኋላ እነዚህ መንግሥታት ኢትዮጵያን ለመርዳትም ሆነ ወረራውን ለመቃወም ባለመፈለጋቸው፥ የዓለም መንግሥታት ማህበርም (ሊግ ኦፍ ነሽንስ) ወላዋይ - ደካማና በመሞት ላይ የነበረ በመሆኑ ወረራው የማይቀር ሆነ።

ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ሀገራቸውን ከወረራ ለመከላከል ብቻቸውን (ያለውጭ እርዳታ) እየተዘጋጁ ነበር። ድንገት ጦርነት ሲመጣ ያልጠበቅነው ነገር ስለነበር መደንገጣችን አልቀረም። በርግጥም ጦርነቱ መጣ፥ የደጃዝማች አበበም ጦር መንቀሳቀስ ጀምሯል።

ጧት ደጃዝማች አበበ እና ጦራቸው የኢጣሊያን ወራሪዎች ለመውጋት ይንቀሳቀሳሉ። መጓሪያዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ አዘጋጅቶ (ይዞ) የመጀመሪያውን ሌሊት ከቤት ወጥቶ በቅርብ ማደር የአማራ የዘመቻ ደንብ በመሆኑ ወታደሮቹ በዕለቱ ከሰዓት በኋላ ከቤተ መንግሥት ወጥተው ከሚሲዮኑ ጣቢያ በታች ባለው ሸለቆ ሰፍረው አደሩ። ከእነዚህ አብዛኛዎቹ ዳግመኛ ወደ ጎሩ የሚመለሱ መሆናቸው ያጠራጥራል።

ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍለ ግዛቶችና የጦር ካምፖችም በሺህ የሚቆጠሩ ተዋጊዎች ሀገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን ከወረራ ለመከላከል ወደ ዋና ከተማውና ወደ ጦር ግንባር በመጉረፍ ላይ ነበሩ። እጅግ በጣም አነስተኛ የጦር ትምህርት፥ ጥሬ ጀግንነትና ወኔ ብቻ ያለው የንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት እጅግ በጣም ዘመናዊና ሜካናይዝድ ከሆነው ከሞሶሎኒ ሠራዊት ጋር ጦርነት ሲገጥም ውጤቱን መተንበይ ሊያስቸግር ይችላል።

ሆኖም ጦርነት ወዳለንበት አካባቢ ከመድረሱ በፊት በጋሞ የሥራ ጉብኝታችንን አጠናቅቀን ወደ ሶዶ ተመለስን። በመንገዳችንም ሁሉ ሀገሪቱ ውብቷ ጠፍቶ ጨለማ መልበሷን ተመለከትን፥ የእኛና የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ዕጣ ምን እንደሚሆን ገና አላወቅንም።

*   *   *

ወጣ ገባ በሆነው በሀገሪቱ የሰሜን ክፍል አንድንሠራ ዶክተር ቢንግሃም (በጊዜው የኤስ. አይ. ኤም. ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር) ለወጣቶች ባደረጉት ጥሪ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መጣሁ። በሕዳር 22 ቀን አዲስ አበባ እንደገባሁ ነበር ዶክተር ላምቤ ወደሶዶ ወርጄ በሆስፒታሉ ሥራ እንድረዳ የነገሩኝ። በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ወረራውና ጦርነቱ የማይቀር መሆኑ ግልጽ እየሆነ ስለመጣ በዚያ ሥራ መጀመሩ የሚያዋጣ መስሎ አልታየንም። በሌላ በኩል ለሚሲዮኑ እንድሠራ በእግዚአብሔር ከመጠራቴ በፊት የአርኪቴክት (የሕንፃ ሥራ) ኢንጂነሪንግ ሙያ ማጥናት መጀመሬ ለሆስፒታሉ ሥራ ወደደቡብ እንድሄድ ይጋብዘኛል። በተጨማሪም ዶክተር ፐርሲ ሮበርት፥ ሚሲስ ፐርሲ እና ሉዊስ ብርግስ በሶዶ ለጀመሩት የሕክምና ሥራ ተስማሚ ሕንፃ ስለሚያስፈልጋቸው የሆስፒታሉን ሕንፃ ማጠናቀቅ አንገብጋቢ ነበር።

ከአዲስ አበባ ሶዶ መጓዝ በፈረስና በቅሎች ሁለት ሳምንት ወሰደብን። ለሆስፒታሉ የተመላላሽ ሕክምናና ሰርጂካል ክፍሎች መሥሪያ ገና መሬት

ሳንቆፈር ጥር 24 ደረሰ። ለህንፃው የሚያስፈልጉ እንደበሮች፥ መስታወት ፍሬሞች፥ ምስማር ጣሪያዎች ያሉ ዕቃዎች በግመሎች ተጭነው ከአዲስ አበባ ሶዶ ለመድረስ ሦስት ሳምንት ፈጀ። ድንጋይ ጭቃና ባሕርዛፍ በአካባቢው በብዛት አለ። በበጉ ፈቃዳቸው ከሚረዱንና በሙያው ሥልጠና ከሌላቸው የወላይታ ሠራተኞችና አንድ ሕንዳዊ አናጢ ጋር ሥራውን በቀስታም ቢሆን ብዙ መግፋት ቻልን። ነገር ግን ከሦስት ወራት በኋላ ገንዘብ በማለቁ ለሕንዳዊው አናጢ የምንከፍለውን አጣን። ወዲያው ጦርነቱ የተጀመረ ቢሆንም የሆስፒታሉ ግንባታ ቀጥሎ ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ባያልቅም አገልግሎት ላይ ዋለ።

1928 ዓ.ም. መስከረም መጨረሻ ላይ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረር ስትጀምር የአሜሪካንና የእንግሊዝ (ብሪትሽ) ኢምባሲዎች ዜጐቻቸው በአስቸኳይ ሀገሪቱን ለቀው ካልወጡ ለደህንነታቸው ኃላፊነት የሌላቸው መሆኑን አስታወቁ። ይኸው ዜና ለዋናው የሱዳን ኢንቲሪየር ሚስዮን (ኤስ አይ ኤም) ዳይሬክተር ለዶ/ር ሮውላንድ ቢንግሃም ተላልፎላቸው አንድ ቀን ከሚሲዮኑ የጸሎት ፕሮግራም በኋላ መልሳቸው ደረሰ። መልዕክታቸውም እንደሚከተለው ነበር።

> እናንተ የምትገኙት ከእንግሊዝ ንጉሥ ወይም ከአሜሪካን ፕሬዝዳንት በሚበልጥ (በእግዚአብሔር) ትዕዛዝ ሥር ነው። ማድረግ ያለባችሁን ትዕዛዝና መመሪያ ከእርሱ (ከእግዚአብሔር) ተቀብላችሁ ፈጽሙ፥ እኛም ከእናንተ ጋር ነን። በተረፈ እናቶች ከሕፃናት ጋር መመለሳቸውን እንደግፋለን።

እኛም በእግዚአብሔር ጥሪ እዚህ የመጣነው ለእነዚህ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወንጌል ለማድረስ ሲሆን አሁን ግን ይበልጥ እኛን የሚፈልጉበት ወቅት ሲመጣ ትተናቸው መሄድ ትክክል ያለመሆኑን ተማምነን በአንድ ድምፅ በኢትዮጵያ ለመቆየት ወሰንን። መቆየት አደገኛ እንደሚሆንብን ብናውቅም እግዚአብሔር ወደ ሌላ አማራጭ አልመራንም። ከዚያን በኋላም በተከታታይ ከታዩት ሁኔታዎች አንፃር የእርሱ ምሪት እንድንቆይ ሆነ።

አዲስ አበባ ሚያዚያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. በጠላት ተያዘች። ንጉሡም ከከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው ጋር የኢትዮጵያን ነፃነት ለማስመለስ የዓለም መንግሥታት ማህበርን ያልተሳካ እርዳታ ለመጠየቅ ሀገር ለቀው ሄዱ። ዋና ከተማይቱ ማዕከላዊ አመራርና ቁጥጥር ስላጣች ግርግር ትርምስና ረብሻ ሞላባት፤ በጦርነቱ የተሸነፉ የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደመንደራቸው ሲያፈገፍጉ ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ በመንገዳቸው እየዘረፉና እያቃጠሉ ስለሚያልፉ በመንገድ መጓዝም የማያስተማምን ሆነ።

እኔም እቃዎቼን ከታትቼና አስሬ ከሶዶ ወደ ሰሜን ወደ ዋና ከተማ (አዲስ አበባ) በእንስሳ ለመጓዝ ተዘጋጅቻለሁ። ታሪኩን የየቀኑ ማስታወሻዬ ራሱ ይናገር።

<u>ሚያዚያ 21 1928 ረቡዕ</u>

ባለፈው ምሽት ሺፋሮ ሳይጠበቅ የጊዜው አስጊ ሁኔታ እስከሚያልፍ ሁላችንም ጸጥ ብለን እንድንጠብቅ የሚያሳስብ ደብዳቤ አዲስ አበባ ከሚገኘው ከክላራንስ ዳፍ ይዞ ደረሰ። በመልዕክቱ እኔ ባልጠቀስም ከሚስተር አሆግን

ጋር ለመመካከር ስለምፈልግ እርሱም በጥቂት ቀናት ውስጥ እስኪመለስ ለመቆየት ወሰኜ ነበር።

ሚያዚያ 29 ሐሙስ

በዚህን ቀን ያልታሰበ ነገር ተፈጸመ። ጧት ሁለት ሰዓት አካባቢ በርካታ የኢጣሊያ አውሮፕላኖች በገዥው ቤተ መንግሥት (መኖሪያ)፥ በከተማውና በገጠሩ ቦምብ እየጣሉና ማሽንጋን እየተኮሱ የገጠሩን ጸጥታና የከተማውን ጎዳናዎችን በጠበጡ።

ግንቦት 1 ቅዳሜ

በዚህ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ከተማው ወጣንና የመንግሥት ፖስታ ገና ያልደረሰና ቴሌፎንም የተቋረጠ መሆኑን አረጋገጥን፥ ብዙ ወሬም እየተዛመተ ነበር።

ግንቦት 3 ሰኞ

አሁንም ፖስታ አልደረሰም

ግንቦት 5- ረቡዕ

ዶ/ር ሮበርትስ እና ሚስተር ዌብ በመመለስ ላይ ያሉ መሆናቸውን የሚገልጽ መልዕክት ያለበት የሲዳሞ ፖስታ በዚህ ቀን ቀትር ላይ ደረሰን። እነሱም ማታ በአሥራ አንድ ሰዓት ሲደርሱ አዲስ አበባ በሚያዝያ 27 ቀን በጣሊያኖች መወረሯን ጦሩም በጣሊያን ተሸንፎና ተበትኖ ወደ ደቡብና ምዕራብ እያፈገፈገ ዋና ከተማይቷንም የዘረፏት መሆኑን አሰሙ። ወታደሮቹ እኛንም በመንገዳቸው ሊያገኙን ይችሉ ነበር።

ግንቦት 6 ሐሙስ

ይህንን አሳዛኝ ዜና ለመንገር ሚስተር አህማን ተጠባባቂ ገዥውንና ባለሥልጣኖቹን ወደ ሚስዮኑ ግቢ ጠራቸው። ባለሥልጣኖቹ በብዛት ሆነው ወደ ግቢያችን ሲደርሱ የአካባቢው ወላይታዎች አይተው በመጠራጠርና ስለ እኛ ደህንነት በማሰብ ጦርና ጎራዴ ይዘው ከመጡ በኋላ በሚሲዮኑ ዙሪያ ያሉ ጥሻዎችን ተጠግተው ቆሙ። በአጠቃላይ የወደፊቱ ሁኔታ ጥሩ ባይመስለንም እግዚአብሔር አሁንም በዙፋኑ ያለና ዜግነታችንም ከሰማይ በመሆኑ እናመሰግነዋለን። ቀጥሎ ምን ይመጣ ይሆን?

ግንቦት 7 አርብ

ውድ ወዳጆቼ የሆኑት ቶም ደቭርስና ክሊፍ ሚቼል በካሲ በረሃ የተገደሉ መሆኑን የሚገልጽ የስልክ መልዕክት ከሲዳሞ ከአላን ስሚዝ ደረሰን። ሚያዝያ 20 ቀን ከሚስተር ዳፍ ወላይታ እንድንቆይ መልዕክት በተቀበልኩበት ጊዜ ሃምሣ ማይሎች ያህል ወደ ምሥራቅ ርቀው በሲዳሞ ለነበሩት ለእነዚህ ወዳጆቼ መልዕክቱን አስተላልፌላቸው ነበር። ምክንያቱም እነርሱም ወደ አዲስ አበባ ለመንቀሳቀስ እቅድ እንደነበራቸው እንዲያውም ቶም ከሦስት ሳምንት በፊት እዚህ መጥቶ በነበረ ጊዜ አብረን ለመጓዝ ተስማምተን ስለነበር ነው። ቶም እኔና እርሱ ለመገናኘት ከወሰንንበት ቦታ ጥቂት ማይሎች ራቅ ብሎ የተገደለ መሆኑን ማመን አልቻልኩም። እንደተነገረው ሚያዚያ 29

በተለመደ አኳኋን ለተለመደ ባሕላዊ ጉዳይ ገደሏቸው። (የእርሲም ሆነ የአንዳንድ ጎሣ አባላት ለጋብቻ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት ሌላ ወንድ ገድለው በመሰለብ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው)። አእምሮአችን ምድራዊ በመሆኑ እነዚህን ነገሮች መረዳት አንችልም። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር ይገልጥልናል።

ግንቦት 8 ቅዳሜ

በአማራና ማረቆች (ሐዲያ) መካከል ጦርነቱ ቀጥሎ ቦዲቲ (ከሶዶ በስተሰሜን የሁለት ሰዓት መንገድ) ደርሷል። (የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ኢጣሊያኖች እስከሚደርሱ በየቦታው የጎሣዎች ግጭት ነበር)። የመጀመሪያው የተሸነፉ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቡድን በዛሬው ዕለት ከገዥው ቤተ መንግሥት ደርሷል። እንደሚባለው ከሆነ ወታደሮቹ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በመንገዳቸው ሁሉ እየዘረፉና እየገደሉ መጥተዋል። አሁን ደግሞ ከአርጌ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት ባለው ሜዳ ሰፍረዋል።

ግንቦት 9 እሁድ

ወታደሮቹ የመንግሥት ገንዘብ ቤት ሰብረው ገንዘብ ለመዝረፍ ቢጥሩም ተጠባባቂ አስተዳዳሪው ይህንን እንዳያደርጉ ሦስት ሺህ ብር እንደሰጧቸው ሲነገር ሰምተናል።

ግንቦት 10 ሰኞ

ቀን መደበኛ ሥራችንን ለማከናወንና ማታ ማታ ግን ሁላችንም በአንድ ቤት ውስጥ ብናድር የሚሻል መሆኑን አምነን ወሰንን። ቁጥራችን ስምንት ነበር፡- ሚስተርና ሚሲስ አህማን፣ ሚስተርና ሚሲስ ሮበርትስ፣ ሚሲስ ሉዊስ ብርግስ፣ ጆን ትሬዊን፣ አላን ዊብ እና እኔ። የቤቱን ቀዳዳዎች ሁሉ ደፈንን፣ በሮችንና መስኮቶችንም በባሕር ዛፍ ግንዶች አጠናከርን።

ግንቦት 16 እሁድ

ጥቂት ቀናት በፀጥታ ከቆየን በኋላ ዛሬ ትንሽ ተደናገጥን። አምነው ከተጠመቁት ውስጥ አንዱ ካምና ቃባ ወደ እኛ መጥቶ ወታደሮች በከተማ ወደ እርሱ ቀርበው ገንዘብ የምናስቀምጥበትን ቦታ ሲጠይቁት የገንዘብ ማስቀመጫ ቦታ የማያውቅ መሆኑንና እንዲያውም ገንዘብ ያላቸው አይመስለኝም ብሎ እንደመለሰላቸው ነገረን። ነገር ግን ፀሐይ ከመጥለቁ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ሃምሳ ያህል የታጠቁ ሰዎች በግቢው በታችኛው መጨረሻ ተሰብስበው ጨለማን የሚጠብቁ መሆኑን ለማወቅ ቻልን። ከመሸ በኋላ በሁለት ሰዓት አካባቢ ፈጣን ተኩስና ጥይቶች ከቤታችን በላይ እያፏጩ ሲበሩ ሰማን። መብራትም በሙሉ በአንድ ጊዜ ጠፋ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሚስተር አህማን እኔና አላን ሦስታችን ውጭ ወጥተን ለመቃኘትና የሚታይ ነገርም ካለ ለማየት ጠይቆን ከቤቱ በኋላ በኩል ወጥተን በማድቤቱ አጠገብ በመሆን ሰዎቹ የሚሲዮኑን ግቢ በመከበብ ላይ መሆናቸውን አየን። የሚሲዮኑ ግቢ የታጠረው በቀላሉ ሊቃጠል በሚችልና የሕፃንን ጉልበት እንኳን ሊቋቋም በማይችል አንድ ሜትር ያህል ከፍታ ባለው የበቆሎ አገዳ ነበር። ግቢውን ፈጽመው ሲከቡና ደጋግመው በጠመንጃቸው ሲተኩሱም ተመለከትን፣ ከአንድ ሰዓት ያህል በኋላ ግን ሁሉንም ትተው

ሄዱ። ወደ ግቢው ለምን እንዳልገቡና ያሰቡትን እንዳልፈጸሙ የምናውቅበት መንገድ አልነበረንም። ቀደም ሲል ድምፃቸውን እንደሰማነው ከሆነ ግን ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመካከላቸው ክርክር ነበር። እኛ ግን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መኖሩ ይታወቀን ነበር። እርሱ እኛን ለማዳን ሲል ምናልባት በእነርሱ ልብ ፍርሃትን ሞልቶ ወይም ሌላ ነገር አድርጎ ይሆናል።

ግንቦት 20 ሐሙስ

የምንኖረው ከቀን ወደ ቀን ነው። ዛሬ ማለዳ አንድ የአርመን ነጋዴ በተረበሸ መንፈስ ከከተማ መጥቶ ሰዶ ያሉ ወታደሮች የውጭ ዜጐችን ሁሉ ገድለው ንብረታቸውን ለመዝረፍ እያደሙ መሆኑን ነገረን። ከሰዓት በኋላ ወልዴና ቱሹዴ ከጋሞ ደርሰው እዚያ ያሉት ወገኖችም ያላቸውን ሁሉ መዘረፋቸውን በሕይወታቸው ላይ ግን ምንም አደጋ እንዳልደረሰ አሳወቁን። ትንሽ የፈራን ብንሆንም እግዚአብሔር በቃሉ እስካሁንም ሆነ ወደፊት ታማኝ ስለሆነ በእርሱ እምነታችን የጠነከረ ነበር። የሚመጡት ቀናትና ጊዜያት ምንም መልክ ቢይዙ እግዚአብሔር ታማኝ አድርጎ እንዲያቆየን ፀሎታችን ነበር።

ግንቦት 21-ዓርብ

ይህ ወርሃዊ የፀሎት ቀን ነበር። ሚስተር አህማንና ሚስተር ሮበርትስ ከሲዳሞ አላን ስሚዝን ከጨንቻ ደግሞ ሐሮልድ ስትሪትን በስልክ ለማነጋገርና ከባለሥልጣኖች ጋር ለመመካከር በሦስት ሰዓት ወደ ከተማ ወረዱ። ሌሎቻችን ተሰብስበን አስደናቂ የፀሎት ጊዜ አሳለፍን። ወደ ከተማ የሄዱትም ሚስተር ስሚዝንም ሆነ ስትሪትን ሳያገኙና ሳያነጋግሩ ተጠባባቂ አስተዳዳሪው ግን የፖሊስ ጥበቃ ለመመደብ ቃል ገብተውላቸው በሰባት ሰዓት ተኩል ላይ ተመለሱ። በስምንት ሰዓት ለከሰዓቱ ፀሎት ገብተን በመንፈስ እጅግ ተባረክን። ሚስተር አህማን ከ2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 20 አነበበልን። በጥዋቱ ፕሮግራማችን ጆን ትሬዊን ያነበበልን ከዚህ ምዕራፍ ቢሆንም ሚስተር አህማን ይህንን አላወቀም ነበር። ይህ አጋጣሚ ለኢዮሳፍጥ «እናንተ በዚህ ሰልፍ የምትዋጉ አይደላችሁም . . . ዝም ብላችሁ ቁሙ» ተብሎ የተሰጠውን መመሪያ ለእኛም አረጋገጠልን።

ግንቦት 22 ቅዳሜ

በጋሞ ያሉ ወገኖቻችን ሁኔታ በጣም ስላሳሰበን እነርሱን ወደ እኛ ለማምጣት በቅሎችና ተሸካሚዎችን ፈልገን አልተሳካልንም። ቦምብ ባይወረውርም አንድ የጦር አውሮፕላን ዛሬ በከተማውና በግቢያችን ላይ ሲበር በውጪው ዓለም ትዝታ ተዋጥን። ቤተሰቤም የላከሁላቸው ደብዳቤዎች ሁሉ በአሁኑ ጊዜ ሊደርሳቸው ስለሚችል እግዚአብሔር እንዲያበረታቸውና ከእኔ ጋር እንዳለ እንዲያረጋግጥላቸው እጸልያለሁ።

ግንቦት 30 እሁድ

ከጦር ሜዳ የሚመለሱ ወታደሮች በቡድን እየሆኑ ግቢያውን በሚያቋርጠው መንገድ አለፉ። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ወዳጅነትን የሚያሳዩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አይደሉም።

እነርሱም እየጮኹ፣ እየዛቱና ጠመንጃቸውንም ወደ እኛ እየደገኑ ሲያስፈራሩ እኔ በቤቱ ፊተኛው በር ቆሜ ነበር። እግዚአብሔር እጃቸውን ይዞ ይሆናል ምንም አልደረሰብንም።

ሰኔ 6 ቅዳሜ

ለመኝታ ወደየቤታችን (ሌሊቱን ለማሳለፍ) ገባን።

ሰኔ 8 ሰኞ

ዛሬ ብዙ ያለመረጋጋት አለ። የአገሬው ሰዎች መጥተው ወታደሮች ሊዘርፉን የሚመጡ መሆኑን ነገሩን። ወታደሮቹ በሀገረ ገዥው ላይ አምጸው የውጭ ሀገር ሰዎችንና የሀገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤትን ለመዝረፍ እንዳይከለከሉ ይጠይቃሉ። ወላይታዎቹ ይህንን በመፍራት መጥተው ነገሩን። እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ጠብቆናል፥ አሁንም ሊጠብቀን ይችላል። ጆርጅ የተባለ የግሪክ ነጋዴ እኔ ለመሄድ ከወሰንኩበት አንድ ሳምንት ቀድሞ ከሶዶ አዲስ አበባ ሲሄድ ሲልጤ አካባቢ መገደሉን ዛሬ ሰማን። አቤቱ እግዚአብሔር ለባሪያህ (ለእኔ) ደግ፥ አፍቃሪና ታማኝ ሆነህለታልና እኔም ታማኝ እንድሆንልህ እርዳኝ። የነርሶች መኖሪያ ቤት የውስጥ ግድግዳዎችን ሥሰራ ዋልኩ።

ሰኔ 12 አርብ

ተጨማሪ እና ብዙ ወታደሮች በቡድን እየሆኑ የሚሲዮኑን ጣቢያ አቋርጠው አለፉ። ወደ ጣቢያችን እስከሚደርሱ ድረስ እየዘረፉና እየገደሉ ከመጡ በኋላ ጣቢያችንን በስነ ሥርዓት አቋርጠው አለፍ እንዳሉ ወዲያው ዝርፊያቸውን ቀጠሉ። የእርሱ ጦር ስለሚጠብቀንና እርሱ ከኛ ጋር መኖሩ በግልጽ ስለሚታወቀን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። . . . የነርሶችን ቤት ልስን ብቻ ሲቀር-አጠናቀቅን።

ሰኔ 13 ቅዳሜ

ፎርስበርግና ባለቤቱ ከስድስት ቀን ተኩል ጉዞ በኋላ ከጎፋ ዛሬ ገቡ። ሚሲስ ፎርስበርግ የትርፍ አንጀት ቀዶ ጥገና ሊደረግላት ነው። ልትወልድም ደርሳለች። የተደረገላት ቀዶ ጥገና በዶ/ር ሮበርትስ በመልካም ሁኔታ የተከናወነ ከመሆኑም በላይ በዚሁ በአዲሱ ሕንፃ ውስጥ ባለው ክፍል ከተካሄዱት ውስጥ የመጀመሪያው ዋና ቀዶ ጥገና ነበር።

ሰኔ 21 እሁድ

እኛ ዕለቱን በሰላም ያሳለፍን ቢሆንም በአቅራቢያ ያሉ ወላይታዎች ከግረቆች ጋር ለመዋጋት አሥራ አምስት እና ሃያ እየሆኑ በቀትር አካባቢ ሄደዋል። ትናንት ገዥው ጦር መወርወር የሚችል ሁሉ ወደ ጦርነቱ እንዲሄድ፥ ያልሄደ ግን በገበያ መሐል በስቅላት እንዲቀጣ አዋጅ አውጥተዋል።

ሰኔ 27 ቅዳሜ

በዚህ ቀን «በባልዲ» ሲያፈስ ስለዋለ ከዚህ ይልቅ በሀገራችን ይሻለን ነበር። እኔና አላን ዌብ ከጋሞ የሚመጡትን ስትሪትንና አብረውት የሚመጡትን ለመቀበል በእንስሶቻችን ተቀምጠን ብንወጣም ልናገኛቸው አልቻልንም። ከሰዓት በኋላ ግን በጣም ደክመውና ልብሶቻቸውም በዝናብ በስብሰው ደረሱ።

ሰኔ 28 እሁድ

ማል ፎርስበርግ ዛሬ ማታ ከ2ኛ ዜና ምዕራፍ 20 ሰበከልን። ይህ ምዕራፍ እንግዲህ በያንዳንዱ ተናጋሪ አስቀድሞ መሰበኩ ሳይታወቅ ወደ አእምሮአችን እንዲመጣ ሲደረግ ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነው።

ሐምሌ 1 ረቡዕ

ዌብ ጎርርውን አሞት በሚያሳዝን ሁኔታ በአልጋ ላይ ተኝቶ ያቃስታል። ዛሬ ጧት እርሱ ጥርሱን ሲቦርሽ የተጠቀመበትን ውሃ በቤቱ የሚያገለግለው ልጅ ሊደፋ ከወሰደ በኋላ የእንግሊዝ ጨው መስሎት ጠጣው። ልጁ መጠጣቱን ሲክድ ከቆየ በኋላ የተወሰነ መጠን መዋጡን አመነ።

ሐምሌ 4 -ቅዳሜ

የጭቃ ጡብ ግምብ (ግድግዳ) ዛሬ ጧት አጠናቀቅን። ቀኑን ሙሉ በሆስፒታሉ ሥራ ስለ ዋልሁ ግታ በጣም ደክሞኛል። ከሚያዝያ 21 ቀን ጀምሮ ከአሥር ሳምንታት በላይ ፖስታ ስላልደረሰን ብቸኝነትም ተሰምቶኛል።

ሐምሌ 20 ሰኞ

ሚስተር አህማንና ሚስተር ሮበርትስ ገዢውን ለማግኘት በሄዱ ጊዜ ገዥው ልብሶቻችንና ዕቃዎቻችንን የምንሸጥበትን ምክንያት ጠየቋቸው። ምግባችንና ገንዘባችን ያላቀብን መሆኑ ሲነገራቸው ይህንን ስላላወቁ በጣም እንዳዘኑልንና ጥቂት ነገር የሚልኩልን መሆኑን ገለጹላቸው። በ11፡30 ሰዓት ከመንጋቸው ተመርጦ የተላከልንን አንድ ትልቅ ቅልብ በሬ እየነዱ አሽከሮቻቸው ወደ ሚሲዮኑ ግቢያ ደረሱ።

ነሐሴ 4 ሰኞ

ለአሥራ አምስት ሳምንታት ከውጭው ዓለም ተለይተን ከቆየን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ ጧት ስለ አዲስ አበባ ዜና ይዘው ሁለት ፖስተኞች ከጂማ መጡ።

ጥቅምት 17 ማክሰኞ

ከሲዳሞ ሸሽተው የመጡ ብዙ የአማራ ወታደሮች ምንም ሳይረብሹ (ሳይተናኮሉ) በአካባቢው በወላይታ ጎጆች ውስጥ ይኖራሉ። በአቅራቢያው ያሉ የወላይታ ሽማግሌዎች ወደ ሚስተር አህማን መጥተው የፈሯቸው በመሆኑ ከዝርፊያው ለማምለጥ ከእኛም ጭምር ወደ ደቡብ አራትና አምስት ሰዓት ጉዞ ፊት ለፊት ወደሚታየው ወደ ሁምቦ ተራራ እንሸሽ አሉን። እኛ ግን ጌታ በተለያዩ ጊዜያት ከ2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 20 ማረጋገጫ የሰጠን ስለሆነ ለቀን እንድንሄድ ከእርሱ ሌላ መልዕክት እስከምናገኝ ድረስ እዚሁ የምንቀመጥ መሆናችንን በስብሰባ ወሰንን።

ሕዳር 14 ማክሰኞ

ሚስተር አህማን፣ ሚስተር ሮበርትስ እና እኔ ነጋዴዎች ወደ ጂማ ሳይሄዱ ቀለባችንን ለመግዛት ወደ ከተማ ሄድን። ነጋዴዎቹ ስለ ፈሩና ስለ ደነገጡ ለመሄድ አስበዋል፣ መንገዱን ግን ፈርተውታል።

ሕዳር 18 ዓርብ

ዛሬ የወርሃዊ ፀሎታችን ቀን ነው። በግሪኩ ነጋዴ መጋዘን ያለው ዱቄትና ስኳር እንዲሸጥልን ፈቃድ የደረሳቸው መሆኑን ከከተማ ነጋዴዎች አንዱ ነገረን። እነዚህን የምግብ ዕቃዎችን ስለምናገኝበት ሁኔታ እርግጠኛ ባንሆንም የፀሎታችን መልስ በመሆኑ በጣም ተደስተናል።

በመጨረሻ ዱቄቱ ከተገኘ በኋላ ነቀዝና ትል የሞላበት ሆኖ ተገኘ። ዱቄቱ የግሪኩ ነጋዴ ለግሙና ማምረቻ የሚጠቀምበት ደረጃውም በጣም ዝቅተኛ የሆነ ነበር። ከዚያም ሌላ ከአንድ ዓመት በላይ በቀዝቃዛ ክፍል የተከማቸ በመሆኑ የሻገተና ጣዕም የሌለው ነበር። መጥፎ ሽታውን ለመቀየር ስንል ዱቄቱን ከቆሻሻው ከለየን በኋላ በሰሌን አድርገን ፀሐይ ላይ አሰጣነው (አስመታነው)።

የየዕለት ማስታወሻዬ ሌላም ብዙ አለው። ለወጣት ሚሲዮናዊው (ለእኔ) የእግዚአብሔርን ጥበቃና ፍቅር የሚገልፁ ድንቅ አጋጣሚዎችና በጣም የሚያስደስቱ ልምምዶች ተመዝግበውበታል። እነርሱም በመከራ፥ በአደጋና በሞት መካከል ክርስቲያን እንዴት መመላለስ እንዳለበት ለወላይታ አማኞች እግዚአብሔር ምሳሌ ለማሳየት የመረጣቸው መንገዶች ናቸው። እግዚአብሔር እነዚህን የስጋትና የችግር ወራትንና የሁለቱ ወንድሞቻችንን አሳዛኝ ሞት በቅርቡ ለሚደርሰው ሁኔታ የወላይታ ክርቲያኖችን ለማዘጋጀት የተጠቀመበት መሆኑ አያጠራጥርም።

የቀሩትም የዓመቱ ቀናት የእግዚአብሔርን የመጠበቅ ኃይሉን በሚመሰክር ስጋት፥ በሚያስፈራ ወሬና ግሩም በሆኑ ልምምዶች የተሞሉ ነበሩ። የበጋ ወቅት ሲደርስ የኢጣሊያ ሠራዊት ለመገስገስ በመቻሉ በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ወደ ሶዶ ከተማ ቀረበ። በከተማውና በአካባቢው የተካሄደው የተደጋገመ የቦምብ ድብደባ፥ የመትረየስ ተኩስና የእጅ-ስጡ ወረቀት ብተና የሕዝቡንና የገዥውን ሞራል ሰበረ።

ምግባችን ጨርሶ ካለቀ ብዙ ጊዜ ሆኗል። በተለመደው አሠራር እነዚህ ምግቦቻችን ከአዲስ አበባ ከተገዙ በኋላ በዓመት ሁለት ጊዜ ከዝናብ ወራት በፊትና በኋላ በአህያዎች ወይም በበቅሎች ተጭነው ይላኩልን ነበር። የግማሽ ዓመት ቀለባችንን መንግሥት ከመውደቁና ፀጥታ ከመበላሸቱ በፊት ስላላገኘን ከአካባቢው በምናገኘው መቆየት ነበረብን። በመጨረሻ በመጣልን ፖስታ አማካይነት በቂ የአትክልት ዘር ያገኘን ሲሆን ይህንን ለመትከል (ለመዝራት) በደረቅ ወራት ባይቻልም እግዚአብሔር ግን ያለ ጊዜው ዝናብ ሰጠን። ገዥውም ብዙ ጊዜ የተቀለቡ በሬዎችን ስለላኩልን ለብዙ ቀናት የምንበላውንና ለሌሎችም አካፍለን ለመስጠት በቂ ሥጋ አገኘን። (ማቀዝቀዣ ስለሌለ ብዙ ማቆየትም አይቻልም ነበር)። አማኝ ወላይታዎችም እምብዛም ለራሳቸው ካልበቃ ቀለባቸው እያካፈሉ ይረዱን ነበር።

በመጨረሻም ጥር 11 ቀን 1929 ዓ.ም. ኢጣሊያኖች ሶዶ በመግባት ከተማውንና አካባቢውን ያዙ። ከዚህም የተነሣ በአስጊ ሁኔታዎች መከበባችንና በሌሎች እጅ መጥፎ ነገር ይደርስብናል ብለን መፍራታችን አበቃ። ኢጣሊያኖችም ለእኛ ምግብ በመስጠትና ብዙ የማንቀይ መሆናችን ባረጋገጥንበት ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ስንሸጥ በመግዛት ከእኛ ጋር ጥሩ ወዳጅነት መሠረቱ።

## ምዕራፍ 10. ቶሮ

እንጀራህን በውሃ ፊት ላይ ጣለው፥
ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና።
መክብብ 11፡1

ኡኡኡኡ . . . ! ጩኸት! ሁካታ! ጫጫታ! ፍንዳታ! በሚሲዮኑ ግቢ በታችኛው መጨረሻ ካለው የሆስፒታሉ ሕንፃ ሆኜ ዞር በማለት ወደ ቤቴ ስመለከት ከአጠገቡ ማርና እንጨት ሲበር ተመለከትኩና የሥራ መሣሪያዎቼን ጥዬ ወደዚያ ሮጥሁ። ለማድቤትነት የምገለገልባት ትንሽ የሣር ጎጆዬ ጧት ለሥራ ሲወጣ አንድ በር ብቻ ነበራት። አሁን ግን ሁለት ሆና አገኘሁት።

ቶሮ በላሜራ ብረት በተሸፈኑ ሦስት ድንጋዮች በተሠራ ምድጃ ማብሰያውን (ፕሬዠር ኩከር) ጥዶ ምሳዬን ያዘጋጅ ነበር። ማብሰያው ሳይበርድ የላይኛውንና የታችኛውን ክፍል አጥብቆ የሚይዘውን የብረት ቀበቶ ሲፈታ በጣም እንዲጠነቀቅ ተደጋግሞ የተነገረውን ምክር ረስቶ ነበር። ቀበቶው በከፊል ላልቶ ስለነበረ ማብሰያው ፈንድቶ የቶሮን ፊትና ራስ ለጥቂት በመሳት ወደ ጣሪያ ወጣ። ቶሮ በፍጥነት መውጣት እንዲችል ዋናው በር ስለራቀበት የራሱን ሌላ በር አበጀ። በኋላም በጣም እየፈራ ብቅ አለ።

ፍርሃቱን ካስወገደ በኋላ «ጎዶ (ጌታዬ) አይገባኝም» አለ።

«ቶሮ! እንዲገባህም አያስፈልግም፥ የነገርኩህን መከተልና መፈጸም እንጂ! የዚህ ማብሰያ ጠባይና አሠራር በጣም ከባድ ወይም ውስብስብ ስላይደለ ቢገባህም ባይገባህም ጥቂትና ቀላል የአሠራር መንገዶችን ማወቅና መከተል አለብህ፥ ያለበለዚያ ትጎዳለህ፥ ነገሩ አይግባህ፥ ዝም ብለህ የታዘዝከውን ፈጽም፥ በቃ» አልኩት።

*　　*　　*

ቶሮ ወንጌል የሰማው ገና ልጅ በነበረ ጊዜ ሲሆን በወጣትነት ዕድሜው ለተለያዩ ሚሲዮናውያን ሠርቷል። ከልብ ጌታን መውደዱ የማያጠራጥር ቢሆንም በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ችግር ራሳቸውን የመከተት ዝንባሌ ካላቸው ሰዎች አንዱ ነበር። ቆንጆና ደስ የምትል የወላይታ ልጃገረድ ሲያገባ የማረፍና መረጋጋት ተስፋ ያለው መስሎን ነበር።

ነገር ግን ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ ከጌታ በስተቀር ሁላችንም ተውነው። ከዚሁ ጋብቻ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ቤቱ በእሳት ተያይዞ ከሰው በስተቀር ከሀብቱና ንብረቱ ጋር ድብን ብሎ ተቃጠለ። ይህና በተከታታይም የደረሱ ችግሮች ቶሮ ዝቅ እንዲልና ከልብ ንስሐ ገብቶ ሁለተኛ ሚስቱን እንዲተዋት አደረጉት። አሁን ለብዙ ዓመታት ከኛ ጋር በመስማማት ቆይቷል።

በምስክርነቱ ቀናኢ፥ ሚስተር አህማን በሳምንት አራት ጊዜ በሚያስተምርበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል በመገኘትም ታማኝ ሆነ።

ቶሮ የወጥቤት ሠራተኛ ነበር። እርሱን የወጥ ቤት ሠራተኛ ብሎ መጥራት አግባብ ባይሆንም ከእኔ ይልቅ እርሱ ለስያሜው ይቀርባል። በየካቲት 1929 አንድ ቀን ማታ ምግብ ተበልቶ ካበቃና ሰሃኖች ታጥበው ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ቶሮ እንደተለመደው ወደ ቤቱ ከመሄዱ በፊት ለነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ለፀሎት መጣ። ፀሎቱ ከበቃ በኋላ በእሳት ማንደጃ አጠገብ ባለው በርጩማ ላይ ተቀምጦ ቆየ። ፊቱ ተረብሿል፥ ጠቁሮአል። ደጋግሞ ወደላይ ተመለከተ፥ ከዚያም ተቆላልፈው ወደፊት የተዘረጉ እጆቹን ለመመልከት አንገቱን ደፋ አደረገ።

እንደሱ ያለ ወዳጅ በልቡ የያዘውን ቶሎ እንዲነግረን ማቻኮል እንደሌለብን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እናውቅ ነበር። ሲዘጋጅ ራሱ መናገር ይጀምራልና። በመጨረሻም ቶሮ ወደ ላይ እየተመለከተ ከሙሉ ጽናት ጋር «ጌታዬ፥ ከሥራዬ ቢያሰናብቱኝ እወዳለሁ» አለ።

ከዚህ ጥያቄ የበለጠ ያስደነቀኝ ነገር አልነበረም። ሚሲዮናውያንና አማኞች እንደምናውቀው ኢጣሊያኖች ላልተወሰነና ለረዥም ጊዜ ችላ ስለማይሉን ውሎ አድሮ ከሀገር እንድንወጣ መገደዳችን አይቀርም። እነርሱ በሚያስተዳድሯቸው ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ያደረጉት ይህንን ነው። በኢትዮጵያ ይህንን የማያደርጉ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከአሁን ድርጊታቸው አልተገኘም፥ ቢገኝም በጣም ጥቂት ነበር። የኢጣሊያን ጦር ሶዶ በገባበት ቀን ወታደሮቹ የሚሲዮኑን ሆስፒታል ሲይዙ በመጀመሪያው እሁድ ቄሱ በሆስፒታሉ ፊት ለፊት ባለው ግልጽ አደባባይ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት (የካቶሊክ) አካሂዶ ነበር።

ስለዚህ ከቶሮ ጋር ተከራከርኩ። «በአሁኑ ጊዜ ከሥራ ለመሰናበት ለምን ጠየቅህ ቶሮ? ውሎ አድሮ የእኔ መሄድና የአንተ ሥራ ማጣት የማይቀር ቢሆንም አንተ ግን አሁን ከለቀቅህ እኔ ደግሞ በጣም እቸገራለሁ። በሆስፒታሉ ውስጥ በሥራ ስውል ቤቴን በመጠበቅና ምግብ በማዘጋጀት የሚያገለግለኝ ሰው የለኝም።»

«አዎን ጌታዬ፥ የሚሉት ሁሉ እውነት ነው። ምናልባት እናንተ ሚሲዮናውያን አንድ ቀን ወላይታን ለቃችሁ ትሄዱ ይሆናል። ከዚህ የተነሣ ነው እኔም ኮይሻ ወደሚገኝ ቤቴ መመለስ እንዳለብኝ የተሰማኝ» አለ ቶሮ። (ኮይሻ ከሶዶ በስተምዕራብ የሚታየውን የተራራ ሰንሰለት አልፎ የሚገኝ ሥፍራ ነው።)

«እሱ ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው ቶሮ? እንደምትለው ይህ ለቅቀን የምንወጣበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፥ ታዲያ ወደ ቤትህ ከምትመለስ እስከዚያ ለምን ከእኔ ጋር አትቆይም?» ብዬ ጠየቅሁት።

«ጌታዬ፥ እርስዎ እስከሚሄዱ ቆይቼ ብመለስ የእኔ ወገኖች ለገንዘብ ሲል ለነጮች ሲሠራ ቆየ፥ አሁን እነሱ ሲሄዱ ወደ እኛ መጣ ይሉኛል። ከዚህም የተነሣ ብመሰክርላቸውና ወንጌል ብሰብክላቸው አይሰሙኝም። ነገር ግን አሁን ሥራዬንና ደመወዜን ትቼ ብሄድ እንደዚያ ሊሉኝ ስለማይችሉ ብሰብክላቸው የማይሰሙበት ምክንያት የላቸውም። እንደሚያቁት በዚያ አካባቢ የሚያምኑ

ሰዎች የሉም። ከብዙ ቀናት ጀምሮ እስካሁን እግዚአብሔር ስለዚሁ ሲናገረኝ ስለቆየሁ መሄድ አለብኝ።»

ፊቱን ስመለከተው የሚናገረው እውነት እንደሆነ አየሁት።

«ቶሮ፥ ይህንን አስበህበታል? አላረስክም፥ በጎተራ አልከተትክም፥ ያስቀመጥከው ገንዘብ የለህም፥ አዝመራው እስከሚደርስ ራስህንና ቤተሰብህን የምታቆይበት ቀለብ የለህም።»

«ይህ የሚሉት ሁሉ እውነት ነው ጌታዬ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ያዘጋጅልኛል። እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን እንደማይተው ከቃሉ ሁልጊዜ ያነቡልኝ አልነበረም? እርስዎስ ራስዎ ከቤተሰብዎና ዘመዶችዎ ርቀው እዚሁ በሰው ሀገር ሲኖሩ የሚያስፈልግዎትን ሁሉ እግዚአብሔር እንዳቀረበልዎት መስክረውልኝ አልነበረም?»

«አዎን! ያንን መካድ አይቻልም፥ እግዚአብሔር ላንተ ሁሉን ያዘጋጅልሃል፥ ብቻ ከመሄድህ በፊት ብንጸልይ» አልኩት።

ራሶቻችንን ዝቅ አደረግን፥ ቶሮ እግዚአብሔር ያዘዘውን ማድረግ እንዲችል የሚያስፈልጉትን ነገሮች እግዚአብሔር እንዲሰጠው በሕፃን ዓይነት እምነት በመጠየቅ አስቀድሞ ጸለየ፥ እግዚአብሔር ጸሎቱን ስለሰማለትም አመሰገነ።

እርሱ እንዳበቃ እኔ ቀጥዬ ስለ እርሱና ስለ እግዚአብሔር ርዳታ ጸለይሁ። ጊዜው የበጋ ወራት አጋማሽ በመሆኑ እስከሚቀጥለው አዝመራ ድረስ ቤተሰቡን የሚያቆይበት እህል ቶሮ እንደሌለው እኔ አውቅ ነበር። ለእኔ ለሚሠራው የምከፍለው ትንሽ ስለሆነ የሚተርፈው እንደሌለ አውቃለሁ።

በጸሎት ላይ እያለሁ በሚቀጥለው ክፍል በዕቃ ማስቀመጫ ላይ ያለች የጨርቅ ከረጢት ወደ አእምሮዬ መጣች። በዚያች ከረጢት ውስጥ አምስት ከብና የሚያንጸባርቁ የኢትዮጵያ ብሮች እንዳሉ አውቃለሁ። ጸሎቴን እንደቀጠልሁ እግዚአብሔር የቶሮን ጸሎት በእኔ ገንዘብ ሊመልስ እንደሆነ ገባኝ። ያለኝ ገንዘብ ይህ ብቻ መሆኑን ለጌታ እየገለጽሁ ደጋግሜ ጸለይሁ። ገንዘብም ሆነ ሌላ አስፈላጊ ነገር ሁሉ ከአዲስ አበባ የምናገኝበት መንገድ በወረራውና በከበባው የተነሣ ተዘግቶ እስካሁን ያልተከፈተ በመሆኑ ላልተወሰነ ጊዜ ሊኖረኝ የሚችል ይኸው ብቻ ነበር። ይህም ቢሆን የተገኘው ዕቃ ተሸጦ ነበር።

ሆኖም እግዚአብሔር ለቶሮ የሚያስፈልገውን ለማሟላት የመረጠው መንገድ ገንዘቤን ለቶሮ እንድሰጥ መሆኑን አጥብቆ ስላሳሰበኝ ያራዘምኩት ጸሎቴን አጠናቀቅሁ።

ተነስቼ በእግሬ ከቆምኩ በኋላ ወደሚቀጥለው ክፍል ገብቼ ያችን ትንሽ ነጭ ቦርሣዬን ይዤ ተመለስሁና ቶሮ ፊት ቆምኩ። በተዘረጉ ሁለት እጆቼ እነዚያን አምስት ብሮች አራገፍኩ። ቶሮም ትላልቅና ጥቋቁር ዓይኖቹን አውጥቶ «ጌታዬ ይህንን ማድረግ አይችሉም፥ ያለዎት ገንዘብ ይህ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ፥ እርስዎም እንደእኔ ያስፈልግዎታል» ብሎ ጮኸ።

«ቶሮ፥ እግዚአብሔር ፍላጐትህን እንዲያሟላ በምጸልይበት ጊዜ ይህንን ገንዘብ ላንተ በመስጠት እንደሚያሟላልህ ተናግሮኛልና ውሰደው። እርሱ

በሆነው መንገድ ለእኔም የሚያስፈልጉኝ ነገሮችን እንደሚያሟላልኝ እናውቃለን።»

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቶር በጣም ልቡ እየተነካና እያመሰገነ በበር ውጪ ወጥቶ ጨለማው ውስጥ ገባ። በሚቀጥለው ቀን ጧት ፀሐይ ሳትወጣ ከሚስቱና ከሕፃን ልጁ ጋር ወደ ገጠር ወደ ትውልድ መንደሩና ዘመዶቹ ተጓዘ።

ከዚያን በኋላ ሶዶን እስከለቀቀን ጊዜ ድረስ ከቶር ጋር ሁለት ጊዜ ብቻ ተገናኝተናል። በሚሲዮን ግቢያ የነበረውን ሥራ ለቆ በመሄድ በዚያ ላሉ ሕዝቦች ለመመስከር መወሰኑ ትክክለኛ እርምጃ እንደሆነ የገባን ከረዥም ጊዜ በኋላ ነበር። በሄደ በጥቂት ሳምንት ውስጥ እግዚአብሔር ለአካባቢው ሕዝቦችና ለዘመዶቹ በቃሉ ይናገራቸውና ይለውጣቸው ጀመረ።

ቶር በመጀመሪያ በትውልድ አካባቢው ከመሰከረላቸውና ከለወጣቸው ሰዎች መካከል አንዱ ካዎና[1] ገበቶ ነው። ቶር የመሰከረለት አንድ ጊዜ ሲሆን ገበቶ ግን ትክክለኛነቱን ተጠራጥር ነበር።

ወላይታዎች ወደጠንቋዮች በሚሄዱበት ጊዜ ጉዳያቸው የሚያልቅላቸው በመመላለስ እንጂ በአንዴ አልነበረም። ስለዚህ ገበቶ ከጠንቋዮች ጋር አስቀድሞ ይገናኝ ስለነበረ ይህን አስደናቂ ቃል ከቶር በሰማ ጊዜ ከጠንቋዮች ጥበብ የተሻለ መሆኑን አይቶ ወደደው።

ቶርም ጥያቄውን ሲመልስለት «ምግብ የምንበላው ሁል ቀን ነው ወይስ አንዳንድ ቀን?» ብሎ ጠየቀው።

ገበቶ «የምንበላው ሁልቀን ነው» ብሎ መለሰ።

«ስለዚህ አንተም ሁልጊዜ (በማንኛውም ጊዜ) የምሰጥህን የእግዚአብሔር ቃል ለመቀበል ወደ እኔ መምጣት ትችላለህ» አለው።

ገበቶ የወንጌሉን መልዕክት በመጀመሪያ የሰማው ዓርብ ሲሆን በሰማውና ቃሉ ለቶር ባለው ትርጉም በመነካቱ በሚቀጥለው እሁድ አሥር ሌሎች ሰዎችን ይዞ መጣ። የመዳንን መልዕክት እንዲሰሙ ሰዎችን በመያዝ ይመላለስና ያለውን ትርፍ ጊዜ ሁሉ ከቶር ጋር ያሳልፍ ነበር። የገበቶ ልብ እንደበጋ አቧራ የተጠማ ይመስላል። ወዲያውም ይህ መልዕክት እሱ ሲፈልገው የነበረ በመሆኑ ከልቡ በማመን በሁለት እጆቹ ኢየሱስ ክርስቶስን አቅፎ ተቀበለ። ከአሥራ ሁለት ሳምንታት በኋላም ተጠመቀ።

ገበቶ ባመነ በሦስተኛው ወር መጠመቁን የቤተ ክርስቲያን መሪ አቶ ብሩ ሲሰማ ተጠራጥሮ ነበር።

«እንዴት ቶሎ ልትጠመቅ ቻልክ? እኛ ሁልጊዜ ለጥምቀት የታሰቡ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረዥም ጊዜ ልናያቸውና ለጥምቀትም ከመዘጋጀታቸው በፊት ምስክርነታቸውን መስማት እንፈልጋለን» ብሎ ጠየቀው ገበቶን።

---

[1] ካዎና ማለት የንጉሥ ልጅ ማለት ነው። ካዎናዎች የወላይታ ንጉሥ ዘር ናቸው ይባላል።

ቶርም «ነገር ግን ለእርሱ ይህንን መጠበቅ አያስፈልግም፣ እርሱ ጌታን ያውቃል ያምናልም» አለ።

ቶር ትክክል ነበር። ይህ እንደሆነ ወዲያው ሌሎች ሰዎች በገበቶ ሕይወት ከፉት ለውጥ የተነሣ እርሱን የለወጠውን ኢየሱስ ክርቶስን አመኑ። የገበቶ ባለቤትና ሌሎችም ብዙ ሰዎች በመጠመቃቸው በዚያ አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ተጀመረ።

## ምዕራፍ 11. በድጋሚ እስክንገናኝ

እርሱ ራሱ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና።
ዕብ. 13፡5

ሚያዚያ 9 ቀን 1929 ዓ.ም. በማለዳ እኛንና ያሉንን ጥቂት ዕቃዎቻችንን ወደ አዲስ አበባ ለማጓጓዝ የኢጣሊያ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች መጡ። እኛም አሥራ ዘጠኝ ሚስዮናውያንና ሰባት ሕፃናት በጠቅላላው ሃያ ስድስት ነበርን። ተሽከርካሪዎቹ የወታደራዊው ጉዞ (ኮንቮይ) አካል በመሆናቸው መኪኖቹ በቶሎ እንድንለቅ አዘዙን። ለመጨረሻው ስንብት መሳሳምና እጅ መጨባበጥ ባለመቻሉ የተለያየነው በእንባና «በድጋሚ እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን» በመባባል ነበር። መቼ ይሆን በድጋሚ የምንገናኘው?

ተሽከርካሪዎቹ ከሚሲዮኑ ግቢ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ወደኋላ ዘወር ብለን የወላይታ ክርስቲያኖችንና ከጥቂት ቀናት በኋላ በጂማ በኩል ለመምጣት የቀሩትን እህማንና ባለቤቱን ቆመው ተመለከትን። በጣም አነስተኛና ደካማ ናቸው። አሁን ደግሞ ለዘመናት በኖሩበት አኳኋን እንዲኖሩ ብቻቸውን ቀርተዋል። ሆኖም በድሮና በአሁን ሁኔታቸው መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ።

በ1920 ዓ.ም. ሚሲዮናውያን ወደ ወላይታ በመጡ ጊዜ አንድ እንኳን አማኝ አልነበረም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በቋንቋቸው አልታተመም፣ ኢየሱስ ክርስቶስንና እርሱን በማመን የሚገኘውን አዲስ ሕይወት ማወቅም አልነበረም። አሁን ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ግን የማይታይ የክርስቶስ አካል ቁራጭ የሆነች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርታለች። አርባ ስምንት የተጠመቁ አማኞችም ወንጌል በወላይታ ሕይወት ላይ ላመጣው አስደናቂ ለውጥ ሕያው ምስክሮች ናቸው።

በተራራው ጥግ የመጨረሻውን መታጠፊያ ስንዞር የወላይታ ክርስቲያኖች ለመሰነባበቻ እጃቸውን ሲያወዛውዙ በተመለከትን ጊዜ ይህን በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚውለበለብ ትንሽ ነበልባል የሚጠብቀው ምን እንደሆነ አሰብን። ለመማርና ለመመራት በቋንቋቸው የተጻፈ ከማርቆስ ወንጌልና ጥቂት ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተመረጡ ጽሑፎች በስተቀር በእጃቸው

ሌላ የእግዚአብሔር ቃል የሌላቸው እነዚህ ወጣት (ጨቅላ) ክርስቲያኖች መምጣቱ የማይቀርለትን ስደትና መከራ ይቋቋሙት ይሆን?

ሐምሌ 1927 ዓ.ም. የአሜሪካና ብርታኒያ ኢምባሲዎች ሚሲዮናውያንን ለማስወጣት ትዕዛዝ ባስተላለፉበት ጊዜ በወላይታ አሥራ ሰባት የተጠመቁ አማኞች ብቻ ነበሩ። ሚሲዮናውያኑ ግን የራሳቸው መንግሥታት የሚሰጧቸውን ጥበቃና ከለላ በመተው ከሕዝቡ ጋር ለመቆየት ወሰኑ። ከሕዝቡ ጋር የምንቆይበት ጊዜ አጭር እንደሚሆን ስለምናውቅ ክርስቲያኖችን ለማስተማርና የወንጌል መልዕክትን ለማዳረስ የሚቻለውን ሁሉ አደረግን። በኢጣሊያ ከበባና ወረራ ጊዜ በብሩ ቤት በየዕለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይካሄድ ነበር። ከሚሲዮኑ ግቢ መውጣት አስተማማኝ ባይሆንም የቀረንን ትንሽ ጊዜ ወጣት ክርስቲያኖችን በማሠልጠን ማሳለፍ አጣዳፊና አስፈላጊ ነበር።

የተጠመቁት አማኞች ቁጥር ወደ አርባ ስምንት አድጓል፤ ቤተ ክርስቲያንም ተቋቁሟል። የቤተ ክርስቲያኑ መሪ ማን መሆን እንዳለበት ያሰብን ቢሆንም አማኞቹ ራሳቸው እንዲወስኑ ጌታ እንደሚመራቸው ተማምነን ነበር። ባሳየነው የምስጢር ድምፅ አሰጣጥ መሠረት ምርጫ ተካሂዶ በሙሉ ድጋፍ ብሩ በመመረጡ በጣም ተደሰትን።

ወላይታን ከለቀቅንበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ለመጨረሻ ጊዜ ለጌታ እራት ሁላችንም አንድ ላይ በተሰበሰብንበት ጌታ ራሱ ከኛ ጋር ስለ ነበረ ልባችን በደስታና በምሥጋና ተሞላ። የመለያየቱ ሐዘንና ዳግመኛ ለመገናኘት ተስፋ ማጣት ይህንን ጊዜ ልዩ አድርጎት ነበር። የመጨረሻ ምክርና የማጠናከሪያ ትምህርት ተሰጠ። ወንጌልን ለሕዝቦቻቸው መስበክ መመስከርና ማዳረስ ከእንግዲህ የራሳቸው የወላይታ አማኞች ተግባርና ኃላፊነት እንደሆነና ይህንን ተግባርና ኃላፊነት ካልተወጡ እግዚአብሔር የሚጠይቃቸው መሆኑ አጥብቆ ተነገራቸው። እኛም እግዚአብሔር ከፈቀደና ካስቻለን የምንመለስ ካልቻልንም በኢየሱስ እግር ሥር (በዕለት) የምንገናኝ መሆናችንን አረጋገጥንላቸው።

የኢጣሊያን ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች አቧራ እያቦነኑ ይዘውን ሲከንፉ ይህንን ደስታና ሐዘን የተቀላቀለበት የስንብት ስብሰባ አስታወስን። እግዚአብሔር ታማኝ በመሆኑ በወላይታዎች መካከል የጀመረውን ይህንን ሥራ ጠብቆ እንደሚያቆየው ብናውቅም ራሳችንን እንጠይቅ ነበር። ዳግመኛ ወደወላይታ መምጣት ብንችል (ብንመጣ) ምን እናገኝ ይሆን?

## ምዕራፍ 12. እግዚአብሔር ግን

በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም
  በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።

የሐዋሪያት ሥራ 2:42

«እናንተ ሚሲዮናውያን ለቅቃችሁ በሄዳችሁበት ጊዜ በወላይታ ክርስቲያን ማግኘት ያስቸግር ነበር። አሁን ግን ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ማግኘት ያስቸግራል።»

ላውሬ እና ሊሊ ዳቪሰን የሰሙትን ለማመን እየተቸገሩ ጥያቄ በተሞላበት ሁኔታ በአዲስ አበባ ቤታቸው አብረዋቸው የተቀመጡትን ወላይታዎች ተመለከቱ። እንዲህ ያለ ወሬ እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል? ምናልባት ጥሩ የወላይታ ተረት ይሆናል። በእርግጥም ያ የወንጌል ብርሃን በመጥፋት ፋንታ እንዲያውም ከመቼም ጊዜ በላይ ጎልቶ እየበራና እየተንቦገቦገ ነው?

ደጋግመው ከወላይታ የመጡትን ሰዎች ቢጠይቋቸውም የሚሰጣቸው መልስ መጀመሪያ የሰሙትን የሚያጠናክር ብቻ ሆነ። አዎን የወላይታ ሰዎች በብዛት ወደ ጌታ ተመልሰዋል። በአጠቃላይ የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍል ጎሣዊ አኗኗር ተቀይሯል። በዚህን ጊዜ በወላይታ አንድ መቶ ያህል ቤተ ክርስቲያናትና አሥር ሺህ ያህል አማኞች ይገኙ ነበር።

ከአርባ ስምንት ወደ አሥር ሺህ! ሃያ ሺህ በመቶ (20,000%) እድገት! እንዲያውም ዳቪሰንና ባለቤቱ ወደ ወላይትኛ የተተረጎሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና ወላይትኛም ሆነ አማርኛ ማንበብ የሚችሉ ሰዎች ጥቂቶች መሆናቸውን ሲያስታውሱ ይህ ዕድገት የማይመስል ነበር። ሆኖም ከወላይታ አዲስ አበባ ድረስ ሊያዩአቸው የመጡትን የወላይታ ሰዎች ብዙ በጠየቁ መጠን ታሪኩም ይበልጥ አስደናቂ እየሆነ ይሄድ ነበር።

በ1935 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በማገገም ላይ ብትሆንም ሚሲዮናውያን እንዲመለሱ ገና አልተፈቀደም። ላውሬ ዳቪሰን በመጀመሪያ በጎሩ የሚሲዮኑን ሥራ በጀመረው ቡድን ውስጥ የነበረ ሲሆን አሁን እርሱና ባለቤቱ ሊሊ ጠላት የያዘው ግዛት አካል በሆነው በአዲስ አበባ እንግሊዝ ትምህርት ቆንስላ ውስጥ ይገኛሉ። የእነሱ እዚያ መኖርና ከወላይታ ከመጡ ሰዎች ጋር መገናኘት ራሱ አሁን ስለ ወላይታ ቤተ ክርስቲያን የሚሰሙት ዜና ያህል አስደናቂ ነበር።

ንጉሡ በ1928 ዓ.ም. አገር ለቀው ከመጡ በኋላ የመመለሳቸው ሁኔታ ፈጽሞ አጠራጣሪ ነበር። ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ያቀረቡት የእርዳታ ጥያቄም ምላሽ ስላልተሰጠው ለማኅበሩ ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ አሰምተው ነበር፡-

> መንግሥታትን ሁሉ ስለሚያሰጋቸው ከፍተኛ አደጋ ለማሳወቅ እወዳለሁ። . . . ይህ የዓለም አቀፍ ውሎችን የማመንና የትናንሽ መንግሥታት አንድነት እንደሚከበር የተገባው ቃል ጠቃሚነት ጥያቄ ነው። በአጭሩ ዓለም አቀፍ ግብረገብነት በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ ነው ያለው። ከእግዚአብሔር መንግሥት በስተቀር በዚህች ምድር ላይ ማንኛውም መንግሥት በሌላው ላይ የበላይነት የለውም። . . . ፍርዳችሁን እግዚአብሔርና ታሪክ ያስታውሱታል።

ሆኖም ንጉሡ ማንም ባልጠበቀው አኳኋን በፍጥነትና በአጭር ጊዜ ተመለሱ። በ1932 እና 1933 ዓ.ም. ኢጣሊያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስትገባ ሰሜን አፍሪካ በጦር ቀጠና ተጨመረ። ከአውሮፓና አፍሪካ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በመሆን ኢጣሊያኖችን ሲያሸንፍ በጦርነቱ ምክንያት ከዙፋን ወርደው የነበሩ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሥልጣናቸው ተመለሱ።

ልክ በሄዱ በአምስት ዓምታቸው በ1933 ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ገቡ። ነፃ የወጣውን ሕዝባቸውን በንግግራቸው አበረታትተው መልሶ ግንባታና ልማት እንዲጀምር አሳሰቡ። በተሸነፈው የጠላት ኃይል ላይ የበቀል እርምጃ አልወሰዱም፥ ሕዝቡም ከበቀል እንዲቆጠብ አስታወቁ።

> ክፉን በክፉ አትመልሱ፥ ጠላት በእኛ የሠራውን ዓይነት የጭካኔ ሥራ በማንም ላይ አታድርጉ።

ከፍተኛ ጭካኔ የተፈፀመበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢጣሊያውን (ሲቪሎችም ሆን ወታደሮች) ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ያለመፈለጉ የሕዝቡን ብስለትና ጨዋነት የሚያመለክት ነበር።

ንጉሡ ሰላምን ለመመለስና ለማስፈን ባደረጉት ጥረት የረዷቸው (እንዲመለሱም ያመቻቹላቸው) የእንግሊዝ ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ነበሩ። እንግሊዞች በኢትዮጵያ የቆዩት በሰሜን አፍሪካ የነበረውን ጦርነት ለማጠናቀቅ ሲሆን ይህ ከፊል ወታደራዊ ዘመናቸው በኢትዮጵያ ሰላምና ብልፅግናን አፋጥኗል።

ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ይዛ በቆየችባቸው ዓመታት ላውሬ ዳቭሰንና ባለቤቱ በጎረቤት ሀገር በሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ነበር የቆዩት። ዳቭሰን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የሚችልበት ጊዜ መድረሱን ባወቀ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ከሚመጡ የእንግሊዝ ወታደሮች ጋር አብሮ ለመምጣት አመልክቶ ተፈቅዶለት ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ለተወሰኑ ጊዜያት ከእንግሊዝ ጦር ጋር በአገሪቱ ውስጥ እየዞረ ጉብኝት ካደረገ በኋላ ሁሉም ተረጋግቶ ሰላም ሲሰፍን ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ተዛውሮ እርሱም ባለቤቱም በአዲስ አበባ ውስጥ በትምህርት ቤቶች የሥራ ኃላፊነት ተሰጣቸው።

ከዚያም ላወሬ በአዲስ አበባ ወደየአካባቢያቸው የሚመለሱ የኢትዮጵያ ወታደሮች ማስተናገጃ አዛዥ ሆነ። በዚያም ወደየቤታቸው ለመመለስ የሚጠባበቁ ብዙ የወላይታ ወታደሮች አገኘ። ቋንቋቸውን የሚችል በመሆኑ በቀላሉ ወዳጅነት ፈጠረ። የወላይታ ክርስቲያኖችም የቀድሞ ሚሲዮናውያን በአዲስ አበባ የሚኖሩ መሆኑን ሰምተው ስለነበረ ክቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብዙዎች ዳቭሰንና ቤተሰቡን ለመጠየቅ ከወላይታ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ረዥም ርቀት በእግራቸው መጥተዋል።

በዚህን ጊዜ ነበር ዳቭሰንና ባለቤቱ አብረዋቸው በእሳት ዙሪያ ተቀምጠው ከነበሩ የወላይታ ክርስቲያኖች ሚሲዮናውያን ባልነበሩባቸው አምስት ዓመታት ውስጥ ምን ዓይነት ሁኔታ እንደነበረ የተነገራቸው። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ያላወቁ በመሆኑ አንዳንድ ችግሮች ተከስተው እንደነበረ ወላይታዎቹ አስረድተዋቸዋል።

አንድ ቀን ማታ ከዳቭሰን ልጆች አንዱ ትንሽ ውሻ አስከትሎ ወደ ግሎን ክፍል ገባ። ውሻው ጨዋታ በመፈለግ ወደ እንግዶቹ ቢሮጥ እነርሱም እንደፈሩ ዓይነት ወደኋላ አፈገፈጉ።

«ይህንን ትንሽ ውሻ መፍራት የለባችሁም፥ በጣም ወዳጃችው ስለሆነ ሕፃናት ቀኑን ሙሉ ከሱ ጋር ሲጫወቱ ይውላሉና አይነካችሁም» አለ ዳቭሰን እየሳቀ።

ውሻውን የመፍራት ጉዳይ ሳይሆን የወላይታ ክርስቲያኖች ውሻ በቤታቸው እንዲያኖሩ ስለማይፈቀድላቸው መሆኑን ከክርስቲያኖቹ አንዱ አስረዳ።

«ይህን አባባል ከየት አገኛችሁት? ክርስቲያን ለምን ውሻ አይኖረውም?»

«ጳውሎስ አማኞችን ‹ከውሾች ተጠበቁ› ያለውን ከአዲስ ኪዳን እናነብ የለም እንዴ» አለ አንዱ ሽማግሌ።

ዴቭሰንና ባለቤቱ ይህ ቃል ምን ማለት እንደሆነ ካስረዷቸው በኋላ የወላይታ ክርስቲያኖች ሁሉንም ነገር (ቃል) እንዳለ ስለሚቀበሉት ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ቀላል አባባል እንኳን ቢሆን ከእነርሱ ጋር መወያየትና ማጥናት እንደሚያስፈልግ ተገነዘቡ።

* * *

ይህን የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የሚያስደንቅ እድገት ዶ/ር ቢንጋሃም በሰማ ጊዜ ወዲያው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በዓይኑ ለማየት ወሰኖ ነበር። በደቡብ ኢትዮጵያ የወንጌልን መንገድ መክፈት ምኞቱ ነበርና ይህም ይኸው እውን ሆነ። ከኢትዮጵያ መንግሥትም ጋር በሀገሪቱ ውስጥ የሚሲዮኑ ሥራ እንደገና ስለሚከፈትበት ሁኔታ ለመነጋገር ይመኝ ነበር። ካናዳንም ለቆ ወደ ኢትዮጵያ ሊጓዝ ሲል ታመመና ኅዳር 29 ቀን 1935 ዓ.ም. በሞት ተለየ።

እርሱን የተካው ጋይ ፕላይፌይር ሰኔ 24 ቀን 1935 ዓ.ም. ለዚሁ የሥራ ጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ሁለት ከቀድሞ ሚሲዮናዊያን (በወላይታ ያልሠሩ ነገር ግን አካባቢውን ከሚያውቁ) ጋር ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ በመኪና ጉዞ ጀመሩ። በሦስተኛው ቀን ማታ ለሶዶ አምስት ማይሎች ርቀት ሲቀር በሚገኘው መንደር በአንድ ክርስቲያን ሰው ቤት አረፉ። ወዲያው «ሚሲዮናውያን ተመልሰዋል» የሚለው ወሬ በገበሬው መንደር ከቤት ወደ ቤት ተዛምቶ በየቤቱ ብዙም እንቅልፍ ሳይተኛ ታደረ።

የክርስቲያኖችን ስሜት እንዴት መግለጽ ይቻላል? መላው ሕብተረሰብ፥ የጎሣው ሕዝብ በጠቅላላው ወንጌልን ሰምቷል። ቅጣትና ስደት ሳያግዳቸው በሺህ የሚቆጠሩ አምነዋል። ሁሉም ሚሲዮናውያንን «የእግዚአብሔርን ነገር ያመጡልን» ናቸው ብለው ያምኑ ነበር እንጂ ደግመኛ እናያቸዋለን ብሎ ያመነ አልነበረም። «ተስፋ ያደረግነው በእግዚአብሔር ቤት ልንገናኛችሁ ብቻ ነበር» ይሏቸው ነበር።

አሁን ግን ሳይጠበቅ መጡላቸው።

በነጋታው ማለትም ሰኔ 27 ቀን ክርስቲያኖች በሁሉም አቅጣጫ በመቶዎች እየሆኑ ሚሲናውያንን በዓይናቸው ለማየት መሰብሰብ ጀመሩ። ዕለቱም እሁድ ነበረ።

«በእርግጥ የኛዎቹ ናቸው? ከሰማይ ይሆን የወረዱት? ሕልም ነው ወይስ እውን? እንኳን በደህና መጣችሁ!» ሚስተር ፕላይፌርም በአጻፋው «የዚህን ደስተኛ ሕዝብ ቋንቋ ባወቅሁ» በማለት ተመኘ።

የጧት አምልኮ ፕሮግራም እንዳበቃ ከሙቶ ለሚበልጡ ቤተ ክርስቲያናት ከሚሲዮናውያን ጋር ለመገናኘትና ከማክሰኞ ጀምሮ ለሦስት ቀናት በሚካሄደው

ኮንፈራንስ እንዲሳተፉ መሪዎቻቸውን እንዲልኩ ጥሪ ተላለፈላቸው። እንግዶቹም ከክርስቲያኖች ጋር መገናኘትና እነርሱንም ማነጋገር ቀጠሉ። አብረዋቸውም ለማምለክ አራት መቶ ያህል ሰዎች በአንድ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ነበር።

ማክሰኞ ማታ ከመላው ወላይታ የመጡ ሰባት መቶ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለስብሰባው ደረሱ። ይህም ስብሰባ ሚስተር ፕላይፈርንና ቡድኑን በሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 15 የተጠቀሰውን የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ አስታወሳቸው።

በሦስቱ ቀናት ስብሰባ ላይ በቤተ ክርስቲያን እድገትና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እጦት ምክንያት በተከሰቱ ችግሮች እና በጣሊያን ወረራ ዓመታት በክርስቲያኖች ላይ በደረሱ ነገሮችና በተሠሩ ሥራዎች ላይ ውይይት ተደርጓል።

ለምሳሌ በየሣምንቱ ዓርብ የፀሎት ስብሰባ ነበር። ይህም የተጀመረው በስደት ጊዜ ሃምሣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲታሠሩ ክርስቲያኖች ለመጾምና ለእስረኞችም ለመጸለይ በወሰኑበት ጊዜ ሲሆን ከተፈቱም በኋላ ልማድ ሆኖ ፕሮግራሙ ቀጠለ። ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በወላይታ በነበረው አመለካከት መሠረት የአምልኮ ወይም የፀሎት ቀኖች አጠባበቅ ወደ ሕግ ወጥመድነት ቢቀየርም ስለ ሕግና ስለተለዩ ቀናት አጠባበቅ ግልጽ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲሠጣቸው መሪዎቹ በሙሉ ልብ ወዲያው ይቀበሉ ነበር። የአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ግልጽ ከሆኑላቸው በኋላ በውስጡ ያሉትን መመሪያዎች ቃል በቃልና ፍጹም በሆነ መንገድ ስለመለከተል የተነሣ ጥያቄም አልነበረም።

ቦርዴ (የአገር ቤት ቢራ) መጠጣት፥ ጥሬ ሥጋ መብላት፥ ትንባሆ ማጨስ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች በወላይታ ቤተ ክርስቲያንና በጎረቤት በስተሰሜን ባለው የሐዲያ ቤተ ክርስቲያን መካከል መለያየትን አመጣ። ጥቂት የሐዲያ ክርስቲያኖች ከተወሰኑ ሚሲዮናውያን ጋር ሆነው ከካምባታ ወደ ወላይታ በመምጣት አቋማቸውን ገለጹ። እነዚህን ተግባራት በመቃወም የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ የወሰነች ቢሆንም በሐዲያ በኩል ግልጽ ሆኖ አልተቀመጠም ነበር። ከዚሁ ስብሰባ የተነሣ ግን የሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት ሕብረት ቀጠለ። ሆኖም ቦርዴ መጠጣትንና ትንባሆ ማጨስን በመቃወም የሐዲያ ቤተ ክርስቲያን አሁንም የወላይታን ያህል ፍጹም አቋም አልያዘችም ነበር። ጥሬ ሥጋ እንዳይበሉ የሚመከሩት በጤና ምክንያት ብቻ በመሆኑ በዚህ ምክንያት አንድ ሰው ጥምቀት እንዳይከለከል ለክርስቲያኖቹ ትምህርት ተሰጣቸው። ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት እንደችግር አልቀረበም፥ እነዚህ ሰዎች እንዳይጠመቁ በሙሉ ስምምነት ቤተ ክርስቲያኒቱ ወስና ነበርና።

የመሪና የሥነ ሥርዓት ጉዳይ የወላይታን ቤተ ክርስቲያን ለመከፋፈል ያሰጋ ነበር። አንዳንድ ሰዎች እንደ አንደኛው ምዕተ ዓመት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የየአካባቢያቸው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መከተል አለብን በማለታቸው ጥምቀትንና የጌታ እራትን አገልግሎት ማን ይምራው? የሚለው ጥያቄ አለመግባባትን አስከትሎ ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ የአከባቢ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎችን ሥልጣን ሚስዮናውያን ከመሄዳቸው በፊት ከተመረጡ ሦስት መሪዎች ሥልጣን ጋር እኩል አድርጋ አትመለከትም ነበር። ቶሮ ገበቶና ዋንዳሮን የመሰሉ በአካባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን መሪና

ሽማግሌ የሆኑ ሰዎች በአጠቃላዩ ቤተ ክርስቲያን አመራር የሚጫወቱት ሚና ወይም ድርሻ አልነበራቸውም።

ከአንድ ሃምሣ አባላት ካሉበት ወይንም ከያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ቢመረጡ ከመቶ ቢያንስ ሦስት መቶ ሽማግሌዎች እንደሚኖሩ ተገልጾ እነዚህ እኩል ሥልጣን የሚኖራቸው ሰዎች ታማኝነታቸው እየተረጋገጠ በመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ መሠረት እንዲመረጡ ተደረገ።

አብያተ ክርስቲያናቱ በሦስት ወረዳዎች (ዞኖች) ተከፍለው አመራሩን ለማቀላጠፍ ከእያንዳንዱ ወረዳ ሰዎች ተመርጠው በየጊዜው ለምክክርና ለአምልኮ ሕብረት በሚሰበሰበው አጠቃላይ ኮሚቴ ውስጥ እንዲገቡ ተደረገ።

በኢጣሊያን ወረራ ጊዜ የወላይታ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ሲሉ ስለተቀበሉት መከራ ሚስተር ፐላይፌርና አብረውት የመጡት ሲሰሙ ተገርመው ነበር። በአንድ ወቅት ሃምሣ መሪዎች ተይዘው እሥር ቤት እንዲገቡ ቢያደርግዋቸውም ኢጣሊያኖቹ ቤተ ክርስቲያኑን ለማጥፋት የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ የቤተ ክርስቲያናትን ብዛትና ጥንካሬ የሚያሳድግ መሆኑን ተገንዘቡ። እያንዳንዱ መሪ አንድ መቶ አንዱ ደግሞ አራት መቶ ጅራፍ የተገረፉ በመሆኑ ለወራት በጀርባቸው መተኛት አልቻሉም፣ ሦስት ሞቱ። ቄሱ መስቀል የሚስሙ ከሆነ ወዲያውኑ የሚለቀቁ መሆኑን ቢገልጽላቸውም እነርሱ ግን በእሥር ላይ ያሉት ስለ ፖለቲካ ሳይሆን ስለ ሃይማኖት በመሆኑ እምነታቸውን ከመካድ መሞትን የሚመርጡ እንደሆነ አስረድተው መስቀል ስመው መፈታትን ሳይቀበሉ ቀሩ።

# ክፍል አምስት፡- በእሳት ተጠመቁ

## ምዕራፍ 13. እሳቱ ተዛመተ

. . . . . ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀበላችሁ . . . . . ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል . . . . በሁሉ ሥፍራ ተወርቷል።

1ኛ ተሰሎንቄ 1፡6+8

«በምብ ሲፈነዳ እሳት እንደሚረጭ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ በመላው ወላይታ ይሠራጭ ጀመር» እያሉ ሚስዮናውያን ከወጡ በኋላ ስለታየው የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የወላይታ ክርስቲያኖች ይገልጻሉ።

በመጀመሪያ ጥቂት ወራት ይህን ያህልም የሚያስገርም ለውጥ አልነበረም። እኛ ተለይተናቸው ከመውጣታችን በፊት ሕዝባቸውን በወንጌል የመድረስ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን አጥብቀን እንነግራቸውና እነሱም ቀድመው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በድፍረት ይናገሩ ነበር። ኢጣሊያኖቹ የፀሎትና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስብሰባ በሚሲዮኑ ግቢ ስለከለከሉዋቸው አማኞቹ ተራርቀው በሚገኙ አካባቢዎቻቸው ይሰበሰቡ ነበር።

ስንለያቸው «እኛ ትተናችሁ ብንለይም እግዚአብሔር አይተዋችሁም» ነበር ያልናቸው። ሆኖም እነዚህ ሰዎች ገና በመጀመሪያ የስደትና የመከራን ምልክት ሲያዩ ተስፋ ቢቆርጡና ቢተው የሚያስደንቀን አልነበረም። ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ከብርቱ ፀሎት ጋር ራሳቸውን የሚፈትኑበትና የሚመረምሩበት ጊዜ ሆነ።

ከዚህ በኋላ ነበር እሳቱ መዛመት የጀመረው። አቶ ግንጃ እንደገለጸው ከሆነ «የተጠማ እንስሳ ወደ ውሃ እንደሚገሰግስ ሰዎች ሰይጣናዊ አምልኮአቸውንና ሥራዎችን እየተው ወደ እግዚአብሔር መመለስ ጀመሩ»

አሥራ ተኛ ቤተ ክርስቲያናት አምነው ከተጠመቁት ሁለት ሁለት ሰባኪዎች እየመረጡ መላክ ጀመሩ። ወዲያው ያላመኑት እንኳን ሳይቀሩ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በጣም ጓጉ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር በመመለሳቸውና ቅርንጫፍ ቤተ ክርስቲያናትም በመቋቋማቸው በሁለተኛው ዓመት ሕንፃዎችን መሥራትና ሽማግሌዎችን መምረጥ አስፈላጊ ሆነ።

መለስ ብለን ያንን ጊዜ ብናስብ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያኑን የሠራበትን ሥልት እናደንቃለን። እንደ ዳና ማጃና ብሩ ያሉ ጠንካራና ብርቱ

ግለሰቦችን አስነስቶ በእነርሱ አማይካይነት ወንጌል በወላይታ ምድር እንደ ሰደድ እሳት እንዲቀጣጠል አደረገ።

ብሩ መሪያቸው እንደሆነ ክርስቲያኖቹ ራሳቸው ይቀበላሉ። የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ስለሚችል ቃሉንም ከሌሎች ይልቅ የተረዳ በዕድሜውም ከፍ ያለና የበሰለ በመሆኑ በእርግጥም ለመሪነት ብቁ ነበር።

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃልና ንባብ ለመማር በብዛት ወደ ብሩ ቤት ይመጡ ጀመር። ሲመጡም እንጨትና እህል በአህያ ጭነው ቅቤ አንዳንዴም በግ ይዘው እንጂ ባዶ እጃቸውን አልነበረም። በተጨማሪም በሳምንት አንድ ጊዜ አጥሩን ይጠግናሉ፥ እርሻውንም ያርሳሉ፥ ከዚህም በላይ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመሥራት ዝግጁ ነበሩ። በመጨረሻም በአውራጃው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች አዳዲስ ቤት ክርስቲያናት ብቅ ብቅ በማለታቸው ብሩም እነዚህን ዞሮ የመጐብኘት ሥራ ስለበዛበት አማኞቹ ፈረስ ሰጡት።

ሚሲዮናውያን ከሄዱ በኋላ በሁለት ዓመታት ውስጥ ዳና ማጃ ከሶዶ ወደ ደቡብ ብዙ ማይሎች ርቆ በሚገኝ አካባቢያቸው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆነው እንደተመረጡ አስከፊ ስደት መጣ። የዚሁ አካባቢ አማኞች በዳና ማጃ በሚመራው ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በሆነው በአንድ ሰው መሬት ላይ ትልቅ ፀሎት ቤት ሠሩ። ሽማግሌው በልቡ የእግዚአብሔር ቃል ሥር ያልሰደደ በመሆኑ ለጠላት ዛቻ በመፍራት ቤተ ክርስቲያኑ ፈርሶ ከመሬቱ እንዲነግለት አማኞችን ጠየቀ። ብዙ የወላይታ አማኞች በጊዜው በመንፈስ ሕፃናት ነበሩ። መጥር ወሬ በሰፊው እየተወራ ስለነበረ ሽማግሌው የሚመጣበትን ተጽዕኖና አደጋ ሊቋቋመው የማይችል መሆኑ ተሰማው። ፍርሃት ተላላፊ ነውና አንዳንድ አማኞችም ጌታን መከተል ቢፈልጉም የሚያስከትለውን በመፍራት በመሬታቸው የፀሎት ቤቱ እንዲሠራ ለመፍቀድ አልደፈሩም። ሁሉም መፍራታቸውን በመመልከት ዳና ማጃ እንዲህ አሉ «አማኞቹ የሚሰበሰቡበት ቤት ስለሌላቸው ቤቴ የእግዚአብሔር ቤት ይሆን ዘንድ ለእርሱ እሰጠዋለሁ። ትንሽ ቤት ሠርቼ ከቤተሰቦቼ ጋር ወደሱ በመዛወር ትልቁን ቤት ፀሎት ቤት አደርገዋለሁ።»

የክርስቲያኖቹ ቁጥር ጨምሮ ከዳና ማጃ ቤት አቅም በላይ በሆነ ጊዜ ስብሰባው በውጪ ይካሄድ ነበር። ዳና ማጃም እንደተለመደው ተነስተው «አንገቶቻችንን ዝቅ አድርገን እንጸልይ» አሉ።

አንድ ሰውም ከሰብሰባው መኻል ድምፁን ከፍ አድርጎ «በቅሎዎቻችንን ሊሰርቁ ነውና አታጐንብሱ፥ አይኖቻችሁንም አትጨፍኑ» አለ።

«አይዞአችሁ፥ አትፍሩ ወንድሞቼ። እኔ አሁን ጌታን አውቃለሁና እንደ ቀድሞ አይደለሁም» አሉ ዳና መጃ።

በኋላም አማኞቹ በወላይታ ባሕላዊ ቤት አሠራር ትልቅ የሣር ቤት ለቤተ ክርስቲያን ሠሩ። ቁጥራቸው እጅግ የበዛ የራሳቸው ሕዝቦች ይህንን አዲስና እንግዳ የሆነ እምነትና የኑሮ መንገድ በመምረጣቸው የተበሳጩት ያላመኑ ሰዎች አንድ ቀን ማታ በእሳት ድብን አድርገው አቃጠሉት። ተስፋ ያልቆረጡ ክርስቲያኖችም ተሰብስበው በቂ ገንዘብ ካዋጡ በኋላ ቆርቆሮ ገዝተው ለእሳት የማይበገር ቤተ ክርስቲያን ገነቡ።

የክርስቲያኖችንና የሚገነቡ ጸሎት ቤቶችን መብዛት ተመልክተው ኢጣሊያኖች ማሳደድ ጀመሩ። በመጀመሪያ በኢጣሊያውያን ቁሶች ጠቋሚነት የቤተ ክርስቲያንን ስብሰባና መንፈሳዊ ሥራ ቢያግዱም የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በመቆም ፈንታ ጭራሽ ኃይል አገኘ። ስደቱ በከፋ መጠን ወጣቲቱ ቤተ ክርስቲያን በአፋጣኝ ሁኔታ አደገች።

የአካባቢ አለቆችና ጭቃ ሹሞች የክርስቲያኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መሄድን ለባለሥልጣኖች ባስታወቁበት ጊዜ ኢጣሊያኖች ቤተ ክርስቲያኖችን እንዲመረምሩና መሪዎችን እንዲይዙ ፖሊሶች ላኩ። ክርስቲያኖች በስደት ላይ ላሉት ንጉሥ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሲጸልዩ በማግኘታቸው በመቆጣት ፀሎት ቤቶችን አፈረሱ፥ መጽሐፍ ቅዱሳትንና መንፈሳዊ ጽሑፎችን ለማውደም ሞከሩ። የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የነበሩዋቸው አማኞች በሸክላ ዕቃ ውስጥ አድርገው ቀበሩዋቸው። ሌሎች በኮባ በመጠቅለል በጣሪያ ላይ ቤቱ በተከደነበት ሣር ውስጥ ደበቁ። ቤተ ክርስቲያኖች የተሠሩባቸው መሬት ባለቤቶች እየተያዙ ወደ እሥር ቤት ተነዱ። መከራው እጅግ የከፋ ከመሆኑ የተነሣ ቤተ ክርስቲያኖቹ የቁርባንና የጥምቀት አገልግሎቶችን ማታ ማካሄድ ጀመሩ።

በዚህን ጊዜ ኢጣሊያኖቹ በይበልጥ የፈለጉት ዋና መጋቢ የሆነውን ብሩን ቢሆንም ሊያገኙት አልቻሉም። ፖሊሶች ለስድስት ወራት ቢፈልጉትም ብሩ በጫካ ውስጥ በመደበቅ ወደ ማይታወቅበት ወረዳዎች እየሄደ በመቆየትና ክርስቲያኖችም በቤታቸው እየሸሸጉት ቆየ። በዚህ ምክንያት ባለቤቱን ይዘዋት ለሷ ሲል እጁን እንዲሰጥ አሰሯት። በመንፈሳዊ ሕይወቷ ጠንካራ ያልነበረችው የብሩ ባለቤት እንኳን በእሥራቱ ምክንያት በእምነቷ በረታች።

አቶ ብሩ ኢጣሊያኖቹ እንደገመቱት የባለቤቱን መታሠር ሲሰማ ወደ ሶዶ መጥቶ እጁን ሰጠ፥ ወዲያውም ኢጣሊያን ወታደራዊ ችሎት ለፍርድ ቀረበ። በዚያን ቀን ማታ ኢጣሊያኖች እንደሚገድሉት በከተማው ተወራ። በፊት ሲይዙት እንደሚገድሉት ዝተው ነበርና።

በዚያን ጊዜ የወላይታ ደቡብ ምዕራባዊ ክፍል በሆነው በኪንዶ የአማራ ሽፍቶች አራት ኢጣሊያኖችን መግደላቸው ስለተሰማ የከተማው ሕዝብ ስሜት ተነሣሥቶ ስለነበረ የብሩ ጉዳይ ለጊዜውም ቢሆን ተረሣ። ብዙ የኢጣሊያ ወታደሮችም ሁኔታውን ለመቆጣጠር በመሄዳቸው የአቶ ብሩ ሕይወት ተረፈ፥ የአማኞችም እምነት ጠነከረ።

## ምዕራፍ 14. በመከራ ውስጥ መዘመር

ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፥ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ።

1ኛ ቆሮንቶስ 1:27

«እምነትህን ካድ፥ ያለዚያ መከራ ትቀበላለህ» አሉ ፊታውራሪ ዶጊሦ በቁጣ።

«ጥሩ! ላዳነኝ ጌታ ስል ደስ እያለኝ መከራ እቀበላለሁ» ሲል ዋንዳር መለሰ።

ፊታውራሪ ዶጊሦ አሥራ አምስት ማይሎች ከሰዶ ወደ ደቡብ ርቆ በዋንዳር ቤት አጠገብ የሚኖሩ ወንጌልን አጥብቀው የሚቃወሙ ባለሥልጣን ነበሩ። ዋንዳርን ተስፋ በሚያስቆርጡ ልዩ ልዩ መንገዶች በዚያ አካባቢ የወንጌል ሥርጭትን ለማቆም ብዙ የለፉ ቢሆንም እቅዳቸው ስለከሸፈ ክፉኛ ተበሳጭተው ነበር።

ለዓመታት ዋንዳር በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እያደገ በመምጣቱ በስብከቱና በምስክርነቱ ቀናኢ ሆነ፥ ተዳፍኖ የነበረ የአመራር ችሎታውም መከራ ሲጀመር ተገለጠ።

ዋንዳር ክርስቶስን ከመካድ መከራ መቀበልን መምረጡ ዶጊሦን ስላስቆጣቸው አሽከሮቻቸው አርባ ጅራፍ እንዲገርፉት አዘዙ። የአለንጋው ቅርንጫፎች ወይም ዘለላዎች አንድ ኢንች ስፋት በጫፎቻቸውም ሹል ብረቶች አሏቸው። በኋላም ዋንዳር ከሕመሙ ሲያገግም ዶጊሦ «ወደ ቤትህ ሄደህ የቤተ ክርስቲያንህ አባላት በሙሉ ማጭዶቻቸውን ይዘው ከቤተክርስቲያን አጠገብ እንዲጠብቁኝ ንገራቸው። ቃጫው፥ ገመዱ ሌላም ቤቱ የተሠራበት ነገር ሁሉ በማጭዱ እየተቆራረጠ ቤተ ክርስቲያኑ ይፍረስ። በአስቸኳይ ሂድና ለዚህ ሥራ ተዘጋጅ ሌሎቻችሁም ሁሉ ተሰብስባችሁ እዚያው ጠብቁኝ። እኔም አሁን እደርሳለሁ» ብለው አዘዙ።

ዋንዳር ትዕዛዙን ተቀብሎ ሄደ። ጎረቤቶቹና የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በትዕዛዙ መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጡ። ዶጊሦም ደስ ብሎአቸው በቅርብ ጊዜ ብዙ ጉልበትና ጊዜ ፈሶበት የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን እንዲያፈራርሱ ትዕዛዝ አስተላለፉ።

«አሁንስ መዘመር ትችላለህ?» ብለው ተንኰል ያዘለ ጥያቄ ጠየቁት።

«አዎን እችላለሁ» አለ ዋንዳር።

እያፌዙም ሲመልሱ «ጥሩ፥ ሚሲዮናውያን ያስተማሩህን ዘምርልኝ፥ ሌሎችም አንተ ያስተማርካቸውን መዝሙር እንዲዘምሩ አድርጋቸው» አሉ። ሰዎችም ሁሉ መዘመር ጀመሩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል (አዝማች)
የራሱን ልጆች ከእርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ ሊወስዳቸው ይመጣል።
እኛን ሊወስደን ይመጣል
በዚያ ምንም መከራ አይኖርም
በዚያ ምንም ሕመም አይኖርም
የራሱ የሆኑትን ሊወስድ ይመጣል

በዚያ ምንም መከራ አይኖርም
በዚያ ምንም ሕመም አይኖርም
በዚያ ምንም እንባ አይኖርም
ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ሊወስደን ይመጣል።

ሰዎቹ ያንን የሚወዱትን ቤት እያፈረሱ መዘመራቸው ዶጊሦን በጣም አስቆጣቸው። በሥራው ላይ የነበሩትን ሰዎች ሴቶችንም ጭምር የፈረሰውን ቤት ክርስቲያን እንጨት ተሸክመው ወደግቢያቸው እንዲወስዱ ካደረጉ በኋላ በዚያ አሰሯቸው። በምሽትም ሌሎች ክርስቲያኖችና የታሰሩት ሰዎች ልጆች፣ ሚስቶችና እናቶች ምግብ አዘጋጅተው አመጡላቸው።

ክርስቲያኖቹ ሌሊቱን ሙሉ የሚደርስባቸው ሁሉ በጌታ ያላቸውን ፍቅር የማይቀንስባቸው መሆኑን በማወቅ ሲዘምሩና እርስ በርሳቸው ሲጽናኑ አደሩ።

በነገታውም እንጨቱንና ሣሩን በራሳቸውና በጀርባቸው ተሸክመው ሰዶ እንዲወስዱ ታዘዙ። በመንገድም እንደሚከተለው ይዘምሩ ነበር።

ኢየሱስ አይተኛም
  እርሱን ተጠባበቀው
እርሱ ባልጠበቅነው ሰዓት ይመጣል
  እርሱን ተጠባበቀው
ብዙ ጊዜ የተለየ ወንድምህን ከምትጠባበቀው ይበልጥ
  እርሱን ተጠባበቀው
ተርበህ ምግብ ከምትፈልገው በላይ ኢየሱስን ተጠባበቀው
  እርሱን ተጠባበቀው

በመንገድ ያዩአቸው ሁሉ የተሸከሙት በዶጊሦ ትዕዛዝ የፈረሰው ቤተ ክርስቲያን እቃዎች ቢሆኑም አማኞቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መቀበላቸውን እንደጥቅም ቆጥረው በደስታ የሚዘምሩ መሆኑን ተረዱ።

ከተማ እንደደረሱ የተሸከሙትን አስቀምጠው ወደየቤታቸው ለመመለስ ነፃ ሆኑ። ያመጧቸው ዕቃዎች ግን በከተማው ለሚኖሩ አንድ ትልቅ ሰው ቤት መሥሪያ እንዲሆኑ ነበር። ዋንዳሮ ግን ከእሥር አልተፈታም። ዶጊሦም እጆቹ የፊጥኝ በገመድ እንዲታሠሩ በከተማው ጠርዝ ወዳለው ገበያ ወሰዱት። በገበያው ባለው ሰው ሁሉ ፊት የታሠሩ እጆቹን ወደላይ ከፍ አድርጎ እንዲያሳይ አዘዙ።

«ሁላችሁም ተመልከቱ ዋንዳር ታስሮአል፥ ተጠፍሮአል። እርሱ ስለታሠረና በዚያ ስለሌለ ቤተ ክርስቲያኑም ስለፈረሰ ለአምልኮ ወደዚያ ቦታ አትሂዱ፥ በዚያ ምንም የለም፥ ዋንዳር የለም ቤተ ክርስቲያኑም የለም።»

ዋንዳርም ከፍ አድርጐ «ሁላችሁም አዳምጡኝ! ለመዳን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ፥ ይህ የምታዩትና የታሠርኩበት ገመድ የመጨረሻ ገመድ አይደለም የታሠርኩትም በሰው እንጂ በእግዚአብሔር አይደለም» ብሎ ተናገረ።

ዶጊሦ የቆሙትን ሁሉ «ኑና ግረፉት» ብለው ጋበዙ። እምቢ ቢሉ የዋንዳር ዕጣ ይገጥመናል ብለው የፈሩ ሁሉ በያዙት ዱላና በትር ለመድረስ ያልቻሉትም ቢሆኑ ተንጠራርተው የቻሉትን ያህል መቱት።

ከዚያ በኋላ ዋንዳር እጆቹ ወደኋላ እንደታሠሩ ከዶጊሦ ፊት ለፊት ወደ ከተማ ተነዳ። በዚያ ዶጊሦ የዋንዳርን ጢም ጨብጠው በመያዝ ፊቱን ወዲያና ወዲህ በኃይል ሲያወዛውዙ ጢሙንም ሲነጩት ፊቱ ቆስሎ በደም ተለውሶ ነበር።

«አሁንስ! በዚያ በነጭ ሰው አምላክ ማመን ትተዋለህ?»

«አልተውም! በፍጹም አልተውም! ለምን እተዋለሁ?»

እንደገናም ተገረፈ፥ ምንም ማድረግ ያልቻሉ ዘመዶቹ ስቃዩን ላለማየት ፊታቸውን አዞሩ፥ ጓደኞቹም አለቀሱ።

በመገረፍ ላይ እንዳለ ዋንዳር ለዘመዶቹና ጓደኞቹ «ክርስቶስም በመሬትከ ነው የተቀበረው! እኔ አሁንም ከእናንተ ጋር ነኝና ለምን ታለቅሳላችሁ? ለምንስ ትፈራላችሁ? እኔ ግን አልፈራሁም» አላቸው።

ዶጊሦ አሁንም በመብሸቅና በመገረም «እንደዚህ እንድትበረታ ማን አስተማረህ?» አሉት።

«ሚሲዮናውያን ናቸው!» አለ ዋንዳር በግልጽና በኃይል።

«ሚሲዮናውያን ሄደዋል፥ ሊረዱህም ሆነ ሊያበረቱህ አሁን እዚህ የሉም፥ አንተ ለምን ትጨነቃለህ?» አሉ ዶጊሦ።

«እውነት ነው እነሱ የሉም፥ ነገር ግን እነሱን የላካቸው አምላክ እዚህ አለ። እኔ የማገለግለው ሚሲዮናውያንን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው። እኔ እንድድን የጠራኝና ያዳነኝ፥ አሁን እዚህ ያለና የሚያበረታኝ እርሱ እንጂ ነጮች ወይም ሚሲዮናውያን አይደሉም።»

ዶጊሦ ተቆጥተው ዋንዳር ወደገበያው ቦታ ተወስዶ እንደገና እንዲገረፍ አዘዙ። በመሬት ላይ በሆዱ ተኝቶ እንዲገርፉት አምስት ሰዎች ተመድበው ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ጀመሩ። አንዱ ሲደክም ጅራፉን (አለንጋውን) ለሌላው እያቀበለ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ገረፉት።

ቀኑ በምሽት ተተካ፥ የዋንዳርም ስቃይ ጨመረ። ምንም ለማድረግ አቅም የሌላቸው ዘመዶቹ በዚያው ሥቃይ መሀል እያመነቱ ተነስተው ወደሚያድሩበት ሄዱ።

ከዚያ በኋላም ገራፊዎቹ ግርፊያውን አቁመው ሊሞት ደርሶ የነበረውን ተሸክመው እሥር ቤት ወሰዱት። ዋንዳር ሰውነቱ ቆስሎ ስለ ነበረና በጣምም ስላመመው መተኛት አልቻለም። ሌሊቱንም ጉልበቱን ኩርምት አድርጐ ሌላ አካሉን በክንዱ ደገፍ አደረ። ሲነጋ ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ ሊያዩት ቢመጡም እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም። ሆኖም በእሥር ቤቱ ያደረ ሌላ ክርስቲያን ስላገኙ ሌሊት ዋንደርን ወደ እሥር ቤቱ አምጥተው እንደሆነ ጠየቁት።

«አዎን» ነበር መልሱ።

«አሁን እንዴት ነው» አሉ እየፈሩና ሁኔታውን ለማወቅ እየጓጉ።

«እስካሁን ነፍሱ ያለች ቢሆንም በጣም መጥፎ ሁኔታ ላይ ነው፥ ለነፍሱ ያስፈራል፥ ግን በጣም አነስተኛ ተስፋ አለ»

የዋንዳር ባለቤትና ዘመዶቹ ምግብና ወተት አምጥተው ክርስቲያኑን ወንድም ለምነው ማስገባት ቢችሉም ምግቡ ሲቀርብለት ዋንዳር ሊመገብ አልቻለም።

ቀኑ ረዥም ነበር፥ ሌሊቱ ተከተለ። ዋንዳር አሁንም በሕይወት አለ። ለቤተሰቡና ዘመዶቹ መልዕክት ለመላክ በቻለ ጊዜ «በዚህ ሁሉ እያለፍኩ ወደፊትም መኖሬን የሚቀጥል ይመስለኛል፥ አትፍሩ አታስቡ፥ እኔ ደህና ነኝ፥ ጌታም ከእኔ ጋር ነው» ብሎ አስተላለፈላቸው።

በሚቀጥለው ሳምንት በየቀኑ እርሱን ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ቢመጡም እንዲያዩት አልተፈቀደላቸውም። ዋንዳርም ተጨማሪ መልዕክት ላከላቸው፥ «እኔ አሁን ስለተሻለኝና እየተሻለኝም ስለሚሄድ ብዙ አትድከሙ» እነርሱም ዳግመኛ ሊጠይቁት አልሞከሩም።

አስከፊ ግርፊያ ካለፈ ከሁለት ሣምንት በኋላ አንድ ቀን ዋንዳር ከሌሎች እስረኞች ጋር በአንድ ትልቅ በርሚል ከወንዝ ውሃ ሞልተው በርሚሉን በዳገቱ መንገድ ሲገፉ ታየ። በርሚሉን ሲገፉ ያዩት ሰዎች አብረውት ላሉ የኢጣሊያ ዘበኞች ይመሰክር እንደነበረ ሄደው ለቤተሰቦቹና ዘመዶች ሲነግሩዋቸው በጣም ተገረሙ። መከራን ተቀብሏል፥ አሁን ለምን የባሰው ይደርስበታል? በምስክርነቱና ስብከቱ ብዙ ቀናኢ እንዳይሆን ለማሳመን ቢሞክሩም እርሱ እንዲህ አለ «እግዚአብሔር አለ፥ እርሱ አሁንም ከእኔ ጋር ነው፥ ታዲያ ለምን ታዝናላችሁ? እርሱ በምድር እንድንኖር እስከፈቀደ ድረስ ስለጌታ መመስከር የኛ ፋንታ ሆኖ ሳለ ለምን ትፈራላችሁ?»

ዓመቱን ሙሉ እሥር ቤት ሲቆይ በየቀኑ ይመሰክር ነበር። አንድ ሰው በየትም ቦታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰክር ቢታይና ቢሰማ እርሱ ዋንዳር ነበር።

እንደ ዮሴፍ ዋንዳርም ለሌሎች አርአያ የሚሆን እሥረኛ ነበር። የፖሊስ አለቆችም ስለዋንዳር «እርሱ ምግብ ወይም መልእክት ወጥቶ ለመቀበል ቢፈልግ አትከልክሉት፥ ታማኝ ስለሆነ አይጠፋም፥ ተመልሶ ይመጣል» ይሉ ነበር። ዘበኞቹ ለአንድ ጉዳይ ወጣ ወይም ዘወር ለማለት ቢፈልጉ ዋንዳርን ነበር ጠባቂ የሚያደርጉት።

በመጨረሻም ዋንዳር ከእስር ተፈቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ዶጊሦ አሁንም በአቅራቢያው ይኖራሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የደረሰ ሰብላቸውን ለመሰብሰብ እንዲረዷቸው በቂ ክርስቲያኖችን እንዲያመጣላቸው ዋንዳርን ጠየቁ። «አንተን መግደል እችላለሁ ብዬ ነበር፥ ሞክሬም ነበር፥ ነገር ግን እግዚአብሔር አድኖሃል፥ እንግዲህ እንድትረዳኝ በእግዚአብሔር ስም እጠይቅሃለሁ» አሉ ለዋንዳር።

ዋንዳር ከአንድ መቶ የሚበልጡ ክርስቲያኖች አስከትሎ መከራ ሲያሳየው የነበረውን ሰው በእህሉ መሰብሰብ ሥራ ሊረዳው ሄደ። ክርስቲያኖቹ ሲሄዱም ሆነ ሲሠሩ ይዘምሩ ነበር።

በኋላም ዶጊሦ ዋንዳርን «በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ከቶር፥ ባሩምና ገበቶ ጋር ብትመጣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቄስ አስጠርቼ ግርዘትና መጠጥ በመጽሐፍ ቅዱስ መከልከሉን ከእናንተም ከቄሱም እንሰማለን። ያልተከለከለ ቢሆን ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከለ ነው ያላችሁት እውነት ስላልሆነ ሦስቱ ሰዎችህ ይሞታሉ» ብለው አስጠነቀቁ። ዶጊሦ ይህን የተናገሩት በአሥራ አምስቱ ቀናት የሚደርስባቸውን ሳያውቁ ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ በቤታቸው በወንበር ላይ ተቀምጠው እንዳሉ ወደኋላ ወድቀው ወዲያው በመሞታቸው በግርዘትና በመጠጥ ላይ ሊካሄድ የታቀደው ክርክርና ውይይት ሳይደረግ ቀረ።

ጥቂት ጊዜ ከዶጊሦ ሞት በኋላ ከዋንዳር አካባቢ ብዙ አማኞች ለስብከት ወደ ጎረቤት ጋሞ አውራጃ ሄዱ። የጋሞ ገዥ ወደ ዋንዳር አካባቢ በላከው መልዕክት «ዋንዳር ወላይታን አበላሽቶ ሲያበቃ ጋሞን ሊበክል ሰዎች ልኳል፥ እርሱ መኖር የለበትምና አጥፉት፥ እስካሁን ብዙ ጥፋት አድርሷልና» ብሎ አስተላለፈ።

በአንድ እሁድ አማኞች በዋንደር ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ሳለ ሰላሣ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች በድንገት ብቅ አሉ። እነዚህ ሰዎች የሚመጡ መሆናቸውን ዋንዳር ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሰማ በመሆኑ ክርስቲያኖቹ ባሳሰቡት መሠረት ከቤተ ክርስቲያኑ ሳይታይ ወጥቶ ለመሸሽግ ቻለ። ታጣቂዎቹም ጉባኤውን በሙሉ ነድተው አሰሩ። እሥራቱና ማስፈራሪያው መንፈሳቸውን በማቀዝቀዝ ፋንታ በደስታ ስለሞላቸው ሌሊቱን ሁሉ ሲዘምሩ አደሩ። ሲነጋም ወደየቤታቸው እንዲሄዱ ተለቀቁ።

ከአምስት ቀን በኋላ አንድ ባለሥልጣን ወደገበያ ቦታ ወጥቶ አዋጅ አሳወጀ። አዋጁ የተጀመረው በወላይታ ምሳሌያዊ አነጋገር ነበር፡- «የአንበጣ ንግሥት ክንፍ ባይኖራትም ብቻዋን ከተተወች ክንፍ አብቅላ መብረርዋ አይቀርም። ስለዚህ ንግሥቲቱን ክንፍ ከማብቀሏ በፊት ያዟት፥ ያለችበትን ለሚያገኝ አሥራ አምስት ብር ለገደላት ደግሞ ሰላሣ ብር ሽልማት ይሰጣል» ብሎ አስታወቀ።

በዚያን ዕለት ሌሊት ዋንዳር፥ ባለቤቱና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሆነው እርሱ ወደሚሸሸግበት ራቅ ያለ ሥፍራ ድብቁን መንገድ ይዘው ይጓዙ ነበር። ወደ አንድ ሌላ መንገድ ማቋረጫ ሲደርሱ ሁለት ሰዎች በበቅሎ ወይም በፈረስ የተቀመጡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያወሩ አለፉ። ሰዎቹ ጨለማ ስለነበር ዋንዳርንና ተከታዮቹን አላዩአቸውም፥ አልሰሟቸውምም።

«በዚህ ዛሬ በገበያ በተነገረው አዋጅ! የአንበጣ ንግሥት የተባለው ዋንዳሮ ካልሆነ ማን ይመስልሃል?»

«ዋንዳሮ ነው እንጂ! በእርግጥ እርሱ ነው፥ ሌላ ማን የአንበጣ ንግሥት ይሆናል? እየፈለጉት ነው ማለት ነው፥ ማንም እርሱ ያለበትን የጠቆመ አሥራ አምስት ብር የገደለ ደግሞ ሠላሳ ብር ይሸለማል አሉኮ!» አለ ሁለተኛው ሰው።

ድምፃቸው ከርቀት የተነሣ እየመነመነ ከሄደ በኋላ እነዋንዳሮ ለጥቂት በማምለጣቸውና ስለ አዋጁ በመስማታቸው እያመሰገኑ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። በሰሙት ዜና ምክንያት የዋንዳሮ መሸሽግ አስፈላጊነቱ ተረጋገጠ።

ዋንዳሮ ወደ መኖሪያ ቤቱና ቤተ ክርስቲያኑ የሚመለስበት አመቺ ሁኔታ እስከሚፈጠር ድረስ ብዙ ወራት አለፉ። ከተሸሸገም በኋላ ጥልቅና ዘላቂ እምነቱ በርሱ ምስክርነት ጌታን የተቀበሉትን እንደድንጋይ ተሸክሞ አቆይቶአቸዋል። በመቶዎች የሚቆጠሩ የአካባቢውና የሀገሩ ሰዎች መሪያቸው አድርገው ይመለከቱታል። ጥቂት በቀላሉ የሚታዩና የሚታወቁ የመሪነት ባሕሪያት አሉት። የዋንዳሮ ውብ ሕይወት እግዚአብሔር «. . . ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር . . . የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፥ የ. . . የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውም ነገር መረጠ» ለሚለው ትክክለኛ ማረጋገጫ ነበር። ዋንዳሮ ራሱን ሙሉ በሙሉ ካለውም አንዳች ሳያስቀር ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሰጠና ታዛዥ ነበር።

* * *

ሚሲዮናውያን ለቀው ከሄዱ በኋላ በሁለት ዓመታት ውስጥ በይበልጥ በቶሮና በገበቶ ምስክርነት አንድ መቶ ሰማኒያ ሰዎች በኮይሻ (ከሶዶ በስተምዕራብ) ተጠመቁ። ከዚያን በኋላ በዚያ ስደት ተጀመረ።

ቶሮና ገበቶን ጨምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ተይዘው እያንዳንዳቸው መቶ ጅራፍ ከተገረፉ በኋላ አሥር ወራት እሥራት ተፈርዶባቸው ወህኒ ቤት ገቡ። የእሥር ቤቱ ወለል አፈርና አቧራማ፥ ግድግዳው በጭቃ ያልተመረገና ነፋስ የማይከላከል፥ መስኮት፥ ንጽሕና፥ ምግብ የሌለውና እሥረኞች ከአቅሙ በላይ የታጨቁበት ነበር። ማታ ማታ ደግሞ በጣም ኃይለኛ ብርድ ስለሚገባ የተዳከሙ እሥረኞችን እየገረፈ የሞቱም እንዳሉ ታውቋል።

ከወህኒ ቤቱ አስተዳደር ስለማይቀርብላቸው ለመሪዎቻቸው ምግብ የማዘጋጀቱን ኃላፊነት የተሸከሙት ክርስቲያኖች ነበሩ። የእነሱ ፍቅርና መተሳሰብ ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች ዘንድ ልዩ ስሜት አሳደረ። ክርስቲያን ያልሆኑት «ችግር ፈጣሪዎች» እያሉ ከክርስቲያኖቹ ርቀው ለመቆየት የሞከሩ ቢሆንም መልካም ኑሯቸውን ለማየትና ለማድነቅ ችለዋል።

የክርስቲያኖቹ የእርስ በርስ ፍቅር በወላይታ ከተለመደው ከሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት በጣም የተለየ ስለነበር በአካባቢውና በእሥር ቤቱ ካሉት ሰዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ በኢየሱስ ክርስቶስና ሕይወትን መቀየር በሚችል ኃይሉ አመኑ።

ገበቶና ቶሮ አብረው መከራ ስለተቀበሉ በጣም ተቀራረቡ። ከእሥር ቤቱ እንደወጡ ገበቶ ለስድስት ወራት ቶሮ ደግሞ ለሥምንት ወራት ተሸሸጉ። በዚያን ጊዜ ውስጥ በኮይሻ የተጠመቁ አማኞች ቁጥር እስከ አራት መቶና ከዚያ በላይ ድረስ አደገ። በእሥር ቤትም ሆነ በውጭ ባሉ ሰዎች ፊት ግልጽ የሆነው የወላይታ ክርስቲያኖች ኑሮ ለቤተ ክርስቲያኑ እድገትና ለወንጌል ስብከት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። ሥቃይና እሥራትን እግዚአብሔር ለክብሩ ተጠቅሟል።

በመጨረሻም በራሱ በቶሮ ትውልድ ወረዳ ባለው ቤተ ክርስቲያን ያሉ አማኞች ከአንድ ሺህ በላይ ሆኑ። ከአካባቢው ገዥዎች ጥላቻና ቅናት እንዲሁም ደግሞ ከኢጣሊያን ባለሥልጣኖች ጭቆና የተነሣ ቶሮ እንደገና ታሠረ። በቆዳ አለንጋ በድጋሚ አርባ ጊዜ ተገረፈ። ይህ አልበቃ ተብሎ ኢጣሊያኑ ባለሥልጣን ሹል ጥርሶች ባሉት ጫማዎቹ በቶሮ ደረት ላይ ቆሞ ለመጨፍለቅ ጥቂት እስኪቀረው ድረስ ዘለለበት። ቶሮም የሕይወቱ መጨረሻ መድረሱን አመነ።

ቶሮ ሰውነቱን ማንቀሳቀስ፥ ማዘዝና መተንፈስም አቅቶት በእሥር ቤቱ ውስጥ እንደተኛ እርሱ እንደገለጸው ጌታ ይገለጥለታል። ይህ የሆነበት ጊዜ ሌሊትና ነገሩም ሕልም እንዳልሆነ ነገር ግን ጌታ ያሳየው ራእይ የመሰለና አስደናቂ ትርኢት ሲሆን ራሱን ጌታ ኢየሱስን በከፍተኛ ድምቀት ሆኖ ያየውና እጅግ የፈራ መሆኑን ቶሮ ተናግሮአል። ኢየሱስም ለርሱ ሲናገር፥ «ቶሮ! አትፍራ። አንተ ልጄና ታማኝ አገልጋዬ ነህ። ልብህ አይታወክ፥ በእግዚአብሔር እመን፥ በእኔም ደግሞ እመን። በአባቴ ቤት ብዙ መኖርያ አለ፥ እንዲህስ ባይሆን ባልሁህ ነበር፥ ሥፍራ ላዘጋጅልህ ዘንድ እሄዳለሁ፥ እኔ ባለሁበት አንተ ደግሞ ትሆናለህ።»

ቶሮ በዚያ ቦታ ፀጥ ብሎ ለረዥም ጊዜ እንደተኛና ከዚያን ወዲህም መቼም ፈርቶ እንደማያውቅ ይናገራል። ቀስ በቀስም ካደረበት ሕመም ዳነ።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከእሥር ቤት ወጣ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች መስበክና ቤተ ክርስቲያናቸውን መልሰው መገንባት ቢከለከሉም እንደቀደሙት የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እግዚአብሔርን መታዘዝ ስላለባቸው የሚሰብኩና ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚሠሩ መሆኑን ወሰኑ።

ክርስቲያኖቹ የፀሎት ቤታቸውን መልሰው ለመሥራት የቆረጡ መሆኑ ሲታወቅ በቶሮና በሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የባለሥልጣናት ቁጣ በከፋ ሁኔታ ወረደባቸው። ወደ ገበያ ሥፍራ ተወስደው በጭቃ መሬት ተደፍተው በመተኛት ራቁታቸውን እያንዳንዳቸው ከመቶ ጅራፍ በላይ ተገረፉ፥ የኢጣሊያን አሳሪዎቻቸው ያፌዙባቸው ነበር፡-

«እስቲ ከእጃችን ሊያድናችሁ የሚችል እግዚአብሔር የታለ? ከዚህ እስር ቤት በሕይወት እንደማትወጡ እወቁ።»

ቶሮ በጣም በደከመና ድምፁን ማሰማት በማይችልበት ሁኔታ «የኔ እግዚአብሔር ፀሎትን ይሰማል - ሊያድነኝም ይችላል - ሊያድነኝ ባይፈልግ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንድኖር ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚወስደኝ ተስፋ ሰጥቶኛል» አለ።

ከዚያን በኋላ አንድ ቀን ጥቂት ክርስቲያኖች በአንድነት ሆነው ሲጸልዩ ከባድ ዝናብና ነጐድጓድ መጣ። ቶሮ እንደዚህ ያለ አስደንጋጭ መብረቅና የነጐድጓድ ድምፅ አይቶና ሰምቶ እንደማያውቅ ይናገራል። በመጸለይና በመዘመር ላይ እንዳሉ ኃይለኛ ነፋስ መጥቶ የእሥር ቤቱን የቆርቆሮ ጣሪያ አንስቶ በታተነው። የዝናብ ውሃ በግድግዳው ላይ ሲፈስ ጭቃው ሟሟቶ በስብሶና ተሰባብሮም ወደቀ። እሥረኞችም ነፃ ወጡ።

ክርስቲያን ያልሆኑ እሥረኞች አብዛኛዎቹ አመለጡ። የእሥር ቤቱ አዛዦች በጣም ፈርተው ይህ ለክርስቲያኖች ሲል እግዚአብሔር በቀጥታ ጠልቃ ሲገባ እንደሆነ በማመን እግዚአብሔር ቁጣውን ያነሣ ዘንድ እንዲጸልዩ ከዚያም የሚለቀቁ መሆኑን ለቶሮ በመንገር ተማፀኑ። በኋላም በገቡት ቃል መሠረት ለቀቋቸው።

አንድ ጊዜ ቶሮ በአስከፊ ሁኔታ ከተገረፈ በኋላ «መከራን ብንቀበል ከእርሱ ጋር እንነግሣለን» የሚል በታሠሩ ክርስቲያኖች ዘንድ የተወደደ መዝሙር ደረሰ:-

በምድር ትንሽ መከራ ብንቀበል በላይ ትንሽ ሽልማት አለን

እንነግሣለን

እዚህ (አሁን) ለምን ትንሽ መከራ አናይም?

እንነግሣለን

ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንነግሣለን

እንነግሣለን።

# ክፍል ስድስት ፡- ቤንዚን መጨመር

## ምዕራፍ 15. ቋጠሮችን መፍታት

*ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።*

1ኛ ቆሮ. 16፡9

የወላይታ አውራጃ ገዥ ግራ ገብቶአቸዋል። በየካቲት ወር 1937 ዓ.ም. አንድ ቀን ማለዳ በሶዶ ከተማ አንድ እንግዳ ነገር ተከሰተ። ወሬውን ለገዥው ያመጡ መልዕክተኞች ቢሮአቸውን ለቀው ከሄዱ ጥቂት ደቂቃዎች አልፈዋል። እርሳቸው ግን የነገሩን ክብደትና ቅለት እያሰቡና እያመዛዘኑ በፀጥታ ተቀምጠዋል።

በረዥሙ ጠረጴዛቸው ላይ በማህተም ያሸበረቁ የመንግሥት ወረቀቶችና ደብዳቤዎች የተዘረጉ ቢሆንም ስሜታቸው ሙሉ በሙሉ ያተኮረው በሰሙት ዜና ላይ እንጂ ደብዳቤዎቹ በያዙት ጉዳዮች ላይ አልነበረም። መልዕክተኞቹ የነገሯቸው አራት እግር ያለው ሚጪት ስለመፈልፈሉ ሲሆን ይህም ችላ ተብሎ የማይታለፍ እንግዳ የሆነ ነገር ነበር።

የማይቀረውን መቀበል ያለባቸው መሆኑን ለማመልከት ‹ግድ የለም› በሚል አኳኋን ትከሻቸውን ነቀነቁ። እጃቸውን በማጨብጨብ ፀሐፊያቸውን ከጠሩ በኋላ በወንበራቸው ወደኋላ በመደገፍ ተዝናንተው ተቀመጡ።

«ነጮቹን አስገባቸው» አሉ።

ላውሬና ሊሊ ዳቪሰን ከሁለት ሴት ልጆቻቸው ጋር እንዲሁም ሰልማ በርግስተንና አልፍሬድ ሮከ እነሱን ተከትለው ሲገቡ ገዥው ክብር ተሰምቷቸው ይሁን ትዕግሥት አጥተው ኮስተር ብለዋል። ፈገግታ ሳያሳዩ ከወንበራቸው ተነስተውና አንገታቸውን ዝቅ አድርገው በኢትዮጵያዊ ትህትና ሰላምታ ከሰጧቸው በኋላ ወደ ወንበሮች መሩአቸው።

በዚያ ቀዝቃዛ ብርዳም ማለዳ ለምን እንደመጡ ሚስዮናውያኑን ከመጠየቃቸው በፊት ለአጭር ጊዜ ዝምታ ነበር። ሚስተር ዳቪሰን ከአንድ ቀን በፊት ሶዶ የደረሱና በዚያ ቀርተው ለመኖር ያቀዱ መሆናቸውን አስረድቶ የጉዞ ፈቃድ ወረቀቶችን ገዥው እንዲመለከቱት አቀረበ። ገዥው የፈቃድ ወረቀቶችንና የመታወቂያዎችን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ በጥንቃቄ መረመሩ። እሳቸው ከሚሲዮናውያንና ከሚሲዮን ሥራ ጋር የቅርብ ትውውቅ የሌላቸው በመሆኑ ሠነዶቹን በሚመለከቱበት ጊዜ የተደናገሩ መሆኑን ፊታቸው ይመሰክር

ነበር። ከዚህም የተነሣ ሚሲዮናውያኑ ወይ የፈቃድ ወረቀቶቻቸው ዋጋ የሌላቸው (የማይሠሩ) ወይንም ደግሞ የገዥውን አእምሮ የሚረብሽ አንድ ነገር እንዳለ አመኑ።

ወዲያው በመድረሻቸውና በቆይታቸው ጉዳይ ውይይት መሐል ገዥው ስለ ባለ አራት እግር ሜጩት አነሱ። ዜናው ሚስዮናውያንን የሚሉትን ሲያሳጣቸው ገዥው ከእነሱ የበለጠ የሚሉትን አጡ። በአእምሮአቸው ውስጥ የሚመላለሱ ነገሮችን ለማስተካከል እየሞከሩ ሚሲዮናውያንን በጥንቃቄ አጠኑአቸው። ያ በዚያን ማለዳ በከተማ የተወለደው ባለ አራት እግር ጉደኛ ሜጩት ምን ቁም ነገር አለው? ከእነዚሁ ነጮች መምጣት ጋርስ ምን ግንኙነት አለው? እንደዚህ ዓይነት ያልተለመደ ክስተት መጥፎ ትርጉም ሳይኖረው አይቀርም። የማይታየው ዓለም ምናልባት ታላቁ መልዕክት እንዲሰማ ፈልጎ ይሆናልና መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመው ይህን ባለአራት እግር ሜጩት መወለድን ነበር። ይህም በእርግጥ በጥንቃቄ ማጥናትን የሚጠይቅ ነበር።

ሚሲዮናውያኑ እንግዳ የሆነባቸውን የገዥውን ጠባይ የመምጣታቸው ጥላቻ አድርገው መተርጎም ስለነበረባቸው በፀሎትና በጉጉት ነበር የተቀመጡት። የመኖሪያ ፈቃዳቸውን የማግኘቱ ጥያቄም ያሳስባቸው ነበር። ስለ እኚህም የተማሩና ትልቅ ባለሥልጣን ሰው ጠባይ ትንሽ ፍንጭ አገኙ። በጠባያቸውም ተማርኩ። በጥንቃቄ ከሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መረዳት እንደሚቻለው የሚያዳምጡት በአብዛኛው የማይታየውን (መንፈሳዊ) ዓለም ድምፅ እንጂ በፊታቸው የተዘረጉትን መንግሥታዊ ሠነዶች አልነበረም።

ሚሲዮናውያኑ በተደጋጋሚ ተመላልሰው ካነጋገሯቸው በኋላ ገዥው በአካባቢው ሊቆዩ እንደሚችሉ (ቢያንስ በጊዚያዊነት) ፈቀዱላቸው። በአዲስ አበባ ያሉ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ሚሲዮናውያኑ ወደ ወላይታ ተመልሰው የቀድሞ ሚሲዮን ጣቢያቸውንና ሕንፃዎቻቸውን እንዲይዙ ቢፈቅዱላቸውም የአውራጃው ባለሥልጣኖች ሐሳብ ከዚህ የተለየ ነበር። የቀድሞ ንብረታቸውን እንዲረከቡ ስላልፈቀዱላቸው ሚስዮናውያኑ ከጣቢያው ከአንድ ማይል በላይ ርቆ በሶዶ ከተማ ቤት ተከራዩ። የጉደኛው ሜጩት የመጨረሻ እድል ወይም እሱ ከሚሲዮናውያን ጋር የነበረው ግኙኝነት እስከመጨረሻ ሳይታወቅ ነበር የቀረው።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ሶዶን ጎበኙ። ወቅቱ በኢትዮጵያ መልሶ ግንባታና ማቋቋሚያ የሚካሄድበትና ብዙ የሚሠራ ነገር የነበረበት በመሆኑ ንጉሡና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በአገሪቱ ውስጥ ከአንዱ ክፍል ወደሌላው በመዘዋወር ሕግና ሥርዓት እንዲሰፍንና አስተዳደራዊ መዋቅሮችም እንዲዘረጉ ያደርጉ ነበር። በሶዶ ከተማ በቆዩባቸው ብዙ ቀናትም ከገዥውና ከአካባቢው (ከወላይታ) መሪዎች ጋር ረጅም ጊዜ የፈጁ ስብሰባዎችን አካሂደዋል።

ኢጣሊያውኖቹ የሚሲዮኑን ጣቢያ ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ሆስፒታሉን ለራሳቸው ሲጠቀሙ የቆዩ ሲሆን ከአነስተኛ ለውጥ በስተቀር ለቀው ሲሄዱ ምንም አላጎደሉበትም ነበር። አሁን ግን ግቢውና ሕንፃዎች የሚጠቀምባቸውን አጥተው የቆዩና ማንም ሲገባና ሲወጣባቸው ስለነበር ሁሉም ነገር

የተዝረከረከ፣ የበሰበሰና የወዳደቀ ይመስላል፣ ጥገናም አልተደረገላቸውም። ንጉሡና የክብር ተከታዮቻቸው መላውን ግቢ እየተዘዋወሩ የተመለከቱ ቢሆንም ባልታወቀ ምክንያት ሚስዮናውያን ወደ ጣቢያቸው እንዲመለሱና እንዲረከቡ አልፈቀዱም።

ላውሬ ዳቭሰን በኋላ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር። «ገዥው በወላይታ ሕዝቦች መካከል የወንጌልን ሥርጭትና ተጽዕኖ ከሚቃወሙት ጋር በስውር ተባብረው ይሠሩ ነበር። እኛ በደረስንበትና ቢሮአቸውን በጎበኘንበት ጊዜ ያሳዩት ፍርሃትና ጥላቻ እንዲሁም ደግሞ የባላ አራት እግር እንግዳ ሚጩት ጉዳይ የመነጨው ከዚህ መጥፎ ጥርጣሬ ሳይሆን አይቀርም።»

ከንጉሡ ጉብኝት ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ የአንድ ሰው ምስቶች የነበሩ ሁለት የወላይታ ሴቶች ወንጌል ሰምተው ይህንን አዲስ መንገድ ለመከተል ወሰኑ። ውሳኔያቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ ባላቸውን ስላስቆጣው እንዲመክራቸውና ሃሳባቸውን እንዲያስቀይራቸው ቄስ ቢጋብዝም ሴቶቹ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ የማይሳተፉ መሆናቸውን ደግመው አረጋገጡ። እምቢታቸው ተቃውሞ በማስነሣቱ ወኅኒ ገብተው በእግር ብረት እንዲታሠሩ ተደረገ፤ በመላ ወላይታ የነበሩ ክርስቲያኖችም እነርሱ እንዲፈቱ ይፀልዩ ነበር።

ንጉሡ ጉብኝቱን በሚያደርጉበት ጊዜ ሚሲዮናውያን የነዚህን አማኝ ሴቶች መታሠር ያውቁ ነበር። ንጉሡን አጅበው ከመጡት ሰዎች ውስጥ አንዱ ቀድሞ የሚሲዮናውያኗ ወዳጅ የነበረ በመሆኑ በጉብኝቱ ቀናት አብሮአቸው ቆይቶ ነበር። ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሚስተር ዳቭሰን ለሰውየው የወላይታ አማኝ ሴቶች በብረት ታስረው እስር ቤት ያሉመሆናቸውን ነግሮት ስለነበር ሰውየው ለንጉሡ አሰማ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሴቶቹን በብረት መታሰር ሲሰሙ በጣም ደነገጡ። በእሥር ቤት አንዳንድ ጊዜ ወንዶች በብረት እንዲታሠሩ ይደረጋል፣ ነገር ግን ሴቶች በፍጹም በብረት አይታሠሩም ነበር።

ንጉሡም ሴቶቹን አስጠርተው በጥንቃቄ ከጠየቋቸውና ካነገሩዋቸው በኋላ ወዲያው እንዲፈቱ አዘዙ። በዚህ አጋጣሚ ሴት እሥረኞችን ተከትለው ለመጡ በመቶ ለሚቆጠሩ ሰዎች ባደረጉት ንግግር አሁን በአገራቸው በመላ የሃይማኖት ነፃነት እንዳለ አውጀዋል። ይህ የንጉሡ ያልታሰበ አመለካከት ገዥውን ከማስከፋቱም በላይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄሶች የበለጠ ጥላቻ እንዲያድርባቸው አድርጓል።

«የሆነ ሆኖ» አለ ላውሬ ዳቭሰን «የታሰሩ ሴቶችን መከራ ማሳወቅ ያለብን መሆኑ ተሰማን። ይህንን ማድረግ አቋማችንን አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን ብናውቅም ሌላ ምርጫ አልነበረም። ጌታም ይህንን የእምነት ሥራ ደግፎአል። ይህ ደግሞ የወላይታ አማኞችን እምነት ለማጠንከር ከመርዳቱም በላይ በክርስቶስ ከማመናቸው የተነሣ በእሥር ላሉት ለሌሎችም እንዲጸልዩ አበርትቶአቸዋል።»

አማኞቹ ወንጌልን ስለ ሰበኩ ብቻ ለዓመታት ሲያዙና ሲታሠሩ ቆይተዋል። ለማስፈታት አቤቱታ በሚቀርብላቸው ጊዜ ሁሉ ንጉሡ ርኅራኄ እያሳዩ ያስፈቷቸው ነበር። በእሳቸው አመለካከት በሕገ መንግሥቱም በግልጽ እንደተቀመጠው በሀገሪቱ የኃይማኖት ነፃነት አለ ቢባልም በብዙ ቦታዎች

በተለይም ከማዕከላዊ መንግሥት መቀመጫ (መናገሻ) ከተማ ርቀው ባሉት ግልጽ ችግሮችና ተቃውሞ ነበር።

*　　　*　　　*

ዋልተር ኦህማን፥ ማርሴላ ኦህማንና ሰልማ በርግሥተን ወደ ወላይታ በተመለሱ ጊዜ የወላይታ አማኞች እንዲህ ብለው ተናገሩ፡- «ከዚህ በሄዳችሁበት ጊዜ በሰማይ በእግዚአብሔር ቤት እንጂ በዚህ ምድር ዳግመኛ ልናያችሁ ተስፋ አላደረግንም ነበር።»

በሐምሌ ወር 1937 ዓ.ም. ኦህማንና ቤተሰቡ ሶዶ ከተማ በደረሱ ጊዜ በወላይታ አሥራ አምስት ሺህ የተጠመቁ አማኞች የነበሩ ሲሆን አብዛኞዎቹ ሚስዮናውያንን ከማመናቸው በፊት ያውቋቸው ነበር። አሁን ክርስቶስ የሚያድናቸው መሆኑን አውቀው ማመናቸውን ለሚሲዮናውያን ለመናገር ሲጎርፉ ማየት ስሜትን ይማርክ ነበር።

በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ዘመናት ኦህማንና ቤተሰቡ በሱዳን ባሉ መባኖች መካከል ሲያገለግሉ የቆዩ ሲሆን አሁን በኢትዮጵያ የአገልግሎት በር እንደገና በመከፈቱ የመጀመሪያ ፍቅራቸው ወደሆነችው አገር ተመልሰው መጡ።

የቀድሞ ግቢ ለሚሲዮናውያን ያልተመለሰላቸው በመሆኑ በመጀመሪያ ሶዶ እንደተመለሱ ያረፉት ለጊዜው በሶዶ ከተማ ቤት ተከራይተው ከሚኖሩ ከዳቭሰንና ቤተሰቡ ጋር ነበር። ሚስዮናውያኑ በገጠሩ ዞረው ቤተ ክርስቲያናትን እንዳይመለከቱ ተከልክለው እንደቁም እሥረኛ ቢቆጠሩም በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ያለ ምንም ገደብ እየመጡ እነዚህን የተወደዱ መንፈሳዊ አባቶቻቸውን ይጠይቁ ነበር። በአንድ ወር ውስጥ ሚሲዮናውያኑን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ከአንድ ሺህ አምስት መቶ የሚበልጡ ሰዎች አንዳንዶቹ ብዙ ማይሎችን ተጉዘው መጥተዋል።

የሚሲዮናውያኑ በከተማ ተወስኖ መቅረት የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናት ቀንና ማታ ለማካሄድ የረዳ በመሆኑ የተደበቀ በረከት ነበር። ጊዜውን ተጠቅሞ ተጨባጭና ዘላቂ ውጤት ለማግኘት እንዲቻል ማስተማሩ በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎችን እንዲይዝና እንዲረዳ ተደርጓል።

እነኦህማን የተከሩዩትና የሚኖሩበት ቤት ሦስት ክፍሎች አሉት። ከሰኞ እስከ አርብ ሌሊት ሌሊት ከየወረዳው አሥራ አምስት (ብዙውን ጊዜ ሰላሣ) ሰዎች ተጋብዘው ይመጡና ለብዙ ሰዓታት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከተካሄደ በኋላ ሰዎቹ በማድ ቤቱና ምግብ ቤቱ ወለል ተኝተው ሌሊቱን ያሳልፋሉ። ሲነጋም ወደየቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት ለአንድ ሰዓት ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይኖራቸዋል።

በእግዚአብሔር ቃል ጥናታቸው ሰዎቹ ብዙውን ጊዜ የሚመለከቱት ሚሲዮናውያን ባልነበሩበት ጊዜ የተነሱትን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ሥነ ሥርዓት ችግሮችን ነበር። በቋንቋቸው የተተረጎመ የእግዚአብሔር ቃል ካለመኖሩ የተነሣ አንዳንድ ነገሮች የተዛቡ ከመሆናቸው በቀር የዶክትሪን ጥራትና ከአማኞች ጋር አብሮ የመኖር ጉዳይ የሚደነቅ ነበር። ይህም መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ተራ ሰዎች በቀጥታ ሊያስተምራቸው የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ነበር።

«ብዙዎቹ እኛ መልስ እንድንሰጥ የተጠየቅንባቸው ጥያቄዎች ናቸው» ሲል ዋልተር አህማን አስታወሰ። «አንድ ቀን አንድ ሰው አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ለምን በምስጢር እንደሚካሄድ ለመጠየቅ እያመላመለ መጣ። በወር አንድ ጊዜ ከሚኖር ስብሰባ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች እንዲወጡ ይጠየቅ ነበር። ሰውየው አማኝ ስላልነበረ እንዲወጣ ተደርጎ ባለቤቱ ግን አማኝ ስለነበረች በስብሰባው እንድትቆይ በመፈቀዱ «እኛ ከወጣን በኋላ በውስጥ ቀርተው የሚያካሂዱት ምን ይሆን?› ነበር ጥያቄው።

«እስከዚያ ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያን መጎብኘት ስላልተፈቀደልን ይህንን ያላመኑትን የማስወጣት ልምድ አላወቅነውም ነበር። በወር አንድ ጊዜ የጌታ እራት ሥነ ሥርዓት እንዳላቸውና ይህንንም ምስጢር ነው ብለው እንደሚመለከቱ አንዳንድ ሽማግሌዎችን ጠይቀን ተረዳን።

«ሚሲዮናውያን አገሪቱን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት የጌታ ራትን ሥነ ሥርዓት ለማካሄድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከክርስቲያኖች ጋር ይሰበሰቡ ነበር። የተጠመቁ አማኞች ቁጥር ብዙ ስላልነበረ የሚሰበሰቡት በሚሲዮኑ ከሚገኙ ቤቶች በአንዱ መሆኑንም በማየት የወላይታ ክርስቲያኖች ሥነ ሥርዓቱ ያላመኑት ባሉበት አይካሄድም የሚል ሀሳብ አደረባቸው። በተጨማሪም ለጥምቀት የታጩ አማኞች በጌታ እራት አወሳሰድ ጊዜ የሚከናወነውን ሥነ ሥርዓት ሁሉ በምስጢር ለመያዝና ለማንም ላለመናገር ቃል ካልገቡ እንደማይጠመቁ ለማወቅ ቻልን። ምንም እንኳን ያልተጠመቁ አማኞችና ያላመኑት እንዲወጡ ቢደረግም ቀጥሎ በሚከናወነው የመባ አገልግሎት እንዲካፈሉ ከጌታ እራት በኋላ እንዲገቡ መደረጉን ባወቅንበት ጊዜ ተደስተናል።»

ስለዚሁ ጉዳይ ዋልተር አህማን ሽማግሌዎችን በጠየቃቸው ጊዜ እነርሱ «እንዴ! እስካሁን ስንሠራ የቆየነው በዚህ አኳኋን ነው፣ ይህንን አሠራር እንወደዋለንና ለመቀየር ፍላጎት የለንም» አሉ። ነገር ግን ከሚሲዮናውያን ጋር 1ኛ ቆሮ. 11፡23-27ን በጥንቃቄ ካጠኑ በኋላ የሥርዓቱን አካሄድ በስህተት የተረጎሙ መሆኑንና እንዲያውም የጌታ እራት ሥርዓት ለማያምኑት ምስክርነት ይሆን ዘንድ የታቀደ መሆኑ ግልጽ ሆነላቸው።

በተከታታይ ማታ ማታ በተካሄዱት ስብሰባዎችና ውይይቶች ሌሎች ጉዳዮችም ተነስተዋል። በአንድ ምሽት ስለልምዶቻቸውና በኑሮአቸው ስለተከሰቱት ለውጦች ሲወያዩ አንድ ሰው ፍየልን ማርባት የሚከለክል ምክንያት ካለ እንዲገለጽለት ጠየቀ። ሰዎቹም በማቴዎስ ወንጌል በጐችና ፍየሎች እንደሚለዩ ስላነበቡ ፍየል በቤታቸው የማያረቡና የማያኖሩ መሆኑን ገለጹ።

የቤተ ክርስቲያናቱ መሪዎች (ፓስተሮች) የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት በትንሹ ብቻ የሚያውቁ መሆናቸውን ከነዚሁ የምሽት ጥናቶች ሚሲዮናውያን ማወቅ ስለቻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በቀደምትነት የሚያስፈልግ መሆኑን ተገነዘቡ። ብዙ መሪዎች ያልተማሩ ከመሆናቸው የተነሣ አንዳንዶቹ

ሕግን ስለመፈጸም ይሰብኩ ነበር። ቤተ ክርስቲያናቱም (አባላቱ) በዓርብ ዕለት ይጾሙ ነበር።

በሌላ በኩል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለፀሎት፥ ስለ ችግሮች ለመወያየትና የትምህርት ጉድለትን ለመቋቋም የሚመካከሩበትን ስብሰባ በየወሩ እንደሚያደረጉ ለሚሲዮናውያን ተገለጸ። ከተለያዩ ወረዳዎች የተመረጡ ሽማግሌዎች (በ1938 ዓ.ም. ስምንት ወረዳዎች) ይሳተፉ ነበር። አንድ መቶ ሃምሣ ቤተ ክርስቲያናት እያንዳንዳቸው ሁለት ተወካዮችን በተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት ለሚካሄዱ ስብሰባዎች ይልኩ ነበር።

ወደቀድሞው የአቶና ሚስዮን ጣቢያ እንድንንቀሳቀስ የተፈቀደልን በ1938 ዓ.ም. መከር ወራት ላይ ነበር። ቀደም ብሎ በ1930 ዓ.ም. ስለተወረሱ ንብረቶች ለኤስ.አይ.ኤም. በኢጣሊያ መንግሥት ካሣ የተከፈለ በመሆኑ የቀድሞቹ የሚሲዮኑ ንብረቶች አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ናቸው። ሚሲዮናውያኑ ጣቢያውንና ንብረቶቹን እንዲጠቀሙ ለሆስፒታሉ ዶክተር እንዲያቀርቡ ከመንግሥት ጋር ውል ተደረገ።

ነገር ግን በመኖሪያ ቤቶችም ሆነ በሆስፒታሉ ሕንፃ ክፍሎች ውስጥ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ከእንስሳዎቻቸው ጋር ይኖሩባቸው ነበር። የወንዶች ሕክምና ክፍል ፍርድ ቤት የተደረገ ሲሆን ዕቃ ቤቱን ዳኛው የፈረስ ጋጥ ያደረገው ይሁን እንጂ ፍጉ እስከ አንድ ሜትርና ከዚያም በሚበልጥ ከፍታ ተቆልሏል። ሚስተር አህማንና ቤተሰቡ ከዶክተር ናታን ባርሎ ጋር በመሆን ወደ ሕንፃዎቹ ተዛውረው እንዲኖሩ መብታቸው ቢሆንም ንብረቶቹን በእጅ ማድረጉ ሌላው አስቸጋሪ ጉዳይ ነበር። ሕጋዊ ያልሆኑ ነዋሪዎችን ከሕንፃዎቹ ማስወጣት ከፍተኛ ዲፕሎማሲ የጠየቀ ቢሆንም አንድ በአንድ ክፍሎቹ ተለቅቀው ተወሰዱ፥ ከጸዱ፥ ዕቃ ከገባባቸውና ከተጌጡ በኋላም እንዲቆለፉ ተደረገ።

በመጨረሻም በጥቅምት ወር ወደ ሕንፃዎቹ መዛወር ተቻለ። ለሆስፒታሉ መገልገያዎች ከመታዘዛቸው በፊት የዶክተሩ መምጣት ከአቶና አልፎና ርቆ ተወርቶ በሽተኞች ለሕክምና መምጣት ጀምረው ነበር።

በመጨረሻም ዋንዳር ከእስር ተፈቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ዶጊሃ አሁንም በአቅራቢያው ይኖራሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የደረሰ ሰብላቸውን ለመሰብሰብ እንዲረዷቸው በቂ ክርስቲያኖችን እንዲያመጣላቸው ዋንዳርን ጠየቁ። «አንተን መግደል እችላለሁ ብዬ ነበር፥ ሞክሬም ነበር፥ ነገር ግን እግዚአብሔር አድኖሃል፥ እንግዲህ እንድትረዳኝ በእግዚአብሔር ስም እጠይቅሃለሁ» አሉ ለዋንዳር።

ዋንዳር ከአንድ መቶ የሚበልጡ ክርስቲያኖች አስከትሎ መከራ ሲያሳየው የነበረውን ሰው በእህሉ መሰብሰብ ሥራ ሊረዳው ሄደ። ክርስቲያኖቹ ሲሄዱም ሆነ ሲሠሩ ይዘምሩ ነበር።

በኋላም ዶጊሃ ዋንዳርን «በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ከቶሮ፥ ባሩምና ገበቶ ጋር ብትመጣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቄስ አስጠርቼ ግርዘትና መጠጥ በመጽሐፍ ቅዱስ መከልከሉን ከእናንተም ከቄሱም እንሰማለን። ያልተከለከለ ቢሆን ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከለ ነው ያላችሁት እውነት ስላልሆነ ሦስቱ ሰዎችህ ይሞታሉ» ብለው አስጠነቀቁ። ዶጊሃ ይህን የተናገሩት በአሥራ አምስቱ ቀናት የሚደርስባቸውን ሳያውቁ ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ በቤታቸው በወንበር ላይ ተቀምጠው እንዳሉ ወደኋላ ወድቀው ወዲያው በመሞታቸው በግርዘትና በመጠጥ ላይ ሊካሄድ የታቀደው ክርክርና ውይይት ሳይደረግ ቀረ።

ጥቂት ጊዜ ከዶጊሃ ሞት በኋላ ከዋንዳር አካባቢ ብዙ አማኞች ለስብከት ወደ ጎረቤት ጋሞ አውራጃ ሄዱ። የጋሞ ገዥ ወደ ዋንዳር አካባቢ በላከው መልዕክት «ዋንዳር ወላይታን አበላሽቶ ሲያበቃ ጋሞን ሊበክል ሰዎች ልኳል፥ እርሱ መኖር የለበትምና አጥፉት፥ እስካሁን ብዙ ጥፋት አድርሷልና» ብሎ አስተላለፈ።

በአንድ እሁድ አማኞች በዋንደር ቤተ ክርስቲያን ተሰብሰበው ሳለ ሰላማ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች በድንገት ብቅ አሉ። እነዚህ ሰዎች የሚመጡ መሆናቸውን ዋንዳር ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሰማ በመሆኑ ክርስቲያኖቹ ባሳሰቡት መሠረት ከቤተ ክርስቲያኑ ሳይታይ ወጥቶ ለመሸሽግ ቻለ። ታጣቂዎቹም ጉባኤውን በሙሉ ነድተው አሰሩ። እሥራቱና ማስፈራሪያው መንፈሳቸውን በማቀዝቀዝ ፋንታ በደስታ ስለሞላቸው ሌሊቱን ሁሉ ሲዘምሩ አደሩ። ሲነጋም ወደየቤታቸው እንዲሄዱ ተለቀቁ።

ከአምስት ቀን በኋላ አንድ ባለሥልጣን ወደገበያ ቦታ ወጥቶ አዋጅ አሳወጀ። አዋጁ የተጀመረው በወላይታ ምሳሌያዊ አነጋገር ነበር፡- «የአንበጣ ንግሥት ክንፍ ባይኖራትም ብቻዋን ከተተወች ክንፍ አብቅላ መብረርዋ አይቀርም። ስለዚህ ንግሥቲቱን ክንፍ ከማብቀሏ በፊት ያዟት፥ ያለችበትን ለሚያገኝ አሥራ አምስት ብር ለገደላት ደግሞ ሰላሣ ብር ሽልማት ይሰጣል» ብሎ አስታወቀ።

በዚያን ዕለት ሌሊት ዋንዳር፥ ባለቤቱና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሆነው እርሱ ወደሚሸሸግበት ራቅ ያለ ሥፍራ ድብቁን መንገድ ይዘው ይጓዙ ነበር። ወደ አንድ ሌላ መንገድ ማቋረጫ ሲደርሱ ሁለት ሰዎች በበቅሎ ወይም በፈረስ የተቀመጡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያወሩ አለፉ። ሰዎቹ ጨለማ ስለነበር ዋንዳርንና ተከታዮቹን አላዩአቸውም፥ አልሰሟቸውምም።

# ምዕራፍ 16. ምግብ ለአካል - ምግብ ለነፍስ

እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው፥ ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው።

የሐዋ. ሥራ 11:23

«አንድ ቀን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ ወደ እኔ መጥቶ ራቅ ብሎ በወላይታ ድንበር አካባቢ ለሚካሄድ የጥምቀት አገልግሎት አብሬው እንድሄድ ጠየቀኝ» አለ ላውሬ ዳቭሰን ሲናገር። «በጣም ጥሩ ቀን ያለመሆኑን ባውቅም ደስ ብሎኝ ሄድኩ። ከርቀቱ የተነሣ ካሰብንበት መድረስ ባለመቻላችን በመንገድ ለአዳር ቆይታ አደረግን። በነጋታውም ጧት ከቦታው ስንደርስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተሰብስበው አገኘን። በድጋሚ ወደ አካባቢው ስመጣና በቤተ ክርስቲያናት መካከል ተገኝቼ ነገሮች እንደነበሩ መሆናቸውን ስመለከት ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። በመሠራት ላይ ካለው አዲሱ ቤተ ክርስቲያን (ሕንፃ) ግማሽ ማይል ያህል ርቆ በሚገኘው ጅረት ለሚደረገው የጥምቀት አገልግሎት ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ሕዝቡ ወደዚያ ጉዞ ሲጀምር እኔም የሚሆነውን ለማየት አብሬ ሄድኩ። ከጥምቀቱ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመለስበት ጊዜ ለሕዝቡ ንግግር የማደርግ መሆኔ ተነግሮኝ ነበር። አንድ መጋቢና (አስተማሪ) ሁለት ሽማግሌዎች ስድሣ ሰዎችን ካጠመቁ በኋላ ሁላችንም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተመለስን። ጥምቀቱም ረዥም ጊዜ ፈጅቶ ነበር።

«በጣም የሚያስደስት ጊዜ ነበር። በመጀመሪያ ለጥምቀቱ ወደ ወንዝ ሲሄድ ዝም ብሎ በፀጥታ ተጉዞ የነበረው ሕዝብ አሁን ከጥምቀቱ ሲመለስ በከፍተኛ ድምፅ ይጮኽና ይዘምር ነበር። የልባቸው ጥልቅ ምንጭ ተነክቶ የማይገታ የደስታ ስሜትን የሚያፈልቅ ይመስላል።

«የሄድንበት ቤተ ክርስቲያን ትልቅና ከብ ቤት ሲሆን ገና በመገንባት ላይ የነበረ ከመሆኑ የተነሣ ግድግዳ ኖሮት ጣራው ባለመሠራቱ ወደላይ ሲመለከቱት ደመናማው ሰማይ ይታይ ነበር። ሕንፃው እንደሌሎቹ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ሁሉ ትልቅና በውስጡ ወለል ላይ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ሊቀመጡ የሚችሉበት ነበር።

«ንግግሬን ስጀምር መዝነብ ጀመረ። ከአማኞቹ አንዱ በፍጥነት ወደውጭ ወጥቶ ከእንሰቱ ትልቅ የከባ ቅጠል ቆርጦ አመጣና ከራሴ በላይ በመያዝ ከዝናቡ እየተጠለልኩ ከፊታቸው ቆሜ ከፍቼ ከነበርኩበት አዲስ ኪዳን ውስጥ አዲስ ስላመኑት ጌታ (ኢየሱስ) ማወቅ የሚፈልጉትን አካፈልኳቸው።

«የከባው ከለላ በነፋስ ወዲያና ወዲህ እየተወዛወዘ ያስቸግር ነበር። ሕዝቡም ከዝናቡ ለመሸሽና ወደየቤቱ ለመሄድ ሳይንቀሳቀስ በተቀመጠበት ፀጥ ብሎ ሰፋ ላለ ጊዜ ያካፈልኩትን የእግዚአብሔር ቃል አዳመጠ።

«ዝናቡ ሲያባራ ለቁርባን አገልግሎት ዝግጅት ተደረገ። ማር በውሃ ተበጥብጦ ለቁርባኑ ወይን ሲዘጋጅ ዳቦው ደግሞ ከቦቆሎ የተሠራ የወላይታ ቂጣ ነበር። ዳቦው በትናንሹ ተሰባብሮ ሕዝቡ አንዳንድ እንዲወስዱ ሽማግሌዎች ያዞሩታል። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሰው የሞላና አቀማመጡም ያለመሥመር በመሆኑ መተላለፊያ አልነበረም። ከዚህም የተነሣ ሽማግሌዎቹ ቁርባኑን ሲያድሉ በሰው መካከል ከቦታ ወደ ቦታ የሚተላለፉት እየዘለሉ ነበር። አስቀድሞ ለተለያየ ግልጋሎት በተሠሩ መጠናቸውና ቅርፃቸው በተለያዩ ጠርሙሶች ተሞልቶ የቀረበውን ወይን አንዱ አማኝ ተቀብሎ በትንሹ ፉት ካለ በኋላ ለሚቀጥለው ያስተላልፋል። በምዕራብ አገሮች ቤተ ክርስቲያናት ዓይን ሲታይ ይህ አስነዋሪ ኋላ ቀርነትና በነዚያ ቤተ ክርስቲያናት ከተለመደው የቁርባን አገልግሎት ክብር በጣም የራቀ ሊመስል ይችላል። ለእነዚህ ሰዎች ግን የእግዚአብሔርን መኖርና ኃይል የሚያመለክት ነዋሪ ምልክት ነበር።»

* * *

የጥምቀት አገልግሎት ካለፈ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ዳቭሰን ወደ አንድ ወራሃዊ የመሪዎች ስብሰባ እንዲሄድ ተጠየቀ። በየጊዜው ሙሉ ጨረቃ ስትወጣ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ወንጌላውያንና መሪዎች በአውራጃው ውስጥ በተለያየ ቤተ ክርስቲያናት በየተራ ይሰበሰባሉ። የስብሰባው የመጀመሪያ ክፍል የመንፈሳዊ ሕይወት ኮንፈራንስ በመሆኑ ለአማኞች ሁሉ ክፍት ይሆናል።

አስተናጋጁ ቤተ ክርስቲያን ለእንግዶቹ ምግብ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በሚደርሱበት ጊዜ እግራቸውን ያጥባል። ይህ ለሃይማኖታዊ ቁም ነገር የተለመደ ሳይሆን ሥር የሰደደ ተወዳጅ የወላይታ ባሕል ነው። ተቀባዩ ቤተ ክርስቲያን ለእንግዳዎች መኝታም ያዘጋጃል። ለወንዶች በቤተ ክርስቲያን ወለል ላይ ሣር ተጐዝጕዞ ለሴቶች ደግሞ በየጐረቤቱ ቤቶች መኝታ ይዘጋጅላቸዋል።

«በአበያ ሐይቅ በኩል ባለው ሜዳማ አካባቢ ለሚካሄድ ለአሁኑ ወር ስብሰባ ለመድረስ በበቅሎ አንድ ቀን ተጓዝን» ሲል አስታወሰ ላወሬ ዳቭሰን። «ከትልቁ የመሰብሰቢያ ቤት ቀጥሎ ባለው ትንሽ ቤት ሌሊቱን እንዳሳልፍ ተደረገ። ሰዎች ወደ ስብሰባው መምጣት ጀምረው ሌሊቱን በሙሉ እስኪነጋ ድረስ ይጎርፉ ነበር። ሌሊቱ አልፎ መንጋት ሲጀምር ምንም እንኳን እስከሚቀጥለው ቀን ይፋ ስብሰባ ባይኖርም መዘመር ምስክርነታቸውንና ልምዳቸውን መካፈል ጀመሩ። ለወርሃዊው ስብሰባ የመጡ ሽማግሌዎች በጎጆው ውስጥ ከኔ ጋር ነበሩ። እንጨቶችን በመሬት ተክለው ለመኝታዬ የሚሆን መደብ (አልጋ) ሠርተውልኛል። እነርሱ ደግሞ በመሬት ላይ በተጐዘጐዘ ሣር ላይ ተኝተዋል።

«ጧት በማለዳ ከእኔ ጋር በጎጆው ካደሩ ሰዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ተቀምጠው ሲነጋገሩ የሹክሹክታው ድምፅ ከእንቅልፌ ቀሰቀሰኝ። ዓይኖቼን ከፍቼ ከተመለከትኳቸው በኋላ የሚያደርጉትን ማየት ጥሩ እንደሆነ በማሰብ ያንቀላፋሁ ለማስመሰል እንደገና ዓይኖቼን ጨፈንሁ። በውጭ ሴቶች ቁርስ ነገር ሲያዘጋጁ ይሰማኛል፤ ቁርስ ብዙውን ጊዜ ንፍሮ እና ቡና ነው።

ሽማግሌዎቹ የሚወያዩበትን ጉዳይ ሳዳምጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሆኑ ገባኝ። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት በጋብቻ ሕይወታቸው ችግር ገጠማቸው። ይህንን የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ዓይነት ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ በግልጽ ሊኖርና በሥራ ሊውል እንደሚገባ የታመነ ነበር። ሽማግሌዎቹም የሚወያዩት በዚሁ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ምንና ምን መካተት እንዳለበትና እንዴትስ በሥራ መተርጐም እንዳለበት ነበር።

«የጧት ፀሐይ ጨረር በተከፈተው በር ገብቶ በተቀመጡት ሽማግሌዎች ላይ ይበራ ስለነበረ የጎጆው በር ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚመለከት መሆን አለበት። ሰዎች ሙሉ ልብሳቸውን ገና ሳይለብሱ አንዳንዶቹ ሱሪዎቻቸውን በእጅ እንደያዙ ሌሎችም ቀስ በቀስ እየለበሱ በወለሉ በተጐዘጎዘው ሣር ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከልብ የሚወያዩበት ይህ ጉዳይ ከፍተኛ ቁም ነገርና በሥራ ሲውል ውጤት የሚኖረው ሆኖ ለቤተ ክርስቲያን መማክርት (ኮሚቴ) ሊቀርብ የሚችል ነበር።

«ራሴ ለራሴ ፈገግ አልኩና በአገሬ ይህንን የመሰሉ ስብሰባዎች በክብርና በምቾት እንደሚካሄዱ አሰብኩ። እነዚህ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን በሣር ጉዝጓዝ ላይ ተቀምጠው በልብሶቻቸው ውስጥ ተባይ ይኖር እንደሆን እየፈተሹ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ዲስፕሊን ጉዳይ ሲወያዩ ተመልክቼ በጣም ተደነቅሁ። እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት መንገድ መሥራቱ ለእኔ ፈጽሞ አዲስ ነገር ነበር። እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች መካከል መኖሩ በመንፈስ ቅዱስ የሞላቸውና በእርሱ ምሪት የቤተ ክርስቲያኑን አቋም የሚያዘጋጁ መሪዎች ያደረጋቸው መሆኑ እጅግ አስደነቀኝ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስብሰባ ሲካሄድ ሕንፃ ተስማሚ ጠረጴዛና ወንበር ከፋይሎችና ወረቀቶች ጋር እንዲሁም ደግሞ ስብሰባው የሚመራበት የተወሰነ ሕግና ደንብ ያስፈልጋል ትሉ ይሆናል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ እጅግ በራቀ በተደበቀና በማይታይ ሥፍራ በሙላት ተገኝቶ፥ ሁሉንም አሟልቶና አስተካክሎ የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ አከናውኗ። ወዲያውም የስንዴና በቆሎ ንፍሮ ከቡና ጋር ቀረበ። እኔም በቀኑ የመጀመሪያ ለሆነው ማዕድ ተነስቼ በአልጋዬ ላይ በመቀመጥ ከሰዎቹ ጋር ተቀላቀልኩ።

«ከቁርሱም በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ታጅቤ ስገባ አማኞች የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመስማት ከዳር እስከ ዳር ሞልተውት ነበር። እግዚአብሔር ያሳያቸውና ያመለከታቸው ነገሮች የወኑ መንፈሳዊ ምግብ እንዲሆኑላቸው መመስከርና መንገር ለእኔ ትልቅ ዕድል ነበር። ከዚያም ስብሰባው አልቆ ሕዝቡ እየተደሰተ፥ እየዘመረና እያመሰገነ እያንዳንዱ ወደየአገልግሎቱ ተበታተነ።»

*  *  *

ዋልተር አህማን እርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘበትን ወርሃዊ ስብሰባ በግልጽ ያስታውሳል። የተደረገውም ቅይሻ ካምና ገበቶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። ለስብሰባው ከሚመጡ እንግዶች አብዛኛዎቹ ጨለማው ዓይን እስኪይዝ አልደረሱም ነበር። ማታ በሁለት ሰዓት ገደማ ስብሰባው ተጀምሮ አራት

ዘማሪያን በየተራ ባሕላዊ መዝሙር ካሰሙ በኋላ የሁለት ሰዎች ንግግር ተሰማ። ይህም ካበቃ በኋላ በትናንሽ መሶብ እራት ቀርቦ ሁሉም እንደበላ ጊዜው በግምት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ሆነ። ሚስተር አህማን ደክሞት ስለነበረ ባመጣው ታጣፊ አልጋ ሊተኛ ቢያስብም አሥራ ስምንት ሽማግሌዎች በጎጆው ውስጥ ከርሱ ጋር ነበሩ። ለመተኛት በመዘጋጀት ላይ እንዳለ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ጉዳዮች ላይ ሊወያዩ ያቀዱ በመሆኑ እርሱም በውይይቱ እንዲገኝላቸው የሚፈልጉ መሆኑ በሽማግሌዎች ተገለጸለት። ከእኩለ ሌሊት በኋላ ስብሰባው አበቃ። ብዙዎቹ ከሩቅ ቦታዎች የመጡና የደከማቸው በመሆኑ ሰዓቱ ስድስት ተኩል ከምሽቱ ሲሆን ሁሉም እንቅልፍ ወስዷቸው ያንኰራፉ ነበር። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እርሱንም እንቅልፍ ወሰደው።

ገበቶ ሌሊት በስምንት ከሠላሣ ሰዓት መጥቶ ምግብ እንዲበሉ ቀሰቀሳቸው። በቅርብ ጊዜ ከማታው አገልግሎት ስብሰባ በኋላ የበሉ እንደነበረ አህማን ቢያውቅም አሁን በድጋሚ ሙሉ ማዕድ ምን ጊዜም ከማይቀረው ከወላይታ ቡና ጋር ቀረበ። ቡና የኢትዮጵያ ባሕላዊ መጠጥ ሲሆን ዛፉ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ይበቅላል። የወላይታ ቡና በቅቤና በጨው ተዘጋጅቶ ስለሚቀርብ መልካም ጣዕም አለው። በዘጠኝ ሰዓት ከሰላሣ እንደገና እንቅልፍ የወሰዳቸው ቢሆንም በአሥራ አንድ ከሠላሳ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በተጀመረው የመዝሙር ድምፅ ተቀሰቀሱ። ይህም የፀሎት ጥሪ በመሆኑ ብዙዎች እየሄዱ በፀሎቱ ሲሳተፉ ይሰማል። በጎጆውም ውስጥ ሽማግሌዎች በጌታ ፊት ተንበርክከዋል። ፀሎቱ እንዳበቃ በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ካሉ ትላልቅ ጋኖች ውሃ እየወሰዱ ሁሉም ታጠቡ። ሌላ የፀሎት ስብሰባ ከተካሄደና ሁለት መልዕክቶች ከተከተሉ በኋላ ሁሉም በድጋሚ ተመገቡ።

ሁሉም ወደየቤቱ የሚመለስበት ጊዜ የደረሰ መስሎት አህማን ለጉዞ ለመዘጋጀት ዕቃዎቹን መሰብሰብ ሲጀምር ገና ሥራ ያልጨረሱ እንደሆነ ተነገረው፤ ጥቂቶች በአንድ ላይ ሆነው ለጥያቄዎቻቸውና ችግሮቻቸው መልስና መፍትሔ የሚፈልጉትን ሰዎች ሲጠባበቁ አብዛኛዎቹ ወደቤታቸው ይሄዱ ነበር። እስከ ጧቱ አራት ሰዓት ድረስ ችግሮቹ ተፈትተው ሲያበቁ ቡናና የበቆሎ ቆሎ ቀርቦ ከበሉ በኋላ ወደየቤታቸው መንገድ ጀመሩ። ነገር ግን በአንድ ቤተ ክርስቲያን ምግብ የተዘጋጀላቸው በመሆኑ ለመብላት በዚያ መቆየት ግድ ሆነ። ሚሲዮናውያንና ከሶዶ የመጡ ሽማግሌዎች የሚያልፉት በሠፈራቸው መሆኑን ስለሚያውቁ የቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ለእረፍትና ለምግብ እንዲቆዩ ግድ አሏቸው።

*　　　*　　　*

ሚስተር አህማን ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ አስታውሶ እንዲህ አለ:- «አንድ ቀን እኔና ባለቤቴ ከሶዶ ሰሜን ምሥራቅ አፍሬ ለአንዱ ወርሃዊ ስብሰባ እንሄድ ነበር። በመንገድ የሚመራን ጃልዶ የሚባል የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በመንገዱ ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ የምንቆምበትንና የምንቆይበትን ፕሮግራም አዘጋጅቷል። ከአንድ ሰዓት ተኩል ጉዞ በኋላ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ደረስንና ስኳር ድንችና ቡና ቀርቦልን በላን። ስኳር ድንቹን ለማጣፈጫ ስጐ በሚመስል ሁኔታ የተዘጋጀውን ትኩስ በርበሬ እያጠቀስን

ከበላንና በቆይታው ከተደሰትን በኋላ ጉዞ ለመጀመር እንደገና በኮርቻ ተቀመጥን። ለአንድ ሰዓት ያህል ከተጓዝን በኋላ ለስብሰባው ለመድረስ ከመጓጓታችን የተነሣ ለመቆየት ባንወድም ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ስንደርስ እንድንቆም ተደረገ። ሁሉም ነገር የተዘጋጀና የማያስጠብቅ መሆኑን ካረጋገጡልንና በእምቢታ እነርሱን ማሳዘን ጥሩ እንዳልሆነ ከተገነዘብን በኋላ ከበቅሎቻችን ወርደን ማዕዱን ከእነርሱ ጋር ተመገብን። ከአንድ ሰዓት በፊት በልተን ስለነበረ ከዚሁ ትንሽ እንደበላን ወጥተን ጉዞ ጀመርን።

ሌላ አንድ ሰዓት ከተጓዝን በኋላ «ስብሰባው ከሚካሄድበት ቤተ ክርስቲያን ለመድረስ ምን ያህል ይቀረናል?» በማለት ጃልዶን ጠየቅሁት።

«ከዚህ ብዙ አይርቅም» አለኝ። «ሃያ ደቂቃ ያህል ከተጓዝን በኋላ ይህንን ሽማግሌዎች ሁሉ የሚገኙበትን ስብሰባ በውስጧ ማስተናገድ ከማትችል ከትንሽ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ስንደርስ ቆምን። ጃልዶንም መሰብሰቢያው ቤተ ክርስቲያን ይህ እንደሆነ ጠየቅሁት።

«እርሱም ፈገግ እያለ ‹አይ!› አይደለም፥ የቤተ ክርስቲያኑ ሰዎች እንድንበላ ምግብ አዘጋጅተውልናል› አለ።

«እንደገና መብላት በጣም ስለሚበብዛብኝ ይህ በሕይወቴ ካጋጠሙኝ መጥፎ ጊዜያት አንዱ አድርጌ ቆጠርኩት። ‹አልበላም እንዲያውም ከበቅሎዬ አልወርድም፥ አንተም ሆነ ሌሎች መብላት ከፈለጋችሁ ቶሎ በልታችሁ ውጡ› አልኳቸው።

«‹መብላት አለቦት ጌታዬ! እነርሱ ያዘጋጁት ለእርስዎ ነው› ብሎ ለመነኝ ጃልዶ።

«ሚሲስ አህማን እነርሱን ላለማሳዘን መሄድ አለብን ብትለኝም ‹አልበላም ዛሬ ትምህርት አስተምራቸዋለሁ› አልኩ።

«ይልቅ እነርሱ ትምህርት አስተማሩኝ። ወላይታዎቹ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው እኛን ወደዚያ ማስገባት የሚችሉበትን ዘዴ ይመካከሩ ነበር። ወዲያው ጃልዶ ወጣና ‹ጎዶ (ጌታዬ) ከፈለጉ አይብሉ ነገር ግን መጥተው ስለማዕዱ እግዚአብሔርን ያመስግኑልን› አለ።

«ከዚህ በኋላ ምንም ማድረግ ስለማልችል ገባሁ። ምግብ ያዘጋጀችውን ሴት ለማስደሰት ስል ትንሽ በላሁ።»

*　　　　　*　　　　　*

ወላይታዎች ምግብ በማቅረብ ጥሩ እንግዳ ተቀባዮች ይሁኑ እንጂ ጊዜያቸውን ሁሉ ምግብ በመመገብ የሚያጠፉ አይደሉም። ለሆድ ጉዳይ ለሚሆን ምግብ በተለይ ክርስቲያኖች ብዙ አይጨነቁም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተቀናበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን አስፈላጊነት በመገንዘብ ትምህርት ቤቱ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ከሚሲዮናውያን ጋር ፀሎት ጀመሩ።

የቀድሞ ጣቢያ ለሚሲዮናውያን በተመለሰላቸው ጊዜ በግቢው ውስጥ በኢጣሊያውያን የተገነቡ በርካታ የድንጋይ ቤቶችም ተሰጥተዋቸዋል። እነዚህ ቤቶች የመጽሐፍ ቅዱስና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ ክፍሎች

ለማድረግ የተመኙ ነበሩ። ሆኖም አብዛኞዎቹ አገልጋዮች (መጋቢዎች) የሚመጡት ከሩቅ ገጠር ስለሆነ የመኝታ ቤቶችም በማስፈለጋቸው ሚሲዮናውያን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ከተመካከሩ በኋላ መሪዎቹ ሁሉ ራሳቸው መጥተው ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ቤቱን የሚሠሩ መሆኑን ወሰኑ።

ስምንቱ የቤት ክርስቲያን ወረዳዎች ለቤቱ ሥራ የሚውሉ እንጨቶችን ለማምጣት ገድገዳውን ለማቆምና ለመገንባት እንዲሁም በጭቃ ለመለወፍ ሥራውን ተከፋፍለው ኃላፊነት ተቀበሉ። ሚሲዮናውያኑ ደግሞ ጣሪያውን ቆርቆሮ ለማልበስ ተስማሙ። ቆርቆሮው የተወሰደው በአገልግሎት ላይ ካልዋለው ሌላ የኢጣሊያን ቤት ነበር።

በ1938 ዓ.ም. በመጀመሪያ ሴሚስተር ትምህርት ቤቱ ስድግ አገልጋዮችን ማስተማር እንደሚችል መልዕክት ቢተላለፍም መማር የሚፈልጉት ሰዎች ከሚጠባበቁት የበለጡ በመሆኑ ቁጥሩ እጥፍ ቢሆን የሚወዱ መሆኑን ሽማግሌዎቹ ገለጹ። ይህም በተለይ ለጤናማ አኗኗር የማይመች መሆኑን ሚሲዮናውያኑ አስገንዝበዋል።

በመጨረሻ ሰባ ሁለት ተማሪዎች መምጣት እንደሚችሉ ስምምነት ተደረሰ። ተማሪዎቹ የራሳቸውን ፍራሽ (ሰሌን) እና አልጋ ይዘው የሚመጡ ከመሆናቸው በላይ በየወሩ ሦስት የኢትዮጵያ ብር ይከፍላሉ። ገንዘቡ ለመሠረታዊ የትምህርትና የጥናት መርጃ ዕቃዎች መግዣ ይውላል። በዚህ መሠረት ለያንዳንዱ ተማሪ ወረቀት፥ እርሳስ፥ አንድ ግመናና ለኩራዙ ጋዝ ይሰጠዋል። አስፈላጊዎቹ ነገሮች በመጨመራቸው ትምህርት ቤቱ ለሁለተኛ ሴምስተር ዘጠና ሦስት ለሦስተኛ ደግሞ ከመቶ በላይ ተማሪዎችን ወስዶ ማስተማር ጀመረ።

## ምዕራፍ 17. ሕልምና መጽሐፍ ቅዱስ

እንዲህም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።
የሐዋ. ሥራ 19፡20

«‹እግዚአብሔር ሲናገር› የተባለች ይህች ትንሽ መጽሐፍ በእጃችን ባትኖር ባለፉት ዓመታት ያሳለፍነውን ፈተና ስደትና መከራ መቋቋም በፍጹም ባልቻልንም ነበር። ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር ቃል የተወሰደች ትንሽ ክፍል መሆንዋን ብናውቅም ሌላ ቅዱስ መጽሐፍ ባልነበረን ጊዜ ተቅዕጆ ፍላጐታችንን አሟልተዋል።»

ይህችን የተበጣጠሰች ባለስምንት ገጽ አነስተኛ መጽሐፍ በግርኪና እጅ በአክብሮትና በጥንቃቄ ተይዛ አየኋት። ይህች ጽሑፍ በ1939 ዓ.ም. እንኳን ጠቃሚ መግሪያ ነበረች። ደጋግመው የተጠቀሙባት በመሆኑ ነው የወሩ ገጾቿ ቆሽሸው ጠቁረዋል፥ ጠርዞቻቸው ተቀደዋል፥ ጽሑፎቻቸውም ለማንበብ

ከሚያስቸግር ደረጃ ደርሰዋል። የተገነጠለውን ሽፋን (ልባስ) ለመጠበቅ ሲባል የትንሿ መጽሐፍ አካል በሙሉ ከአሮጌ ኮት ወይም ሱሪ በተወሰደ ቡናማ ጨርቅ ተሰፍቶና ተሸፍኖ ተመለከትኩ። ለብዙዎች የወላይታ ክርስቲያኖች በቋንቋቸው ተተርጉሞ ያላቸው የእግዚአብሔር ቃል፥ እንዲሁም በረሃብና በችግር ጊዜ እግዚአብሔር ደግፎ ያቆያቸው በዚህች የሕይወት እንጀራ ነበር።

እነዚህ ጥቂት ኮፒዎች ለብዙ ጊዜ በአገልግሎት ከመዋላቸው የተነሣ ቢቆሸሹና ቢቀደዱ አያስደንቅም። በእጆቻቸው ያሉ ኮፒዎች እያለቁ አዳዲሶችን ማደልም በመቋረጡ አማኞቹ የየራሳቸውን ኮፒዎች እንደ ሕይወታቸው ሲጠብቋቸው በግል እንዲኖራቸው የፈለጉ ደግሞ በእጅ እየገለበጡ ለራሳቸው ቢይዙም በእጅ መጻፉ በውጭ ከታተመው ጋር ሲወዳደር የበለጠ አድካሚና ውድ ነበር።

ስክሪፕቸር ጊፍት ሚሲዮን በተባለ ድርጅት የታተመችው ይህች ትንሽ መጽሐፍ በኢጣሊያ አስተዳደር በነበረው የመከራ ጊዜ የወላይታ አማኞችን ለመደገፍ እግዚአብሔር የተጠቀመባት መሣሪያ ነበረች። ለመጀመሪያ ጊዜ በቋንቋቸው ከእግዚአብሔር ቃል የተወሰደች በመሆኗ በታላቅ አክብሮት ይመለከቷታል። ይዘቶቿ ማብራሪያ የሌላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሲሆኑ ኮፒዎቿ የተከፋፈሉት ከኢጣሊያ ወረራ በፊት በሚሲዮናውያን ያለክፊያ ነበር።

ዋልተር ኦህማንም የማርቆስ ወንጌልን ወደ ጎፋ ቋንቋ ተርጉሞት ነበር። ጎፍኛ ከዋናው ወላይትኛ በመጠኑ ይለያል። ይሁን እንጂ ሌላ የተሻለና ግልጽ የሆነ ትርጉም ባልነበረበት ሁኔታ የጎፍኛ ማርቆስ ወንጌልም ለአማኞቹ እጅግ ጠቃሚ ነበር። ኮፒዎቹ በጣም የተወሰኑ በመሆኑ በብዙ የጉልበትና የገንዘብ ወጪ በእጅ ይገለበጡ ነበር።

ወላይታን ከመልቀቃችን በፊት ዋልተር ኦህማን የዮሐንስ ወንጌልን በመተርጎም ላይ የነበረ ቢሆንም ለቀን ከመውጣታችን በፊት ለሕትመትና ለእደላ አልበቃም ነበር። ነገር ግን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ገዳማ የሀገሪቱ በሮች እንደገና ስለተከፈቱ ዘጠኝ መቶ ያህል ኮፒዎች ተዘጋጁ። የወላይታ አማኞች ዳቭስንና ቤተሰቡን ለመጎብኘት አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቋንቋቸው ሌላ መጽሐፍ በመተርጎሙ እጅግ በጣም አስደሰታቸው። የዮሐንስ ወንጌል ኮፒዎች በአንድ ሰው ሸክም መጠን ከተከፋፈሉ በኋላ ከሌቦችና ከውሃ ለመከላከል በከብት ቆዳ ተጠቅልለው ወደ ወላይታ ተወሰዱ።

በአማርኛ የተጻፈ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ እጥረት በወላይታ ክርስቲያኖች ዘንድ አልነበረም። አንዳንዶቹ የራሳቸው ኮፒ ነበራቸው። ሆኖም የሚችሉት አማርኛ እና የሚያውቁት የመጽሐፍ ቅዱስ (መንፈሳዊ) ቃላት ውስን በመሆኑ ማንበብና መገንዘብ ያስቸግራቸው ነበር።

ኢትዮጵያ በሯን ለሚሲዮን ሥራ እንደገና እንደከፈተች ወዲያው ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ የሚጻፍና የሚታተም ሥነ ጽሑፍ ሁሉ በአማርኛ እንዲሆን ደንብ ወጣ። የደንቡ ዓላማ አንድ ብሔራዊ ቋንቋን በመጠቀም አገሪቱንና ሕዝቡን አንድ ማድረግ ነበር። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል በቋንቋቸው ማንበብ ለሚፈልጉ አማርኛ ተናጋሪ ላልሆኑ ሕዝቦች እንቅፋት

ሆኖባቸው ነበር። ማለትም የትውልዱ ጎልማሶች የእግዚአብሔርን ቃል አጥርተው በሚችሉት ቋንቋ ተዘጋጅቶ አያገኙትም ማለት ነው። ካለ መንፈሳዊ መጻሕፍት መንፈሳዊነትን ማሳደግ አይቻልም።

ትምህርት የሚሰጠው በአማርኛ ስለሆነ ከአንድ ወይም ሁለት ትውልድ በኋላ ችግሩ ተወግዶ አዲሱ ትውልድ የእግዚአብሔርን ቃል በአማርኛ ማንበብና ማወቅ ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል የሚወደው ያሁኑ ጎልማሳ ትውልድ ይህ ተነፍጎታል።

ሆኖም ይህ እንቅፋት ተስፋ አላስቆረጣቸውም፤ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ለማሰላሰልና እውነትንም ሁሉ ለመቅሰም የተወደደ ስጦታ ነበር። ማንበብ የማይችሉት ሌሎች ሲያነቡ እየሰሙ ያንን በቃል ማጥናት፤ ለሌሎች ማስተላለፍ መታዘዝና በሥራ ማዋል ጀመሩ። እንደ ሌሎችም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የእነዚህንም ፍላጐት ማሟላት የሚችል መሆኑን አረጋገጠ። ቃሉ ባልደረሰበት ቦታ እግዚአብሔር ሊገናኙት ለሚፈልጉ ሁሉ ራሱን በሕልም በራዕይና በመሳሰሉት መንገዶች ይገልጻል።

* * *

ለቀን እንድንወጣ ከመገደዳችን ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ እኔና ዋልተር ኦህማን አማኞችን ለማጥመቅ በወላይታ አውራጃ በምዕራብ በኩል ወደሚገኝ ኮይሻ ወደተባለው አካባቢ ሄድን። ተጠማቂዎቹ የቤተሰብ አባላት ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል ያመጡላቸው በወረዳው የወንጌላዊ ሥራ ጉብኝት ያደረጉ ሚሲዮናውያን ነበሩ። ያመኑት በወር በአንደኛው እሁድ ሃያ ማይሎች ያህል እየተጓዙ ከመንደራቸው ሶዶ ሚሲዮን ጣቢያ ድረስ ይመጡ ነበር።

ከተጠመቁት ውስጥ ሚሴቦ እና ሳካሉ የተባሉ ወንድሞችና ወላጆቻቸው እንዲሁም ደግሞ ዳና ጋዳቦ የተባለ ዝቅተኛ ሹም ይገኙበታል። («ዳና» ማለት ሹም ማለት ነው)።

ሳካሉና አባቱ ኢጣሊያኖች በሚያስተዳድሩበት ጊዜ በባለሥልጣኖች ተወስደው የደረሱበት አልታወቀም። ሚሴቦ በወላይታ ደረጃ እንኳን ሲታሰብ በጣም ድሃ ሲሆን በጣም ቆንጆና በክርስትና ባሕሪዋ ተዋዳጅ ልጅ ነበረችው። አንድ ሃብታም ሰው ሊያገባት ፈልጐ አንድ በሬ በስጦታ ቢሰጠውም ሚሴቦ ግን «አመሰግናለሁ፤ እኔ የምፈልገው ስጦታ ሳይሆን የሚያገባት ሰው እንደኔ እንዲወዳትና እንዲያፈቅራት ነው» ብሎ መለሰ። ልጅቱ በመጨረሻ ስታገባ የፈለገችውና የተሰጣትም ስጦታ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር።

ዳና ጋዳቦ ሀብታም ሹም ቢሆንም ንባብ የመማር ዕድል አላጋጠመውም። መጽሐፍ ቅዱስን ያወቀው የተጠቀሰለትንና የተነበበለትን ቃል በማሰላሰልና በቃል በማጥናት ነበር።

ሚስቱም አማኝና በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላት አዲስ ሕይወት በጐረቤቷ ላሉት ለመናገርና ለመመስከር የምትወድ ሴት ነበረች። በኋንም ሁልጊዜ «የቤት ሥራ ሁሉ እርሻውንም ጭምር ለእኔ ተወውና ወጥተህ ወንጌልን ስበክ፤ እኔ ጠንካራ ስለሆንኩ ልጆቻችን እያገዙኝ ሁሉን እሠራዋለሁ» ትለው ነበር።

ስለዚህ ዳና ጋዳቦ ወንጌላዊ ሆነ። በፀሐይና በዝናብ ተራራዎችን በረሃዎችንና ወንዞችን እያቋረጠ በመቶዎች የሚቆጠሩ ማይሎች ርቀት ተጓዘ። ባሕሪው ልዩ እምነቱ ቀጥተኛ እና ስለጌታ መመስከር የማይሰለቸው ሰው ነበር። የሚሰማውን ሰው ሲያገኝ በቃሉ ካጠናው የእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሰ መስበክ ይጀምራል። ስብከቱንም በመጎል አቋርጦ መዝሙር ወይም አዝማች ይዘምራል። ከሚወዳቸው አዝማቾች አንዱ የሚከተለው ነው። ይህን አዝማች በብዙ ቦታዎች ዘምሯል፥ አስተምሯል።

*መሄድ እንፈልጋለን፥ መሄድ እንፈልጋለን*
*ወደዚያ ሐዘን፥ በሽታና ሞት ወደማይኖርበት አገር*
*መሄድ እንፈልጋለን፥ መሄድ እንፈልጋለን።*

አንድ ቀን ዳና ጋዳቦ ወደ አንድ ሰው ቤት ተጠርቶ ሄደ፥ ሰውየው ባለፈው ሌሊት በነበረው ስብሰባ ዳና ጋዳቦ አዝማች ያስተማረው ሰው ነበር። አሞትም ተኝቶ ስለነበረ «እንድፈወስ ጸልይልኝ» ሲል ጋዳቦን ጠየቀው። ጋዳቦም «ባለፈው ሌሊት ‹መሄድ እንፈልጋለን፥ መሄድ እንፈልጋለን› እያልክ ስትዘምር በእርግጥ መሄድ የምትፈልግ መስሎኝ ነበር፥ አሁን ትንሽ ስትታመም ለመፈወስ እንድትችል እንድጸልይልህ ለምን ትጠራኛለህ?» አለው።

* * *

ግንጃና ወልዴ በጣቢያው የመጀመሪያ ዓመታት በሶዶ ከሚሲዮናውያን ጋር የሠሩ አማኞች ነበሩ። ሁለቱም ክርስቶስን ያመኑት አንድ ላይ ሲሆን ሉዊስና ባለቤቱ ማንበብ ያስተማሯቸውም በአንድ ላይ ነበር። ወልዴ በሚስተር ሉዊስ ወጥ ቤት ይሠራና ምግቡን ያዘጋጅለት ነበር።

ሚሲዮናውያን ከአገር ከወጡ በኋላ ግንጃ ራሱን መመርመር ጀመረና ተረበሸ። የሰማውንና አምናለሁ የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ያለመታዘዝ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ተገነዘበ።

«እኔና አንተ ከነጮች ጋር ሰርተናል፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተናል፥ አምነናል እንላለን . . .። ነገር ግን በርግጥ እናምናለን? በእውነት ንስሐ ገብተናል?» አለ ግንጃ።

በዚህ ጉዳይ በማሰብ ላይ ሳሉ ለመወያየትና ለመጸለይ ሌሊቱን በአንድ ትንሽ ጎጆ ለብቻቸው ሊያሳልፉ ተስማሙ። በዚያም ሌሊት ሁለቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመን ለመታዘዝና ለመከተል ወሰኑ።

ነገር ግን ግንጃ «በጌታ ፊት በምቆምበት ጊዜ ምን መልስ እሰጠዋለሁ» እያለ አሁንም ይጨነቃል። በአንድ ሌሊት በጣም ደክሞት የተኛ ቢሆንም እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም። በፊቱ በጣም ደማቅ መብራት የበራ መሰለው። «ግንጃ መጽሐፍ ቅዱስህን በሸክላ ማሰሮ ውስጥ አስቀምጠህ ተኝተሃል? ቃሌን አታነብም? ለምን በማሰሮው ውስጥ ደበቅከው? ከዚያ አውጥተህ ካላነበብከው አንድ ቀን እፈርድብሃለሁ» የሚል ድምፅ ሰማ።

ግንጃ በፍርሃት ወደ ወልዴ ሄዶ «ጌታን ለማገልገል ወስኛለሁ» አለው። እግዚአብሔር በተመሳሳይ ሁኔታ ለወልዴም ሲናገረው ነበርና ሁለቱም እርሱን

ለማገልገል ራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡ መሆናቸውን ወሰኑ። ከዚያም በሄዱበት ሁሉ መመስከር ጀመሩ። ወልዴ በሚስዮኑ አቅራቢያ ባለው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነ። እርሱ ለብዙ ዓመታት በታማኝነት ካገለገለ በኋላ ሲሞት መጋቢነቱን ግንጃ ተቀበለ።

የእግዚአብሔር ቃል ኃይል በወላይታ ሕዝብ መካከል ሁልጊዜ ጎልቶ ይታያል። ቃሉን የሚያውቁት ጫፍ ጫፉን ቢሆንም በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሁሉ ለመጠቀም ይኸው ትንሽ ዕውቀት በቂ ነበር። ምናልባት የቃሉ ኃይል ከወላይታ አማኞች ከልብ የመነጨና ቅን እምነት ጋር ሲሆን ዓለማውን ለማሳካት በሙላት በሥራ ላይ ውሏል።

## ምዕራፍ 18. ፈውስና ፀሎት

ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም
በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ . . .
የሐዋ. ሥራ 4፡30

«ጌታ ሆይ! ይህን ሰው አድነሃል፥ እርሱም ልጅህ ሆኗል። ማየትና ስላንተ መመስከር እንዲችል ዓይኑን ዳስሰው።»

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ፈተና ገጥሟት ትፀልይ ነበር።

አንዱ አማኝ ለአሥራ ስድስት ዓመታት ዓይኑ ታውሯል። አንድ ጊዜ በጌታ መዳኑን እያሰላሰለ ሳለ እግዚአብሔር ሕይወቱን መለወጥ ሲችል ዓይኑ እንደገና እንዲያይ ማድረግ አይችልም ወይ? ሲል ራሱን ጠየቀ። ስለጉዳዩ ከቤተሰቡ ጋር ከተወያየ በኋላ በአንድ ላይ ወደቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መጥተው ተመካከሩ። ሽማግሌዎቹም ለቤተሰቡ እግዚአብሔር ይህ ጉዳይ ለክብሩና እንደ ፈቃዱ ከሆነ ጸሎታቸውን ሰምቶ የሚፈውሰው እንደሆነ አረጋገጡላቸው።

እግዚአብሔርም የአማኞቹን ፀሎት በመስማት ተዓምር በማድረጉ የሰውየው ዓይኖች ሙሉ በሙሉ ተከፈቱ። አስደናቂ ታሪክ በዚህ ብቻ አላበቃም። በአንድ ጊዜ ዕውር የነበረውና አሁን የተፈወሰው ይህ አማኝ ሰው ራሱ ታሪኩን እንደሚከተለው ይተርክልናል።

«ወራት ካለፉ በኋላ የዳንኩበትንና ዓይኖቼም የተከፈቱበትን አዲስ ኑሮ ለመድኩት። ዛፎችን፥ ላሞችን፥ ሰዎችን ማየት ቻልኩ። እንደቀድሞ ጌታን ማመስገን ሳይሆን በተለያዩ ጉዳዮች ተጠመድኩ። አንድ ቀን በመንገድ ሳልፍ ድሮ ከእኔ ጋር ለሰይጣን መስዋዕት ያቀርቡ የነበሩ ጓደኞቼ በመንገድ ዳር ተቀምጠው አገኘሁዋቸው። እነርሱ በዚያ ቦታ አንድ እንስሳ አርደው ለሰይጣን መስዋዕት ያቀርቡ ነበር። እኔ ከእነርሱ ጋር ባልተባበርም በአጠገባቸው ተቀምጨ መመልከት ጀመርኩ። ስለመስዋዕቱም ከእነርሱ ጋር አወራሁ፥ እኔ ድሮ እንደማደርገው መስዋዕቱን ተሸክመው ሲያደርሱም ተመለከትኳቸው።

«ከነዚያ ሰዎች ጋር ተቀምጬ ሳለሁ ዓይኔ በድንገት ታወረ። በፍጥነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለስኩና የሆነውን ሁሉ ለሽማግሌዎች ከነገርኩዋቸውና ኃጢአቴን ከተናዘዝኩ በኋላ እንደገና እንዲጸልዩልኝ ጠየቅኋቸው። ለሰይጣን መስዋዕት ያቀርቡ ከነበሩ ሰዎች ጋር ተቀምጬ እንደነበር፥ እንዳወራሁና መስዋዕቱን ሲያቀርቡም የተመለከትኩ መሆኔን ተናዝዤ በድንገት ጌታ ዓይኔን እንዳጨለመ ገለጽኩላቸው።

«ሽማግሌዎችንም ‹እባካችሁ ዓይኔ እንደገና እንዲበራና ማየት እንድችል፥ ቤተሰቤን ባላቤቴን ልጆቼንና ቤቴንም ማየት እንድችል እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግልኝና ዓይኔን እንዲያበራልኝ ጸልዩልኝ› ብዬ ለመንኋቸው።

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ጸለየችልኝ። ሽማግሌዎቹ ‹ኃጢአትህን ለጌታ ከተናዘዝክ በኋላ በጸሎቱ እንረዳሃለን› አሉኝ። በተሰበሰቡ ቁጥር ዓይኔ እንዲከፈትና እንደገና ማየት እንድችል ደግመው ደጋግመው ጸለዩልኝ። ለብዙ ወራት ከጸለዩልኝ በኋላ ጌታ ዓይኖቼን አበራ። ነገር ግን የማየት ችሎታዬ እንደበፊቱ በጣም የጠራ አልነበረም። የጸሎቱም መልስ እንደፈተኛው መልስ የፈጠነ አልነበረም። ሆኖም ጌታ ዓይኖቼን እንደገና ስላበራ አመሰግነዋለሁ። እኔ ይህ የሚገባኝ አልነበርኩም ነገር ግን እርሱ ስላደረገው አመሰግነዋለሁ። ወደ ቀድሞ አሮጌ ሕይወት ተመልሼ ከርሱ እንዳልለይና እርሱን እንዳገለግል ጸልዩልኝ።»

* * *

እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ የታልጎሬ ታሪክ ሌላው ምሳሌ ነበር። ስትወለድ ከነበረባት ጉድለት የተነሣ መራመድ አትችልም ነበር። ታልጎሬ ወንጌል ሰምታ ባመነችበት ጊዜ የአሥራ አራት ዓመት ልጅ ነበረች። በተጠመቀችበት ጊዜ ወደ ወንዙ የተወሰደችውና የተመለሰችው በቃሬዛ ተሸክመዋት ነበር።

በዚያን ቀን የታልጎሬ እናት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥታ ለልጅዋ እንዲጸለይላት ሽማግሌዎችን ጠየቀች። እርሷም እግዚአብሔር ለልጅዋ መዳንን እስከሰጠ ድረስ ሸባነቷን ፈውሶ ሊያቆማት የማይችልበት ምክንያት የለም ስትል አሰበች። ማታውኑ ሽማግሌዎች ለታልጎሬ ሊጸልዩ ተሰብስበው መዝሙር እየዘመሩና ከእግዚአብሔር ቃል እያነበቡ ጸለዩላት። በነጋታው ታልጎሬ ተፈውሳ አምስት ወይም ስድስት ማይሎች ያህል ከቤቷ እስከ ቤተ ክርስቲያን በእግሯ መጣች።

ለክርስቲያኖቹ ጸሎት መልስ የሚሆኑ ሌሎች ፈውሶችም ታይተዋል። የሶዶ ሆስፒታል እንደገና ከተከፈተ ከሁለት ዓመት በኋላ ሚሲዮናውያን በወላይታ ውስጥ ከዳር እስከዳር እየተጓዙ የወንጌል ሥራ ይሠሩና ሕዝቡን ለሚያጠቁ ለአንዳንድ በሽታዎች መከላከያ የሚሆን መድኃኒት ያድሉ ነበር።

በአንዱ ወረዳ አንድ እርኩስ መንፈስ ያለበት ሰው ዓይኑን ታሞ ይሰቃይ ስለ ነበረ ወደ ሶዶ ሄዶ መድኃኒት እንዲወስድ ክርስቲያኖቹ ቢነግሩትም ሰውየው አልፈለገም ነበር።

እንዲያውም «አአአይ! እኔ በሰይጣን የተያዝኩና እርሱን የማመልክ ስለሆነ ስለኢየሱስ ወደሚወራበት ቦታ አልሄድም፥ የኢየሱስ ተከታዮችንም መድኃኒት አልጠይቅም» ይል ነበር።

ሆኖም ይህ የሰይጣን አምላኪ ሰው ብዙ ምሽቶችን ያለ እንቅልፍ ካደረና ከሕመሙም የተነሣ ለረዥም ጊዜ ከተሰቃየ በኋላ የክርስቲያኖችን ሃሳብ ስለተቀበለ አንዲት ሚሲዮናዊት ወዳለችበት ወደ አካባቢው ቤተ ክርስቲያን በበቅሎ ተወሰደ።

የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢና ሽማግሌዎች ከዚህ የተነሣ ፈነደቁ። እነርሱ ይህን ሰው ለመርዳት ሁልጊዜ ቢሞክሩም እርሱ ሳይቀበላቸው ቆይቶ ዛሬ ራሱ ፈልጎ መጣ። ለዚህም የመጋቢው ቤት ተዘጋጀ፥ በወለል እርጥብ ሣር ተጎዝጉዞ አዲስ ስሌን ተነጠፈ።

ሚሲዮናዊቷ ስታክመውና የመድኃኒት ጠብታ በዓይኑ ስትጨምር ክርስቲያኖቹ ምርጥ ምግብ አዘጋጁለት። መድኃኒቱ ሕመሙን አስወግዶ ከሥቃዩ ፋታ ስላገኘ ምስጋና አቀረበ። ክርስቲያኖቹም እግዚአብሔር አካላዊና መንፈሳዊ ፈውስ እንዲሰጠው ፀለዩ። ለእርሱም «እኛ ያለን ደስታ ለአንተም እንዲሆን እንፈልጋለን» ብለው ነገሩት።

በዚያን ሌሊት ሰይጣን አምላኪው ሰውዬ ያለሕመም እንቅልፍ ወስዶት አደረ። በነጋታውም እስከ ሳምንቱ መጨረሻ ቆይቶ በቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት እንዲገኝ መጋቢው ጋበዘው። በዚያም ተገኝቶ ብዙ ደስተኛ ሰዎች አንድ ላይ ተሰብስበው መዝሙር ሲዘምሩና ጌታን ሲያመልኩ ባየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ደንዳና ልቡን አራራ። በጉባኤው ፊትም ቆሞ «እኔ ለረዥም ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን ሳልቀበል ቆይቻለሁ፥ አሁን ግን ተቀብዬ ልከተለው እፈልጋለሁ፥ እንደ እናንተ ጌታን እከተላለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር» ሲል ተናገረ።

ሰውየውም ተነስቶ እውነተኛ የጌታ ተከታይ እንደሆነ ለቤተሰቡና ለጐረቤቱ ለመናገር ሄደ። ሚስቱ አማኝ ስለነበረች ስለእርሱም ለብዙ ወራት ስትጸልይ ኖራለች።

ከጥቂት ወራት በኋላ በአንድ እሁድ ሰይጣን «ዛሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለምን ሄድክ?» አለው።

በነጋታውም የሰይጣን ድምፅ እንደገና መጥቶ «ትናንት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለምን ሄድክ? እኔ ዓይንህን ሳሳውር አንተ ወደ ሚሲዮናዊቷ ቤት ሄደህ መድኃኒት ለምን ወሰድክ? ሁለት ልጆችህን በአንድ ቀን የገደልኩት እኔ እንደሆንኩ አታውቅምን? ቤትህ በእሳት ተቃጥሎ እንዲወድም ያደረግሁ እኔ አይደለሁምን? እንዴት ደፈርከኝ? ኃይል እንዳለኝ አታውቅምን? ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ስትሄድ እንድትወድቅና እንድትጎዳ ያደረግሁ እኔ እንደሆንኩ አታውቅምን? የፈለግሁትን ለማድረግ ኃይል እንዳለኝ አታውቅምን?» አለው።

«ከሠራኸው ሥራ ነፃ ለመሆን አሁኑኑ አንድ ነጭ በሬ ለመስዋዕት አቅርብ። ቤተ ክርስቲያን ስለሄድክና ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝ አድርጌ

ተቀብያለሁ ስላልክ ከዚሁ ታጥበህ ለመንፃት አዲስ ደም ያስፈልጋል» ሲል አስጠንቀቀው።

ይህ ከርኩስ መንፈስ የሚመጣው ድምፅ ለብዙ ቀናት እየመጣ ማስፈራራቱን ስለቀጠለ የሰውየው አካል መንምኖ ጉልበቱም ተዳክሞ ለሞት ተቃረበ፥ መንቀሳቀስም አቃተው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ለርሱ መጸለይዋን ቀጠለች፥ ከብዙ ውጊያ በኋላ ሰውየው ድኖ ብርታት አገኘ። ቆሞ ለመሄድ በቻለ ጊዜ ጌታ እንደገና ስለፈወሰውና ስላዳነው ለማመስገን ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣ። የሰይጣንን መንገድ ትቶ ኢየሱስን መከተል መጀመሩን ካሰማው ምስክርነትና ከተደጋገመ የጸሎት ጥያቄ በግልጽ ማወቅ ይቻላል።

«ሰይጣን ይብቃኝ፥ ሰይጣን ይብቃኝ፥ በጌታ አምናለሁ፥ በርሱ እበረታለሁ። ሰይጣን ሊያሰቃየኝ ነውና እባካችሁ ሳታቋርጡ ጸልዩልኝ፥ ካልጸለያችሁልኝ እርሱን መቋቋም አልችልም። ጌታም እንደሚጠብቀኝ አውቃለሁ።»

ክርስቶስን ለመከተል እውነተኛ ውሳኔ ካደረገ በኋላ እንዴት ሊታወክ እንደቻለ ተጠይቆ እንዲህ አለ፥ «ትምባሆ ማጨስ ባቆምም ትምባሆ መትከልና መሸጥ አላቆምኩም። ድሮ ከማደርጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዳንዶቹን አሁንም ማድረግ እችላለሁ፥ ሁሉንም መተው የለብኝም ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ ትምባሆ ሞልቼ ጋያ ካጨስኩ በኋላ በጣም ደስ አለኝ። በዚያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ከቀድሞ ጓደኞቼ ጋር ሆኜ ዋልኩ። ወደኋላ ተመልሼ ድሮ የማደርጋቸውን ነገሮች ሳደርግ መጥፎ መንፈስ መጥቶ ረበሸኝ።

«አጥፍቻለሁና ኃጢአቴን እናዘዛለሁ። የተውኳቸውን ነገሮች እንደገና ሰርቻለሁና ጌታ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ እለምናለሁ። ሌሎችም ብዙ ነገሮች አድርጌአለሁና ለሰይጣን ተሸንፌአለሁ። እርሱ ወደ አሮጌ ሕይወት ሊመልሰኝ እንደሚሞክር አውቃለሁ። ለርሱ ስለተሸነፍኩ ነው የተረበሽኩት።»

ውሳኔው ቁርጠኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በቤቱ ውስጥ ያሉትን የሰይጣን ማምለኪያ መሣሪያዎችን ሁሉ ሲያወድም እንዲረዱትና እንዲመለከቱት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ጠራ። ሆኖም ሽማግሌዎቹ ከመድረሳቸው በፊት ራሱ እነዚህን ዕቃዎች ጋያውንም ጭምር ከቤቱ አውጥቶ እውጭ ሰብስቦ በአንድ ቦታ ቀለላቸው። ወደጓሮ በመሄድ የትንባሆ ተክሎቹን በሙሉ ነቅሎ ካመጣ በኋላ በቁልሉ ጨመረ።

«ከአሁን ጀምሮ ከእነዚህ ነገሮች ጋር ጉዳይ የለኝም» አለ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ሰው እግዚአብሔር በብርታትና በእውነት እንዲጠብቃቸው ሚስቱንና ልጆቹን በየዕለቱ እየሰበሰበ መጸለይ ጀመረ።

* * *

ከ1938 ዓ.ም. ጀምሮ ሚሲስና ሚስተር ናታን በርሎ በሚሠሩበት በሶዶ ሆስፒታል ውስጥም በሕዝብ ዓይን ያልገቡ ጥቃቅን ተዓምራዊ ፈውሶች ሁነዋል። እንደ ሌሎቹ በዚሁ ሆስፒታል ውስጥ የተከሄዱት ...ዎች በአብዛኛው በተለመዱ ...ሰታዎች ላይ ቢሆንም በአንዳንድ የተለዩ

በሽታዎች ላይ የተደረገው ቀዶ ጥገና አስደናቂ ነበር። ማንኛውም የሕክምና ሥራ የሚጀመረው በጸሎት ነበር። እያንዳንዱ ሕክምናና ፈውስም ተዓምራታዊ የጸሎት መልስና የኢየሱስ ፍቅር ታሪክ ሌላው አካልና መግለጫ ነበር።

ወደ ሆስፒታሉ ከሚመጡና ከሚታከሙ በሽተኞች ውስጥ ብዙዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሰሙ በማመን ራሳቸው እንደሚሉት «በሆዳቸው ውስጥ ሰላምን የሚሞላ» አዲስ የሕይወት መንገድ አገኙ። የሚሰብኩላቸው ሚሲዮናውያንና ሠራተኞች ብቻ አልነበሩም። አንድ ቀን ሁለት በሽተኞች ሲነጋገሩ ነርስ ትሰማቸዋለች፡-

«በእኔ አካባቢ ቤተ ክርስቲያንም አማኞችም ስለሌሉ ወንጌል ለመስማት ብዙ ዕድል የለኝም» አለች አንዲት በሽተኛ።

«ለመሄድ የፈለግሽው ገበያ ቢሆን . . .» አለቻት ሌላይቱ። «ሩቅ ነው ብለሽ ትቀሪያለሽ? ቦሎሶ ድረስ ሄደሽ ከገበያ የፈለግሽውን ገዝተሽ መመለስሽን ሩቅ ነው አትይውም። አንድ ሺልንግ ትርፍ ለማግኘት ስትይ እንደገና ቦዲቲ ድረስ ሄደሽ ያንን ትሸጭያለሽ። የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት አንድና ሁለት ሰዓት መሄድን ግን እንደችግር ትቆጥሪዋለሽ። የእግዚአብሔር ቃል ከገበያ ከምታገኚው ነገር አይበልጥም?»

ባርሎና ባለቤቱ ወደ ሶዶ ሆስፒታል መጀመሪያ በመጡ ጊዜ ለወላይታ ወጣቶች የሕክምና ማሠልጠኛ ለማቋቋም የነበራቸው ሕልም የጤና ረዳቶች ማሠልጠኛ ት/ቤት ሲቋቋም እውን ሆነ። የትምህርት ቤቱ ዓላማ ችሎታ ያላቸውን ወንጌላዊ የጤና ባለሙያዎችን ለማፍራት የሦስት ዓመት የቲዎሪና ተግባራዊ ዕውቀት ሥልጠና መስጠት ነበር። ከዘመናዊ ሕክምና ሳይንሳዊ ቴክኒክ በተጨማሪ ግልጽና የመታዘዝ ክርስቲያናዊ ሕይወት አስፈላጊነት ትኩረት ይሰጣል። የተመረቁት የጤና ረዳቶች ከሶዶ አልፈው በመላው ወላይታ እና በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛቶች ተመድበው ሠርተዋል።

## ምዕራፍ 19. ተግባራዊ ቤተ ክርስቲያን

በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል።
2ኛ ቆሮንቶስ 8፡2

ከአራት ሺህ የሚበልጡ ክርስቲያኖች በአቶና ዳገታማ ሜዳ በሣር ላይ ከባሕረዛፍ ቅጠል በተሠራ ዳስ ሥር ተቀምጠው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ስላለባቸው ኃላፊነት እየዘመሩ ያመልኩ ነበር።

የጧቱ ፀሐይ ጨረር ዳሱ በተከደነባቸው ቅጠሎች መካል ሾልኮ በሴቶቹ ራስ ላይ ባለው በባለ ብዙ ቀለም ሻሽ ላይ አርፏል። ሰዎቹ ከመዝሙሩ መሪ አዝማቹን ሲቀበሉ ነጫጭ ጥርሶቻቸው ብልጭ ይሉ ነበር።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ሞት ምንነትና ታላቅነትን የሚገልጹ ፊልሞችና መንፈሳዊ መልዕክቶች የሚተላለፉለትና የሚታዩበት ጊዜ ነበር።

ሁለተኛው ተናጋሪ ተነስቶ መልዕክቱን ሲጀምር ሕዝቡ ፀጥ አለ። ጠቃሚ እውነት ሁሉ እንዳያመልጠው መልዕክቱን ቃል በቃል በጉጉት አዳመጠ። ከወላይታ ውጪ የሚኖሩ ሰባኪዎች መልዕክት እንዲያቀርቡ መጋበዝ በብዙ አይዘወተርም ነበር።

ሰባኪው መልዕክቱን እንዳበቃ ወንጌል ወዳልደረሰባቸው አካባቢዎች ለመስበክና ለማስተማር መሄድ ለሚፈልጉ በጐ ፈቃደኞች ጥሪ ባደረገ ጊዜ ከአንድ መቶ በላይ ሰዎች ተነሱ። እነርሱ ለኢየሱስ ክርስቶስና እርሱን ለማገልገል የወሰኑት በአክብሮትና ፀጥ ባለ መንፈስ ነበር እንጂ በስሜት አልነበረም።

የመጀመሪያ ዓመታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈራንስ የተካሄደው ኅዳር 1941 ዓ.ም. ነበር። ይህንን ካሳሰቡት ምክንያቶች ውስጥ አንዳንዶቹ የአማኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ውስን መሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የጠለቀ እውቀት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቁጥር ማነስ፥ የወላይታ ክርስቲያኖች በአውራጃው ውስጥ በተለያዩና በተራራቁ ቦታዎች የሚኖሩ በመሆኑ፥ ከዚህም የተነሣ ለመደጋገፍና ለአንድነት ሲባል አብሮ መሰባሰብ አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ ነበር።

ሀሳቡ ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጋለ ስሜት ተቀበሉት። ለኮንፈራንሱ ምን ያህል ሰዎች እንደሚመጡና የመጡትም ምን ያህል ቀናት መቆየት እንደሚችሉ የሚያውቅ አልነበረም። አንዳንድ ሽማግሌዎች ምናልባት አንድ ሺህ ያህል ሰዎች ሊመጡ ይችላሉ ብለው ሲያስቡ ሌሎች ደግሞ በግምት ሁለት ሺህ ያህል ይመጣሉ ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር። ታዲያ ይህ ሁሉ ሕዝብ የት ነው መሰብሰብ የሚችለው? በወላይታ ሰዎች አቀማመጥ እንኳን ቢሆን ይህን ያህል ሕዝብ የሚችል አዳራሽ በሚሲዮኑ ግቢ አልነበረም።

ሕዳር የማይዘንብበት ወር በመሆኑ ስብሰባዎቹ ከቤት ውጭ ሊካሄዱ ይችላሉ። በሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ሕንፃዎች መካከል ያለው ሣር የበዛበት ቦታ ሁሉም ማየትና መስማት በሚችሉበት በቁልቁለቱ መጨረሻ ጊዜያዊ መድረክ ከተሠራ ተስማሚ ቦታ መሆኑ ተረጋገጠ።

ከቀትር ፀሐይ መከላከያ እንዲሆን በቋሚ የባሕርዛፍ አጠናዎች ላይ ረብራብ ከታሠረ በኋላ በላዩ ላይ ቅጠሎች ተጨምረው ዳስ ተሠራ።

ለዚህ የመጀመሪያ ኮንፈራንስ አራት ሺህ ተሳታፊዎች በመምጣታቸው ሰው ሁሉ ተደነቀ። ከፊሎቹ ለሁለትና ለሶስት ቀናት ከቆዩ በኋላ ለሌሎች ቦታ ለቀው ወደቤታቸው ሲመለሱ ቤቱን ሲጠብቁ የቆዩት የቤተሰብ አባላት በተራቸው ይመጡና ፕሮግራሙን ይካፈላሉ። የወላይታ ቤት ከውጭ የማይቆለፍ በመሆኑ ቤትና ንብረት ለመጠበቅ እንዲሁም ከብቶችን ለማሰማራትና ለማስገባት ቢያንስ አንድ ሰው በቤት መቅረት ነበረበት። ኮንፈራንሱ ቀናት የሰው ቁጥር ሁለት ሺህ አምስት መቶ ያህል ሆኖ ከቆየ

በእግዚአብሔር ፊት በምትቆምበት ጊዜ
ምን መልስ አለህ?
እርሱ የላካቸውን ካልደገፍክ
ምን መልስ አለህ?
በደልህን ካላረምክ
ምን መልስ አለህ?
መዋሸትን ካላቆምክ
ሐሜትን ካልተውክ
ቁጣህን ካልገታህ
ፈቃዱን ካላደረግህ
ወንጌልን ካልመሰከርክ
ወንጌልን ያልሰሙ በፊቱ በሚቆሙበት ጊዜ
በጨለማ ወዳሉት የሚሄዱትን ካልደገፍክ
ምን መልስ አለህ? . . .

በሜዳው ዝቅተኛ በኩል ካለው የመናገሪያ ሥፍራ ላይ ሆነው ሲመለከቱት በሺህ የሚቆጠሩ የጥቁር ዳማ ፊቶች ይታያሉ። ሁሉም እስከ ትከሻቸው የለበሷቸው ከጥጥ ፈትል የተሠሩና ደማቅ ጥለት ያለባቸው ነጭ ጋቢዎች ልዩ ድምቀት ሰጥተዋቸዋል።

ሕዝቡ ሲዘምር ሽማግሌዎቹ ተጠጋግቶ ያለመስመር በተቀመጠው ሕዝብ መካከል እየተዘዋወሩ ከአንዱ ወደ አንዱ ቦታ በሰው ላይ እየዘለሉ በማለፍ ስጦታ ይሰበስቡ ነበር። እያንዳንዱ ሰው እጁን እየዘረጋ በሽማግሌዎች እጅና በያዟቸው ባርኔጣዎች ልዩ ልዩ ሳንቲሞችን፥ የምርት ውጤቶችን፥ ኮቶችን፥ ሸማዎችን፥ ሹራቦችን፥ ጫማዎችን . . . ወዘተ ይጥል ነበር። በዚህና በዚያ ሰው እየቆመ ልብሱን አውልቆ ለእግዚአብሔር ስጦታ ይሰጥ ነበር።

መዝሙሩ ሲያበቃ ሽማግሌዎች የሰበሰቡትን የስጦታ ገንዘብና ዕቃዎችን በሕዝብ ፊት በመነጋገሪያው መድረክ ላይ ዘረገፏቸው። ገንዘቡ ከአገልግሎቱ በኋላ የሚቆጠር ሲሆን ሌሎች ዕቃዎች ደግሞ በገበያ ተሸጠው ሂሳቡ ከተሰበሰበው ገንዘብ ጋር ይደመራል።

ይህ እንግዲህ በዓመቱ ከፍተኛ በሆነው በወላይታ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ ኮንፈራንስ ላይ ነው። በዚሁ የአንድ ሳምንት ኮንፈረንስ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከሥራው ተለይቶ ቢያንስ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን እንኳን ቢሆን ይካፈላል። ኮንፈራሱ ገና ፀሐይ ሳትወጣ በተደረገው የአንድ ሰዓት ፀሎት ተጀመረ። ይህ ስብሰባ በሦስት ሰዓት ቀጥሎ ምፅዋት ከተሰበሰበ በኋላ ሁለተኛ ሰው ሰበከ። ከዚያም ምሳ ተበልቶ ይህንኑ የመሰለ ፕሮግራም ተካሄደ። በማታ የሚኖረው ደግሞ በተለይ ክርስቲያን ላልሆኑት የጌታ

በኋላ በመዝጊያው ቀን ስድስት ሺህ ደረሰ። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ምግብ ይዞ ይመጣ ነበር።

በኮንፈራንሱ ዋናው ተናጋሪ ሚስተር ፕላይፌር (የኤስ.አይ.ኤም. ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር) ነበር። እርሱ ከአምስት ዓመት በፊት ወላይታን ከጎበኘ በኋላ በድጋሚ መጥቶ ነበር በዚህ ኮንፈራንስ የተገኘው። ሚስተር ፕላይፌር በወላይታና በጉረቤት ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወንጌልን የማሰማት አስፈላጊነትን በማስገንዘብ ከፍተኛ ሚስዮናዊ ጥያቄ አቅርቦ አርባ ወጣቶች ፈቃደኝነታቸውን በመግለጽ መልስ ሰጡ። በዚያ ዓመት ወዲያው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ተመደቡ።

በተከታዩ ዓመት ማለትም በ1942 ዓ.ም. እነዚሁ አርባ ወጣቶች ቤታቸውን ትተው በመውጣት ለወንጌል ስብከት ሊሄዱ በተዘጋጁ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ በዓመታዊው ኮንፈራንስ ለተገኙ ክርስቲያኖች ቀረበ። በኮንፈረንሱ መጨረሻ ላይ ከስጦታ የተገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ሦስት መቶ ስድሣ ስምንት ብር መሆኑ ታወቀ። ይህም ከአጠቃላይ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ገንዘብ ሲሰበሰብ የመጀመሪያ ነበር።

«እኛም በመስጠት እንደነሙች ሆነናል» ይሉ ነበር ክርስቲያኖች በ1943 ዓ.ም. ዓመታዊ ኮንፈረንስ የተሰበሰበው ስጦታ አንድ ሺህ ስምንት መቶ መድረሱን ተመልክተው። አብዛኛዎቹ ገቢያቸው በሳንቲሞች የሚቆጠር ነበር። ክርስቲያኖቹ በመስጠት ብቻ ሳይሆን በእምነትም አድገዋል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ላልሰሙት የወላይታና ሌሎች ሕዝቦች ያለባቸውን ኃላፊነት በመገንዘብ በቤተ ክርስቲያኑ ከሚሰበሰበው ምፅዋት ግማሹን ለወንጌላውያን ድጋፍ እንደሚያውሉት ቃል ገቡ።

ወላይታዎች ድሃ ቢሆኑም ሁልጊዜ ስጦታዎቻቸውን በማሳደግ ይደሰቱ ነበር። በክርስቶስ የነበራቸው ደስታና ፍቅር ስላደገ ካላቸው አካፍለው ለሌሎች ሲሉ የመለገስ ፍላጐትም አደገ። በእጃቸው ገንዘብ ወይም ደግሞ የሚጨበጥ ንብረት አልነበራቸውም። በሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈራንስ ጥቂት ክርስቲያኖች በስብሰባው መኻል ቆመው በመጪው ዓመት የተወሰነ ገንዘብ ለጌታ እንደሚሰጡ ቃል ገቡ። የገቡትንም ቃል ለመጠበቅ እንዲችሉ ጌታ በቂ ገንዘብ እንደሚሰጣቸው ያምኑ ነበር።

ወዲያው በጥቂቶች የተጀመረው የስጦታ ቃል ኪዳን በሌሎች መካከልም ተቀጣጠለ። ክርስቲያኖች እየተነሱ የየራሳቸውን ስጦታ በእምነት እየገለጹ ቃል ገቡ። በግ፥ አህያ፥ ፈረስ፥ ቡሉኮ (ሸማ)፥ አሥር ብር፥ አሥር የቡና ዛፎች ምርት ወዘተ። ቃል ኪዳኖቹ በቀላሉ የተደረጉ አልነበረም። በሰጪውና በጌታ መካከል ግዴታውን በመገንዘብ የተደረጉ ልባዊ ስጦታ እንጂ። ሰጪዎቹም ለኢየሱስ ክርስቶስ ካላቸው ፍቅር የተነሣ ይህን ያህል ለመስጠት በመቻላቸው (ጌታ ስለሚያስችላቸው) ደስ ብሏቸው ነበር። በጠቅላላው በዕለቱ የተሰበሰበውና ቃል የተገባው ስጦታ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ብር ነበር።

በሚቀጥለው ዓመት ቃላቸውን ጠብቀው መክፈል ይችሉ ዘንድ ጠንክረው መሥራት ጀመሩ። ክፍያውን በየጊዜው በማድረግ ሙሉ በሙሉ አጠናቀቁ። በተከታዩ ኮንፈራንስ መዝገቡ ሲመረመር ቃል የተገባለት ሁሉ አንዲት ሳንቲም ሳትቀር መከፈሉ ተረጋገጠ።

ከዚያን ዓመት ጀምሮ በእንደዚህ ዓይነት ለጌታ ሥራ መስጠት እያደገ መጥቷል። ወላይታዎች ከዓለም ደሃ ሕዝቦች ጋር የሚቆጠሩ ሆነው ሳሉ ለወንጌል ሥራ የሚሰጡትን ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲያሳድጉ ስናይ እንግዳ ነገር መስሎ ሊታየን ይችላል። የወላይታ ኑሮ እንደ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ከእጅ ወደ አፍ ሆኖ ለኑሮ መሠረታዊ በሆኑ አካላዊ ፍላጐት ላይ ያተኮረ ነው። ከበለጸጉት ሀገሮች ሕዝቦች ጋር ሲወዳደር በወላይታ ሀብታም የተባለ ሰው እንኳን ምንም የሌለው ተብሎ ሊቆጠር ይችላል። ወላይታዎቹ በሕይወታቸው ይደሰታሉ። ይህ ማለት ሕይወታቸው ምቹና የጥጋብ ሕይወት ነው ማለት አይደለም። ክርስቲያን ከሆኑ በኋላም የኑሮአቸው ደረጃ አደገ ማለት አይቻልም። ክርስቲያኖች በእምነት ቃል የገቡበትን ስጦታ እንኳን ለመክፈል ቀላል ሆኖ ባያገኙትም ክፍያውን ያልፈጸሙበት ወይም ጨርሶ ያልከፈሉበት ጊዜ የለም። አንዳንድ ጊዜ ከፋዩ በሙሉም ሆነ በከፊል ቃል የገባውን ሳይከፍል ቢሞት ቀሪው የትዳር ጓደኛ (ባል ወይም ሚስት) እንደራሱ ግዴታ በመቁጠር ከፍሎ ያጠናቅቃል። ይህ ሲሆን ክፍያው ብዙውን ጊዜ ከዓመት በላይ ጊዜ ይወስዳል።

አንድ ቀን አንድ ሰውዬ መቆም እስኪሳነው ድረስ ደክሞት ሶዶ ከሚሲዮኑ መጽሐፍ መሸጫ ቤት መጣ፣ ሰልማ በርግስተን ባቀረበችለት ወንበር ላይ እንዳረፈ ደጋግሞ «ጌታ ሆይ እዚህ ስላደረስከኝ አመሰግንሃለሁ» ካለ በኋላ ታሪኩን መናገር ጀመረ።

ድሃ በመሆኑ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሚስቱንና ቤተሰቡን በመተው ወደ ዶርዜ ሀገር ሄደ። በዚያ ሸማኔ ሆኖ ለራሱና ለባለቤቱ ልብስ አዘጋጀ። በእምነቱ ለወንጌል ሥራ ሊሰጥ ቃል የገባበትንም ለመክፈል የሚበቃ ገንዘብ አገኘ።

ወዲያው ከኮቱ ኪስ ከረጢት አውጥቶ በውስጡ ያለውን ገንዘብ በሚሲስ በርግስተን እጅ ዘረገፈ። ሚሲስ በርግስተንም መዝገቡን ስትመለከተው ሰውየው ቃል የገባው የዛሬ አምስት ዓመት መሆኑን ካየች በኋላ ለመክፈሉ መዝግባ ገንዘቡን አስቀመጠችው። ሰውየውም በረዥሙ ከተነፈሰ በኋላ «አሁን ቀለለኝ በረታሁም። ቃል የገባሁትን እስከምከፈል ጌታ እንዲያኖረኝ (በሞት እንዳይጠራኝ) ለብዙ ወራት ስጸልይ ቆይቻለሁ» ሲል ተናገረ።

በአሁኑ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈረንስ ላይ የስጦታ ቃል መቀበልና መመዝገብ በተሻለና በተቀነባበረ መንገድ ይሠራል። ለስጦታ ቃል መግባት የሚፈልጉ ሰዎች በጧትና ከሰዓት በኋላ ፕሮግራም መጨረሻ ቆመው ለሚጠባበቁ ሽማግሌዎች ወይም አስተማሪዎች ቀርበው ዝርዝር መረጃ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ሰው ለስጦታው ቃል መግባት በፈቃደኝነት ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር የሚደረግ መሆኑን የሚያውቅ ቢሆንም ትክክለኛ ለመሆን ሲባል የሰጪው ስም ወረዳና የሚሰጠው ስጦታ ዓይነት ይመዘገባል። በወላይታ የባንክ አገልግሎት ተቋም ስላልነበረ መዝገቦቹና ገንዘቡ በሚሲዮናውያን ይጠበቅ ነበር።

ለመስጠት ያለው አጋጣሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈረንስ ምፅዋትና ስጦታ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ሁልጊዜ እሁድ ከአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ምፅዋትና አሥራት ይሰበሰባል። ከዚህም በሁለተኛው ዓመታዊ ኮንፈራንስ

በተገባው ቃል መሠረት ግማሽ ለቤተ ክርስቲያኑ ሲውል ሌላው ግማሽ ደግሞ ለሚሲዮንና ወንጌል ሥራ ድጋፍ ይውላል። ይህ ለወንጌል ሥራ የተመደበው ገንዘብ ወደ አውራጃው የሽማግሌዎች ስብሰባ ይቀርብና በጋራ ግምጃ ቤት (ገንዘብ ቤት) ይቀመጣል።

ዘወትር ሐሙስ ጧት በነበረው የፀሎት ፕሮግራም ለችግረኞች መርጃ የሚውል ምፅዋት ይሰበሰባል። በወር አንድ እሁድ ማለት በቁርባን ቀን የሚሰበሰበው ምፅዋት እህል፥ ድንች፥ ቅቤ፥ ልብስም ጨምር ለመጋቢው ይሰጣል።

ሴቶችም የራሳቸው የሆነ ብዙ ባይኖራቸውም መጽሐፍ ቅዱስ ለመማር በሚሰበሰቡበት ጊዜ ምፅዋት ይጥላሉ።

አንድ ጊዜ ሳምንታዊ የሴቶች ስብሰባ ተፈጽሞ ሁሉም ወደየቤታቸው ጉዞ ሲጀምሩ ሳልማ በርግስተንም ወደ ቤትዋ መንገድ እንደጀመረች አንዲት አሮጊት ፈጥና ወደ እርስዋ ስትሮጥ ተመለከተች። ዳገቱን ጨርሳ ወደ እርስዋ ስትደርስ አሮጊቷ ላብ በላብ ከመሆኗም በላይ በመጨረሻም እያቃተተች «ጌታ ሆይ ተመስገን፥ በጊዜ እዚህ ድረስ ስላደረስከኝ አመሰግናለሁ» አለች።

«በጊዜ እንዳልደረሰች ስለማውቅ አባባሏ ግራ ቢገባኝም ሳቅ አልኩና ‹ደጋግመሽ እግዚአብሔር እዚህ በጊዜ ስላደረሽ የምታመሰግኚበትን ምክንያት ልትነግሪኝ ትችያለሽ?› አልኳት» አለች ሰልማ በርግስተን ያለፈውን አስታውሳ።

«እንደገናም ‹ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ› ካለች በኋላ መቀነቷን መፍታት ጀመረች። ‹ሳምንቱን ሙሉ በዚሁ በሴቶች ስብሰባ ነበር የቆየሁት። ከእግዚአብሔር ቃል ባነበብሽልንና እግዚአብሔርም ለእኛ ያደረገውን ሁሉ እንድናውቅ በረዳሽን መሠረት ለእርሱ የምሰጠው ነገር እንዲኖረኝ ፈለግሁ። ሌሎች ሴቶች የየራሳቸውን ስጦታ ሲሰጡ እኔ ግን የምሰጠው አልነበረኝም።

«‹ያሉኝን ጥቂት ሳንቲሞች ወስጄ ከገበያ ጥጥ ገዛሁ። ቀን ቀን ይህን የሴቶች ስብሰባ እየተካፈልኩ ማታ ማታ እያመሸሁ ስፈትል ከቆየሁ በኋላ ባለፈው ሌሊት ጨረስኩ።

«‹ዛሬ ማለዳ ፀሐይ ከመውጣቱ በፊት ከመኝታዬ ተነስቼ ወደ ገበያ ሄድኩ።›

«እስከ ገበያው አምስት ሰዓት የእግር ጉዞ ይፈጃል። በዚያ ፈትሏን ሸጣ ‹ጌታ ሆይ በጊዜ ደርሼ ስጦታዬን እንዳደርስ እርዳኝ እያለች ተመልሳ ወደ ሰዶ ጉዞ ጀመረች።

«‹ተመልከቺ› አለችን ‹እግዚአብሔር ይህንን ገንዘብ እንድሰጠው ነግሮኝ ቶሎ እንድደርስ ረዳኝ።›

«እጇንም ዘርግታ ሃያ ሣንቲም በእጄ አስቀመጠችው።»

# ክፍል ሰባት፡- ቋሚ ብርሃናት

## ምዕራፍ 20. ናና

እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፥ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተውም ነበር።

የሐዋ.ሥራ 5፡41-42

«እሽ፥ ትፈልገዋለህ?» ሲል ሽማግሌው ሚሲዮናዊውን ጠየቀ። ወደ ናናም ዞሮ «እስቲ ውጪ ቆይ፥ ስንፈልግህ እንጠራሃለን» አለው።

ረዥምና ቀጭን ለግላጋ ወጣት ክፍሉን ለቆ ከወጣ በኋላ «እንቅልፋም ይመስላል፥ ሲሠራ ፍጥነትና ቅልጥፍና ይኖረው እንደሆን አላውቅም» አለ ሚሲዮናዊው።

«እንቅልፋም ነው ብለህ አትጨነቅ። ዛሬ ከመንደሩ ተነስቶ በእግሩ ስለመጣና ፀሐይ ስለአደከመው ነውና ሲቆይ ይሻለዋል። ቅሬታህ ይኸው ብቻ ከሆነ ግድ የለህም ሞክረው» አለው ሽማግሌው እየሳቀ። ከዚያም ተስማምተው ናና በሚሲዮናዊው ቤት እንዲሠራ ተቀጠረ።

ናና ከተጠበቀው የበለጠ ሥራ ሠራ። ማንበብ የሚችል መሆኑንም ሲያውቁ ሚሲዮናውያን ደስ አላቸው። ታሪኩን ሳይነግራቸው ብዙ ወራት ከሠራ በኋላ አንድ ቀን ማታ ጠየቁትና ይነግራቸው ጀመር። ልጅ በነበረበት ጊዜ ጌታን ሊያውቅ የቻለው በአካባቢው በነበሩ ክርስቲያኖች በተለይም ወደ ሚሲዮናዊው እንዲሠራ ባመጣው ሽማግሌ ምስክርነት ነበር።

ናና እንዳለው ከሆነ እርሱ በእግዚአብሔር ሲያምን ታላቅ ወንድሙም አመነ፥ ነገር ግን በእምነቱ ጠንካራ አልነበረም። የሽማግሌው ሕይወት ግን ጠንካራ፥ እውነተኛና ደስተኛ መሆኑን ናና አይቶ እንደ እርሱ ጌታን ለመከተል ፈለገ። በቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱ አገልግሎቶችንና ስብሰባዎችን በተለይም የሐሙስ ማለዳውን የፀሎት ፕሮግራም በታማኝነት ተከታተለ። ናና ቤተ ክርስቲያን ለመድረስ የሚጓዝበት ሞንገድ ረዥም ከመሆኑም በላይ ቤተሰቦቹ መሄዱን ስላልወደዱ ለማስቀረት ያላደረጉት ነገር አልነበረም። ሁልጊዜ ሐሙስ ጧት ከመኝታው ሲነሣ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄድ ልብሶቹን ይደብቁበታል።

አንድ ቀን ልብሶቹን መደበቅ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን በሚሄድባቸው ሐሙስና እሁድ ዕለታት ምግብ የማይሰጠው መሆኑን እናቱ ብትነግረውም ናናን ልታስተወው አልቻለችም። ይህ በጣም ከባድ ወይም ትልቅ ቅጣት

አይደለምና እችለዋለሁ። የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ስል አንድ ቀን ያለምግብ መዋል በጣም አይከብደኝም ብሎ አሰበ። ግን የልብሱን ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለበት ሊያውቅ ባለመቻሉ በቤተ ክርስቲያን ለነበሩ አንዳንድ ሰዎች ሲነግራቸው ሌላ ተደራቢ ልብስ ሰጡት። በየጊዜው ከቤተ ክርስቲያን ሲመለስ አውልቆ እስከሚቀጥለው አገልግሎት ቀን ድረስ በጎረቤት ሰው ቤት ያስቀምጥ ነበር።

በሌሎች ቀናት በቤት ውስጥ ሆኖ ምግብ ሲቀርብለት ከመመገቡ በፊት ጌታ እንዲባርክለት ለመጠየቅና ለማመስገንም ሲፈልግ አይፈቀድለትም። ወላጆቹም «እኛ አንተ የምታምነውን ስለማናምን በቤታችንና በምግብ ሰዓታችን መጸለይ አትችልም» ይሉት ነበር።

ናና ግን ለራሱ ሲናገር እንዲህ አለ፥ «እግዚአብሔር የምበላውን ምግብ የሰጠኝ ሆኖ ሳለ ሳላመሰግነው እንዴት እበላለሁ?» በመጨረሻም ምግብ ሲቀርብ ከመብላቱ በፊት ቁርጭምጭምቱን እያከከ ዓይኑን ጨፍኖ ስለምግቡ ጌታን ሊያመሰግን ስለወሰነ ቁርጭምጭምቱን አሞት ይሆናል እያለች እናቱ ዝም ትለው ነበር።

ናና የፀሎት ጊዜ እንዲኖረው ሲፈልግ ወደ ቦቆሎው ተክሎች ውስጥ ይሄድና በጉልበቱ ተንበርክኮ ከጌታው ጋር አስደናቂ ጊዜ አሳልፎ ይመለሳል።

የናና አባትና እናት ልጃቸው ነጮች ባመጡት አዲስ እምነት ማመኑን እንዲተው ለማድረግ የሚችሉበት ዘዴ ግራ ገብቷቸዋል። ምናልባት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚገናኝበት መንገድ ቢዘጋ ይመለስ ይሆናል ብለው አሰቡ። ወደ ኢጣሊያኖች መጥተው ናናን ወደ ቆላው ጥጥ እርሻ እንዲወስዱትና እንዲያሠሩት ጠየቋቸው። «በዚያ አስቀምጣችሁ ወደዚህ እንዳይመጣ እየጠበቃችሁ እንደፈለጋችሁ አድርጉት። ሥራ ስጡት፥ በኃይል እንዲሠራም አድርጉት» አሏቸው። ኢጣሊያኖችም ለጥጥ እርሻዎቻቸው ጤናማ ወጣት ሠራተኞችን ይፈልጉ ስለነበር ደስ እያላቸው ናናን ወሰዱት።

ናና ቀደም ብለው በጥጥ እርሻው የነበሩ ሰዎች ስለደረሰባቸው ችግሮች ብዙ ታሪክ ያውቅ ነበር። ስለሆነም የሚጠብቀውን በመፍራት ጌታ ጤናማ አካሉን እንዲጠብቅለት ለመነ። ላልተወሰነ ጊዜ ከጌታ ጋር ባለው ሕብረት መቀጠል የሚችል መሆኑ ቢታየውም ከታመመ ግን ምን እንደሚደርስበት ለማወቅ ይቸገራል። በቆላው ወባ በብዛት ስላለ የሚይዘውም ከውሃ መሆኑን ስለሚያውቅ ውሃ እንዳይጠማና እንዳይጠማውም እግዚአብሔርን ይለምን ነበር።

«ትሰሙኛላችሁ! በዚያ በቆላ አንድ ቀን እንኳን አልተጠማሁም። በጌታም በጣም ደስ ይለኝ ነበር። በመጨረሻም አንድ ቀን አጋጣሚ አገኘሁና ጠፍቼ ወጣሁ» አለ።

ወላጆቹ እርሱን በማየት ብዙ ባይደሰቱም ናና ወደ ቤቱ በመድረሱ በጣም ተደሰቱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ከአማኝ ወንድሞቹ ጋር እንደገና በመገናኘቱ ደስ አለው።

በዚያ ሰሞን እናቱ ታመመች። ናና እቤት ሆኖ ሲያስታምማትና ሲረዳት ቢቆይም በአንድ ረቡዕ ማታ እናቱ አረፈች። በነጋታው ሐሙስ ጧት ከሚኖረው የፀሎት ፕሮግራም መቅረት ስላልፈለገ ገና ሳይነጋ ከቤት ወጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ።

ከስብሰባው በኋላ አማኞቹ ወደ ለቅሶ ቤቱ በመሄድ ናናን እንዲያጽናኑ ማሳሰቢያ ተሰጠ። እዚያ ሲደርሱም ከሰዓት በኋላ ለሚኖረው ቀብር ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር። ናና በቤተሰቡ መካከል ሆኖ በእናቱ ሞት በጣም ያዘነ ቢሆንም እንደሌሎች የቤተሰቡ አባላት አላለቀሰም፣ ደረቱን አልደለቀም፣ ፊቱን አልቧጨረም። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ የአካባቢ ሽማግሌዎች ተበሳጭተው አስፈራሩት፣ እነርሱ ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ወጉንና ሥርዓቱን ተከትሎ በለቅሶው ካልተሳተፈ አስፈሪ አደጋ እንደሚደርስበት አስጠነቀቁት።

ናናም «እናንተ የምታደርጉትን በማድረግ ጌታዬን አላዋርድም። ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኜ ነው። እርሱ ደስታን ስለሰጠኝ ይህን በመሰለው የሐዘን ጊዜ እንኳን ደስተኛ ነኝ» ሲል መለሰላቸው።

እንደገና ቢያስጠነቅቁም ናናን ሊያስለቅሱ አልቻሉም። ስለዚህም ይዘው እጆቹን ከሌላው ሰውነት ጋር በገመድ ካሰሩ በኋላ ጎትተው በመውሰድ በዛፍ ላይ ሰቀሉት።

በመጀመሪያ ስቅላቱን መቋቋም አልከበደውም።

ጌታዬን ከማሳፈር ይህንን መቀበል ይሻለኛል ብሎ አሰበ። ለብዙ ሰዓታትም እንደተሰቀለ አቆዩት።

ናና ስለዚያ ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር። «በዚያን ጊዜ ሰውነቴ በጣም የከበደ ይመስለኝ ነበር። ገመዱም ሰውነቴ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ይቆራርጠኝ ነበር። በጣም የጎዳኝ ይሁን እንጂ እኔ አልተሰማኝም። ተሰቅዬ ሳለሁም ከጌታ ጋር እንዳልነጋገር የሚከለክለኝ ነገር እንደሌለ አወቅሁ። ጌታም አነጋግሮኝ ደስታንና ስቃዩን የምቋቋምበት ጥንካሬ ሰጠኝ። በዚያ መከራ ምክንያት ያጣሁት አንዳች ነገር አልነበረም።»

የማታው ሰዓት ሲደርስ አባቱ «ልጄ እኔን ትቶ ሌላ እምነት ለመከተል ከቆረጠ ከዚህ በላይ መቀጣት አያስፈልገውም። ከዚህ በኋላ እሽ ብሎ አይተውም። ሄዶ ላሞችን ይጠብቅ፣ ሲመሽም ወደ ቤት ይመልስ።» በቤት ለቅሶ (ሐዘን) እያለ ወደ ላሞች መላክ ለቤተሰቡ አባል እንደውርደት ይቆጠር ነበር።

«ላሞችን ለመጠበቅ ስላክ ደስ ብሎኝ ነበር። በዚያም ከኢየሱስ ጋር መነጋገር ለዘመዶቼ እንድናገርና እኔንም ለራሱ እንዲያበረታኝ ጠየቅኩት» አለ ናና።

ከዚያ በኋላ ለብዙ ዓመታት ናና በቤት ከአባቱ ጋር ኖረ። አሁን ግን ለምግብና ለልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ማግኘት ለሚያስችል ሥራ ወደ ሚሲዮኑ መጣ።

በሚሲዮናዊው ቤት ብዙ ሳይቆይ አንድ ቀን «ጌታ ወንጌልን ለሚያስፈልጋቸው ሄጄ እንድናገር ሊልከኝ ስለሆነ በዚህ ሥራ ብዙ ጊዜ የምቆይ አይመስለኝም» አለ።

«በእርግጥ ጌታ የጠራህ ከሆነ እዚህ መቆየት የለብህምና መሄድ አለብህ» ብሎ ሚሲዮናዊው አበረታታው። ናናም ከሁለት ሳምንታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለወንጌል ሥራ የሚሄድ መሆኑን ወሰነ።

ሁለት ሳምንት ሊሞላ ጥቂት ሲቀረው ናና «አሁን ወዲያው ልሄድ የምችል አይመስለኝም ተጨማሪ ሱሪና ሌሎች ልብሶች ያስፈልጉኛል። ይህን አንድ ሙሉ ልብስ ብቻ ይዤ መሄድ አልችልምና ትንሽ ቆይቼ ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘት ያለብኝ ይመስለኛል» ሲል ሚሲዮናዊውን አማከረ።

ሚሲዮናዊውም «ጌታ የጠራህ ከሆነ ተጨማሪ ልብሶችን በመፈለግ እዚህ የምትቆይበት ምክንያት የለም። ጌታ ራሱ የሚያስፈልግህን ልብስ ያሟላል» ብሎ ካስጠነቀቀው በኋላ ናና ብርታት አግኝቶ ወንጌልን ለመስበክ ሄደ።

ከቤቱ ትንሽ ራቅ ብሎ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረ ይሁን እንጂ መጋቢ አልነበረውም። ለዚህ ጥቂት አማኞች ለነበሩበት ቤተ ክርስቲያን ናና መጋቢ ሆኖ እሁድ እና ሐሙስ ይሰብክ ነበር። በሳምንቱ ቀናትም ጧት ጧት ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ተማሪዎችን ያስተምራል። ተማሪዎቹ አዲስ አማኞችና ማንበብና መጻፍም የማይችሉ በመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ አዲስ ኪዳን አልነበራቸው። ናና የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰብክላቸውና ራሳቸውም እንዲያነቡት ሊያስተምራቸው ሙሉ ሸክም ተሰማው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የወንጌል ጠላቶች ቤተ ክርስቲያኑን አቃጠሉ። ናና እና ሌሎች ሽማግሌዎች «በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ አናቆምም። ምናልባት ጌታ ከበፊቱ ይበልጥ የሰፋ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖረን ፈልጐ ይሆናል» በማለት ሰዎችን አስተባብረው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መገንባት ጀመሩ። ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይመጣ ስለ ነበረ ብዙዎች ዳኑ። ጌታም ቃሉን ባረከ። አነስተኛ የነበሩ አማኞችም ቁጥራቸው በየሳምንቱ ያድግ ነበር።

ናና በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በአንድ እሁድ ጧት በጉባኤው መካከል ተነስቶ «ዛሬ ጧት ስንት መጽሐፍ ቅዱስና አዲስ ኪዳን ይዛችኋል?» ሲል ጠየቀ። «አሥራ ሁለት! ጥሩ! አሥራ ሁለት ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ያላችሁና ማንበብ የምትችሉ ስለሆነ ከአሁን በኋላ የመስበክና የማስተማር ሥራ የናንተ ይሆናል። እኔ ግን ወደ ሌላ አካባቢ ሄጄ ወንጌልን ላልሰሙት እንዳሰማ ጌታ እየጠራኝ ነው» አላቸው።

አማኞቹ ሀሳቡን ባለመቀበል እንዲህ አሉ፥ «አይሆንም። እንድትሄድ አንፈቅድም። በሚመጡት ዓመታት ከኛ ጋር እዚህ ሆነህ ካልጠበቅከንና ካልመገብከን ከጌታ ጋር እንዴት መቀጠል እንችላለን? በዚህ ሁኔታ እያለን ትተኸን የምትሄደው ለምንድነው? ወደ ቀድሞ አሮጌ ሕይወት እንድንመለስ ትፈልጋለህ ማለት ነው?»

«አአአይ! አልፈልግም። ነገር ግን እስካሁን እናንተ ስትቀለቡ የኖራችሁ ስለሆነ ከአሁን ጀምሮ ራሳችሁ መሥራት አለባችሁ። ጌታ እየጠራኝ እንደሆነ ይሰማኛል። እኔ ሄጄ ወንጌል እንድሰብክ እንዲሁም እናንተ ደግሞ እዚህ ያለውን መሥራት የምትችሉትን እንድትሠሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።»

የመሄዱ ጉዳይ ከፍተኛ ተቃውሞ ስለገጠመውና ክርስቲያኖችንም ተለይቶ ቸኩሎ በመሄድ ሥራውን ላለመጉዳት ትቂት ጊዜ ቆየ። እርሱ ጥሩ መጋቢ፥ ጥሩ ሰባኪ፥ ታጋሽና የሚቀርቡትን ሰዎች ለመርዳትና ለማገልገል የሚወድ ሰው ነበር።

ናና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ሄዶ «አሁን መሄድ አለብኝ። እኔ ከሄድኩ በኋላ ጌታ እዚህ ያለውን ሥራ በጥሩ ሁኔታ ይዞ የሚያገለግል መጋቢ ይሰጣችኋል። እንድሄድ ከፈቀዳችሁልኝ ከደገፋችሁኝና ከጸለያችሁልኝ ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን እስካሁን ከባረከው በላይ ይባርክላችኋል» አላቸው።

የቤተ ክርስቲያኑ ሰዎች እንዲሄድ ባይፈልጉም ናና ስለለመናቸውና የተልዕኮውን አስፈላጊነት ስለተገነዘቡ በሌላ ቦታ ሄዶ እንዲያገለግል ፈቀዱለት።

«ጥሩ! እንድትሄድ ፈቅደንልሃል። ጌታ ለቤተ ክርስቲያናችን መሪ እንዲሰጥ እንጸልያለን።»

በዚያን ጊዜ ናና ሚስትና አንድ ልጅ ነበረው። «ሚስትህንና ልጅህን አትውሰዳቸው። በምትሄድበት የመኖሪያ ቦታ ካዘጋጀህ በኋላ ተመልሰህ ይዘሃቸው ጌታ ወደሚመራህ ሥራ ትሄዳለህ። እስከዚያ እኛ እንከባከባቸዋለን» አሉት።

እንግዲህ በወላይታ ቤተ ክርስቲያን እንዲያድግና እንዲስፋፋ የረዱት ናናን የመሰሉ ለመከራም ሆነ ለምቾት ሳይበገሩ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የምሥራቹን ወንጌል ለሌሎች ሳያቋርጡ የሰበኩ ሰዎች ናቸው። በተጨማሪም ከናና ታሪክ ኢየሱስ በምሳሌው እንዳስቀመጠው እርሱ የዘራው የሕይወት ዘር እየበዛና እያደገ እንደሄደ እንማራለን፥ የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን አደገ፥ አዳዲስ ሰባኪዎች ወደ አዳዲስ ቦታዎች ተላኩ፥ አዳዲስ ፍሬዎችም ተገኙ፥ በዚሁ ዓይነት የማባዛቱ ሂደት ቀጠለ።

## ምዕራፍ 21. ባሎቴ

. . . አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፥ ጳውሎስም
የሚናገረውን ታደምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።
የሐዋ..ሥራ 16:14

በወላይትኛ ማንበብና መጻፍ ከተማሩት ከመጀመሪያዎቹ ልጃገረዶች ውስጥ አንዷ ባሎቴ ነበረች። ጌታን ያወቀችው በኢጣሊያን ወረራ ዘመን

ነበር። በምትሠራው ሥራ ሁሉ በጣም ቀልጣፋ ከመሆኗም በላይ በመዳን ያገኘችውን አዲስ ደስታና ሰላምን ለሌሎች ሴቶች ለማሳወቅና ለመመስከር በጣም ትጥራለች። ጦርነቱ ካበቃ በኋላ ሰልማ በርግስተን የሴቶችን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖችን ለማስተባበር በየቤተ ክርስቲያኑ በምትዘዋወርበት ጊዜ አብረዋት ከሚዘዋወሩት አምስት ወይም ስድስት ሴቶች ውስጥ አንደኛዋ ባሎቴ ነበረች።

በአካባቢያዋ ባለ ቤተ ክርስቲያን የሚያመልክ አሞጬ የተባለ ወጣት ባሎቴን ወደዳት። አሞጬ ልጅ ሆኖ ከብት ሲጠብቅ አንድ ቀን ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ስለ መጣበት ራሱን ለመከላከል መሬት ለመሬት እየተንፏቀቀ ወደ አንድ ትንሽ ጉድጓድ ሲጠጋ ሳያየው አንድ ነብር የሚመስል አውሬ በቁጣ መጥቶ ጉንጬን ቢጨረው። በኋላም ቁስሉ ሲድን ከቀኝ ዓይኑ በታች ጠባሳ ሆኖ ቀረ። እርሱ ረጋ ያለና ዝምተኛ ልጅ ሲሆን ባሎቴ ግን ንቁ ነበረች። አስፈላጊዎቹ ስምምነቶች ከተደረሱ በኋላ ሁለቱ ተጋቡ። አሞጬም በወላይታ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ ወንጌል መስበክ ጀመረ።

የመጀመሪያ ልጃቸው ሴት ስትሆን በአካባቢው ካሉ ልጆች የበለጠ ቆንጆና ተወዳጅ ነበረች። ስሟ ፔርሲ ይባል ነበር፥ ባሎቴና ፔርሲ መቼም አይለያዩም ነበር። ባሎቴ ከልጅዋ ጋር ስትነጋገር የምትለውን ሁሉ ልጅዋ የምትረዳ ይመስል ነበር። ባሎቴ ስለችግሯዋም ሆነ ስለደስታዋ ታወራላታለች። ባሎቴ ጥጡን እንዝርቱንና የማስታወሻ ደብተሯን የምትይዝበት በላዩ ላይ በክር ጥልፍ ወይም በእጅ ስፌት «ባሎቴ» ተብሎ ስሟ የተፃፈበት ከጥጥ ጨርቅ የተሠራ ከረጢት መሰል ቦርሣ ነበራት። ፔርሲም እንዲሁ ለሦስት ዓመት ልጅ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የምትይዝበትና በላዩ ስሟ የተፃፈበት ተመሳሳይ ቦርሣ ነበራት። ባሎቴና ፔርሲ አይለያዩም፥ ባሎቴ በሄደችበት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቦታዎችም ጭምር ፔርሲም አብራት ትገኝ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ፔርሲ ታመመች። ባሎቴ እርጉዝ ስለነበረችና ከዚህም የተነሣ አቅም አጥታ ስለነበር ሆስፒታል ልትወስዳት አልቻለችም። አሞጬም ለስብከት ርቆ ሄዷል። ዘመዶችና ጎረቤቶች ተሸክመው ሶዶ ወደ ሚሲዮኑ ሆስፒታል ቢያደርሷትም ምንም ሊደረግላት አልተቻለምና ሞተች።

«በጣም የምትወዳትን የትንሿን ፔርሲ ሞት ባሎቴ እንዴት ትቀበለዋለች?» የሚለው በሁሉም ሰው አእምሮ የሚጉላላ ጥያቄ ነበር። ወደ ሆስፒታል ተሸክመው የወሰዷት ዘመዶች አስከሬን በሸማ ጠቅልለው በመሸከም ወደ ባሎቴ ተመለሱ። ከሆስፒታሉ የባሎቴ ቤት የሁለት ሰዓት ጉዞ ነበር።

በነጋታው ሰልማ በርግስተን ይህንን መንገድ ተከትላ ወደ ባሎቴ ቤት ስትሄድ ምን ብላ እንደምታጽናናት እያሰበች እግዚአብሔር ከቃሉ የምትለውን እንዲሰጣት ጠየቀችው። ወደ ባሎቴ ቤት የሚያስገባውን እግር መንገድ ይዛ ስትሄድ ባሎቴ በበር ቆማ አየቻት፥ ቀርባም ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ። ሚሲዮናዊቷ የማጽናኛ ቃል ከመጀመርዋ በፊት ባሎቴ « ያቺ ትንሽ ልጄ ከጌታ ጋር መኖሯ አያስደንቅምን? ባለፈው ሳምንት እዚህ ከኔ ጋር የነበረች ዛሬ ግን ከጌታ ጋር መሆኗ አያስደንቅምን? ብዙ ተወዳጅ የሆኑ ትናንሽ ልጆች እያሉ ጌታ የኔን መምረጡ! አያስደንቅምን?»

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በቤቱ እንድትኖር ልጅዋን መርጦ ስለወሰዳት እንዳከበራት ስለቆጠረች ከፍተኛ ደስታና አድናቆት አደረባት እንጂ ምንም ሐዘን አልተሰማትም። የልጇን መሄድ እንደድል ስለቆጠረች በመመረር አላለቀሰችም።

አሞጩ የፔርሲን መታመም ሰምቶ ሆስፒታል በተወሰደችበት ዕለት ማታ ወደ ቤቱ ጉዞ ከጀመረ በኋላ ልክ የፔርሲ አስከሬን ከሆስፒታል ወደ ቤት ተወስዶ ለቀብር ሲዘጋጅ ደረሰ።

ከፔርሲ ሞት በኋላ ደሲታ ተወለደ። ደሲታ በጣም ዝምተኛ ከመሆኑም በላይ ንቁ ስላልሆነ ከፔርሲ የተለየ ነበር። ባሎቴ እንደ ፔርሲ ሁሉ በጣም ትወደውና ትንከባከበው ነበር።

በዚህን ጊዜ ባሎቴና ባለቤቷ በስተደቡብ ምዕራብ ሁለት ሣምንት ያህል የእግር ጉዞ ርቆ በሚገኝ በጎፋ ወንጌል እንዲሰብኩ እግዚአብሔር እየጠራቸው እንደሆነ አወቁ። አሞጩ ቤት ሊሠራ የሚችልበትን ቦታ ለመፈለግና ለመምረጥ አስቀድሞ ወደ ጎፋ ሄደ። በዚያም ወንጌል ያልደረሰበትን ጎሣ በማግኘት በአካባቢው ባለ ኮረብታ ጎን ጥሩ መሬት መርጦ ቤት ከሠራና አትክልት ከተከለ በኋላ ባሎቴንና ደሲታን ለመውሰድ ወደ ወላይታ ተመለሰ። የተመለሰውም ዓመታዊው ኮንፈረንስ ሊከፈት ጥቂት ቀናት ሲቀረው ነበር።

ኮንፍራንሱ አልፎ ጎፋ የሚሄዱበት ጊዜ ደረሰ። ሌላም ወንጌላዊ ከሚስቱ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ወደ ጎፋ የሚሄድ በመሆኑ የሚያስፈልጋቸውን እቃ በራሳቸው ከመሸከም ይልቅ በአህያ ጭነው እንደሚጓዙ ሁለቱ ቤተሰቦች ተስማሙ። ስንቃቸውን ሰብስበው በአንድ ትንሽ አህያ ጫኑ። ባሎቴ በአንድ እጇ በትንሽ ማሰሮ ወተት በሌላ እጇ ደግሞ በቅል የተሞላ የስንዴ ዱቄት ከመያዟም በላይ ደሲታን በጀርባዋ አዝላለች። አሞጩ አህያውያንና ላሚን ይነዳ ነበር።

እንግዲህ አሞጩና ባሎቴ ሁሉንም ትተው ቤታቸውንም ለቀው ወጡ። ጥሩ ጎረቤቶችን እንዲሁም ደግሞ ሁሉ የሚገኝበትና የሚገዛበት ገበያ በቅርብ ያለበትን አካባቢ ወደኋላ ትተው ጉዞ ጀመሩ። ካላቸውም ሁሉ ካንዲት ላም በስተቀር ቤታቸውን፥ የእርሻ መሣሪያዎቻቸውን፥ የውሃ እንስራዎችንና የሸክላ ምጣዳቸውን አልያዙም። እነዚህ በገንዘብ ሲተመኑ ብዙ ላይሆኑ ቢችሉም ለእነሱ ግን ትልቅ መስዋዕት መክፈል ያህል ነበር። ሆኖም ወንጌልን ላልሰሙት አሰምተው ክርስቶስን ለማሳወቅ ወደ ጎፋ ለመሄድ ሲሉ ምቾቶቻቸውን በወላይታ ጥለው መሄድ በመቻላቸው ተደሰቱ።

የእንስሳዎቹ እርምጃ በቀስታ በመሆኑና ባሎቴ ልጅ ስላዘለች ጉዞአቸው ሁለት ሳምንት ፈጀ። በእግር የተጓዙት ድንጋያማ ተራሮችን፥ ጥልቅ ወንዞችን፥ በረሃዎችን፥ አውሬዎችና ወንበዴዎች የሚያደፍጡባቸውን ጫካዎችን እያቋራረጡ ነበር። ዝናቡ በዝቶ ሰፋፊ ወንዞች ሞልተው መሻገር እንዳይከለክሉ በመስጋት ቶሎ ቶሎ ተጉዘው በመጨረሻ ጎፋ ደረሱ። ባሎቴ ባሏ ያዘጋጀላቸውን ቤትና አትክልት ስታይ ደስ አላት።

ሦስት ሳምንታት ከቆዩ በኋላ አሞጩ ለሥራ ጉዳይ ሶዶ መመለስ ነበረበት። ባሎቴ ብቸኛ ብትሆንም አልፈራችም። አስቀድማም ከአካባቢው

ሴቶችና ልጆች ጋር ወዳጅነት ፈጥራ ስለነበር ከእግዚአብሔር ቃል እያነበበችላቸው ስለ ጌታ ትነግራቸው ነበር። ብዙ ሥራ እየሠራች ጊዜን በማሳለፍ የባሏን መመለስ ትጠባበቅ ነበር። አሞጩ ቶሎ ቶሎ ይሄድ ስለነበረ ተመልሶ ወላይታ መድረስ ከአንድ ሣምንት ትንሽ የሚበልጥ ጊዜ ወሰደበት።

«ወደ ሶዶ በደረሰ ጊዜ ቤቴ መጥቶ ነበር» አለች ሰልማ በርግስተን አስታውሳ። «እብረን ቡና ጠጣን፥ ስለባሎቴም ጠይቁው ‹በጣም ደህና ነች፥ እኔ እስክምመለስ ጥናቶችን ትመራለች፥ የመሳሰሉትንም ትሠራለች› ብሎኝ ነበር። ደግሞም ከጎረቤቶቻቸው ሁሉ ጋር በጣም ወዳጅ መሆንዋንም ነገረኝ። ውይይቶችንም ማንም ማቆየት እስከማይችልበት ጊዜ ድረስ ተካፋዮችን እያስደሰተች ማቆየት ትችላለች። ተመልሶ ሊጠይቀን የሚመጣበትን ቀን ተቀጣጥረን ተለያየን ቀኑንም ተጠባበቅን።»

አሞጩ ይመለሳል ተብሎ በተጠበቀበት ቀን ጧት በቀማኞች የተገደለ መሆኑን የሚነግር መልዕክተኛ ደረሰ።

አሁንም ጥያቄዎች መጡ። ባሎቴ ከትንሽ ልጇ ደሲታ ጋር ሁለት ሣምንት የእግር ጉዞ ርቆ በጎፋ ብቻዋን ትኖራለች። የአሞጩን ሞት ስትሰማ ምን ትሆን? ባለችበት አካባቢ (በጎፋ) የሚያጽናናት ክርስቲያኖች የሉም። ታዲያ አሞጩ የማይመለስ መሆኑን በምትሰማበት ጊዜ የምታደርገው ምን ይኖራታል? ማንስ ሊያጽናናትና ሊያበረታት ይችላል?

የሶዶ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አሳዛኙን መልዕክት ይዞ ወደ ባሎቴ የሚሄድ መልዕክተኛ ቢያገኙም እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ የባሏን ያለመመለስ እንድታውቅና መርዶውንም እንድትሰማ ያዘጋጃት ነበር።

አሞጩ ወደ ወላይታ ከሄደ ከጥቂት ቀናት በኋላ በአንድ ሌሊት «ባሎቴ ባልሽ ባይመለስ ምን ትሆኛለሽ?» የሚል ድምፅ ከእንቅልፍ ቀሰቀሳት።

ባሎቴም «ይመለሳል እንጂ። ጌታ ሆይ! እንድናገለግልህ እዚህ ያመጣኸን አንተ ነህ። ባሌም ገና ስብከቱን በደንብ አልጀመረም። ስለዚህ ጌታ ሆይ ባሌ ይመለሳል» ብላ ተመልሳ ተኛች።

ያ ድምፅ በድጋሚ መጥቶ ከእንቅልፍ ቀሰቀሳት፥ «ባሎቴ ባልሽ ባይመለስ ምን ትሆኛለሽ? ምንስ ታደርጊያለሽ?»

ለትንሽ ጊዜ ተጠራጠረች። ፈራ ተባም እያለች «እንግዲህ ጌታ ሆይ! የምትጠይቀኝ አንተ ከሆንክ እርሱ (ባሌ) ያንተ ነው እኔም ያንተ ነኝ። ስለዚህ የራስህ በሆነው የፈለግከውን ማድረግ ትችላለህ» ብላ ተመልሳ ተኛች። ግን እንቅልፍ አልወሰዳትም። ነገሩ ምን ማለትና ምንስ ሊያስከትል እንደሆነ ለብዙ ጊዜ አሰበች።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየቀኑ ከወላይታ የሚመጣ ሰው ትጠባበቅ ነበር። የሚመለስበት ቀን አለፈ። እንደገናም ቀናት አለፉ። አሁንም አልተመለሰም። ወሬም የለም። ባሎቴም ታስብ ጀመር።

ከዚያም በኋላ ከወላይታ ከእርስዋ አካባቢ የሆነ አንድ ሰው ከሩቅ እየመጣ ወደ ቤትዋ ሲቃረብ ተመለከተች። ወዲያው ያ ደጋግሞ ከእንቅልፍ የቀሰቀሳት

ድምፅ ያላት እውነት መሆኑን ተገነዘበች። ከዚያም «አይመጣም ወይ?» አለችው ሶኾ ብላ።

መልዕክተኛውም «አዎን አይመጣም» ብሎ መለሰላት። ይህንን እንደሰማች ባሎቴ ወደጎጆዋ ተመልሳ ገባች። ተንበርክካ ማድረግ ያለባትን ጌታ እንዲያሳያት ጠየቀችው። «ጌታ ሆይ ተመልሶ የማይመጣ ከሆነ አንተ በነገር ሁሉ አብዝተህ ምራኝ» ብላ ጸለየች።

ብዙ የምታስብበት ጊዜ አልነበራትም። ወዲያው ጎረቤቶቿ ተሰብስበው ዋይታና ልቅሶ ጀመሩ። የጎሩዎች አለቃቀስ ኃይለኛና አስቃቂ ነበር። ወደ አየር ከፍ ብለው በመዝለል ከዚያ ራሳቸውን በመሬት ላይ በጀርባቸው ይጥሉ ነበር። በዚህ አኳኋን የወደቀ ሰው መትረፉ በጣም ያስደንቃል።

የአካባቢው ሰዎች በቡድን እየሆኑ ሊያለቅሱና ሐዘናቸውን ለመግለጽ ሲመጡ ባሎቴ ወደ ውጭ ወጥታ «ለምን ታለቅሳላችሁ?» እያለች ትጠይቃቸው ነበር።

«ባልሽ ስለተገደለ! ባልሽ ስለተገደለ ነው የምናለቅሰው! ለእርሱ ነው የምናለቅሰው።»

«ለምን? ለምን ለባሌ ታለቅሳላችሁ?»

«ተመልሶ ስለማይመጣ» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው። «ባሌ ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እናንተ የሞተ መሆኑን ነግሬአችሁ ነበር። እርሱ ስለ እናንተ ለመሞቱ አንድ ጊዜ እንኳን አላለቀሳችሁለትም። ለባሌ ግን ለምን ታለቅሳላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ እርሱ ስለ እናንተ አልሞተም።»

ከዚያም ባሎቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገላቸውንና አዳኛቸው አድርገው ከተቀበሉ እንዴት እንደሚያድናቸው ደጋግማ ታስረዳቸዋለች።

በነዚሁ የልቅሶ ቀናት ሀዘናቸውን ለመግለጽ ይመጡ የነበሩ ሰዎችን በመገናኘት ባሎቴ በረታች። ከሶዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ወደ ጎፋ መልዕክተኞች ተላኩላት፣ መልዕክቱም «አሁን ብቻሽን ስለሆንሽ ጎፋ መቆየት የለብሽም። ስለዚህ ወደ ወላይታ መመለስ ትችያለሽ እዚህም ብዙ የሚሠሩ ነገሮች አሉና» የሚል ነበር። ባሎቴ ለዚህ ስትመልስ «ለምን እመለሳለሁ? እዚሁ እቆያለሁ እንጂ! ጌታ ባሌን ለአገልግሎት ሲጠራው እኔንም ጠርቶኛልና እርሱ ተመለሺ እስከሚለኝ ከዚህ አልለቅም» አለች።

ባሎቴም በጎፋ በተለያዩ አካባቢዎች የሚሠሩ ወንጌላውያን የርሷን ሥራ የሚሸፍን ሰው እስኪያገኙ ድረስ በዚያ ቆየች። በቆየችባቸው ጊዜያት ሥራውን ብቻዋን በመወጣት በሳምንቱ ሁሉ ሰዎችን እየሰበሰበች ታስተምር ነበር።

በዚያ የተመደበው ወንጌላዊና ባለቤቱ ሲደርሱ ባሎቴ በጎፋ አካባቢ ተዘዋውራ እናቶችንና ልጃገረዶችን ለማስተማር ነፃ ሆነች። ሰዎች ወንጌል ሰምተው ጌታን በተቀበሉበት አካባቢ የሚሠሩ ወንጌላውያንና ሚስቶቻቸው ባሎቴን ሁልጊዜ ወደ እነርሱ ይጠሩዋት ነበር። ሚሲዮናውያን በሶዶ እንዳደረጉት እሷም የየሁለት ሣምንት ትምህርት እያዘጋጀች እናትና ወጣት ሴቶችን ታስተምር ነበር። የሥራው ብዛትና የክርስቲያኖች ቁጥር በጨመረ

ጊዜ ባሎቴ ረዘም ላለ ጊዜ ማለት በሁለት ሳምንት ፋንታ ሁለት ሁለት ወር እንድትቆይና እንድታስተምር ቤተ ክርስቲያናት ጠየቁአት።

ባሎቴ በየቤተ ክርስቲያኑ ተዘዋውራ ከማስተማሯ ጎን ትንሽ ልጇን ደሲታን ትንከባከበዋለች። የስንዴ ዱቄት በቅል እንዲሁም ደግሞ የልጅ ወተት በትንሽ ማሰሮ በሁለቱም እጆቿ አንጠልጥላ ድንጋያማ የእግረ መንገዶችን እያቋረጠች ስትሄድ ደሲታ ከጀርባዋ አይለያትም። አዲሱ ወንጌላዊ ከሚስቱ ጋር መጥቶ ሥራዋን ሲረከብ ባሎቴ አሞጩ የሠራላትን ቤት ለቅቃ ወጣች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባሎቴ የራሷ የሆነ ቤት ወይም ደግሞ «ይህ ቤቴ ነው፣ ይህ አልጋዬ ነው፣ በዚህ እኖራለሁ» የምትለው ቦታ አልነበራትም።

ሴቶችንና ሕፃናትን ለማስተማር ከቡድን ወደ ቡድን ትዘዋወር ነበር። ማለዳ ከብቶች ሳይለቀቁ ሃምሣ የሚያህሉ ሕፃናትን ሰብስባ ካስተማረች በኋላ የሥራ ሰዓት ሲደርስ ታሰናብታቸዋለች። ሕፃናት ሲለቀቁ ሴቶቹ ይመጡና ቀኑን ሙሉ እስከ ማታ ሰዓት ድረስ ይማራሉ። በምሽት ሰዓት ሁልጊዜ ወንዶችና ሴቶች ተሰብስበው መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚያስችላቸውን ፊደል ይማራሉ።

ከአሞጩ ሞት በኋላ በተካሄደው የሶዶ ዓመታዊ ኮንፈራንስ ባሎቴ ተገኝታ ነበር። በጎፋ ለምታገለግላቸው ሰዎች ለኮንፈራንሱ የምትሄድ መሆኗን በነገረቻቸው ጊዜ «በፍጹም መሄድ የለብሽም። እኛም አንፈቅድልሽም» አሏት።

«ሄጄ ልቀር አይደለም እመለሳለሁ።»

«አይሆንም! ውሸትሽን ነው፣ አትመጪም።»

ባሎቴ የምትሄደው ለኮንፈረንሱ ብቻ እንደሆነና ተመልሳም የምትመጣ መሆኗን ደጋግማ በማስረዳት ለማሳመን ሞከረች።

አሁንም «ትተሽን መሄድሽ ነው፣ ዳግመኛም እንደማትመለሺ ልትነግሪን አልፈለግሽም» አሏት።

«በውነት እመለሳለሁ» አለቻቸው ባሎቴ።

ባሎቴ ምንም ብትሞክር ልታሳምናቸው አልቻለችም። ሰዎቹ ከዚያ በፊት ብዙ አገልጋዮች የመጡላቸውና እንመለሳለን እያሉ በመሄድ ሳይመለሱ የቀሩ መሆኑን ነገሯት።

ስለዚህ «አንቺን አንለቅም» አሏት።

«የምናገረው እውነት እንደሆነና ከሄድኩ በእርግጥ የምመለስ መሆኔን በምን ልታምኑኝ ትችላላችሁ?» አለች ባሎቴ ከፍ አድርጋ በመናገር።

«ከወላይታ ኮንፈረንስ በኋላ በእርግጥ እመጣለሁ የምትዪ ከሆነ ይህንን ለማረጋገጥ ሕፃንሽን (ደሲታን) በኛ ዘንድ ትተሽው ሂጂ።»

ባሎቴ ለጥቂት ጊዜ አሰበች። እነዚህ ይህንን የሚጠይቋት ሰዎች አማኝ ያልሆኑ ናቸው። ፔርሴንና አሞጩን በሞት ምክንያት አጥታቸዋለች። አሁን የቀራት ገና ዕድሜው አንድ ዓመት ያልሆነው ትንሹ ደሲታ ብቻ ነው። ይህ

ብቻ አይደለም። ደሲታ ብቸኛ ወገኗ ነው። ሌላ የሥጋ ዘመድ ወይም ወገን የላትም። በጎፋ ያሉ ያላመኑ ሰዎች ታዲያ «ተመልሰሽ የምትመጪ መሆኑን ለማረጋገጥ ደሲታን በኛ ዘንድ ተይው» ይሏታል።

«እሺ! ጥሩ! እንደምመለስ በዚህ የምታረጋግጡና የምታምኑኝ ከሆነ እግዚአብሔር በእውነት ተመልሼ እንደምመጣ ያውቃልና ደሲታን ከናንተ ጋር እንዲቆይ ትቼ እሄዳለሁ» ብላ መለሰች ፈገግ እያለች።

ከዚያም ባሎቴ ወደ ወላይታ በመሄድ በኮንፈረንሱ ተካፈለች። በአንዱ ፕሮግራም መጨረሻ ባሎቴ ሁለቱንም እጆች ገጥማ እንደያዘች ወደ ሰልማ በርግስተን መጣች። ሌሎች የሚያደርጉትን ንግግር ሲያበቁ እርሷ ወደፊት ወጥታ ቆመች። እጇንም ዘርግታ የተወሰነ ገንዘብ በሚሲዮኗ እጅ አስቀመጠች። ገንዘቡ ባሏ (አሞጩ) ባለፈው ዓመት ለጌታ ሊሰጥ ቃል የገባውና እርሱ በመሞቱ ግን ሳይፈጸም የቆየ ነበር። ከአገር አገር እየዞረችና የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረች ከዚህም በተጨማሪ ሕፃን ልጅዋን እየተንከባከበችና እያሳደገች ባሏ ለጌታ ሊሰጥ የገባው ገንዘብ እስኪሞላ ድረስ ቀስ በቀስ ሳንቲሞችን እየሰበሰበች ከቆየች በኋላ የከፈለችው መሆኑ ነው።

ኮንፈራንሱ እንዳበቃ ባሎቴ ወደ ጎፋ ተመለሰች። ልቧ በርትቶ የጌታዋን ፍቅር ላላመኑ በጎፋ ላሉ ጎረቤቶቿና ለሌሎች ሰዎች ለመመስከር ያላት ፍላጐት ይበልጥ አደገ። የእናት ፍቅር በቶሎ እንድትመለስ ያስገደዳት ይሁን እንጂ ለክርስቶስ ያላትን ፍቅር ሌሎችም እንዲያውቁትና እንዲለማመዱት መመኘቷ ሌላው አስገዳጅ ምክንያት ነበር። እንደደረሰችም ደሲታን በደህና አገኘችው። ያላመኑ ጎረቤቶቿም እርሷን በማየታቸውና ቃሏን ጠብቃ በመመለሷ በጣም ተደሰቱ።

ባሎቴና መሰሎቿ በትልቅ መስዋዕትነትና በመከራ እያለፉ በታማኝነት እግዚአብሔርን ከማገልገላቸው የተነሣ በጎፋ ወንጌል ሥር ሰደደ።

- የጎፋ አማኞች ወንጌል ከየት እንደመጣ ለማወቅ ፈለጉ። ወንጌልን ወደ ጎፋ ያመጡ የወላይታ ወንጌላውያን ሚሲዮናውያን ከሀገረቸው ወደ ወላይታ ያመጡት መሆኑን ነገሯቸው። ወደ ጎፋ ወንጌልን ስላመጡ ክርስቲያኖቹ ለሚሲዮናውያን የምስጋናና የአድናቆት ደብዳቤ ጻፉላቸው።

> ወንጌል ይዛችሁ ወደ ወላይታ ስለመጣችሁ ልናመሰግናችሁ እንወዳለን። ወደ ጨለማው ብርሃን ይዛችሁ ስለመጣችሁ ልናመሰግናችሁ እንወዳለን። በወላይታ ከምትሠሩት ሥራ የተነሣ ወላይታዎች ጌታን ከማወቃቸውና ወንጌልን ይዘው ወደጎፋ መምጣት በመቻላቸው እናመሰግናችኋለን።

በደብዳቤው ፍፊርማቸውን አኖሩ።

> ልብስ ከማይለብሱ ሰዎች ቤት ክርስቲያን ወይም ልብስ ለብሰው ከማያውቁ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የተላከ (አሁን ግን ጌታን በማወቃችን ከቀድሞ በተለየ አኳኋን ስለምንኖር ደስ ይለናል)።

## ምዕራፍ 22. አሞኔ

የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች
ብቻዋን ትቀራለች፥ ብትሞት ግን . . .
የዮሐ. 12፡24

«ዝም ብሎ መኖር ሳይሆን እንደ አሞኔ ነው መኖር የምፈልገው።»

የአጆ እናት ለአሞኔ እናት በላከችው ደብዳቤ ነበር ይህንን የአጆን ምስክርነት የጠቀሰችው። የኮይባ ተራሮችን አቋርጠው በመሄድ አጆና በኋ በወንጌላዊነት የሚያገለግሉት ከአሞኔ የተነግ ነበር። ይህም የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራ ውጤት ነበር።

ወንጌል በኑሮም በአፍም ይሰበካል። አሞኔና ሻንካ በሕይወታቸው በኩል የእግዚአብሔር ቃል የሚናገርባቸው ሕያው መልዕክቶች ነበሩ። ቅርብ ጊዜ የተጋቡ ደስተኛ ሙሽሮች እንደሆኑ ለሻንቂላ ሕዝቦች የወንጌል ሚሲዮናውያን ሆነው ወደ ጎፋ ሄዱ። በአፍሪካ ሆነ በሌላ ምድር እንደአሞኔ ያለ ዝምተኛና ደግ የሆነች ወጣት ሴት ማግኘት ያስቸግራል። አሞኔ ምንም ሳትቆጥብና ሳታስቀር በሙሉ ልብና ፈቃደኝነት ራሷን ለጌታ ሥራ ከመስጠቷም በላይ በሻንቂላ ሕዝቦች መካከል ሕይወቷን ሁሉ ለጌታ መኖር ነበር ምኞቷ።

ለክርስቶስ ስትል በዚያ መኖር ቢያስደስታትም በመጀመሪያ ከሻንቂላ ሴቶች ጋር ወዳጅነት መፍጠር አልቻለችም። ምክንያቱን አታውቀውም። ስትጎበኛቸውና ስታነጋግራቸው ፍላጎት አያሳዩአትም። ወደ ቤታቸውም አይጋብዟትም። ወደ ቤታቸው ስትሄድ ከበር ውጪ ቆመው ነበር የሚያነጋግሯት። አንዳንድ ጊዜ ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ወደ ውስጥ ይጋብዟታል። ሆኖም በገዛ ቤቷ ከሻንካ ጋር ደስተኛ ነበረች። ከሻንቂላ ሴቶች ጋር ወዳጅ የምትሆንበትን መንገድ እንድታገኝ እግዚአብሔር ይረዳት ዘንድ አብረው ይጸልዩ ነበር።

ሻንካ ለመቀራረብ እንዲመቸው ሻንቂላዎችን ወደ ቤቱ እንዲመጡ ይጋብዛቸዋል። በሚመጡም ጊዜ በእርሱና በእነሱ ቤት ውስጥ ብዙ ልዩነት እንዳለ ይመለከቱ ነበር። አሞኔ ቡና ወይም ምግብ ስታቀርብ ምን ያህል እንደምታስተናግዳቸው፥ ባሏንም የምታከብርና የምትወድ መሆኗን እንደባሕላቸው ምግብ ከመበላቱ በፊት ፈጥና ሞቅ ባለ ውሃ እጃቸውን ስታስታጥብ እንዲሁም ደግሞ ማታ ማታ በትህትና በመቅረብ የሻንካን እግሮች ስታጥብና በአጠቃላይ በቤት ውስጥ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ጠንቃቃ እንደሆነች አይተው የመጡት ሁሉ ይህ ቤት በእርግጥ ደስተኛ ቤት እንደሆነ አረጋገጡ።

በመጨረሻ የሻንቂላ ወንዶች ሚስቶቻቸው መጥተው አሞኔን እንዲጎበኙ ሻንካን ጠየቁት። ሻንካ ቢመጡ ደስ እንደሚለው ገለጸላቸው። አሞኔም በፍላጐታቸው ደስ ተሰኝታ መምጫቸውን በጉጉት መጠባበቅ ጀመረች። ሻንቂላዎችም ሚስቶቻቸውን «የዚያን በቅርብ ወደ አካባቢያችን የመጣውን ሰውዬ ሚስት ለምን አትጠይቋትም? በዚህ አካባቢ ዘመድ ወይም የምታውቀው

ሰው የላትም። ሄዳችሁ ካልጠየቃችኋትና ካላነጋገራችኋት ብቸኝነት ይሰማታል» አሏቸው።

«ከዚያን በኋላ ሴቶቹ ወደ አሞኔ ለመሄድ ተስማሙ። አንዳንድ ቀን ወደ አሞኔ ሲሄዱ ዝም ብለው የምታደርገውን ብቻ ይመለከታሉ። የአሞኔ ሁኔታ ለእነርሱ ሊገባቸው የእነርሱም ሁኔታ ለእርሷ ሊገባት አልቻለም። ከዚህም የተነሣ አሞኔ የሻንቂላ ሴቶች አልወደዱኝም ይሆናል ስትል አሰበች።

በመጨረሻ አንድ ቀን ብዙ ሴቶች በአንድ ላይ ሆነው በሚነጋገሩበት ጊዜ «አሞኔ በዚህ አካባቢ እንድትቆይ ከፈቀድንላት ባሎቻችን እንደርሷ ሁሉን ነገር እንድንሠራ ያስገድዱናል» ሲባባሉ ሰማች።

እስከዚሁ ጊዜ ድረስ ሻንካና አሞኔ በሻንቂላ ባሕል መሠረት በቤተሰብ ውስጥ የበላይነት ያላት ሴት መሆንዋን አላወቁም ነበር። ማታ ማታ ሴትየዋ ተቀምጣ እረፍት ስታገኝ ወንድየው በሥራ ደፋ ቀና ይላል። ባል በጋያ ትንባሆ ጨምሮ እሳት ካደረገበትና ካቀጣጠለ በኋላ እንድታጨስ ለሚስት ያቀርብላትና እርሷ ተቀምጣ ስታጨስ እርሱ የቤት ውስጥ ሥራ ያከናውናል። በመንገድ በሚጓዙበትም ጊዜ የሻንቂላ ሴቶች ጋያ እያጨሱ ከፊት ለፊት ሲሄዱ ወንዶቹ ዕቃ ተሸክመው ይከተሏቸዋል። አሞኔና ሻንካ ማታ ማታ የሻንቂላዎችን ቤቶች እየተዘዋወሩ በሚጎበኙበት ጊዜ በባሕላቸው መሠረት ወንዶች የሴቶችን እግር የሚያጥቡ መሆኑን ለማወቅ ቻሉ። ሚስት መቼም ቢሆን የባሏን እግር አጥባ አታውቅም ነበር።

ስለዚህም የሻንቂላ ሴቶች «በዚህ አካባቢ እንድትኖር መፍቀድ የለብንም። ፈጽሞ! ፈጽሞ እዚህ እንድትኖር ማድረግ አንችልም» ቢሉ አያስደንቅም።

ወደ ቤቷ ደጋግመው ስለመጡና ስላዩ ከረዥም ጊዜ በኋላ ሴቶቹ አሞኔ በእርግጥ የምትወደድ ሴት መሆኗን ተገነዘቡ። በአሞኔና ሻንካ ቤት የሞላውን ሰላምና ፀጥታ ተመልክተው ወደ ቤታቸው እየመጣች እንድትጎበኛቸው አብዝተው ይጋብዟት ጀመር። አሞኔም የሚወዷትና የሚያምኗት መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እያነበበች ታስተምራቸው ጀመር። ጌታ ያደረገላትንና እርሱን ካወቀች በኋላ በሕይወቷ ስለመጣው ደስታ ነገረቻቸው። ሴቶቹም ያዳመጧት ይሁን እንጂ አሮጌ አኗኗራቸውንና ልማዳቸውን ለመተው ፈቃደኛ አልሆኑም።

ሻንካና አሞኔ ለጎረቤቶቻቸው ለሦስት ዓመታት መሰከሩላቸው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ሻንቂላዎቹ ፍላጐት እያሳዩ ቢሄዱም ፍላጐታቸው አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ ሲል ቆየ። ባልና ሚስት አገልግሎታቸው ከፍተኛ ደረጃ ቢደርስም ሻንቂላዎች ጌታን ለመከተል ምንም ዓይነት (ውጫዊ) ምልክት ሳይታይባቸው የሦስተኛው ዓመት መጨረሻ ደረሰ። በመጨረሻም ጥቂቶች ወደ ክርስቶስ ተማረኩ።

አሞኔ ካሌብ ብለው የሰየሙትን የመጀመሪያ ልጃቸውን እንደወለደች በጣም ታመመች። በዚያን ጊዜ ሴቶች ወደ ቤቷ እየመጡ ያስታምሟት ነበር። «ይህችን ለእኛ ብዙ ያደረገችልንን ሰው ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን?» እያሉ ይጠይቁ ነበር።

አሞኔ አያሌ ቀናት በጠና ታማ ከቆየች በኋላ ሞተች። ሞቷ በሁሉም ዘንድ ታላቅ ድንጋጤ ከመፍጠሩም ሌላ በጊዜው የነበሩ ጥቂት አማኞች ተደናገሩ። ሻንካ ትንሹን ሕፃን ብቻውን ሊንከባከበውና ሊያሳድገው እንደማይችል ግልጽ ሆነ።

ክርስቲያኖቹ ለሻንካ «ሕፃኑን ብቻህን ሆነህ መጠበቅና ማሳደግ ስለማትችል ለአሞኔ እናት መውሰድ አለብህ። እኛም የሚሸከምልህን ሰው እንፈልግልሃለን» የሚል ሀሳብ አቀረቡ። ይህም ሻንካ አስቀድሞ በልቡ የወሰነው ነበር።

ልጁን ለመሸከም ፈቃደኞች አልጠፉም። በርካታ ሴቶች «እኔ እሸከመዋለሁ። እኔ እሸከመዋለሁ። አሞኔ ለእኛ ብዙ አድርጋ ነበር። እርሷ እናታችን ከመሆኗም በላይ ወደ ክርስቶስ መርታናለች። ማገበብና ቤታችንም እንዴት ደስተኛ ማድረግ እንዳለብን አስተምራናለች። ለእርሷና ለጌታችን ያለንን አድናቆት ለመግለጽ ልጅዋን ለአያቱ ወላይታ ድረስ ተሸከመን ለመውሰድ ፈቃደኞች ነን» አሉ።

በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያኑ ሕፃኑን ተሸክሞ ለአያቱ የሚወስድ ሰው ከአያቱ ጋር በእድሜ የሚመጣጠን ሰው መሆን አለበት በማለት አንዲት አሮጊት ሴት መረጠ። ምንም እንኳን ሕፃኑን ተሸክማ የምትሄድበት ቦታ ሁለት ሳምንት የእግር ጉዞ ቢሆንም ሴትየዋ ለዚህ ዕድል በመመረጧ ደስ አላት። የአሞኔን ትንሽ ልጅ በጀርባ አዝላ መሄድን ነበር እንደ ልዩ መብት የቆጠረችው።

ካሌብም በሰላም ከአያቱ እጅ በገባ ጊዜ በጣም ከመከሳቱ የተነሣ ደምና ሥጋ ያልነበረው ለሞትም የተቃረበ ነበር። ያለ በቂ ምግብና ውሃ ይህን የመሰለ ረዥም ጉዞ በጣም ይበዛበት ነበር። ሆኖም እንደምንም ነፍሱ ከተረፈ በኋላ ደስ የሚል ልጅ ሆነ።

አሞኔ ከመሰከረችላቸው የሻንቅላ ሴቶች መካከል አጀ የምትባል ወጣት ሴት ነበረች። አሞኔ ሕይወቷና መልዕክቷ በሌሎች ሰዎች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ሳታውቅ ነበር የሞተችው። እነዚህ ሰምተው የማይሰሙ፣ የማያምኑና ወዳጅነት የሌላቸው ሰዎች ወንጌልን መስማታቸው መረዳታቸውና አምነው መቀበላቸው የክርስቶስን ወንጌል ታላቅ ኃይል ይመሰክራል። በእርግጥም ወንጌል አዲስ ሕይወትን አዲስ አመለካከትን ከሁሉም በላይ ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዲስ ፀጋ አመጣላቸው።

ስምንት ዓመታት አለፉ። የክርስቲያኖችም ቁጥር ጨመረ። አሞኔ ከሞተች ከስምንት ዓመታት በኋላ በጎፋ የሴቶች ኮንፍራንስ መዝጊያ ላይ የአጀ እናት ቀርባ ለአሞኔ እናት መልዕክት ለመላክ የምትፈልግ መሆኗን ገለጸች። መልዕክቱም የሚከተለው ነበረ፣

> አሞኔና ባሏ ለወንጌል ሥራ ጎፋ እንዲመጡ በመፍቀዷ የአሞኔ እናት እንዳታዝን ንገሩልኝ። ልጇ በጎፋ ስለ ሞተች እንዳታዝን ንገሩልኝ። እኔ፣ አጀና የአጀ እህት ማርታ ጌታ ኢየሱስን የምንወደው ከአሞኔ የተነሣ ነው።

አሞኔ ከሞተችበት ጊዜ ጀምሮ አጆ «ዝም ብሎ መኖር ሳይሆን፥ እንደ አሞኔ ነው መኖር የምፈልገው፥ እንደ አሞኔ መሥራት፥ አሞኔ እኛን እንዳስተማረችን ሌሎች ሴቶችን ማስተማር ነው የምፈልገው፥ ዝም ብሎ መኖር አልፈልግም» ትላለች። ያንን በሩቅ ያለውን ተራራ ታያላችሁ? አጆ ከወንጌላዊ ባሏ ጋር በዚያ ትኖራለች። ልክ አሞኔ እንዳስተማረችን እርሷም ሴቶችን ታስተምራለች። አሞኔ እዚህ ስለሞተች እናቷ እንዳታዝን ነገሩልኝ። አሞኔ የዘራችው ዘር ፍሬ እያፈራና ይበልጥ ማፍራትም እየጀመረ ነው። ስለዚህ አሞኔ ጎፋ እንድትመጣ ስለፈቀድሽ ደስ ይበልሽ በሉልኝ።

## ምዕራፍ 23 . ግፋቴ

በሄዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ፥ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።
መዝ. 125(126):6

«እኔ አልሄድም፥ መሄድ ካለብህ ራስህ ሂድ፥ ተመልሰህ እኔን ትወስደኛለህ» አለችው ግፋቴ።

ግፋቴ ባሏ በሲዳሞ ወንጌልን እንዲሰብክ እግዚአብሔር የጠራው መሆኑን ሲነግራት ተቃወመችው፥ አብራ ላለመሄድም «በመጀመሪያ ራስህ ሂድና ተመልሰህ ስትመጣ እኔንም ትወስደኛለህ» አለችው። እርሱም ብቻውን ሄደ። ተመልሶ ሚስቱንና ልጆቹን ከመውሰዱ በፊት የሚኖሩበትን ሥፍራ በመፈለግ በዚያ ብዙ ወራትን አሰለፈ።

ሊወስዳት ተመልሶ በመጣ ጊዜ «አብሬህ ልሄድ አልችልም፥ እዚያ ብሄድ ለረዥም ጊዜ መቆየት ስላለብኝ እዚህ ያሉ ዘመዶቼንና ወላጆቼን መለየት አልፈልግም። አንተ ብቻህን ሂድ እኔ እዚህ ሆኜ ልጆቻችንን አሳድጋለሁ» ብላ መለሰችለት።

ሁለቱ በጉዳዩ ላይ ከረር ባለ ሁኔታ ሲነጋገሩ ጊዜያት አለፉ። እሷ ፈጽሞ አልሄድም ስትል እሱ ደግሞ ብቻዬን አልሄድም በማለት ነበር ሲከራከሩ የቆዩት። ራቅ ወዳሉ አውራጃዎች ሄደው ወንጌል ለሚሰብኩ ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ወራት ብቸኝነት፥ ሌሎችም ፈተናዎችና ችግሮች የሚበዙባቸው ጊዜያት መሆኑን ያውቅ ነበር።

በመጨረሻ ግን ሁሉንም ትቶ ወደ ሥራው መስክ ተመለሰ። ብዙ ወራትም አሳለፈ። በዚህ ረዥም ጊዜ ሁሉ ሚስቱ ቤቱንና ልጆቹን ስታስተዳድር ብቻዋን ስለቆየች ከእርሱ ጋር መሄድና መኖርን ትፈልግ ይሆናል ብሎ ተስፋ በማድረግ ሊወስዳት መጣ።

ለሦስተኛ ጊዜ ለመሄድ ሲነሣ «ይህንን ሥራ ብቻዬን ልወጣው ስለማልችል ከእኔ ጋር መሄድ አለብሽ፣ ጌታ ሥራውን አብረን እንድንሠራ ነው የጠራን። ስለዚህ አሁን አብረን እንሂድ» ብሎ ለመናት።

የመሄዱ ነገር ለርሷ የማትችለው መስዋዕትነት መሆኑን በማስረዳት ለማሳመን የቻለችውን ሁሉ ስታደርግ ጥቂት ቀናት አለፉ። በመጨረሻም ያልተሳካላት መሆኑን ስታውቅ «እሺ እንግዲህ እሄዳለሁ» አለችው። በልቧ ግን «ግድ የለም እሄዳለሁ! ነገር ግን በተቻለኝ መጠን የምትሠራው ሁሉ እንዳይሳካና እንዲከብድብህ አደርጋለሁ፣ ያኔ ከወገኖቻችን ጋር በደስታ እንድንኖር ወደ ቀድሞ መኖሪያችን እንመለስ ትል የለ?» ብላ አሰበች።

በአዲሱ ሥራ ላይ ሆነው ምግብ እንኳን የማያገኙባቸው ብዙ ቀናት ነበሩ። ችግራቸውን ተገንዝቦ የሚያዝንላቸው ማንም በአቅራቢያቸው የሌለ መሆኑን ገፉቴ አየች። ከዚህም የተነሣ ባሏ ለስብከት ሥራ በመስክ ውሎ ደክሞት ሲመለስ ገፉቴ ትቆጣና ትነጫነጭ ጀመር።

ገፉቴ በሶዶ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ስለዚሁ እንደሚከተው መሰከረች፣ «ከስብከት ሥራ ላይ እርቦትና ደክሞት ሲመለስ ምግብና ቡና እንዳቀርብ ይጠይቀኛል። እኔ ግን በጎጆአችን ውስጥ በሸንበቆ (መቃ) ወደ ተከለለው ጓዳ ገብቼ እራት ወይም ቡና የተጣደበትን እሳት እንኳን በትክክል አላነድም ነበር። በማኩረፍና በማጉረምረም ቁጭ ብዬ ቡናው የሚቀርብበትን ጊዜ አራዝምበታለሁ። በዚህ ዓይነት ለእርሱ ሁሉንም ነገር ለማክበድ ወሰንኩ፣ አከበድኩበትም። ምክንያቱም እኔ ወደ ወላይታ ተመልሼ በዘመዶቼ አጠገብ ደስ ብሎኝ መኖር እፈልጋለሁ። የወላይታን ቅቤና እንደልብ ከቤት የሚታፈሰውን እህል እፈልጋለሁ። አሰብኩም፣ አቤት ወደ ቤታችን ብንመለስ እንዴት ጥሩ ይሆን ነበር! ግድ የለም! ችግር መፍጠሬን ልቀጥልና ሲሰለቸው ራሱ ይመልሰኛል።»

«በየቀኑ ባሌን ብፈታተነውም እርሱ ግን ሁልቀን ግልዶ እየተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ያደርስ ነበር። ሙሉውን ቀን ከቦታ ወደ ቦታ እና ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወረ ሲመሰክር ውሎ በጣም ደክሞት ወደ ቤት ይመለስ ነበር። ከዚያም ‹ቡና አለ? እራት ደረሰ?› ብሎ ሲጠይቀኝ በቁጣ ‹ቡና? እራት? ከየት ያመጣሁት?› ብዬ እመልስለታለሁ። ደስ ካለኝ ቡና አፍልቼ ከደረቅ የቦቆሎ ቆሎ ጋር አቀርብለታለሁ። ረጋ ብዬ በቀስታ ደግሞ እራት አዘጋጃለሁ። በዚህ ሁሉ ጊዜ እርሱ በጣም የደከመውና የራበው ቢሆንም ቁጭ ብሎ በትዕግሥት ይጠብቃል። አንዳንዴም ብዙ ከመጠበቅ የተነሣ እንቅልፍ ይወስደዋል። ቡናውንና ቆሎውን አቅርቤ ‹እራት ቀርቧል› ብዬ እቀሰቅሰዋለሁ።

«ወይ እራት! ይህ በወላይታ እራት የሚባል አልነበረም። መክሰስ እንጂ። ለእራት የሚበላው ሙሉ ማዕድ ማለት መሶብ ሙሉ ስኳር ድንች ወይም ንፍሮ ነበር። ባሌ በሁኔታዬ አልተበሳጨም፣ ግድም አልነበረውም። ዘወትር የሚነግረኝ በቀኑ ውስጥ ስለመሰከረላቸው ሰዎች እንዴትስ እንደመሰከረላቸው ነበር። ስብከቱንና ምስክርነቱን በጥሞና ሲሰሙ በጣም ደስ ይለው ነበር።

«‹ወንጌልን እንዴት እንደሰማንና ለምንና እንዴት ልንመሰክርላቸው እንደመጣን ስነግራቸው ደስ ብሏቸው ያዳምጡኛል› ይለኛል።

«እርሱ በጣም ይደሰታል፤ እኔ ግን እበሳጭና እናደድ ነበር። ማታ ወደ ቤት ሲገባ በጥሩ አላናግረውም። በቤት ብቻዬን ትቶ ሙሉውን ቀን ለሌሎች ስለ ጌታ ሲሰብክ ስለሚውል እኔ ተመልሼ ወደ ዘመዶቼ ለመሄድ ፈለግኩ።

«ከብዙ ወራት በኋላ አንድ ቀን ከአንድ ሰው ጋር ወደ ቤት መጣ። ወደ ቤቱ እየቀረበ ገና ሳይገባ ‹ግሩቴ! እስቲ ወጣ በይ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የግል አዳኝ መሆኑን አምኖ ከተቀበለ የመጀመሪያ ሰው ጋር ላስተዋውቅሽ። አስቢ እስቲ! ጌታ እርሱን የተቀበለ የመጀመሪያ ሰው ስለሰጠን ከእኔ ጋር ደስ ይበልሽ። በዚህ አስቸጋሪ ቦታ ካለን ከዚህ አንድ ሰው ጋር ጥሩ ቡና አፍልተሽ ብንጠጣስ!› አለኝ።

«እኔ ግን ለራሴ አሰብኩ፤ ወይ ጉድ! ያንተ አንሶ ለሌላ ተጨማሪ ሰው ቡና ላፈላ? ያለፈው አንሶ ሌላ ተጨማሪ ልፋት? ለአንድ ሌላ ሰውም ጭምር ቡና ማፍላት ያለብኝ መሆኑን ሳስበው ውስጤ በንዴት ከሰለ። የሞቀ ቤቴን፤ ውድ ዘምዶቼን፤ እህቴን፤ እናቴንና ጎረቤቶቼን ትቼ መምጣቴ አይበቃም? ሁሉን ነገር ለመግዛት የሚቻልበት ገበያ ያለበትን አካባቢ ትቼ መምጣቴ አይበቃም? ሺህ አማኞች ቢኖሩ ለሁሉም ቡና ማፍላትና ምግብ መሥራት አለብኝ? እያልኩ ነበር የምበሳጨው።

«ከዚያም ወደ ጎጆው ጓዳ ገብቼ እያጉረመረምሁ ቡናውን ማፍላት ብጀምርም ለማድረስ ረዥም ጊዜ ወሰደብኝ። ባሌ ውጪ በጎጆው አጠገብ ከመሰከረለት ሰውዬ ጋር ተቀምጦ ያወራና ይደሰት ነበር። በጣም ይደሰት ነበር። ከሰውየው ጋር ሆነው ሲጸልዩና መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡ እኔ ግን ጭስ የበዛበትን እሳት እፍ እያልኩ በምድጃ አጠገብ ተቀምጬ ነበር። ከዚያ ምን ደስታ ይገኛል?

«በመጨረሻም እንደምንም ቡናውን አደረስኩና ሳቀራርብ ነበር ጌታ የተናገረኝ። ባሌ በጣም ተደስቶ እያለ እኔ ግን ቅንጣት ደስታ እንኳን አልነበረኝም።

«በዚያን ጊዜ ጌታ እንዲህ ብሎ ተናገረኝ፤ ‹ግሩቴ ከእነርሱ ጋር አትደሰችም? ዛሬ ባልሽ በሚደሰትበት ጉዳይ አንቺ ድርሻ የለሽም? ከዚህ ደስታ አልፈለግሽምና ፈጽሞ አታገኚም። ባልሽ ወንጌልን ይዞ እግሩ እስኪቆስል ድረስ ሜዳውንና ተራራውን እያቆራረጠ ሲሄድ ከዚያም እርቦትና ደክሞት ሲመለስ አንቺ ረድተሽዋል? ጸልየሽለታል? በዚህ ደስታ አንቺ ድርሻ የለሽም። ወደ ቤት በሚገባበት ጊዜ ጸልየሽለት አበረታተሽና መግበሽ ቢሆን ኖሮ አብረሽ ትደሰቺ ነበር። ያኔ ‹ይህን ነፍስ ያገኘው እኔም ስለረዳሁት ነው› ማለት ትችይ ነበር።›

«ጌታ ግን ‹በጭራሽ አንቺ በዚህ ድርሻና ተሳትፎ የለሽም። ባልሽ ግን ከደከመውና ከተራበው በላይ ሊደሰት ይገባዋል። አንቺ ለርሱ ምን አደረግሽለት? ለእኔስ ምን ሠራሽልኝ?› አለኝ።

«በዚያን ጊዜ በጣም አለቀስኩ፤ ጌታ አጥብቆ የተናገረኝና የተገናኘኝ መሆኑን አስቤ በጣም አዘንኩ። በእግዚአብሔርና በባሌ ፊት ወድቄ ‹አ ጌታ

ሆይ! ባሌ ሲያገለግልህ እኔ እርሱን ባለማገዝ ኃጢአት ሠርቻለሁና እንደገና ይቅር በለኝ። አንተ እንድረዳው ስትፈልግ እኔ ግን ጭራሽ አገልግሎቱ እንዲደናቀፍ የቻልኩትን ሁሉ አድርጌያለሁና ይቅር በለኝ። ጉልበቴን ፍቅሬን ሁሉ እሰጥሃለሁ። በዚህ አካባቢ ያሉትን ሰዎች መንገድህን አስተምራቸዋለሁና ጌታ ሆይ ከአሁን ጀምሮ ይህን እንዳደርግ እርዳኝ› ብዬ ለመንሁ።

«ኃጢአቴን ለጌታና ለባሌ ከተናዘዝኩ በኋላ በአንድነት በጌታ ደስ አለን። ቀደም ሲል ባሌ ብቻውን ይሠራ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር አሁን በጋራ ስለምንሠራው ሸክሙም ቀለለ።»

ግፋቴ ይህንን ምስክርነት የተናገረችው በሰልማ በርግስተን ቤት ለሚሰበሰቡ የሴቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አባላት ነበር። ሁሉም ዓይኖቻቸውን ከግፋቴ ሳይነቅሉ እያንዳንዱን ቃል በጥሞና ካዳመጡ በኋላ ግፋቴ ታሪኩን ስትደመድም እንዲህ አለች።

«ሁላችሁም ጸልዩልኝ። ጌታ ለእኔና ለባሌ ስለሰጠን አገልግሎት፥ እዚሁም በቤተ ክርስቲያናችን ስለተመደብንበት ሥራና ከዚህም የተነሣ ስለሚደረግልን የገንዘብ እርዳታ ጸልዩልን። ጌታ እንድሆን የሚፈልገው ዓይነት ሰው እሆን ዘንድ ጸልዩልኝ። ከፉና ቸልተኛ ሆኜ ጌታን በማገልገል የሚገኘውን ደስታ ሳላውቅና ሳልካፈል ያሳለፍኩባቸውን ቀናትና ዓመታትን መካስ እንድችል ጸልዩልኝ።»

## ምዕራፍ 24. የአዳ ሚስት

ባንዘልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም
ሥራን ለመሥራት አንታክት።
ገላ. 6፡6

አዳ ልቡ ታንቡር ይመታ ነበር፥ ለቅሶ ሲደርስ ማድረግ ያለበትን በጊዜ መወሰን ይጠበቅበታል። ምን ይሆን ማድረግ ያለበት?

የአዳ ሚስት ወንድሟ ስለሞተ አዳና እርሷ ለቀብሩ ሥነ ሥርዓት ለመሄድ ከቤት ወጡ። አዳ ምንም እንኳን ክርስቲያን ቢሆንም እንደሌሎች አማኞች በክርስቲያናዊ መንገድ ሐዘኑን ለመግለጽ ሳይሆን ሚቴ የቅርብ ዘመድ በመሆኑ ክርስቲያናዊ ባልሆነ የወላይታ ልማዳዊ አለቃቀስ ለመሳተፍ ወሰነ።

ወደ ለቅሶው ቤት እንደደረሱ አዳ ከሚስቱ ተለይቶ በብዛትና በአንድ ላይ ሆነው ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ስሜት በከፍተኛ ድምፅ ከሚጮኹና ከሚያለቅሱ ሰዎች ተቀላቀለ። በክብር በታጀበ የለቅሶ ዘፈንና ጭፈራ ከተሳተፈ በኋላ በሬውንም ከሌሎች ጋር ሆኖ አረደ።

አዳ ሆን ብሎ ይህንን ለማድረግ መምረጡ በሕይወቱ ትልቅ ቀውስ መሆኑን አረጋገጠ። ምክንያቱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጌታን መከተል ተወ።

የአዳ ሚስት በሁኔታው በጣም ያዘነች ቢሆንም ለባሏ በታማኝነት መጸለይዋን አላቋረጠችም። በለቅሶው የተቀመጠችውና ከለቅሶም በኋላ ተነስታ ወደ ቤቷ (ወደ ልጆቿ) የተመለሰችው ብቻዋን ነበር። እርሱ ግን ከደናሽ አልቃሾች ጋር በመሆን የሳቅ ጊዜ አሳለፈ።

ሞትና በሞት ምክንያት የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች ለወላይታ አማኞች ብርቱ የፈተና ጊዚያት ነበሩ። እነዚህ ሥርዓቶች በባሕሉ ውስጥ ሥር የሰደዱ መሆናቸው ከወላይታ ላልሆነ ሰው ብዙ ላይገባው ይችላል። በለቅሶ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ያለው ቁም ነገር ለሟች ማዘን ብቻ ሳይሆን ዕርዳታ፥ ትሕትና፥ መከባበር ማሕበራዊ ግዴታና በማሕበረሰብ ውስጥ ያለውን ቦታ ያጠቃልላል። ከዚህም የተነሣ አንዳንዴ ቃሉን በበቂ ላልተማሩና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ለቀዘቀዘ አማኞች ለቅሶዎች የማሰናከያ ድንጋዮች ቢሆኑ አያስደንቅም። የአዳም ጉዳይ ይኸው ነበር።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዳ ኃላፊነቱን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተዉ የቤት ውስጥ ሥራ፥ እርሻ ማሳረስ፥ ለቤተሰቡ ምግብ ማቅረብ፥ ለልጆች ልብስ ማዘጋጀትና መግዛት በሚስቱ ትከሻ ላይ ወደቀ። አዳ በለቅሶ ብዙ ቀናትን አሳልፎ ሲመለስ እርሷ ምንም አላለችውም። ቃሉን ንቆ ለጌታ ጀርባውን ስላዞረ በማማረር ወይም በመዝለፍ አልተናገረችውም። ይልቅ ስለርሱ በመጸለይ ተጋች። በቤት ውስጥ ሆና ቤቱን እየጠበቀችና ልጆቿን እያሳደገች በጸሎት ብትበረታም አዳ ግን ከቀን ወደ ቀን በጌታ ነገር ፍላጐት እያጣ ወደ አሮጌ ሕይወቱ ዘልቆ ገባ።

በየጊዜውም ሚስቱን «ከአሁን ጀምሮ እዚህ ቤት መኖር የለብሽም፥ ለቀሽ ውጪልኝ። እኔ ያለ አንቺ መኖር እችላለሁ» እያለ ያስቸግራት ነበር።

እርሷም «አይሆንም እዚሁ እኖራለሁ። እዚሁ እየኖርሁ አንተ ወደ ጌታ እስከምትመለስና ከቤተሰብህና ከሌሎች ክርስቲያኖች በኅብረት የምትደሰትበትን ሕይወት እስከምታገኝ ለአንተ እጸልያለሁ» ስትል መለሰችለት።

አዳ ቤቱን ለቃ እንድትሄድ ደጋግሞ ከማዘዙም በላይ ቢደበድባትም እርሷ ብዙ አልተሰማትም፥ አልተጨነቀችም፥ ከቤት ወጥታ እርሱ እንዳዘዛት አልሄደችም። ይህንን አይቶ እርሱ ግን ተበሳጨ።

«አንተን እየረዳሁና ላንተ እየጸለይሁ የሚሆነውን እዚሁ ሆኜ እጠባበቃለሁ። እኔ ሚስትህ ነኝና ቤቱን ለቅቄ አልሄድም» አለችው።

«እሺ ጥሩ! ቁጭ በይ እንግዲህ!»

አዳ ሚስቱን እንድትሄድ ያዘዘው ብቻውን ለመሆን ፈልጎ ሳይሆን እንደርሱ እምነቷን እንድትተው ቢሆንም እርሷ አልተወችውም።

አንድ ቀን አዳ ቡልኮዋን ወሰደ። የወላይታ ሴቶች ቡሉኮውን ቀን ይለብሱታል፥ ማታም እንደብርድልብስ የአልጋ ልብስ ያደርጉታል። ቡሉኮ ማሠራት ሳምንታትን ሊፈጅ ይችላል። ጥጡ ተገዝቶ ወይም በሌላ መንገድ ከተገኘ በኋላ ተጣርቶ ይፈተላል። ከዚያም ለሸማኔ በቂ ገንዘብ ተከፍሎ ይሠራል። ይህን በመሰለው ድካምና መስዋዕት የተሠራ የሚስቱን ቡሉኮ አዳ

ወስዶ በገበያ ከሸጠ በኋላ ገንዘቡን አጥፍቶ ያለ ማንቲም ወደ ቤት ተመልሶ መጣ። እርሷም ልብስ አጥታ በጣም የተቸገረች ቢሆንም «ልብሴን ለምን ወሰድክ?» አላለችውም። በታማኝነት ስለ እርሱ መጸለይዋን ሳታቋርጥ ወደ ጌታ የሚመለስበትን ቀን በእምነት ተጠባበቀች።

አዳ ሚስቱን አናድዶ እርሱን እንድትጠላው ለማድረግ ያልፈጸመባት ጨካኝ ድርጊት አልነበረም። ወደ ሴቶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዳትሄድ ከለከላት። በዚህም አልተበሳጨችም። በሥርጓ ስጦታ እንድትሆናት ከወላጆቿ የተሰጣትን አንዲት ላም ገበያ ወስዶ ሸጠባት። ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ ስለላሟ ምንም አላነሳችበትም።

ሚስቱም ላሟን የት እንዳደረሳት አልጠየቀችውም። በዚህን ጊዜ አዳ በጣም ተገረመ፥ ተናደደም። እንድትበሳጭና እንድትጠላው ለማድረግ ብዙ ቢለፋም ሊሳካለት አልቻለም።

«ለምን እንደምትወጂኝ አላውቅም። እኔ ግን ፍቅርሽን አልፈልገውም። ከአሁን በኋላ አንቺን ከውለታሽና ከትዕግሥትሽ ጋር የምታገስበት አንድ ቀን አይኖረኝም» አላት።

አዳ ላይሳካለት ከሚስቱ ለመገላገል የተለያዩ ዘዴዎች ቢሞክርም ጌታ ለአዳ ሚስት የሚያስፈልጋትን ጸጋና ትዕግሥት አብዝቶ ሰጣት። በመጨረሻም አዳ አንድ ተጨማሪ ነገር ለመሞከር በመወሰን ሌላ ሚስት አገባ። አዲስቱን ሚስት ይዞ ወደ ግቢው ከገባ በኋላ በአካባቢው ያለ ሁሉ እንዲሰማው ከፍ ባለ ድምፅ «ይህ ቤትሽ ነው» አላት።

የመጀመሪያ ሚስቱ ይህንን ሁሉ ብትመለከትም በአዳ አልተማረረችም። «ስላንተ መጸለዩን አላቋርጥም» እያለች ልጆቿን ማሳደግና ሌላም ሥራ መሥራት ቀጠለች። ከቀን ወደ ቀን አዳ በሁለት ሚስቶቹ መካከል ችግር ይፈጠራል በማለት ሲጠብቅ ቆየ። አንድ ቤት ለሁለት ሴት ስለማይሆንና በራሷ ቤትም ሌላ ሴት ስትኖር በእርግጥ ትናደዳለች ብሎ አሰበ።

ሳምንት አልፎ ሳምንት ቢተካም የተፈጠረ ነገር የለም። ሁልጊዜ ውጭ ውሎ ወደ ቤት ሲገባ ሁለቱ ሚስቶቹ ሲጫወቱ ያያቸው ነበር። የመጀመሪያ ሚስቱ ለሁለተኛይቱ በጣም ደግ ከመሆኗም በላይ ስለ ጌታ የምትመሰክርላት መሆኗን ለመገመት ቻለ።

አንድ ቀን አዳ ወደ ቤት ሲገባ ሁለተኛ ሚስቱ ታማ ያገኛታል። የመጀመሪያ ሚስቱ እርሷን በመጠበቅና በማስታመም ተሰላችታ ትማረራለች ብሎ ገመተ። ሁልጊዜ ማታ ከእርሻ ወይንም ደግሞ ከገበያ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሲገባ ይህ ይሆናል እያለ ይገምት ነበር። ነገር ግን የመጀመሪያ ሚስቱ ለሁለተኛይቱ መሆን የምትችለውን ያህል ደግ ሆና አገኛት።

በመጨረሻ የመጀመሪያ ሚስቱ ቤቱን ለቅቃ አልወጣችም፥ አልሄደችምም። ጭራሽ ሁለተኛ ሚስቱ አመነች። ይህ ሁኔታዋ ስላስቆጣው አዳ ሁለተኛ ሚስቱን አባረራት። ከእርሱ የበለጠ የመጀመሪያ ሚስቱ በሁለተኛይቱ ላይ ተጽዕኖ ስታሳድርና በእርሷ ዘንድ ተሰሚነት ሲኖራት ባሷን ምን ያህል እንደሚያናድደው መገመት ይቻላል።

ይህ ሁሉ የበዛበት በመሆኑ አዳ ሚስቱን «ከአንቺ ትዕግሥት፥ ደግነትና ፍቅር የተነሣ እኔም ዛሬ ወደ ጌታ ለመመለስ ወስኛለሁ» ሲል ነገራት። ሚስቱን ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ ተግባሩን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንዲያውቁ አደረገ። እነርሱ ባሉበት በእግዚአብሔር ፊት ተደፍቶ ከከዳበት ቀን ጀምሮ ለሠራው መጥፎ ሥራ፥ ለገባበት ጥልቅ ኃጢአትና ቤተሰቡን ለበደለበት ይቅርታ በመጠየቅ ልቡን አፈሰሰ።

በሚቀጥለው እሁድ አዳ ከሚስቱና ከቤተሰቡ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ። ሚስቱ በጽኑነት፥ ለርሱ ታማኝ በመሆንና በቅን ጸሎት ወደ ጌታ መለሰችው።

# ምዕራፍ 25. ላፋሜ

በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም
የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል።
2ኛ ቆሮ. 9፡6

«ጌታ ሆይ! እሽ ላሜን እሰጥሃለሁ፥ ግን . . .!» ላፋሜ በመቶዎች ከሚቆጠሩ አማኞች ጋር በሚዳው ሣር ላይ ተቀምጣ ታዳምጣለች። ላሟን ለጌታ እንድትሰጥ ለቀረበላት ጥያቄ ልቧ በአዎንታ ቢመልስም ያላት ግን ይህችው ላም ብቻ ነበረች።

ላፋሜና ባሏ በደቡብ ምዕራብ በጎፋ ተራራማ ቦታዎች ለሚኖሩ ለተረሱ ሕዝቦች ወንጌል ለማድረስ እንዲሄዱ እግዚአብሔር ያቀረበላቸውን ጥሪ ተቀበሉ። ባሏ ቤት የሚሠራበትን ቦታና ለእርሻ የሚሆን መሬት ለመምረጥ አስቀድሞ ብቻውን በሄደ ጊዜ ላፋሜ ልጆቿን እየተንከባከበችና ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ስታዘጋጅ በቤት ቆይታ የባሏን መመለስ ትጠባበቅ ነበር።

በዚህን ጊዜ ነበር ከአንድ ቀን ሙሉ ጉዞ በኋላ በሚደረስ በሶዶ ዓመታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፈራንስ የተካሄደው። በኮንፈራንሱ መገኘት ለላፋሜ የሚቻል አልነበረም። ሆኖም ጌታ ቤቷና ልጆቿ የሚጠብቁበትን ሁኔታ አመቻችቶላት በኮንፈረንሱ እንድትገኝ ረዳት። ከፊት ለሚጠብቋት ፈታኝ ቀናት የሚረዱ የሚያጠናክሩና የሚጠግኑ መልእክቶችን ለመስማት በጣም ጓጓች።

ከመጀመሪያዎቹ ስብሰባዎች በአንዱ ለወንጌላውያን የገንዘብ ርዳታ እንዲደረግ ጥያቄው ለሕዝቡ ቀረበ።

ወዲያው ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ አልተቻለም። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች መስጠት አልቻሉም ነበር። ገንዘብ ያላቸው የወላይታ ሰዎች ጥቂቶች ነበሩና። ነገር ግን ወደፊት ለመስጠት በእምነት ቃል የመግባት ዕቅድ ወጥቶ በዚሁ መሠረት ሁሉም ሰው መስጠት ቻለ።

አንድ በአንድ እየተነሡ ለስጦታቸው ቃል መግባት ጀመሩ። አንዱ ላም ለመስጠት ቃል ሲገባ ሌላው ጥጃ ሌላውም በግ። ብዙዎች ደግሞ የተለያየ ብዛት ያላቸውን የቡና ዛፎች ሰጡ። አንዳንዶች ከሌላ ሰው ጋር በጋራ አንዲት ላም ቢኖራቸው የራሳቸውን ድርሻ (ግማሽ ላም) ይሰጡ ነበር። ይህም ማለት አማኙ ድርሻውን ለሌላ ከሸጠ በኋላ ገንዘቡን ለጌታ ይሰጣል ማለት ነው።

ሌሎች እየተነሱ ለስጦታ ቃል በሚገቡበት ጊዜ ላፋሜ በጣም ተክዛ እርሷም እንድታደርግ ጌታ የሚፈልገውን ለማወቅ እያሰበች ነበር የተቀመጠችው። ለጌታ አንድ የምትችለውን ስጦታ ለማድረግ ፈልጋለች። በጸሎት መንፈስ ሆና በምታስብበት ጊዜ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጋ ለመስጠት ያላት ነገር ዋጋ የማያወጣና ዋጋ ቢያወጣም ደግሞ አነስተኛ መስሎ

ታያት። ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ «ላፋሜ! ላምሽን ለእኔ መስጠት ትችያለሽ» ሲል ተናገራት።

ወላይታዎች በጣም የሚያስደስት ልማድ አላቸው። ሴት ልጅ ስታገባ ወላጆቿ ለሠርግ ስጦታ ላም ይሰጧታል። ተጋቢዎች በቤታቸው ሌሎች ላሞች ሊኖራቸው ቢችልም ለሠርግ ስጦታ ከወላጆቿ የምትሰጥ ላም የሚስት የራሷ ሀብት ትሆናለች። ይህ በጣም ጠቃሚ ጥሎሽ ነበር፥ ምክንያቱም ለቤት እመቤት ላም መጠበቅና መንከባከብ አይከብድባትም። ላፋሜም በጣም የምትንከባከባት እንደዚህ ዓይነት ላም ነበረቻት። ይህችን ላም ነበር ጌታ «የእግዚአብሔር ቃል ይዞ አዲስና ወዳልሰሙ ሰዎች ከሄዱት ወንጌላውያን አንዱን መደገፍ እንዲቻል ላምሽን ብትሰጪኝ» ብሎ ላፋሜን የጠየቃት።

ላፋሜ ጥቂት ደቂቃዎችን እያሰበች ካሳለፈች በኋላ «ጌታ ሆይ! እሺ! ላሜን እሰጥሃለሁ፥ በእርግጥ እሰጥሃለሁ» አለችው። ሌሎች እየተነሡ የሚሰጡትን ይናገሩ ነበር። ሰዓቱ እያለፈ ሲሄድ ላፋሜ በድጋሚ ለጌታ ስትናገር «ጌታ ሆይ! ላሜን እሰጥሃለሁ፥ ግን ባሌ ተመልሶ ሊመጣና ሊወስደን ቦታ ፍለጋ እንደሄደ አንተ ታውቃለህ። እርሱ እስከሚመለስ ምግብ ልብስና ለልጆቻችን ወተት ስለሚያስፈልገን እርሱ መጥቶ እኔንና ልጆቻችንን ሲወስደንና አብረን ስንሄድ ላሜን ላንተ እሰጥሃለሁ» አለች።

ከስብሰባውም ተነስታ በኮንፈራንሱ ሳምንት ወደምታርፍበት ቦታ ሄደች።

በነጋታው ላፋሜ እንደገና ለኮንፈራንሱ መጣች። ለጌታ የሚደረግ የስጦታ ጥሪ እንደገና ቀረበ። ላፋሜ በሣሩ ተቀምጣ እንዳለች የከፍተኛ እርዳታ አስፈላጊነት ጥያቄ ሲቀርብ በመስማቷና ሰዎች እየተነሱ ስጦታዎቻቸውን ሲያሳውቁ በማየቷ ስሜቷ ተነካ። ጌታ በቀስታና በፀጥታ «ላፋሜ! ላምሽን ስጪኝ» ሲል በድጋሚ ተናገራት። ሌሎች የሚሰጡትን መናገር ቀጥለዋል። ላሞች፥ አህዮች፥ በጎች፥ የቡና ዛፎች፥ ባሕረ ዛፎች፥ ብር። ላፋሜም ‹ጌታ ሆይ! ሰዎች አሁን በደንብ እየሰጡ ስለሆነ እኔም ላሜን በምንሄድበት ጊዜ እሰጥሃለሁ። ለምግብ ለልብስና ለሌሎች ለእኔና ልጆቻችን ለሚያስፈልጉ ነገሮች ማግኛ እጠቀምባታለሁ እንጂ ሌላ ነገር አላደርጋትም። ላሜን ላንተ ጠብቄ እቆያታለሁ› ብላ አሰበች።

በሦስተኛው ቀንም በኮንፈራንሱ ከሌሎች ጋር ተቀምጣ ሳለች «አሁንም ላሞችን፥ ፈረሶችን፥ አህዮችን፥ ገንዘብ . . . መስጠት የምትፈልጉ ካላችሁ? ስንት ናችሁ?» የሚል ጥሪ ሰማች።

ላፋሜ ከስብሰባው ወጥታ ጥቂት የራሷን አካባቢ ሰዎች ካገኘች በኋላ «ይህን ያህል ብር የምታወጣ ላም እሰጣለሁ» ማለት እንድትችል ላሟን እንዲገምቱላት ጠየቀቻቸው። እነርሱም «የላምሽ ዋጋ ሃያ-ሰባት ብር ይሆናል» ካሏት በኋላ ተመልሳ ከስብሰባው ገብታ ተቀመጠች። «ሃያ ሰባት ብር! ሃያ ሰባት ብር! በሃያ ሰባት ብር ለእኔ አዲስ ቀሚስ፥ ለባሌ አዲስ ኮት፥ ለልጆቻችንም ልብስ፥ ቀለብም ጭምር መግዛት ይቻላል። አረ ብዙ ነገር ማድረግ ይቻላል! አዎን ጌታ ሆይ! እኛ ስንሄድ ላንተ እሰጣለሁ። ግን አሁን አይደለም የምሰጥህ! በኋላ! ስንሄድ! አሁን ላሜን በጥብቅ እንፈልጋታለን።»

ስብሰባው ሲያልቅ ላፋሚ ላሚን ለጌታ ለመስጠት በይፋ ቃል ሳትገባ ተነስታ ሄደች። መቼ እንደምትታዘዝ ከጌታ ጋር የተወያየችና የተከራከረች ቢሆንም በዚያን ጊዜ የማትታዘዝ መሆንዋን ወስናለች። በርግጥ መቼ መታዘዝ እንዳለባትም አላወቀችም። በሚቀጥለው ስብሰባ ሌሎች ቃል ሲገቡ ላፋሚ ቁጭ ካለችበት አልተንቀሳቀሰችም። ተነስታ በእግሯ መቆም አልቻለችም።

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ክርስቲያን ያልሆነ የላፋሚ ጎረቤት ሰው በትንሽ ጎጆዋ በር ቆሞ በቁጣ ይጮኽ ጀመረ «ላምሽ ከቡቃያዬ ገብታ ስለበላችና ስላበላሸች ነይ ከእኔ ጋር ሕግ ፊት እንቀርባለን፤ እዚያ ለጥፋትሽ መክፈል ያለብሽን ትሰሚያለሽ» አላት። አዎን! ላሚ በሜዳ ከታሰረችበት ባልታወቀ ምክንያት ገመዱ ተበጥሶ ነበር ከጎረቤት ማሳ የገባችው።

ላፋሚ ሕግ ፊት ከመቅረብ በስተቀር ማድረግ የምትችለው አልነበረም። ላፋሚና ላሚ ተይዘው ከጭቃ ሹሙ (ዳኛው) ፊት ቀረቡ።

«ምን ያህል እህል ነው በላሚቱ የተበላብህ?» ብሎ ጠየቀ ጭቃ ሹሙ ከሳሹን።

«በጣም ብዙ ነው፥ ብዙ ነው ጌታዬ! ስለዚህ ዋጋውን ትክፈለኝ» አለ ከሳሹ ጎረቤት። ዳኛውም በተለመደው የዳኞች አሠራር መሠረት ፍርዱን ለማዘግየት «የዛሬ አሥራ አምስት ቀን እንደገና ትቀርቡና ጉዳያችሁ ይታያል» ብሎ አሰናበታቸው።

ከአሥራ አምስት ቀናት በኋላ ላፋሚና ላሚ እንደገና ለፍርድ ቀረቡ። ዳኛውም ላፋሚንና ከሳሿን እንደገና ጠየቀ። ከሳሽ ጎረቤቷ አሁንም በጣም ተቆጥቷል። ይበልጥ የተናደደውም ምናልባት የፍርዱ ሒደት ስለረዘመ ይሆናል። ዳኛውም «ይህ ከባድ ጉዳይ በመሆኑ የዛሬ አሥራ አምስት ቀን ተመለሱ። በዚያን ጊዜ ላሚቷ ምን መደረግ እንዳለባት ይወሰናል» አላቸው።

ላፋሚ ላሚን ይዛ ወደ ቤቷ ተመለሰች። ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ እንደገና ቢቀርቡም ምንም የተወሰነ ነገር አልነበረም። ከዚያን በኋላ ተደጋግሞ እየተቀጠረ ውሳኔው ዘገየ።

በመጨረሻም ዳኛው ፍርዱን ሲያስታውቅ «ይህች ላም በጣም አጥፍታለች። የበላችው እህል በጣም ብዙ በመሆኑ መክፈል አለበት» አለ። ላፋሚ መክፈል የነበረባት ላሚ ለበላችው እህል በተጨማሪ የፍርድ ቤቱንም ልፋት ጭምር ነበር። በጠቅላላው ሃያ ሰባት ብር እንድትከፍል ተፈረደባት።

ላፋሚ ምድርና ሰማይ ዞረባት። «ሃያ ሰባት ብር? ልክ ላሚን ለጌታ ልሰጣት ስንት ታወጣለች ብዬ በሽማግሌዎች ካስገመትኩት ጋር እኩል» ካለች በኋላ ምርር ብላ አለቀሰች።

ላፋሚ በደነዘዘ አእምሮ ወደ ቤቷ ተመልሳ ሄደች። ለገበሬው ጎረቤቴና ለዳኛ የምከፍለውን ሃያ ሰባት ብር ከየት አመጣዋለሁ? ብላ አሰበች። እንደ እውነቱ ከሆነ የራሷ የሆነ ሃያ ሰባት ብር የላትም። ያላትን ልብስ ሁሉ ምንም ጨርቅ ሳታስቀር ከሸጠች በኋላ የሚጎድለውን ከጎረቤት ተበድራ ሃያ ሰባት ብር ሰበሰበች። ከዚህ የተነሣ ላፋሚ ራሷን ከማደህየቷም በላይ በዕዳ ተዘፈቀች።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ቀን ጧት ላፋሚ ከእንቅልፏ እንደነቃች በደብዛዛው የማለዳ ብርሃን ላሚ ወደምትቆምበት ቦታ ተመለከተች። አንድ

ነገር ተከስቷል። ሌሊቱን ላሟ ሞታ አድራለች። ዋጋ ቢስም ሆና ያለ እንቅስቃሴ በመሬት ላይ ተጋድማለች።

ላፋሜ በሁለት እጆቿ ራሷን ይዛ በአፈር ወለል ላይም ተቀምጣ መጮህና ማልቀስ ጀመረች። ደጋግማ «ጌታ እንድሰጠው በጠየቀኝ ጊዜ ላሟን ለእርሱ በሰጠሁ። በመጨረሻ ሁሉን አጣሁ። አዲስ ቀሚስ ለባሌ አዲስ ኮትና ለልጆቻችንም አዲስ ልብስ አይኖራቸውም፥ ለጎረቤቴ ያለብኝን ዕዳ የምከፍልበት የለኝም። ከሁሉም በላይ ለጌታዬ የምሰጠው ላም አይኖረኝም» አለች።

በኋላም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በአማኞች መካከል ቆማ ላፋሜ የደረሰባትን እንዲህ ብላ መሰከረች «ወገኖቼ ይህንን ታሪክ የምነግራችሁ ለአንድ ምክንያት ነው። ይኸውም ጌታ አንድን ነገር እንድታደርጉለት ሲጠይቅ ያንን ወዲያው መታዘዝና መፈጸም ያስፈልጋል። ከጌታ ጋር መከራከር ይቻላል ብላችሁ አታስቡ። እርሱ ከጠየቀውና ከፈለገው ሌላ የተሻለ መምረጥ አትችሉምና የጠየቀውን ወዲያው አድርጉት። ወዲያው ከታዘዛችሁለት በኋላ ትደሰታላችሁ። እኔ የፈጸምኩትን ስሕተት እናንተ አትፈጽሙ።»

# ክፍል ስምንት ፡- ያልጠፋው እሳት

## ምዕራፍ 26. የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ[1]

> . . . ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም
> ደጆችም አይችሉአትም።
>
> ማቴ. 16፡18

ዛሬ ቤተ ክርስቲያንና አገልግሎቷ የወላይታ ክርስቲያናዊ ኑሮና አስተሳሰብ እምብርት ናቸው። ክርስትና ወደ ወላይታ በገባ በሠላሳ ዓመታት ውስጥ የሕዝቡ ማህበራዊና ባሕላዊ ሕይወት ከዚሁ አዲስ አስተሳሰብ ጋር ፈጽሞ ተዋሐደ፥ ተላመደ።

ሕይወት በሁሉም አቅጣጫ ተለውጧል። ከእነዚህም አንዱ አባባል ወይም ንግግር ነው። ለምሳሌ መከራ ያጋጠመውን ሰው ለማጽናናትና መከራው የራስም እንዲሆን በመመኘት የሚገለጽ የተለመደ አነጋገር «እኔን ይብላኝ» የሚል ነበር። ክርስቲያኖች ይህንን አባባል ለምን እንደማይጠቀሙ ተጠይቀው «እኛ ይህንን አባባል ያቆምነው ውሸትና ከልብ ስላልሆነ ነው።

---

[1] በዚህ ምዕራፍ ሥር የተገለጹት የዛሬ ሠላሳ ዓመት አካባቢ የነበሩ ሁኔታዎች ናቸው።

በእርግጥ የዚያ ሰው መከራ የኛ እንዲሆን አንፈልግም ነበር። ስለዚህ አሁን ‹እኔን ይብላኝ» በማለት ፋንታ ‹እግዚአብሔር ይርዳህ› እንላለን።»

ከረዥም ዘመናት ጀምሮ ባላቸው ልማድ መሠረት ወላይታዎች በሕፃን ልጆቻቸው ፊት በዓይንና ጆሮ መካከል በሁለቱም በኩል ምልክት ያደርጉ ነበር። ምልክቱ ያልተደረገለት ሕፃን ዓይኑ ጤናማ አይሆንም ብለው ያምኑ ነበር። ክርስቲያኖች ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለአስተማረችና ስለ መከረች በልጆቻቸው ላይ ይህንን ማድረግ አቆሙ።

ቤተ ክርስቲያናቱ ሥነ ሥርዓት የማያከብሩ አባላትን ያስተምሯቸዋል፥ ይመክሯቸዋል፥ እርምጃም ይወስዱባቸዋል። ይህ የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሽማግሌዎች ኃላፊነት ነው። ከአቅማቸው በላይ የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥማቸው ግን እርዳታና ምክር እንዲደረግላቸው ወደ ክፍለ ማህበር (ወረዳ) ሽማግሌዎች ስብሰባ ያቀርቡታል።

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አሥራ አንድ ክፍለ ማህበራት የነበሩት ሲሆን ይህም የታዳጊውን ቤተ ክርስቲያን ፍላጐት ለማርካት ታስቦ የተደረገ አዳረጃጀት ነበር። ከያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ለፀሎት ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በቤተ ክርስቲያን ችግሮች ላይ ለመመካከር ይሰበሰባሉ።

ከየክፍለ ማህበሩ ኮሚቴ ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ተመርጠው «ጠረጴዛ» በመባል በሚታወቀው በአውራጃ ሽማግሌዎች ወርሃዊ ስብሰባ ክፍለ ማህበራቸውን ይወክላሉ። ለስብሰባው «ጠረጴዛ» የሚል ስያሜ የተሰጠው ከሚሲዮናውያን ልምምድ የተነሣ ነበር። ሚሲዮናውያን በየወሩ በመጨረሻ ዓርብ ለጸሎትና ለምክክር በ«ጠረጴዛ» ዙሪያ ይሰበሰቡ ነበር። ሚሲዮናውያን በኢጣሊያኖች አስገዳጅነት ከወጡ በኋላ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚሲዮናውያኑ አሠራር ዘዴ ለመቀጠል በመወሰን ስብሰባቸውን በጠረጴዛ ዙሪያ ማድረግ ጀመሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስብሰባው (በኋላም የቤተ ክርስቲያኑ ጽ/ቤት) «ጠረጴዛ» ተብሎ ተጠራ። የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር (አሁን የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን) አካል ነው።

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም በቤተ ክርስቲያኗ ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጉድለት ነበር። ለዚህ ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ማንኛውም ሥነ ጽሑፍ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ እንዲሆን ከሚያዘው ደንብ የተነሣ የመጽሐፍ ቅዱስ በወላይትኛ ቋንቋ ያለመኖር ነበር። የእግዚአብሔር ቃል በራሳቸው ቋንቋ ሲኖራቸው ክርስቲያኖች የበለጠ ያድጋሉ። የቃሉ በቋንቋቸው ያለመኖር በተለይ ለቆዩ ክርስቲያኖች እንቅፋት ነበር።

ሚሲዮናውያን ለቀው ከወጡ በኋላ በነበሩ ዓመታት የአማኞች ቁጥር ባልተለመደ ሁኔታ ፈጥኖ ቢያድግም ክርስቲያኖቹ በጣም አነስተኛ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ነበራቸው። ስለሆነም ባለፉት ዓመታት

ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶ ትልቅ ውጤት ተገኝቷል። ሆኖም መሠረታዊ የሆነው የቀለም ትምህርት አብሮ ባለመሰጠቱ እርምጃው አዝጋሚ ነበር።

በመጀመሪያ ሕዝቡ ለትምህርት ያለው ፍላጐት ቀዝቃዛ ነበር። በተከተሉት ዓመታት ግን ይህ ተቀይሮ ሁሉም ልጆቹን ትምህርት ቤት ለማስገባት ይጋፋ ጀመር። በሺህ የሚቆጠሩ የወላይታ ክርስቲያን ወላጆች የመማር እድል ስላልነበራቸው ዛሬ ደግሞ ይህ እድል ልጆቻቸውን እንዳያመልጣቸው ይፈልጋሉ።

የወደፊት ተስፋ የሚጣልባቸው እነዚሁ ተማሪዎች በብዛት መጉረፋቸው ሚሲዮናውያንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አሳስቧቸው ነበር። እነርሱ እንደሚያምኑት ለልጆች የትምህርት እድል መከፈት ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን እድገት ወሳኝ ቢሆንም የመማሪያ ድርጅት እጦት አንደኛው ችግር ነበር። በሶዶ የሚገኘው የማዕከላዊ ኤስ አይ ኤም ትምህርት ቤት በአሁኑ (ይህ መጽሐፍ በእንግሊዘኛ በተጻፈበት) ጊዜ ከስድስት መቶ ተማሪዎች በላይ ይዟል። ትምህርት ቤቱን ለማስፋፋትም ሆነ በሌሎች ሥፍራዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መሥራት አይቻልም ነበር። ይህንን ለማድረግ ብቃት ያላቸው የሚሲዮን ሠራተኞች ካለመኖራቸውም በላይ የሚያስፈልገው ገንዘብ መጠንም ሲታሰብ ሥራውን ጭራሽ የማያስሞክር ሆነ።

በኋላ የራስ አገዝ ትምህርት ቤት እቅድ በመውጣቱ ለትምህርት ችግር ከፊል መፍትሔ ተገኘ። ቤተ ክርስቲያናቱ «እኛ ብዙ ዕቃና መማሪያ አያስፈልገንም። ለግድግዳው ጭቃ ለጣሪያው ደግሞ ሣር ተጠቅመን ለምን የራሳችን ትምህርት ቤቶች አንሠራም?» ብለው ጠየቁ። በሶዶ ትምህርት ቤት አራተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ወጣቶች ሌሎችን ፊደል ማንበብና መጻፍ ያስተምራሉ። ከዚያም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች በሚቻላቸው ሁሉ በመንግሥት በጸደቀ ሥርዓተ ትምህርት ወደ ማስተማር ያድጋሉ። ትምህርት ቤቶቹ አንደኛ ክፍል ከፍተው ማስተማር ሲጀምሩ የሶዶ ትምህርት ቤት አንደኛ ክፍሉን በመዝጋት በፋንታው አምስተኛ ክፍልን ከፍቶ ተማሪዎች እንዲቀበል እንዲሁም በሁለተኛ ክፍል ፋንታ ስድስተኛ፥ በሦስተኛ ፋንታ ሰባተኛ እያሉ እንዲቀጥሉ በቤተ ክርስቲያናትና ሚሲዮናውያን መካከል ስምምነት ተደረገ።

ሀሳቡን በሥራ መተርጎሙ በመጀመሪያ በዝግታ ሆኖ በኋላ ግን በፍጥነት አደገ። በሦስት ዓመታት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ቁጥር ከምንም ወደ ዘጠና ስድስት ከፍ አለ። በ1957 ዓ.ም. አጋማሽ ከአሥር ሺህ በላይ ተማሪዎችና አንድ መቶ አሥራ አምስት አስተማሪዎች በነዚሁ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። አሥራ ሰባቱ ትምህርት ቤቶች አንደኛና ሁለተኛ ክፍል የነበራቸው ሲሆን አምስቱ በተጨማሪ ሦስተኛ ክፍል ነበራቸው። የሶዶ ትምህርት ቤት ደግሞ ስድስተኛ ክፍል የከፈተ ሲሆን ወደ ፊትም ሌሎችን ክፍሎች ጨምሮ ለመክፈት ተስፋ ያደርግ ነበር።

ከዚያን በኋላ ትኩረቱ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዞሮ በሶዶ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በሰለጠኑ አስተማሪዎች እየተረዱ የአሥራ ሁለቱ ክፍለ ማህበራት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ያስተምሩ ነበር። እነዚሁ

ትምህርት ቤቶች የዝቅተኛውን ደረጃ ሥልጠና ሙሉ በሙሉ በሚያካሄዱበት ጊዜ ማዕከላዊው የሶዶ ትምህርት ቤት የሚሰጣቸውን ኮርሶች ከፍ እንዲያደርግ ታቀደ።

በዚህ አኳኋን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እጦት ላይ ጦርነት ተካሂዶ ቀስ በቀስም ድል ለመቀዳጀት ተቻለ።

* * *

ወንጌል በየሄደበት ሁሉ ለውጥን ያስከትላል። በጳውሎስ ጊዜም በትንሹ ኢስያና በግሪክ የታየው ይኸው ነበር። በወላይታም ወንጌል ይህንን ሠርቷል። በአንድ በኩል እንግዲህ የሚያስከትለውን ውጤት አውቆ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ወደ ሕዝቦች ሕይወት ማምጣት ድፍረትና ልበ-ሙሉነትን ይጠይቃል። የወንጌል መምጣት ደም መፍሰስን፥ መከራን፥ ስቃይን፥ ረሃብን፥ በሽታን፥ አልፎም ሞትን ያስከትላልና። ቁጭ ብሎ ያሰበ አንድ ሰው ወንጌል አማኞቹን ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል ሊገምት ይችላል። በእርግጥ ወንጌል ለአማኞቹ ያን ያህል ዋጋ አለው?

የወላይታ አማኞች ወንጌል ለእነርሱ ከከፈሉት ዋጋ ሁሉ የበለጠ እንደሆነ ይናገራሉ። «ወንጌል ወደ እኛ በመምጣቱ በጣም ደስ ይለናል፥ መከራና ሥቃይ የሚመጣና የሚያልፍ ሲሆን የእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር የተገኘ ሕይወት መቼም ቢሆን አይለወጥም» ይላሉ ወላይታዎች።

እነርሱም በሚከተለው የሐዋሪያው ጳውሎስ አገላለጽ ይስማማሉ፥

> በየአቅጣጫው መከራ ይደርስብናል፥ ነገር ግን አንሸነፍም። ብዙ ጊዜ ግራ ይገባናል ግን ተስፋ አንቆርጥም። ጠላቶች ያሳድዱናል፥ ግን ወዳጆች እጥተን አናውቅም። ተመትተን እንወድቃለን፥ ግን አንሞትም። የኢየሱስ ሕይወት በእኛ ሰውነት እንዲገለጥ ዘወትር የኢየሱስን ሞት በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን።
>
> . .
>
> ስለዚህ ተስፋ አንቆርጥም፥ ምንም እንኳ ውጫዊው ሰውነታችን ቢጠፋ ውስጣዊው ሰውነታችን በየቀኑ ይታደሳል። ይህም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነ መከራችን ወደር የሌለውን እጅግ ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ክብር ያስገኛልና። እኛ የምንመለከተው የማይታውን ነገር እንጂ የሚታየውን አይደለም። ምክንያቱም የሚታየው ነገር ጊዜያዊ ነው፥ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው።

2 ቆሮ. 4፡8-10፥ 16-18

(ከአዲሱ የአማርኛ ትርጉም)

# ምዕራፍ 27. ለምን በወላይታ ሆነ?

ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን
ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፥

ዮሐ. 3፡8

ለእኛ አይደለም አቤቱ ለእኛ አይደለም፥ ነገር ግን ለስምህ .
. . ምስጋናን ስጥ።

መዝሙረ ዳዊት 115፡1

በምዕተ ዓመቱ መግቢያ አካባቢ እሣ ስለሚባል ሰው በወላይታ አውራጃ በሰፊው ይወራ ነበር። እሣ መነሻው ከጋሞ ቢሆንም ዝናውና ትምህርቱ በሁሉም አካባቢዎች ታወቀ። እርሱም ሰማይንና ምድርን ከፈጠረው አንድ እግዚአብሔር ራእይ እንዳለው ተናገረ። ራእዩም የወላይታ ሕዝብ ሰይጣንን ማምለክ ትቶ አንድና ፈጣሪ የሆነውን አምላክ ብቻ እንዲያመልክ የሚያሳስብ ነበር። በተጨማሪም እሣ በሳምንት አንድ ቀን በተለይም እሁድ እሁድ ሕዝቡ እንዲጸልይ አስተማረ። ሲጸልይም ጣቱን ማር ውስጥ አጥልቆ ካወጣ በኋላ ያንን ወደ ሰማይ በመርጨት ጸሎቱ ለሰይጣን ሳይሆን ለእግዚአብሔር መሆኑን ያሳይ ነበር። እሣ ያስተማራቸው ሕጎች አሥርቱ ትዕዛዛትን የሚመስሉ ነበሩ።

ትምህርቱ እየተስፋፋ ተከታዩም እየበዛ ሲሄድ የጥንቆላ ሥራ ተጋታ። የሰይጣንን አምልኮ ይመሩ የነበሩ ጠንቋዮች የእሣን ትምህርት ሲቀበሉ የቀሩት ደግሞ በድብቅ ይሠሩ ነበር።

በመጨረሻ ንቅናቄው በፖለቲካ በመዋጡ እሣ ታሥሮ ከቆየ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን ሶዶ ከተማ ከመግባታቸው ከጥቂት ዓመታት በፊት ሞተ። ንቅናቄውም ከእርሱ ጋር የሞተ ይሁን እንጂ የዚሁ አምልኮ ቅሪት በመላው ወላይታ ቀይቶ ነበር። በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ያመኑ ሰዎች በእሣ ትምህርት ተገፋፍተው አልነበረም። ነገር ግን ከአንዱና እውነተኛው አምላክ የተሟላ ራእይ አንድ ቀን እንደሚመጣ ሕዝቡ ይጠብቅ ነበር። ምክንያቱም እሣ ነጭ ሰዎች የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይዘው እንደሚመጡ ትንቢት ተናግሮ ይህም መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ይበልጥ የሚያስረዳቸው ስለሆነ እንዲከተሉት አሳስቦ ነበርና።

የእግዚአብሔርን ሥራ መመርመር የሚችል የለም። ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሲገልጽ የነፋስን ምሳሌ ተጠቅሞ ነበር! ነፋስ ከየት እንደሚነሣና ወዴት እንደሚቸኩል አናውቅም። ወደ ፈለገበትም ይነፍሳል። ነገር ግን ድምፁን እንሰማለንና ውጤቱን ወይም ደግሞ መኖሩን ማወቅ እንችላለን።

«ይህ ሁሉ ለምን በወላይታ ሆነ?» ለሚለው ጥያቄ የመጨረሻው መልስ አይታወቅም። በወላይታ የታየው የወንጌል ሥራ ውጤትና የቤተ ክርስቲያን እድገት የተሠራው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነበር። ብዙዎች ለዚህ ሲሉ ራሳቸውን

አሳልፈው በመስጠት ችግር መከራ ስደትና ጉድለት ቢቀበሉም በወላይታ የሆነው ሁሉ በሰው ጥረትና ሥራ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም ነበር።

ከዚህ ጋር አብሮ ሌሎች ምክንያቶችንም ማየት ይቻላል። የእግዚአብሔርን አሠራር ለማወቅ በምንሞክርበት ጊዜ የጸጋው ኃይል ይበልጥ ጎልቶ ይታየናል እንጂ አይደበዝዝም። ከእግዚአብሔር በታች ሆነው፥ እግዚአብሔር ራሱ፥ ዓለምና ቤተ ክርስቲያን በዓለም ወንጌልን ለማዳረስ ለተነደፈው የተሟላ ሥልትና እግዚአብሔር በወላይታ የተጠቀመባቸውን መንገዶችና ምክንያቶችን ለማሳወቅ ባለውለታዎች ናቸው።

በወላይታ የታየውና ዛሬም በብዙዎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚታየው ሁሉ ያልተለመደ የእግዚአብሔር ኃይል መግለጫ ሆኖ መቆጠር የለበትም። በአንደኛው ምዕተዓመት ተጀምሮ እስካሁን የቀጠለና ጌታ ተመልሶ ሲመጣ ለራሱ ሲረከባት የሚያበቃው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንጂ። የወላይታዎችን ክርስትና ልዩ የሚያደርገው እግዚአብሔር በዚያ ቦታና ጊዜ ይህንን ንቅናቄ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ መሥራቱ ነው። በዚህም እግዚአብሔር በደቡብ ኢትዮጵያ ኃይሉ ይበልጥ የሚገለጽበትን መንገድ ፈጠረ።

እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ለዓለማው ማስፈጸሚያ ይጠቀማል። ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን እድገት ተጨባጭና የሚታዩ ምክንያታዊ ነገሮች ትግሂና ገላዊ ባሕሪያት፥ ማህበራዊ አቋም፥ ፖለቲካዊ አደረጃጀት፥ ብልጹ ሃይማኖትና የመሳሰሉት ነበሩ።

በመሠረቱ ወላይታዎች ዳሃና ታታሪ ሰዎች ናቸው። በደቡብ ኢትዮጵያ እንደሚኖሩ የኦሮሞ ጎሣ አባሎች ሁሉ ወላይታዎችም ለብዙ ምዕተ ዓመታት ለፊውዳል ነገሥታት ሲገብሩ ኖረዋል። ወላይታዎች ከሚደርስባቸው ማህበራዊ ፖለቲካዊና ባሕላዊ ጭቆና ለመላቀቅ መንፈሳዊ ኑሮአቸውና አስተሳሰባቸው እንዲለወጥ ተመኙ። ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ወላይታዎች ከቅድመ አያት ተያይዞ በመጣ ጥብቅና ረቂቅ በሆነ መንፈሳዊ እምነት ለሰይጣን ሲያመልኩ የኖሩ ቢሆንም በዚህኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በአግ ስብከት ምክንያት ይህ ሥርዓት ተደከመ። ይህ ሰይጣናዊ አምልኮ በመቋረጡና ሥርዓታዊ የሆነው ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሕዝቡን መንፈሳዊ ጥማት ማርካት ባለመቻሉ ለወንጌል መግባት አመቺ ሁኔታ ተፈጠረ።

ስለሆነም ሚሲዮናውያን መጡ። የቆዩት ለዘጠኝ ዓመታት ብቻ ቢሆንም እነዚሁ ዓመታት ከቀደሙት ጋር ሲነፃፀር ሰላማዊ ፖለቲካ የሰፈነባቸው ነበሩ። ምንም እንኳን ቋንቋ መማሩ ብዙ ጊዜ የወሰደና የቤተ ክርስቲያን እድገት ዝግተኛ ቢሆንም ሚሲዮናውያን ለቀው እንዲወጡ በተገደዱበት ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብለው የነበረውን ሁኔታ ሲመለከቱ በግልጽ የሚታይ መንፈሳዊ መነቃቃት ነበር።

በኋለኛዎቹ ዓመታት በወላይታ ለታየው መልካም ውጤት አስተዋጽዖ ካደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከመጠመቃቸው በፊት በጥንቃቄና በሚገባ መመርመራቸው (መጣራታቸው) ነበር። ከመጀመሪያዎቹ ሃያ ሦስት አማኞች አሥራ ስድስቱ ቀርበው ከእነዚሁ

ውስጥ አሥሩ ብቻ መጠመቃቸው ምን ያህል ጥንቃቄ ይደረግ እንደነበረ ያሳየናል።

ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ከመጀመሪያዎቹ አሥር ተጠማቂዎች ውስጥ አንዱ ብቻ ከእምነቱ ወደ ኋላ ተመለሰ። ከአሮጌው ሕይወት ለመለየት የተደረገ ቁርጥ ውሳኔ ለመጠመቅ አስፈላጊ መሆኑ ከመጠን የበለጠ ግምት ሊሰጠው አይገባም። ከዚህም የተነሣ በመጀመሪያ ቀርበው ካልተጠመቁ አማኞች ውስጥ አብዛኛዎቹ በኋላ እንዲጠመቁ ተደርጓል።

በሌሎች ተመሳሳይ ማህበራዊ ባሕላዊና መንፈሳዊ ንቅናቄዎች የቡድኑ ወይም የማህበረሰቡ መለወጥና ተቀባይነት አስፈላጊ ነገር ነበር። በተቃራኒው ወደ ክርስቶስ መመለስ ግን የግል ውሳኔና ከጌታ ጋር ቃል መግባትን ይጠይቃል። በግለሰቦቹም ላይ ልዩ ልዩ ችግሮች ይደርሱ ነበር። ግለሰቦች ክርስቶስን በመቀበላቸው ቤተሰብ ተከፋፍሏል፥ ባሎች ከሚስቶቻቸው ልጆች ከወላጆቻቸው ተለያይተዋል። በዚህ ንቅናቄ መካፈልና መሳተፍ ከአሮጌው ሕይወት ወጥቶ ወደ አዲሱ የመቀላቀልን ዋጋ ያስከፍል ነበር።

ይህም በመጀመሪያ የንቅናቄው ሂደት እንዳይፋጠን ያደረገ ቢሆንም የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የተገነባችበትን መሠረት አጠንክሯል። ከዚህም የተነሣ በቡድን (በማህበር) ሳይሆን በግል የእምነት ውሳኔ ምክንያት በእግዚአብሔርና በአማኝ ግለሰብ መካከል እውነተኛ የመንፈስ ልውውጥ ስላለ በመከራ ጊዜ ጽናት እንዳስገኘ ታምኖአል።

የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን በሕዝቡ ላይ ምዕራባዊ ባሕልን ሳይጭኑ ራሳቸውም ሕዝቡን መስለው መኖር መቻላቸው በጣም ጠቃሚ ሆኖአል፥ ከዚህም የተነሣ የወላይታዎች አኗኗርና አመላለክ ከውጫዊ ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው ማለት ይቻላል። ሚሲዮናውያኑ ለሕዝቡ «የእግዚአብሔርን ነገር» ያመጡላቸው መሆኑን ሁልጊዜ ይናገሩ ነበር። ይህን እንዲያምኑና እንዲቀበሉ የግድ ከሌሎች ነገሮች በተለይም ከምዕራባዊ አመለካከት ጋር ተወዳድሮ መቅረብ የለበትም።

በቋንቋ ምክንያት አስቸጋሪ ሆኖ ቢቆይም ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከመጀመሪያም ትኩረት በመሰጠቱ የእግዚአብሔር ቃል በሥራና በሕይወት ተገቢ ቦታ ተሰጥቶታል። ወላይታዎች እንደ ሕፃን ማመን መቻላቸውንና በእግዚአብሔር ቃል የታዘዘውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን አስመስክረዋል። ሚሲዮናውያን በነበሩበትም ሆነ ባልነበሩበት ጊዜ ሁሉ በሥራ ላይ የዋለው ጥብቅ የሥነ-ሥርዓት (ዲሲፕሊን) ደንብ የቤተ ክርስቲያኑን ጥራት በሚገባ እንዲጠበቅ አድርጓል።

የወንጌል ሥራ በወላይታ መልካም ውጤት እንዲያሳይ ከረዱት ነገሮች አንዱ ክርስቲያኖቹ ወንጌል ለመመስከር ያላቸው ቅንዓትና ኃይል ነበር። እነርሱ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት በግልጽ ያለፍርሃት ይናገሩ ነበር። እንዲያውም «ሳሮ፥ ሳሮ» (ሰላም፥ ሰላም) የሚለውን የተለመደ ሰላምታ አስከትለው «እኔ አማኝ ነኝ» ይሉ ነበር።

ለወላይታ ቤተ ክርስቲያን ስደት የሁልጊዜ ዕጣ ሆኖ ቢቆይም አማኞች ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ፍቅር ይበልጥ የሚያድገው ስደቱ ሲበረታ መሆኑ ታውቋል። ዛሬም ቢሆን ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅር የሞቀና የጠበቀ ሆኖ እንዲቀጥል

የሚያስችል ብቸኛ መንገድ ስደት ከሆነ ተመልሶ እንዲመጣ መጸለይ በወላይታ ክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ ነው።

ሌላው ቀርቶ ገና ከመጀመሪያ አማኞቹ የሰይጣንን አምልኮ ትተው ኢየሱስን ለመከተል በመወሰናቸው የጠንቋዮች እርግማኔና ስደት ነበረባቸው። በሁሉም የወላይታ ሕይወት ዘርፍ ዘልቆ የገባው አረማዊ ሥርዓትና አምልኮው አሮጌውን እምነትና አኗኗር ከደው ለወጡ አማኞች ትልቅ ችግር ፈጥሮባቸው ነበር።

የኢጣሊያ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መሪዎች ቤተ ክርስቲያኑ ወደ ፊት ችግር ያስከትልብናል ብለው በመስጋት ለማፈን ብዙ ደክመዋል። በኢጣሊያን ቅኝ ገዢ መንግሥት እየተደገፈ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የወላይታን ቤተ ክርስቲያን በቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት ቢሞክርም ሊሳካለት ባለመቻሉ ስደት ጨመረ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በወላይታ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ስሜት ቀራጥነትና ሕብረት ላይ ቅንአት ነበረው።

ምን ጊዜም ቢሆን የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የነበሯት መሪዎች የአገሬው ሰዎች ናቸው። እነርሱ በአመራር ጠንካራ ይሁኑ እንጂ በአካል በአስተሳሰብና ማህበረሰብ ውስጥ ባላቸው ቦታ ታዋቂነትና ተሰሚነት ያላቸው አልነበሩም። በክርስቶስ ላይ ያልተለመደ ልዩ እምነት ያላቸው ተራ ሰዎች ነበሩ፥ አሁንም ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል 10:21 ላይ «በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ» ያለው ይህን ለማስገንዘብ ነበር።

የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎችና አማኞችም በሙሉ ችግር መከራና እጦትን ለመቀበል ፈቃደኞች መሆናቸው ለቤተ ክርስቲያኑ እድገት አስተዋጽዖ አድርጓል። እሥራት ግርፊያ ውርደትና ጭካኔ ተደጋግሞ ቢደርስባቸውም በጀግንነትና በደስታ አሳልፈዋል። የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራቹን ቃል ለማሰማት በርካታ ቤተሰቦች ወላጆችና ዘመዶች ቀየያቸውን ለቀው ወደ ሩቅ አካባቢዎች ሄደዋል። በመጀመሪያ ለወንጌላውያኑ መጠነኛ እርዳታ እንደሚደረግላቸው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ቃል የተገባላቸው ቢሆንም ከእግዚአብሔር በቀጥታ ከመጣላቸው በስተቀር የቤተ ክርስቲያኑ ድጋፍ የሚበቃቸው አልነበረም።

በብርቱ መከራ ጊዜ ክርስቲያኖቹ አንዱ ለሌላው ያሳዩት የነበረው የሞቀ ፍቅር ባላመኑት ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት አተረፈላቸው። በእሥር በነበሩበት ጊዜም ምግብ ከእሥር ቤት ስለማይቀርብላቸው ወዳጆች ዘመዶችና አማኞች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ስለሚያመጡላቸው የማያምኑ እሥረኞችም ጭምር ይመገቡ ነበር። ይህን የመሰለ ሕያውና ተግባራዊ ምስክርነት ብዙዎችን ወደ ጌታ አምጥቶአቸዋል። ሌሎችም ስለዚሁ አዲስ የሕይወት መንገድ ይበልጥ ለማወቅ ክርስቲያኖችን መቅረብ ጀመሩ። የዚህ ያልታወቀና ያልተሰማ ፍቅር ዜና በሩቅ አካባቢዎች ሁሉ ተዛመተ። በእሥር ቤት ያመኑ ሰዎች ተፈትተው ወደ ቤታቸው በሚሄዱበት ጊዜ በአካባቢያቸው በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀላሉ።

አማኞቹ ከአብዛኛው የወላይታ ሕዝብ የተለየ ጠባይ ነበራቸው። በአንድ ወቅት በአንድ እሥር ቤት ለነበሩ እሥረኞች ምግብ እንዳያደርሱ አማኞቹ

ተከለከሉ። በመጨረሻም አንዲት አሮጊት የተዘጋጀውን ምግብ ይዛ ወደ እሥር ቤቱ ኃላፊዎች በመሄድ ለወንድሞቿ ምግብ ለማቀበል የተከለከለች መሆኗን ነገረቻቸው። ኃላፊዎቹ እሥረኞቹ የሥጋ ወንድሞቿ መስሏቸው ምግብ እንድትሰጣቸው ፈቀዱላት። አሮጊቷ በኋላ ስለዚሁ ተጠይቃ የተናገረችው እውነት መሆኑን «በእናት ብንለያይም አንድ ሰማያዊ አባት አለን፥ ከዚህ የበለጠ ወይም የቀረበ ወዳጅነት በሰማይ ሆነ በምድር አይኖርም» በማለት አስረድታለች።

ወንጌል በወላይታ እንዲዳረስ ሴቶች የራሳቸውን ድርሻ አከናውነዋል። ሴቶች ለከፉ መንፈስ የሚያመልኩበት አሮጌ ልማድን ለማጥፋትና ምንም ዓይነት መስዋዕትነትን ቢያስከፍል ለክርስቶስና ለወንጌል ታማኝ መሆን ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ልጆቻቸው እንዲያውቁ ለማድረግ ችለዋል። እነዚሁ ያልተማሩ ሴቶች በመከራ የነበሩትን ወንዶች እያበረቱ በታማኝነት ከጐናቸው ቆመዋል። እንደ ወንዶቹ ሁሉ እነርሱም የሚያደርጉትን ሁሉ በሙሉ ልብ ያደርጉ ነበር። ከልብ አሮጌውን መንገድ ይከተሉ እንደነበረ ሁሉ አሁን ክርስቶስን በመከተል የጸኑ ሆነዋል።

ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ራሳቸው የሚሠሩትና የሚያሳድጉት መሆኑን ወላይታዎቹ እንዲያውቁት ተደርጓል። እርግጥ ነው በመጀመሪያ ወንጌል የመጣው በሚሲዮናውያን አማካይነት ነበር። ነገር ግን በወንጌል የሚያምኑ ሰዎች ከተገኙ በኋላ እነኚሁ ይህንን የመዳን ምሥራች ለሌሎች የማስተላለፍ ኃላፊነት ያለባቸው እንደሆነ አውቀዋል። ወንጌልም ሊስፋፋ የቻለው አስቀድሞ ሚሲዮናውያን የእግዚአብሔርን ቃል አስተምረው ካሳመኑ በኋላ አማኞቹ ደግሞ የተማሩትን ወዲያው እና በተደጋጋሚ ለሌሎች በማስተላለፍ በወላይታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ «የሁሉ አማኝ ወንጌላዊነት» ዘዴ በመመስረታቸው ነበር።

ለቤተ ክርስቲያኑ ዘላቂ ምስክርነትና የማያቋርጥ እድገት ዋናው ምክንያት የቤተ ክርስቲያኑ ወንድና ሴት መሪዎች መንፈሰ ጠንካራነት ነበር። እነዚህ ሰዎች በምንም አንፃር ጎልተው የማይታዩ ቢሆንም የጠለቀ መንፈሳዊ አመለካከት ያላቸውና በሙሉ ልባቸው ሊያገለግሉ ቃል የገቡ ነበሩ። ጌታ በምድር በተመላለሰባቸው ጊዜያት የመረጣቸውና የተከተሉትም ወንዶችና ሴቶች ተራ ሰዎች ነበሩ።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያኑ በሚገባ ከመዋቀሩም በላይ የክርስቶስን ጌትነት በሚያስተምሩና በሚያውጁ ጠንካራ መንፈሳዊ ሰዎች ይመራል። ዋናዎቹ መሪዎች ከየክፍለ ማህበሩ የሚመረጡ ሲሆን በየጊዜው በዋናው ጽ/ቤት በመሰብሰብ በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፥ ይጸልያሉ። ለብዙ ዓመታት ቀድሞ ባሪያ ፈንጋይና አሳዳሪ የነበሩት ዳና ማጃ ተመርጠው ያገለገሉ ሲሆን ታላቅ ልጃቸው አቶ ማርቆስ ማጃ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ዋና ፀሐፊ እንዲሁም ደግሞ በኢትዮጵያ-አቀፍ የወንጌል አማኞች አንድነት ማህበር ሥራ አመራር ውስጥ ሠርቷል።

እነዚህ መሪዎች «ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፥ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ» (1ኛ ቆሮ. 1፡27) ለሚለው የእግዚአብሔር ቃል እውነትነት ማስረጃዎች ናቸው።

እጅግ ብርቱ የሆነው የወንጌል አሠራር እምብዛም ጎልቶና ደምቆ አይታየንም። እግዚአብሔር ወንጌል የሚመጣበት ጊዜ ሲደርስ የተለያዩ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ሁኔታዎችን መንገድ ጠራጊዎች አድርጎ እንደሚጠቀምባቸው ልብ አናደርግም። የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ከሁሉ በላይ የሆነው በሰው ውስጥ በወንጌል አማካይነት የራሱን ፈቃድ የሚሠራ የእግዚአብሔር ጸጋ ሐውልት ነው።

## መደምደሚያ

ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው።
ሉቃስ ወንጌል 12፡43

በወላይታ በቆየሁባቸው ሁለት ዓመት ተኩል ጊዜያት የሆስፒታሉ ሕንፃ ሲገነባ ከእኔ ጋር ይሠሩ ከነበሩ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ተገኘ ይባላል። ሁልጊዜ ጧት ከሥራ በፊት ወንጌል ሲሰበክ ይሰማ ስለነበረ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነ ይህ ወጣት አምኖ ተቀበለ።

ተገኘ ባሪያ እንደመሆኑ መጠን በወሰደው እርምጃ ጌታው ተቆጥቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዳይሳተፍ ከመከልከሉም በላይ አካላዊ ጉዳትም ያደርስበት ጀመር።

የተደጋገመ ደብደባ የደረሰበት መሆኑና ከሌሎች አማኞች ጋር በነበረው ሕብረት እንዳይገኝ መከልከሉን ስናይ እምነቱ በፈተና ላይ መውደቁን አረጋገጠልን። እርሱ ነፃ የሚወጣበት ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ከተረዳን በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በጉዳዩ ተመካከረን ዋጋውን ለመክፈል ወሰንን። ስለሆነም በርካታ ጣሊያናውያን ሠላሣ ብር (አሥራ ሁለት አሜሪካን ዶላር) አዋጥተን ከከፈልን በኋላ ነፃ አወጣነው።

ተገኘ ነፃ በመውጣቱ ከልብ አመሰገነን። ውለታውን ለመመለስም የሚያደርግልንና የማይሠራልን ነገር አልነበረም።

ጣሊያናውያን ከአገር እንዲወጡ ተደርጎ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ጥቂቶቹ ሲመለሱ ሌሎች እንደወጡ ቀሩ። እኔ ግን በወቅቱ ናይጀሪያ በነበረው ሥራ ተይዤ ስለነበር ወደ ኢትዮጵያ ያለመመለስን መረጥሁ።

ሃያ አራት ዓመታት ተለይቼ ከቆየሁ በኋላ እንደገና ወደ ወላይታ ተመለስኩ። ያሁን ከአዲስ አበባ እስከ ወላይታ ጉዞዬ እንደፈተኛው ሁለት ሳምንት በበቅሎ አልነበረም። በአውሮፕላን በርረን በዳሞት ተራራ እግር ከሶዶ ከተማ አጠገብ ባለው ሜዳ ስናርፍ ጥቂት እኔ የማውቃቸው የመጀመሪያ ክርስቲያኖች እኛን ለመቀበል ይጠብቁ ነበር። ከሩብ ምዕተ ዓመት ያህል በኋላ እንደገና መገናኘት በጣም አስደናቂ ነበር። ቀድሞ ያሳለፉትን መከራና ችግር እያሰብኩ አሁን እንደገና እነርሱን ለማየት በመቻሌ የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ ቃላት አልነበረኝም።

ከዚያም ስድስት ማይሎች ርቆ ወደሚገኘው የሚሲዮን ጣቢያ ጉዞ እንደጀመርን በመንገዱ ግራና ቀኝ ሌሎች የማውቃቸው ክርስቲያኖች የእንኳን ደህና መጣችሁ መግለጫ ለማስተላለፍ ቆመዋል።

በሚሲዮኑ ጣቢያ አቅራቢያ ከመጨረሻው መጠምዘዣ ስንደርስ ተገኘ ከመንገዱ ዳር ቆሞ አየሁት። የእኔንና የተገኘን ወዳጅነት ሾፌሩ ሚሲዮናዊ የማያውቅ በመሆኑ ወደ ሚሲዮኑ ግቢ መኪናውን ማብረሩን አላቆመም። መኪናውን አስቁሜ እጄን ወደ ውጪ ስዘረጋ ተገኘ በሩጫ መጥቶ እጄን እስኪረጥብ ድረስ ደጋግሞ ከሳመው በኋላ «ይኸውላችሁ! እዩት! እኔን ነፃ ካወጡት ውስጥ አንዱ ተመልሶ መጣልኝ» ሲል አብረው ላሉት አወጀ።

እዚያው ከመኪና እንደወረድኩ ተገኘ በጉልበቱ ተንበርክኮ እግሮቼን በእጁ ጥብቅ አድርጎ በመያዝ አቧራ የሞላበት ጫማዬን ይስም ጀመር። እኔም ቀና አድርጌው በእግሩ ከቆመ በኋላ ተቃቅፈን ደረቶቻችን እስኪረጥቡ ድረስ አለቀስን።

ቀናችን በትክክል ለመወሰን የቀን መቁጠሪያ የሌለው ተገኘ ከእኔ ጋር ለመገናኘት እርግጠኛ ሆኖ ወደ ሚሲዮኑ ጣቢያ መምጣቱ በኋላ ተነገረኛል። በእጁም ሰዓት ሳይኖረው ለደቂቃ እንኳን ሳይቀድምና ሳይዘገይ በመጣሁበት ዕለት ማለዳ በሚሲዮን ጣቢያ መገኘቱን ለማወቅ ችያለሁ።

ይህ ልባዊ ስሜት የወላይታ ክርስቲያኖች ነፃ ላወጣቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ፍቅርና ታማኝነት ያሳየኛል። ለርሱ ሲሉ ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው። በማንኛውም ሰዓት ተመልሶ እንደሚመጣ ስለሚያውቁ በናፍቆት ይጠባበቁታል። የወላይታን ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ያበቃው ምናልባት ይህ ለአዳኛቸው ያላቸው ጉጉትና ፍቅር ይሆናል።